# የገላጭ ስብከት አዘጋጃጀት

በዶክተር ራሜሽ ሪቻርድ
Dr. Ramesh Richard

ተርጓሚ
ገበየሁ አየለ

ኤዲተርና ልዩ ረዳት
ስምዖን ሙላቱ

Published by
የላፕስሊ/ብሩክስ ፋውንዴሽን
LAPSLEY/BROOKS FOUNDATION
Dallas, Texas --- Addis Ababa
U.S.A. Ethiopia
2003 - 1995

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved
ይህ መጽሐፍ የተተጎመው
"Scripture Sculpture"
by Dr. Ramesh Richard
Originally published in the USA
First Edition Copyright 1995
Revised Edition Copyright 2001
Baker Book House
Grand Rapids, Mich. U.S.A.
ከሚለው መጽሐፍ ሲሆን የታተመውም በደራሲው ፈቃድ ነው።
የላፕስሊ/ብሩክስ ፋውንዴሽን
ስልክ 201464 -- ፖስታ 41221
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
Publisher
Lapsley/Brooks Foundation
Dallas, Texas, U.S.A.
1st printing
1995 -- 2003

# ማውጫ

መግቢያ ........ 4
የዝግጅት ማነሣሻ፣ ገለጣ እና አጠቃላይ እይታ ........ 7
1. ክፍለ ምንባቡን ማጥናት ........ 23
የጽሑፉ ላይኛ አካል (ሥጋ)
2.ክፍለ ምንባቡን ማቀናጀት ........ 45
የምንባቡ ውስጣዊ አካል (አጥንቱ)
3. የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ ........ 58
የክፍለ ምንባቡ ‘‘ልብ’’
4. የዓላማ መሸጋገሪያ ወይም ድልድይ ........ 70
የስብከቱ ‘‘አንጎል’’
5. የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ ........ 77
የስብከቱ ‘‘ልብ’’
6. ስብከቱን ማቀናጀት ........ 86
የስብከቱ ውስጣዊ አካል ‘‘አጥንቱ’’
7. ስብከቱን መስበክ ........ 122
የስብከቱ ‘‘ሥጋ’’

ተቀጥላ 1. መንፈስ ቅዱስና የመድረክ አገልግሎትዎ ውጤታማነት ..... 135
ተቀጥላ 2. ለስብከትዎ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሲመርጡ ........ 141
ተቀጥላ 3. የስብከት መገምገሚያ መጠየቅ ተቀጥላ ........ 143
ተቀጥላ 4. ርእሳዊ ስብከት ........ 148

የአሳታሚው ማስታወሻ ........ 155

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የተጀመረው፥ ደቡብ ሕንድ፥ ማድራስ ከተማ ገበያ ውስጥና ጎዳናዎች ላይ፥ ለወጣቶች ይደረግ በነበረ ስብከት ነው ለማለት ይቻላል። በዚህ የእድገቴ ወቅት፥ አማኑኤል ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ ፓስተር ሳሙኤል ካሚልሰን የተባለ አገልጋይን ጥሩና ተደማጭ ስብከቶች የመከታተል ዕድል ገጥሞኛል። በአሸዋማ የባሕር ዳርቻዎችና በኤሌክትሪክ ኃይል በሚሽከረከሩ ባቡሮች ላይ በምንሰብክበት ጊዜ፥ ወጣት ጓደኞቼ ይሰጡኝ የነበረ ማበረታታት ለዚህ መጽሐፍ እዳር መድረስ የራሱ አስተዋጽኦ አለው። ክርስቶስን፥ አገልግሎቱንና መጽሐፍት ማንበብን ይወድ የነበረው አባቴ፥ ጆን ሪቻርድ ጳኑ ሕይወት፥ ከፍተኛ ጥቅም ያለው ውርስ ሆኖኛል።

ዳላስ ሴሚናሪ ከገባሁ በኋላ ደግሞ፥ የነበረኝን የስብከት ስጦታ እንዳዳብረው ተገድጃለሁ። እዚያ የነበሩ ደጋግ ፕሮፌሰሮች ያለኝን የስብከት ልምድ ተቀበሉትና አረጋገጡት። አንድ ጊዜ፥ “የገለጣዊ ስብከት መግቢያ 603” በተሰኘ የኮርስ ዝግጅት ጊዜ ሀዶን ሮቢንሰን የተባሉ መምህሬ:- “ሚስተር ሪቻርድ፥ አንተ ስትሰብክ የመስማት ፍላጎቴ እምብዛም ነው” በማለት የተናገሩኝን አልረሳውም። ይህ አነጋገር፥ የስብከት ዝግጅቴንና ስብከቴን እንዳሻሽል ገፋፍቶኝ ይሆን?

ሰሜን ሕንድ፥ ኒውዴሊሀ ውስጥ አገለግለው በነበረው ጉባኤ፥ እስጥ ለነበረው ወደ መድረክ ያደላ መጋቢነቴ፥ ከጉባኤው ይሰማ የነበረው መልስ፥ የስብከት አገልግሎቴን በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ዋናው ሳምንታዊ ክንውን እንዲሆን ከፍ አድርጌ አጠናክረው ዘንድ አስገደደኝ። ከኒው ዴሊሂ ወደ ቦምቤ ከተዛወረ አንድ የቤተሰብ አባል ኅብረቱን አስመልክቶ ቀጥሎ ያለው ደብዳቤ ደረሰኝ፥ “የቦምቤ አየር ከዴሊሂ ይሻላል። ሕዝቡ ግን እዚህ ይበዛል። ጥሩ የአቶቡስ አገልግሎትም ሥርዓት አለው። ሕያው የሆነው ሳምንታዊ ስብከትና ኅብረት ግን እዚህ የለም። እዚህ ከመጣሁ ሁለት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶችን ተካፍያለሁ። እውነቱን እንድናገር ይፍቀዱልኝና፥ ስብከቶቹ የሚያረኩ ሆነው አላገኘኋቸውም”

አገልግሎቱ ያብብ ጀመር፤ እያደገ የመጣው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ በማቆጥቆጥ ላይ ያሉ ወጣቶችን ለማነጽ የሚረዳ የስብከት አዘገጃጀትን በየሳምንቱ እንዳስተምር ገፋፋኝ። አንዳንዶቹ ወጣቶች ዛሬ ግሩም ሰባኪዎች ወጥተዋል።

ያገኘኋቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ የመስበክ ሰፋፊ ዕድሎች፥ በየሳምንቱና ብዙ ጊዜ በትላልቅ ጉባኤዎች ላይ ከሚሰብኩ አያሌ መጋቢያን ጋር አገናኘኝ። እነዚህ ሰባኪያን ጥቂት መደበኛ የአሰባበክ ሥልጠና ያገኙ

ወይም ምንም የሥልጠና ዕድል ያልገጠማቸው ቢሆኑም፥ የስብከት ስጦታ አላቸው ተብለው ለአገልግሎቱ የተሾሙ ናቸው። የስብከት አዘገጃጀት ዘዴዎችን ለነሱ የማደርስበት ሁኔታ ነበርን? በቀላሉ የቀረበ፥ በሁሉም ባሕል ሊሠራ የሚችል፥ ለየትኛውም ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሥነ-ጽሑፍ ዓይነት የሚሆን የስብከት አዘገጃጀት ዘዴ አለ?

የዳላሱ ሴሚናሪ ሌላ ዕድል ሰጥቶኛል። የስብከት አዘገጃጀት ጥበብን ወደ ማስተማሩ የሚያደላ ተቋም እንደ መሆኑ፥ ለመጋቢነት በሚዘጋጁ ሰዎችና የሚነሡ ሰባኪዎች እንዲሁም የሚተገበሩ ጉዳዮችን እንዳከማችና እንዳጠናቸው አድርጎኛል። ዓለም አቀፍ የራሚሽ ሪቻርድ የወንጌልና የቤተ ክርስቲያን እርዳታ ድርጅት መጋቢያንን፥ ሰባኪያንንና የኢኮኖሚ አቅም በሌላቸው የዓለም አካባቢዎች የሚገኙ የስብከት ማሠልጠኛ ተቋማትን ይረዳል፤ የማጥኛና የመገልገያ ቁሳቁሶችንም ያቀርባል።

በዚህ ድርጅታዊ ተምሳሌት በሆነ መድረክ ተጠቅሜ፥ አስፈላጊነቱ ከፍተኛ በሆነባቸው አገሮች ውስጥ ለሚገኙ መጋቢያንና የአቢያተክርስቲያን መሪዎች ያገለግል ዘንድ ይህን ባለ ሰባት ደረጃ የሆነ መልእክት የማቅረቢያ ዘዴ አዘጋጀሁ። ዝግጅቱ፥ በመቶ ከሚቆጠሩ የሴሚናሪ ተማሪዎችና፥ በዓለም ዙሪያ በሺህ የሚቆጠሩ መጋቢያን በተካፈሉባቸው የስብከት አቀነጃጀት ዘዴ ሴሚናሮች ላይ ከተከሠቱ ስሕተቶች ያጠናቀርኩት ስለሆነ፥ ለስብከት የሚመረጥን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልን፥ እንዲሁም አሰባበኩን በተመለከተ ሊወገዱ የሚገባቸውን ነገሮች ለይቼ አውቂያቸዋለሁ! ሰብአዊ ጉድለቶችንና የተማሪ ችግሮችን ወደተቃና አቀራረብ ለውጫቸዋለሁ የሚል ተስፋ አለኝ። የተለያየ ባሕል ያላቸው ሰባኪያን ይህ ዝግጅት ለየሳምንቱ የስብከት አገልግሎታቸው የሚጠቅም ሆኖ ያገኙት መሆኑን ስለገለጡልኝ ደስ ብሎኛል።

ሌላው የሚያረካ ነገር፥ ይህ ዘዴ፥ የሦስቱን ዓመት የስብከት አዘገጃጀት ሥራ በጥሩ ሁኔታ ያሰባሰበና ያሳጠረ መሆኑን የሴሚናሩ የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች መግለጣቸው ነው። ይህ የስብከት ዝግጅት መመሪያ፥ ልምዱ ላላቸው ሰባኪያን የቀረበ ባይሆንም እንኳን፥ የሚጠቅማቸው ሆኖ እንደሚያገኙት አምናለሁ።

ሥራው በሦስት ተከፍሎ ነው የቀረበው። መግቢያው ስለገላጭ ስብከት ማብራሪያና አዘገጃጀት አጠቃላይ ሁኔታ ይገልጣል። የስብከት አቀነጃጀቱ በሰባት ደረጃዎች ተመድቧል። ደረጃዎቹ በገላጭ ስብከት አዘገጃጀት ወቅት እንደ መመሪያ ያገለግላሉ። ምዕራፎቹ እርስዎ የሚሠሯቸው “የድርጊት እርምጃዎችም” አሏቸው። የቀረበውን ዘዴ

# የዝግጅት ማንሣሻ፥ ገለጣ እና አጠቃላይ እይታ።

ናይጀሪያ ውስጥ ከዋራ በተባለው ክፍለ አገር፥ አንድ ሆቴል በር ላይ፥ በሚገኝ አንድ መደብር ውስጥ አስደናቂ ቅርፃ ቅርፆችን የሚሸጥ ዳንኤል የሚባል ሰው አለ። ደህና ጥቁር እንጨት ይመርጥና በሞያው አስጊጦ፥ እሱ እንደሚለው ወደ "ዘላለማዊ ውበት (ለአንዳንዶች ደስታ)" ይለውጠዋል።

ዳንኤል ከእንጨት ቁራጭ ቅርፃ ቅርፆችን ሲሠራ ለማየት ዕድል አግኝቻለሁ። በእጁ የያዛቸው ቁርጥራጭ እንጨቶች ወደ መልካም ነገር የመለወጥ ተስፋ ነበራቸው። ቅርፃ ቅርፆችን ከእንጨት መሥራት፥ ሥነ-ጥበብም ሳይንስም ነው። የቅርፃ ቅርፅ ሥራ ሳይንሳዊ ጎኑን ጥሩ የሞያው ባለቤቶች ሁሉ ይጋሩታል። ሥነ-ጥበባዊ ጎኑ ግን፥ እውነተኛና ጥሩ ሥራ መፍጠርን ይጠይቃል። እያንዳንዱ የዳንኤል ቅርፃ ቅርፅ ሥራ፥ የሥነ-ጥበባዊ ስጦታው፥ የትምህርቱና የሥራ ትጋቱ ድንቅ አሻራ ነበር።

ውይይት ጀመርንና፥ ብልህ በሆነ አነጋገር እንዲህ በማለት ስለ ዝግጅቱ ገለጠልኝ፤ "ዛፉን እግዚአብሔር ፈጠረው፤ ቅርፃ ቅርፆቹን ደግሞ፥ እግዚአብሔር ከፈጠረው ዛፍ ዳንኤል ሠራቸው።"

እርሱ በተናገረው ጥልቅ አሳብ ውስጥ፥ ከገላጭ ስብከት ዝግጅትና አቀራረብ ሂደት ጋር የሚመሳሰሉ ብዙ ሁኔታዎች አገኘሁ። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ሲሆን፥ ስብከቶች ደግሞ እኛ ከእግዚአብሔር ቃል የምናዘጋጃቸው ናቸው። ብዙ ሰዎች የገላጭ ስብከት አዘገጃጀት ዘዴን ይጠቀማሉ። ጥሩ ሰባኪዎች ደግሞ ጥናትንና አቀራረብን በተመለከተ ተመሳሳይ አሠራር አላቸው። እንደ ሥነ-ጥበብነቱ ግን፥ ስብከት የሰባኪው የራሱ ብቻ ነው። የሰባኪው ስጦታ፥ የተማረው ትምህርትና ትጋቱ ሥራውን የግል ያደርጉታል።

> መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ስብከቶች ደግሞ እኛ ከእግዚአብሔር ቃል የምናዘጋጃቸው ናቸው።

እውነት ነው፥ ከእንጨት በተሠራው ቅርፅና በርስዎ ስብከት መካከል ልዩነት አለ- ሕይወት እራሷ! ሕይወት ያለው ዛፍ፥ ግዑዝ ወደ ሆነ ትንሽ ውብ ነገር ተለውጧል። የእርስዎ ስብከት በሕያው እግዚአብሔር ተቆጣጣሪነት፥ ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል፥ በአድማጮች ውስጥ ሕይወትን ወደሚያቀርብና ወደሚፈጥር ስብከት ይለውጠዋል። ስብከትዎ ውበት ካለውና ደስታ ከሚሰጥ ነገር ይበልጣል፤ የዘላለማዊ ሕይወት ጉዳይ ነውና።

## የገላጭ ስብከት አስፈላጊነት

አለመታደል ሆነና አንዳንድ ሰባኪዎች፥ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ያዘጋጀው ቃል መሆኑን አያምኑም። የመናገሪያ መድረኮችን የሚይዙና ያልተለወጡ ሰባኪዎች በምድራችን ሞልተዋል። የጌታን ቃልም ሆነ የቃሉን ጌታ አያምኑም። ከአንድ ጳጳስ ጋር በተከታታይ ደብዳቤ እንጻጻፋለን። ባልተለወጡ ሰባኪዎች የተከበበ ውድ የእግዚአብሔር ሰው ነው። ከወንጌላዊነት አቋሙ የተነሣ፥ ከአገልግሎቱ ሊያስወግዱት አስፈራሩት። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ያዘጋጀው መሆኑን ሰዎቹ አያምኑም።

ሌሎች ሰባኪዎች ደግሞ ስብከት ያለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊዘጋጅ ይችላል ብለው ያምናሉ። ስለሆነም የጊዜውን አባባልና ለመድረክ ስብከት ይጠቅማሉ የሚሏቸውን ዜናዎች ይከታተላሉ። እንዲህ ያሉ ስብከቶች ብዙ ጊዜ የሚደመጡት፥ ከስፖርት፥ ከሙዚቃ፥ ከፖለቲካ እና ባሕል የተወሰዱ መግለጫዎች በሚሰሙባቸው ምሁራዊ መድረኮች ሲሆን፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘታቸው በጣም ጥቂት ነው። በእስያ በምትገኝ ከተማ የሚኖር አንድ አስተዋይ አማኝ፥ የመጋቢው ስብከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት የሌለው መሆኑን ለመግለጥ በኀዘን እንዲህ አለ፥ "መጋቢዬ መጽሐፍ ቅዱስ ለአድማጮቹ በቂ የሆነና የረቀቀ አሳብ አለው ብሎ አያምንም፤ በጎችን አይመግብም ለቀጭኔዎች ግን ንግግር ያደርጋል"።

ስብከቶቻቸውን ማዘጋጀት ያለባቸው መሆኑን የማያምኑ ሰባኪዎችም አሉ። እንዲህ ያሉት ሰዎች ለመድረክ አገልግሎት ብዙም አይደክሙም። የስብከቱ መጀመሪያ ጊዜ ሲቃረብ መለኮት በድንገት በመልእክቱ ይሞላናል ብለው ይጠብቃሉ። የስብከት ዝግጅትን አስመልክቶ እንዲህ ያለውን ፍልስፍና የሚከተልና መጋቢ የሆነ አንድ ጓደኛዬ፥ መስበኪያ መድረኩ ላይ ቆሞ በመጨረሻው ደቂቃ ከሰማይ የሚመጣለትን ቃል ሲጠብቅ፥ አንድ አስደንጋጭ ነገር ገጥሞታል። ፍጹም ፀጥታ ሰፍኖ ነበር። ጓደኛዬ በመድረክ ላይ እያለ፥ ባሪያዎቹን በመለኮታዊ መልእክት እንደሚሞላ ቃል ከገባው እግዚአብሔር ጋር ሙግት ጀመረ። አሁንም ጸጥታ ሆነ። በመጨረሻም እጅግ ተስፋ ቆረጠና እንዲህ ሲል ተማጠነ፤ "እግዚአብሔር ሆይ! ስለዚህ ጠዋት ስብከት አንድ ነገር ንገረኝ" እግዚአብሔር ደግሞ እንዲህ አለው፥ "ልጄ ሆይ አልተዘጋጀህም!"

አንዳንድ ሰባኪዎችም ዋና አገልግሎታቸው የሆነውን የስብከት ሥራ ቸል በማለት ላይ ናቸው። የስብከት አገልግሎትን ገለል በማድረግ፥ የምክር አገልግሎትን፥ መሪነትን ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን አስቀድመዋል። የአገልግሎት ቅደም ተከተልን በተመለከተ፥ መጽሐፍ

ቅዱስን መስበክ ሁለተኛ ስፍራ የተሰጠው ሆኗል። የሰባኪዎች ዋነኛ ጉልበት የሚባክነው፥ በማኅበረሰቡ አስቸኳይ ጉዳዮች ላይ ነው።

አንድ ቀን ጠዋት ጓደኛዬ ከቤተ ክርስቲያን ሲመለስ አገኘሁትና፥ ሰባኪው በዕለቱ የሰበከው ስለምን መሆኑን ጠየቅሁት። የዚያ እሁድ ጠዋት ስብከት ርዕስ "ማንኛውም ክርስቲያን ሊናገራቸው የሚገባው ሦስት ቃላት" የሚል መሆኑን ነገረኝ። "ምን ነበሩ ቃላቱ?" አልኩት። " 'አመሰግናለሁ፥ እባክህ እና አዝናለሁ' የሚሉ ነበሩ" አለኝ።

አንድ ሰው እነዚህን ማኅበራዊ ሥነ-ሥርዓቶች መማሩ በጣም ትክክል ቢሆንም፥ እነርሱን ለመማር ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ አያስፈልገውም። በቦርድ ስብሰባዎች ላይ እንዲህ ያለ ሥርዓት ያለው ውይይት እንዲደረግ የማይፈልግ ሰባኪ የለም። በመደበኛው የሰንበት ማዕድ ላይ የሚቀርቡ ነገሮች እነዚህ ከሆኑ ግን፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ፥ መጋቢው እና ጉባዔው በመንፈሳዊ ርሃብ ይጠቃሉ።

ይህ መጽሐፍ፥ ከላይ የተዘረዘሩትን የመድረክ ስብከት ጉድለቶችን እንዲያስወግዱ ሊረዳዎ፤ እንዲሁም ገላጭ ስብከትን የሕይወትና የአገልግሎትዎ ዓላማ ለማድረግ ይጥሩ ዘንድ ሊጋብዝዎ የታቀደ ነው።

## የገላጭ ስብከት በጎ ተጽዕኖ

ገላጭ ስብከት በሕይወትዎ ላይ ልዩ በጎ ተጽዕኖ ሊያደርግና ቀጥሎ ባሉት ነገሮች ሊረዳዎ ይችላል።

- ሥርዓት ባለው ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት፥ በእውቀትና በታዛዥነት እንዲያድጉ
- ለእያንዳንዱ ሳምንት የሚሆን ስብከት ሲመርጡ፥ የሚያባክኑትን ጊዜና ጉልበት እንዲቆጥቡ
- በሚገባ በሚያውቋቸውና በሚመርጧቸው ርእሶች ብቻ ላይ ከማትኮር ይልቅ፥ ሰፊ ከሆነው የእግዚአብሔር ቃል እንዲሰብኩ

ገላጭ ስብከት ለጉባኤው መንፈሳዊ ሕይወትም ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ምክንያቱም እርስዎን በሚከተሉት መንገዶች ይረዳዎታልና።

- በዕለት ተዕለት አገልግሎትዎ ለቃሉ ታማኝ እንዲሆኑ፥ እንዲሁም ላሉበት ሁኔታ ወይም አካባቢ የሚጠቅም መልእክት እንዲያስተላልፉ
- ሕዝብዎ ሁልጊዜ ለእግዚአብሔርና ለአገልግሎቱ ታማኝ ይሆን ዘንድ ቃሉን የማስታጠቅና ብርቱ የማድረግ ዘዴን በሥራ ላይ እንዲያውሉ

♦ ስብከትዎን በተለየ ሰው ወይም ቡድን ላይ ያተኮረ እንዲሆን የማድረግ ዝንባሌዎን ለማስወገድና ከሚቀርብብዎም ወቀሳ እንዲድኑ

♦ በስብከትዎ ዕለት ካሉበት ስሜት ጋር ወይም ከምርጫዎ ጋር የማይሄዱ የሚመስሉዎትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በዝምታ እንዳያልፉ ወይም እንዳይዘሏቸው

♦ እንደ መጋቢነትዎም ያለቦትን ሰፊና የተለያየ የአገልግሎት ኃላፊነት በተገቢው መንገድ እንዲፈጽሙ

♦ በሚሰብኩበት ጊዜ የሚቆሙት በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ሥር ስለሆነ፥ ለመጋቢነት ሥራዎ ሞገስን በመስጠት

♦ የሳምንቱን የስብከት መልእክት አስመልክቶ በቤተ ክርስቲያኒቱ ዙሪያ ያለው ውይይት እንዲጣጣም በማድረግ

♦ በሰብአዊዎቹ መሪዎች ዓይን የታየውንና እግዚአብሔር ለጉባኤዎ ያለውን ዓላማ በመግለጥ

♦ ሰዎችን በጋራ ራእይ ዙሪያ በማሰባሰብ፥ ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የሰው ጉልበት ይጠይቁ ዘንድ በመርዳት

♦ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ የተመሠረተውን የቤተ ክርስቲያን ዕቅድ በመተግበሩ ረገድ ሰውን ለሥራ በማነሣሣት

♦ ቤተ ክርስቲያኒቱን ወደ ለውጥ የመምራቱን አስፈላጊነት ወይም ተዓማኒነት በማዳበር

♦ ለጋራ መንፈሳዊነት የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን በማስገንዘብ

♦ ጉባኤዎ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት እንዲኖረው በመርዳት።

ባጠቃላይ፥ ገላጭ ስብከት፥ ሰባኪው እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን አጀንዳ ያሳውቅ ዘንድ ይረዳዋል።

ስብከት ማዘጋጀት እንግዲህ፥ ሥነ-ጥበብ፥ ሳይንስ፥ ሙያና ግንኙነት ነው። ውጤታማ ስብከት ከመንፈሳዊ ኃይልና ብርቱ ጥረት ይወለዳል። የስብከት ዝግጅት ኃይል የሚገኘው፥ ሰባኪው የጽሑፉ ባለቤት ከሆነው ጌታ ጋር ከሚኖረው ግንኙነት ነው። ሥራው በጸሎት የሚከናወን ብርቱ ልምምድ ሲሆን፥ ሰባኪው ከስብከት ክፍሉ ጋር ካለው ግንኙነት የተነሣ በመንፈስ ቅዱስ አስቻይነት ይከናወናል (ተቀጥላ 1 ይመልከቱ)።

ይሁን እንጂ፥ የዚህ መጽሐፍ ዓላማ፥ የስብከት ዝግጅት ዘዴዎችን፥ ማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ ስብከትን የማቀናጀት ጥበብን ወይም ሳይንስን ማስጨበጥ ነው።

## ማብራሪያ

የገላጭ ስብከት ትኩረት መጽሐፍ ቅዱስና የሚያገለግሉት ሕዝብ ነው። ገላጭ ስብከትን አስመልክቶ ብዙ መልካም ትርጉሞች አሉ። የእኔ ትርጉም ይህ ነው፥ የአንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማዕከላዊ አሳብ ትክክለኛ የአተረጓጎምን ሥርዓት ተከትሎ በማግኘትና ማዕከላዊ አሳቡን ከወቅቱ ጋር በማዛመድ ወይም በማገናዘብ (Contemporization) ውጤታማ በሆነ የአሳብ ግንኙነት (Communication) የአማኞችን የአእምሮ መረዳት ለማሳደግ፥ ልባቸውን ለማቅናትና፥ ባሕርያቸው እግዚአብሔርን ወደ መምሰል እንዲያድግ መርዳት ነው።

### *የገላጭ ስብከት "ምንነት"*

የገላጭ ስብከት ትርጉም "ምንነት" ጥያቄ መልስ፥ ከይዘት ጋር ይዛመዳል። የገላጭ ስብከትን ትርጉም መሠረታዊ ይዘት ለመረዳት ይቻለን ዘንድ፥ ወደ ትርጉሙ ተመልሰን እንመልከት። ገላጭ ስብከት የመጽሐፍ ቅዱሳዊውን የስብከት ክፍል ማዕከላዊ አሳብ ካለንበት ጊዜ ጋር ያገናዝባል። ይህም ማዕከላዊ አሳብ ትክክለኛ የአተረጓጎም ሥርዓትን በመከተል የሚገኝ ነው። አሳቡም የሚተላለፈው አጥጋቢ በሆነ የአሳብ የግንኙነት መንገድ የአድማጮችን አእምሮ መረዳት ለማሳደግ፥ ልባቸውንም ለማቅናት፥ ባሕርያቸውም እግዚአብሔርን እየመሰለ እንዲሄድ ለማድረግ ነው።

## ከጊዜው ጋር ማገናዘብ

አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከወቅቱ ጋር ማገናዘብ፥ የገላጭ ስብከት አቅራቢው ዋና ሥራ ነው። ከዘመናት በፊት የተጻፉትን እነዚህን ክፍሎች ይወስድና፥ ለአሁኑ ዘመን አንባቢያን ወይም አድማጮች በሚሆን መንገድ ያቀርባቸዋል። በዚህ ድርጊቱ የመጽሐፍ ቅዱስን ደረጃ ከፍ ያደርገዋል ማለት አይደለም። የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ለሰው ልጆች ጉዳዮች ሁሉ አግባብነት አለው። ሰባኪው የሚያደርገው፥ እግዚአብሔር የሚገልጥለትን ነገር መልእክቱን ለሚያቀርብለት ጉባኤ ግልጥ በሆነ መልኩ ማቅረብ ነው። ገላጭ ስብከት እግዚአብሔር ከጉባኤው ወይም ከአድማጭ በጊዜው የሚፈልገው ምላሽ ምን ምን መሆኑን ያስገነዝባል።

ሰባኪው ከሁለት እውነታዎች ማለት፥ ከጥንታዊው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽሑፍ እና፥ አሁን እርሱ ካለበት ዘመን ሁኔታ ጋር ይጋፈጣል። አንዳንድ ሰባኪዎች የክፍሉን አሳብ ያጎሉና ካሉበት ዘመን ሁኔታ ጋር ሳያዛምዱ ይተዉታል። ሌሎቹ ደግሞ፥ ያሉበትን ዘመን ሁኔታ ያጎሉና ለመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ (ለጽሑፉ) ታማኝ ሳይሆኑ ይቀራሉ።

መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጠናና የሚተረጉም ሰው፥ የሚያጠናው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በተጻፈበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር በዚያ ጽሑፍ ያስተላለፈውን መልእክት ለማግኘት ይጥራል። አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰባኪ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ ያለውን መልእክት በሚገባ በመረዳት በዚህ ዘመን ለእኛ ያለውን ጠቀሜታ በማገናዘብ ስብከቱን ያቀርባል። ጥንታዊው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚሰጠውን እውነትም ሆነ፥ የአሁኑን ዘመን ሁኔታ ችላ ሊልና ሊለውጥ አይችልም።

የሚቀጥለው ምሳሌ፥ የእግዚአብሔር ቃልን መልእክት ከጊዜ ሁኔታ ጋር እንዴት እንደምናዛምድ ይገልጣል።

| | | |
|---|---|---|
| ቃል<br>መጽሐፍ ቅዱስ<br>የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል<br>ፍች/ትርጉም<br>“ጌታ እንዲህ ይላል” | ማዛመድ | ዓለም<br>ባሕል<br>አንባቢ/አድማጭ<br>ጠቀሜታ<br>“ያ ሰው አንተ ነህ” |

## የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ክፍል ማዕከላዊ አሳብ

በገላጭ ስብከት ታሪክ (እና በግንኙነት ፅንሰ-አሳብ)፥ ብዙዎቹ ጸሐፍት ወይም የስብከት ጥበብ አዋቂዎች፥ አንድ ስብከት በአንድ ዋና አሳብ መጠቃለል አለበት በሚለው ውሳኔ ያምናሉ። ሰባኪው ይህን አንድ አሳብ ከየትና እንዴት ያገኘዋል? የሚለውን ጥያቄ በመመለሱ ረገድ ግን ልዩነቶች አሉ።

በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት የስብከቱን ዋና ማዕከላዊ አሳብ ለማግኘት ሁለት ምንጮች አሉ። የመጀመሪያው ሰባኪው ራሱ ሲሆን ሁለተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ ነው። በርእሳዊ ስብከት ጊዜ ሰባኪው የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ይመርጣል። መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ በተመሠረተ ስብከት፥ ማዕከላዊ አሳቡ የሚገኘው ከክፍሉ ነው። ቀጥሎ ያለው ሰንጠረዥ የርእሳዊ ስብከትንና፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ የተመሠረተን ስብከት (ክፍለ ምንባባዊ) ገለጣ በጎና ደካማ ጎናቸውን በማነጻጸር ያሳያል።

## *የመጽሐፍ ቅዱስ ገለጣ ዓይነቶች*

| ጉዳዩ | ርእሳዊ የገለጣ ስብከት | ክፍለ ምንባባዊ የገለጣ ስብከት |
|---|---|---|
| ዘገባ | - የስብከቱን ዋና አሳብ የሚመርጠውና የስብከቱን አካሄድ የሚመራው ሰባኪው ነው። | - የስብከቱን ዋና አሳብ፥ የስብከቱን ዓላማ፥ በስብከቱ ውስጥ የሚካተቱትን አሳቦችና ዝግጅቱን የሚመራው የስብከት ክፍሉ ነው። |
| ጥንካሬ | - ጠቃሚነቱ ወዲያው ይታወቃል።<br>- ለማዘጋጀት ቀላል ነው። | - የረጅም ጊዜ ጠቀሜታ።<br>- የሰባኪውን በትጋት ማጥናት ይጠይቃል የሚቀጥለው የስብከት ክፍል ዛሬ ከተሰበከው የሚለጥቅ |
| ደካማ ጎን | - ሰባኪው ጽሑፉን እንደፈለገው ያደርገዋል።<br>- ለእያንዳንዱ ስብከት አርእስት በመምረጥ ጉልበትና ጊዜ ይባክናል ። | - ሰባኪውን የሚመራው ክፍሉ ነው።<br>- ሰባኪው ትጋት እንዲኖረው ይጠይቃል።<br>- ሰባኪው በማይጠቅሙ የትርጉም ሁኔታዎች ይያዝ ይሆናል። |

..................................

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገለጣ ያብራራል፥ ይገልጣል፤ መጽሐፍ ቅዱስን ለአንባቢው፥ አንባቢውን ደግሞ ለመጽሐፍ ቅዱስ ያቀርባል፥ ያገናኛል። ክፍለ ምንባባዊ ገለጣ፥ የመጽሐፍ ቅዱሳዊውን ክፍል ፍችና ለአሁኑ ዘመን ያለውን አገባብ ወይም ጠቀሜታ ያብራራል። ስብከቱን በአንድነት የሚያያይዘውን ዋና አሳብ ይገልጣል። እንዲሁም በሰባኪው ዘመን ወይም ጊዜ ያለውን አድማጭ በአንድ በተለየ ጊዜ ውስጥ ከተጠቀሰ የእግዚአብሔር ቃል እውነት ጋር ያገናኘዋል።

## የክፍለ ምንባባዊ ይዘትን አስመልክቶ ሊነሡ የሚገቡ ሦስት ጥያቄዎች

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉን ምንባብ ትርጉም በሚገባ አብራርቼዋለሁ?

2. የክፍለ ምንባቡን ማዕከላዊ መልእክት (አሳብ) በግልጥና ለጊዜው በሚሆን መልኩ ገልጬዋለሁ?

3. ለአንባቢዎች ወይም ለአድማጮች የእግዚአብሔርን እውነትና ከእነርሱ የሚፈልገው ምን እንደሆነ በሚገባ እንዲረዱና እንዲታዘዙ በሚገባ ግልጬላቸዋለሁ?

*የገላጭ ስብከት "እንዴትነት"*

የገላጭ ስብከት "እንዴትነት" ከስብከት አዘገጃጀት ጋር ይዛመዳል። የገላጭ ስብከት ትርጉምን (ፍቺን) ከስብከት አዘገጃጀትና አቀራረብ ጋር በማዛመድ እስቲ እንመልከተው። የአንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማዕከላዊ አሳብ ትክክለኛ የአተረጓጎም ሥርዓት ተከትሎ በማግኘትና ማዕከላዊ አሳቡን ከወቅቱ ጋር በማዛመድ /በማገናዘብ (Contemporization) ውጤታማ በሆነ የአሳብ ግንኙነት (Communication) የአማኞችን የአእምሮ መረዳት ለማሳደግ፥ ልባቸውን ለማቅናትና፥ ባሕርያቸው እግዚአብሔርን ወደ መምሰል እንዲያድግ መርዳት ነው።

**መተርጎም**

የትክክለኛው አተረጓጎም ዋና መመዘኛ፥ የመጽሐፉ ጸሐፊና የመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ስለ ጽሑፉ የነበራቸው መረዳት፥ እኛ ከምንሰጠው ትርጉም ጋር ያለው ቀጥተኛ ግንኙነት ነው።

የስብከት ዝግጅት ደረጃ 1 ይህን አሠራር በበለጠ ዝርዝር ያስረዳል።

መጽሐፍ ቅዱስ ማንኛውንም እኛ እንዲልልን የምንፈልገውን ነገር እንዲል ማድረግ እንችላለን። ዋናው ጥያቄ ግን፦ "መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ነው እኛ የምንለው?" የሚለው ነው። ለምሳሌ፥ ሉቃስ 19፡29-40 ላይ የተመሠረተና ቀጥሎ ያሉትን እውነቶች የሚያቀርብ አንድ ጥሩ ስብከት ሰምቻለሁ።

**ኢየሱስና አህያይቱ**

I. እንደ አህያይቱ ነዎት (ቁጥር 29-30)

ሀ. የጌታዎ ሳይሆኑ የሌላ ሰው ንብረት ሆነዋል (ቁጥር 30)

ለ. ማንም ያልተቀመጠብዎ፥ ገና ውርንጭላ ነዎት (ቁጥር 30)

II. ነጻ እንዲወጡ ኢየሱስ ያዝዎታል (ቁጥር 30)

ሀ. በደቀ መዛሙርቱ በኩል ነጻ ያወጣዎታል (ቁጥር 31-32)

ለ. ክርስቶስን ለማገልገል ነጻ ሲወጡ ተቃውሞ ይገጥምዎታል (ቁ. 33)

መ. እሱ ግን ይፈልግዎታል (ቁጥር 34)

III. የክርስቶስ አህያ ነዎት? (ቁጥር 35-40)

ሀ. ይጋልብዎታል?

ለ. እንዲመሰገን በማድረግ ላይ ነዎት?

ይህ መልእክት ሊሰበክ ይችላል? ተሰብኳል! ለጽሑፉ ወይም ለቃሉ ታማኝ ነው? አይደለም! ለምን? እስቲ እነዚህን ወሳኝ ጥያቄዎች ይጠይቁ። የጽሑፉ ደራሲ ሊያስተላልፍ የፈለጋቸው ነጥቦች እነዚህ ናቸው? የመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ከትረካው የተረዱት ይህን ነበር?

ይህን ዓይነቱ ስብከት "ግብረ ገባዊ" ስብከት ነው። ግብረ ገባዊ ስብከትን አስመልክቶ ከሚገጥሙ ችግሮች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው።

*እንዲህ ያለውን ግብረ ገባዊ ትምህርት ለማቅረብ መጽሐፍ ቅዱስ አያስፈልግዎትም።* ለሰዎች የሚቀርብ ማንኛውም ታሪክ ግብረ ገባዊ ፋይዳ ሊኖረው ይችላል። ባሕል ሁሉ፥ የሕዝቡን የአኗኗር ሥርዓትና፥ ባሕርይ የሚመራበት ምሳሌዎች፥ እንዲሁም ተረቶችና አፈ-ታሪኮች አሉት። መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ትረካ ከባሕላዊው ትረካ የሚለየው፥ መንፈስ ቅዱስ በሰብአዊው ደራሲ አማካይነት ለመጀመሪያዎቹ ተደራሲያን በገለጠውና እነሱም በተረዱት ዓላማ ነው። ግብረ ገባዊ ስብከት፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መልእክት ጥሩ ታሪክ ብቻ በማድረግ ዝቅ ያደርገዋል።

*ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፥ የከፍተኛ ግብረ ገባዊ ደንብ መግለጫ ይሆናል።* በዚህ ሁኔታ ክፍሉ የመልእክቱ ዋና አሳብ ምንጭ መሆኑ ይቀርና፥ ለማብራራት የምንጠቀምበት ምሳሌ ይሆናል። "በውርንጭላይቱ" ታሪክ፥ ሰባኪው ውርንጭላይቱን ሊጠቀምባት የፈለገው፥ ለሰዎች መግለጫ ወይም ምሳሌነት ነው።

*በዚህ ዘዴ ከተገለገሉ፥ ስብከትዎ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥልጣን አይኖረውም።* በውርንጭላይቱ ታሪክ፥ ሰባኪው አህያን ከሰው ጋር የማስተካከልን ሥልጣን ያገኘው ከየት ነው? በሌላ ምሳሌ ደግሞ፥ ዳዊትና ጎልያድን አንሥቶ መልእክት የሚያቀርብ ሰባኪ፥ ክርስቲያኖች ግዙፍ ችግሮችን መግጠም ወይም መጋፈጥ አለባቸው ይል ይሆናል። ጎልያድ ዳግመኛ የማይነሣ ስለሆነ ይህን የሚያደርግ ሰባኪ፥ ምሳሌው ውድቅ ይሆንበታል። ከሕይወት እውነት እንደምንረዳው፥ ግዙፍ ችግሮች ተደጋጋሚ የትንሣኤ ኃይል አላቸው! በመሆኑም፥ ምሳሌው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥልጣን አይኖረውም። መጽሐፍ ቅዱሳዊው ደራሲ ጽሑፉ ለዚህ ዓይነቱ አሠራር እንዲያገለግል ዐቅዶ የጻፈው መሆኑን ስብከቱ ካላሳየ፥ ሥልጣን አይኖረውም።

*እንዲህ ያለው አተረጓጎም ተጨባጭ መመሪያ የለውም።* ማንኛውም ሰባኪ ከአንድ ክፍል ውስጥ የቱንም ያህል ምሳሌ ሊያወጣ ይችላል። የስብከቱን ዋና አሳቦች የሚቆጣጠርበት ምንም ሁኔታ የለም። ስብከቱ ውስጥ የሚያነሣቸው ነጥቦች ከአምስት ይልቅ ለምን ሦስት ሆኑ? ወይም ሰባት በመሆን ፋንታ ለምን ሁለት ብቻ ሆኑ? ለሚሉት ጥያቄዎች

መልስ አይገኝም!!

*የሰባከትዎ ማዕከላዊ አሳብ ጥርት ባለ ሁኔታ ከክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ ጋር አልተዛመደም፥ ወይም ከዚያ የወጣ አይደለም።* በዚህ አሠራር የሰባኪው አተረጓጎም (የመልእክቱም ጉልበት) በዘፈቀደ የሚሠራ ይሆናል። ሕዝቡም የሰባኪውን መልእክት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልን በዘፈቀደ መንገድ በመጠቀም የቀረበ አድርጎ ይቆጥረዋል።

ትክክለኛ የአተረጓጎም ሥርዓት የስብከቱ የጀርባ አጥንት መሆን አለበት። ሰባኪው የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ገላጭ ከመሆኑ በፊት፥ የቃሉ ተርጓሚ ወይም ፈቺ ሊሆን ይገባል።

## ግንኙነት

ትክክለኛ አተረጓጎም (የትርጉም መንገድ)፥ከጽሑፉ ደራሲና መጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ስለ ክፍሉ (ጽሑፉ) ካላቸው ግንዛቤ ጋር የሚዛመድ እንደመሆኑ፥ እንዲሁ በሰባኪውና በአድማጮቹ ስለ መልእክት ክፍሉ ባላቸው መረዳት መካከል ካለው ግንኙነት ጋር ይዛመዳል።

ለምሳሌ፥ አንድ ጊዜ፥ እኔና ጓደኛዬ ዕቅድን አስመልክቶ ሩቅ ምሥራቅ አገሮች ላሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንድ ሴሚናር አዘጋጀን። በመጀመሪያው የስብሰባ ክፍለ-ጊዜ ጓደኛዬ፥ ማቀድ ያለብን ለምንድነው? በሚል ርእስ አስተማረ። የመጀመሪያ ዋና ትኩረቱ፥ እግዚአብሔር ስለሚያቅድ፥ እኛም ማቀድ አለብን የሚል ነበር። እግዚአብሔር፥ ሥርዓተ- ፍጥረትን፥ ሥርየትንና መንግሥቱን ዐቀደ። ስለዚህ እኛም ማቀድ አለብን።

*የዚህ ዓይነቱ አቀራረብ ችግር፥ ተሰብሳቢዎቹ ወይም አድማጮቹ ስለ እውነት ያላቸውን መረዳት ከግንዛቤ አለማስገባቱ ነበር። በዚህ ሳቢያ አመለካከታቸው፥ አስተሳሰባቸው ፋይዳቸውና እምነታቸው ሁሉ የጓደኛዬን ትምህርት በተመለከተ ያላቸውን ግንዛቤ አቃወሱት። እናም ስለ መለኮታዊው ዕቅድ ከተማሩ በኋላ የደረሱበት ማጠቃለያ፥ የጓደኛዬ አሳብ ተቃራኒ ነበር። እግዚአብሔር የሚያቅድ ከሆነ፥ እኛ ማቀድ የለብንም ከሚል ድምዳሜ ላይ ደረሱ።*

*መልእክታችን ውጤታማ ይሆን ዘንድ፥ የአንባቢዎቻችንን ወይም የአድማጮቻችንን አመለካከት፥ አስተሳሰብና ባሕል መገንዘብ አለብን። ከዚያም ማመሳሰልን፥ ምሳሌዎችን፥ ተገቢውን የማስተላለፊያ ዘዴ እና አግባብነት፥ በተግባር የሚውሉበትን መንገድ ተጠቀምን ታዛገች እንዲሆኑ እናደርጋቸዋለን።*

*የገላጭ ስብከት "ለምንነት?"*

የገላጭ ስብከት "ለምንነት" ከዓላማ ጋር ይዛመዳል። አንድን ገላጭ ስብከት የማዘጋጀትዎና የመስበክዎ ዓላማ ምንድነው? የአንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማዕከላዊ አሳብ ትክክለኛ የአተረጓጎም ሥርዓት ተከትሎ በማግኘትና ማዕከላዊ አሳቡን ከወቅቱ ጋር በማዛመድ /በማገናዘብ (Contemporization) ውጤታማ በሆነ የአሳብ ግንኙነት (Communication) የአማኞችን የአእምሮ መረዳት ለማሳደግ፥ ልባቸውን ለማቅናትና፥ ባሕርያቸው እግዚአብሔርን ወደ መምሰል እንዲያድግ መርዳት ነው። በአእምሮ መረዳት፥ በስሜቶችና፥ ተግባራዊ በሆኑ የክርስትና ልምምዶች ላይ በዋናነት ያተኩራል።

**አእምሮን መመገብ**

አድማጮቻችን ስብከቱን ካደመጡ፥ የእግዚአብሔርን እውነት ማወቅና መረዳት አለባቸው። ብዙ ጊዜ ይህ እውቀት ከስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ ጋር ይዛመዳል። በስብከታችን አማካይነት ሰዎች እግዚአብሔር የሚናገራቸውንና ከነሱ የሚጠብቀውን ካልተረዱ፥ ስብከታችን አስፈላጊ አይደለም። ጌታ ኢየሱስ ስለ ታላቂቱ ትእዛዝ በገለጠ ጊዜ፥ እግዚአብሔርን በፍጹም አሳባችን መውደድ ያለብን መሆኑን አክሎ ተናግሯል (ማቴ. 22፥32-36)።

**ልብን ማቅናት**

የሰዎች ውሳኔዎች ሁሉ በአእምሮ በማገናዘብ የሚወሰኑ አይደሉም። በታላላቅ ውሳኔዎች ጊዜ፥ ስሜታዊ ሁኔታዎች ትልቅ ድርሻ አላቸው። ይሁን እንጂ፥ መስበክ ያለብን ስሜትን ለማነሣሣት ብቻ መሆን የለበትም። አእምሮ ሲረዳ፥ ልብም መገንዘብ አለበት። በገላጭ ስብከት አማካይነትም የስሜቶች ሁሉ ማረፊያ ስሆነው ልብ ለመናገር ይቻላል፤ አስፈላጊም ነው። ሰባኪው አድማጮቹን ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ የተነሣሣ ልብ እንዲኖራቸው ማድረግ አለበት። በስብከቱ የቀረበው ቃል አድማጮቻችን ልብ ከደረሰ፥ በዚህ ሳቢያ የሚፈጠሩት ስሜቶች ቀላል ወይም ሰው-ሰራሽ እንዳልሆኑ እርግጠኞች እንሆናለን። አድማጮቻችን በስብከታችን ሳቢያ፥ ለእግዚአብሔር እውነት በግል የመታዘዝ አስፈላጊነት ሊሰማቸውና ፈቃደኝነት ሊያድርባቸው ይገባል።

**በሰዎች ጠባይ ላይ ተጽዕኖ ማሳድሩ**

የጥሩ ስብከት ተግባራዊ መመዘኛ፥ በሕይወት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ለባሕርይ ለውጥ ነው የተሰጠን (2ኛ ጢሞ. 3፥16-17)። ሥራ እምነትን መከተል አለበት (የያዕቆብ መልእክትን

ይመልከቱ)። በስብከታችን ምክንያት አድማጮቻችን የሚያደርጉት ነገር ይኖራል፥ ይታዘዛሉ። እግዚአብሔርን መምሰልም በሕይወታቸው ሊታይ ይገባል። እግዚአብሔር ምን እንደሚጠብቅባቸውና፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ውስጥ የተሰጡትን ትእዛዛት በምን ሁኔታ መታዘዝ እንዳለባቸው ማወቅ ይኖርባቸዋል። ስብከት፥ ሰዎች ለእግዚአብሔር እንዲገዙ፥ እንዲታዘዙትና እንዲወዱት የማድረግ ውጤት ሊኖረው ይገባል።

ኒው ዴልሂ (ሕንድ) ውስጥ ላሉትና ለማገለግላቸው ሰዎች እንዲህ በማለት ቃል ገባሁላቸው፥ “በእግዚአብሔር ቃል ዙሪያ ሆነን ቃሉን ከመማራችን የተነሣ፥ በተጨማሪ የምታውቁት ነገር፥ ተጨማሪ በስሜታችሁ የሚፈጠር ነገርና ተጨማሪ ልታደርጉ የሚገባችሁን ነገር ካልሰጠኋችሁ፥ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን መብራት ማጥፊያ ጊዜ ደርሷል ማለት ነው።”

## ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ ወደ ስብከት

የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልን ለስብከት በማቀናጀት ጊዜ ሊታሰቡ የሚገባቸው ሰባት ደረጃዎች ቀጥሎ ተዘርዝረዋል። እነዚህን ደረጃዎች በቃል ማስታወስ ይኖርብዎታል።

የመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ክፍል አቀነባበር ሰባት ደረጃዎች

| | |
|---|---|
| 7. ስብከቱን መስበክ | “በሥጋ” |
| 6. ስብከቱን ማቀናጀት | “በአጥንት” |
| 5. የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ | “ልብ” |
| 4. የዓላማ መሸጋገሪያ | “አንጎል” |
| 3. የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ | “ልብ” |
| 2. ክፍለ ምንባቡን ማቀናጀት | “አጥንት” |
| 1. ክፍለ ምንባቡን ማጥናት | “ሥጋ” |

በሰንጠረዡ፥ በስተቀኝ በእያንዳንዱ መልእክት ጊዜ ከሕያው የእግዚአብሔር ቃል ልናዘጋጅ የምንሞክራቸውን ክፍሎች ዘርዝሬአለሁ።

*1. ክፍለ ምንባቡ ያጥኑ።* ክፍሉን በዝርዝር በማጥናት፥ የክፍሉን “ሥጋ” እናገኛለን።

*2. ክፍለ ምንባቡን ማቀናጀት።* ክፍሉን ስናዋቅር፥ አጥንታዊ ግጥምጥሞሽ የመሰለ የጽሑፍ ክፍል ይኖረናል። ሥጋና አጥንቱ በአንድነት ስብከቱ የሚሠራባቸው ጥሬ ዕቃ ይሆናሉ።

*3. የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ ሐሳብ።* ከአጥንታዊ ግጥምጥሞሹ የክፍሉን ዋና አሳብ ለይተን እናወጣለን። ያም የክፍሉ ትርጉም “ልብ” ነው።

*4. የዓላማ መሸጋገሪያ።* በክፍሉ ልብ ውስጥ ለአድማጪችን የሚሆን የስብከቱን ዓላማ እናወጣለን። ይህ የስብከት ዓላማ፥ በመጨረሻ መልእክቱ የሚዘጋጅበትና የሚሰበክበት “አንጎል” ነው።

*5. የስብከቱ ማዕከላዊ ሐሳብ።* አንጎሉ የመልእክቱን ልብ አቅጣጫና ቅርፅ ይሰጣል።

*6. ስብከቱን ማቀናጀት።* መልእክቱ እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ የራሱን ቅርፅና ንድፍ ይይዛል። የመልእክቱ አጥንት ግጥምጥሞሽም ገሀድ ይሆናል።

*7. ስብከቱን መስበክ።* በመጨረሻ፥ የመልእክቱን ዝግጅት በማጠናቀቅ ላይ እያለን፥ ስብከቱ ለአድማጪችን ተስማሚ ሆኖ ይቀርብ ዘንድ፥ በሥጋው ላይ ጥቃቅን ማስተካከሎችን እናደርጋለን።

## ሰባቱን ደረጃዎች ሰሌዳ ላይ የማስቀመጫ ሌላ ዘዴ

### ከጽሑፍ ወደ ስብከት

| | | |
|---|---|---|
| 1. ምንባቡን ማጥናት<br>2. ምንባቡን ማቀናጀት<br>3. የምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ | 4. የዓላማ መሸጋገሪያ | 5. የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ<br>6. ስብከቱን ማቀናጀት<br>7. ስብከቱን መስበክ |

ይህን የመልእክት አዘገጃጀት ሥርዓት ካጠናቀቅሁ በኋላ፥ ሰባቱን ደረጃዎች የማስታወሻ ቀላል መንገድ አገኘሁ። ቅደም ተከተሉን ለማስታወስ ይረዳዎ ዘንድ ቀጥሎ ያሉትን ምክሮች አቀርብልዎታለሁ።

- ደረጃ 3 (በክፍለ ምንባቡ በኩል) እና ደረጃ 5 (በስብከቱ በኩል) ማዕከላዊውን አሳብ የሚመለከቱ ተጓዳኞች ናቸው።
- ደረጃ 2 (በክፍለ ምንባቡ በኩል) እና ደረጃ 6 (በስብከቱ በኩል)፥ ሁለቱም መዋቅሩን ወይም አጥንቱን ይመሠርታሉ።

- ደረጃ 1 (በክፍለ ምንባቡ በኩል) እና ደረጃ 7 (በስብከቱ በኩል)፥ ሥጋውን ወይም መሠረታዊ ክፍሎችን ማዘጋጀት ናቸው።
- ደረጃ 4 ከክፍለ ምንባቡ ወደ ስብከቱ ለመሸጋገር የሚረዳን ድልድይ ወይም አንጎል ነው።

ደረጃዎችን በቁጥር ወይም በፊደላት ማመልከት ቀላል የማስታወሻ ዘዴ ነው። 1234321 ወይም ሀለመሰመለሀ። እንዲህ ያለው ተጓዳኝነት በዕብራይስጥኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም አለ። የዚህ ስብከት አዘገጃጀት ዘዴ በውጪያዊ ሁኔታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር መመሳሰሉ፤ የመልእክቱን ዝግጅት ሥርዓት መንፈሳዊና ስሕተት አልባ አያደርገውም። ይሁን እንጂ፥ ዘዴው ፍጹምነት የሌለው ሰው፥ ሕይወት የሚቀሰቅስ ስብከትን እንዲያዘጋጅ ያስችለዋል።

ቀጥሎ የተዘረዘሩት፥ የእያንዳንዱ መልእክት አዘገጃጀት ደረጃዎች ማጠቃለያ ናቸው። እነዚህ ደረጃዎች ለመመሪያው ቀሪ ክፍሎች እንደ አጠቃላይ እይታም ያገለግሉዎታል።

### *ደረጃ 1፥ ክፍለ ምንባቡን ማጥናት- የስብከት ክፍሉ ሥጋ*

ደረጃ 1፥ ተማሪውን አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማጥኛ ከሆኑት መሠረታዊ አሠራሮች ጋር ያስተዋውቃል፥ የጽሑፉን ፍች ወይም ትርጉም ማግኛ የሆኑ ብዙ ቁልፎችን ይሰጣል። መጽሐፍ ቅዱስ ለሰዎች ሁሉ ለማስተላለፍ የሚፈልገውን፥ በትክክል "ማየት" እና "መፈለግን" በተመለከተ፥ ጠለቅ ላለና ለትክክለኛ ጥናት መሠረት ይጥላል።

### *ደረጃ 2፥ ክፍለ ምንባቡን ማቀናጀት*

በዚህ የስብከት ዝግጅት ዘዴ ስብከትን በማዘጋጀት ጊዜ ዋናው እርምጃ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ደራሲ ጽሑፉን ያቀናበረበትን ሁኔታ መገንዘብ ነው። በዚህ አሠራር፥ ደራሲው ያለውን ለመስበክ ብቻ ሳይሆን፥ አባባሉንም ለማጉላት እንችላለን። ደረጃ 2፥ እያንዳንዱ የምንባቡ ክፍል የሚያስተላልፈውን ትምህርት ጠቅለል ባለ መልክ ለማቅረብ ይችሉ ዘንድ፥ አከፋፈሉን የሚያገኙበትን ፍንጭ ይሰጥዎታል።

### *ደረጃ 3፥ የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ- የክፍሉ ልብ*

ልብ ለሰዎች ዋና አካል እንደሆነ ሁሉ፥ ማዕከላዊ አሳብም ለክፍለ ምንባቡ ዋና ነው (በኋላ ደግሞ ለስብከቱ)። ደረጃ 3 የክፍሉን ዋና አስተምህሮና አሳቡን ቀጥሎ ባሉት አርእስት መሠረት ያገኙ ዘንድ ይረዳዎታል።

ርእሰ ጉዳዩ፡- ስለምንድነው ደራሲው የሚናገረው? መልእክቱ፡- ስለሚናገረው ነገርስ ምንድነው የሚለው?

ምንባቡ ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ በአንድ ጭብጥ ዙሪያ ይሽረባል። ርእሰ ጉዳዩንና መልእክቱን በትክክል የተረዳ ሰባኪ፥ ስብከቱ ከእግዚአብሔር ቃል የወጣ ስለሆነ፥ በመለኮታዊ ሥልጣን ሥር ሆኖ በልበ ሙሉነት ይሰብከዋል።

*ደረጃ 4፡- የዓላማ መሸጋገሪያ*

የመልእክቱ አንጓል ገለጣዊ ስብከቱ ከአድማጮች ሕይወት ጋር የተገናኘ በማድረግ ረገድ ደረጃ 4 ዋነኛ ነገር ነው። ዓላማው የመልእክቱ አንጓል ነው፤ ክፍሉን ከመልእክቱ ጋር የሚያገናኝ ቁልፍ። ከአድማጭዎ ጋር በተዛመደ ሁኔታ የመልእክቱን ዓላማ በግልጥ መናገርን ይማራሉ።

*ደረጃ 5፡- የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ-የመልእክቱ ልብ*

ክፍሉ ነጠላ ርእሰ ጉዳይ እንዳለው ሁሉ፥ ስለ ስብከትዎም ነጠላ ርእሰ ጉዳይ ሊኖረው ይገባል። የመልእክትዎ ማዕከላዊ አሳብ መንትያዎች የሆኑትን "ርእሰ ጉዳይና መልእክትን" የሚያጎላ ይዘት ይኖረዋል። እዚህ ላይ ነው መጽሐፍ ቅዱሳዊው አሳብ (ደረጃ 3)፥ በዓላማው አማካይነት የሚተላለፈው (ደረጃ 4) እና፥ አድማጮች ይገነዘቡት፥ እንዲሁም ይታዘዙት ዘንድ ከሁኔታቸው ጋር የሚዛመደው።

*ደረጃ 6 ፡- ስብከቱን ማቀናጀት - የመልእክቱ አጥንት*

በዚህ ደረጃ፥ የስብከት ማዳበሪያ መሠረታዊ መንገዶች የሆኑትን ማለት አንድነትን፥ ቅደም ተከተልንና እድገትን ልብ ይላሉ። በቀላሉ መረዳትንና ወደ መታዘዝ የሚመሩ ስብከቶችን እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል የሚያሳዩ ምሳሌዎችም ይቀርባሉ።

*ደረጃ 7 ፡- ስብከቱን መስበክ-የመልእክቱ ሥጋ*

በምሳሌዎች፥ በተገቢ የቃላት አጠቃቀምና፥ በአካላዊ ሁኔታዎ አማካይነት ስብከትዎን ሊያጎለብቱ ይችላሉ። የራስዎንና የሌሎች ሰዎችን ስብከቶች ለመመዘኛነት ያገለግልዎ ዘንድ፥ ተቀጥላ 3 ውስጥ አጠቃላይ መጠይቅ ተካቷል። መልእክትዎን ከመስበክዎ በፊት፥ በተቻለዎ መጠን በጥሩ ሁኔታ በጽሑፍ እንዲያሰፍሩት እመክርዎታለሁ።

ቀጥሎ ባሉት ሁኔታዎች ላይ የሚገኙ ከሆኑ፥ በዚህ መመሪያ መሠረት ትክክለኛው ስፍራ ላይ ነዎት፡-

♦ ገላጭ ስብከትን ለመስበክ ዝግጁ ከሆኑ፤

♦ ለስብከትዎ የሚያገለግሉ ነገሮችን ከአንድ ክፍል የሚያወጡበትን ዘዴ ለመረዳት ከፈለጉ። ስብከትዎ ውስጥ የሚካተቱትን ነገሮች ከአንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚያወጡበትን ዘዴ ለመረዳት የሚፈልጉ ከሆነ።

# 1

# ክፍለ ምንባቡን ማጥናት

የጽሑፉ ላይኛ አካል (ሥጋ)

ደረጃ 7: ስብከቱን መስበክ

ደረጃ 6: ስብከቱን ማቀናጀት

ደረጃ 5: የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ

ደረጃ 4: የዓላማ መሸጋገሪያ ወይም ድልድይ

ደረጃ 3: የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ

ደረጃ 2: ክፍለ ምንባቡን ማቀናጀት

**ደረጃ 1: ክፍለ ምንባቡን ማጥናት**

መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ክፍለ ምንባብ ማጥናት የመልእክቱ ዝግጅት ሂደት የመጀመሪያ እርምጃ ነው። ብዙ ጊዜ ገለጣዊ ስብከት ላይ ባተኮረ የፑልፒት አገልግሎት፥ የስብከት ክፍል በመምረጥ ጉልበት እንዲሁም ጊዜ አይባክንም። ምክንያቱም፥ ባለፈው ከሰበኩት የመልእክት ክፍል ቀጥሎ ያለውን ክፍል ስለሚሰብኩ ነው። (ወቅታዊና ለጉባኤው የሚሆኑ መልእክቶችን ስለመምረጥ ሊታሰቡ የሚገባቸው ነገሮች በተቀጥላ 2 ውስጥ ተመልክተዋል።)

የአንድን ክፍለ ምንባብ ገላጭ ስብከት (Expository Preaching) በሚያዘጋጁበት ጊዜ፥ ምንባቡን ከሕይወትዎ ጋር በማገናዘብ በጥልቀት ማጥናት ይኖርብዎታል። ምንባቡን በጥልቀት የሚያጠኑበት ምክንያት፥ አእምሮዎን ጨምሮ እግዚአብሔርን በሁለንተናዎ ስለሚወዱት ነው። የምንባቡን መልእክት በመረዳት የሚያጠኑበት ምክንያት፥ በምንባቡ ውስጥ ለእርስዎና ለአድማጮች ያለውን የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመረዳት ነው። ምንባቡን ከሕይወትዎ ጋር በማገናዘብ ሲያጠኑ፥ እግዚአብሔር እራስዎን ሙሉ ለሙሉ ለእርሱ እንዲያስገዙና እንዲለውጡ የሚጠራዎ መሆኑን ይገነዘባሉ።

እንዲህ ያለው ጥናት ሁለት ገጽታዎች አሉት፦

ደረጃ 1

ክፍለ ምንባቡን ማጥናት
- የምንባቡን ዝርዝር አሳብ መመልከት
- ከዝርዝር አሳቦቹ ውስጥ ትርጉምን መፈለግ

*ምልከታ፡-* የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍለ ምንባቡ ጥናትዎ፥ በውስጡ የተካተቱትን ዝርዝር አሳቦች ሁሉ "ማየትን" ይመለከታል።

*መፈለግ፡-* በምንባቡ ጥናትዎ መሠረት የሚደርሱበት ማጠቃለያ በምንባቡ ውስጥ ስላሉት ዝርዝር ነገሮች የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎችና ለጥያቄዎቹ የሚያገኙዋቸው መልሶች ውጤት ነው።

## የክፍለ ምንባቡ ዝርዝር አሳቦች ማየት

አንድን ምንባብ ማየት ማለት፥ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱሳዊው ምንባብ ውስጥ ያለውን መልእክት መገንዘብ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ መሆኑን ስለምናምን፥ ምንባቡ ውስጥ ያሉ ዝርዝር አሳቦች ሁሉ ጠቃሚዎቹ ናቸው። ምንባቡ ውስጥ መመልከት የሚገባዎትን ሁሉ ደኅና አድርገው ይመልከቱ። ይህን ካደረጉ በኋላ፥ የማያስፈልጉዎትን አሳቦች በኋላ ሊተዉአቸው ይችላሉ።

ማስተዋል የሚኖርብዎ ምንድንነው? ቃላቱንና በቃላቱ መካከል ያለውን ተዛምዶ ነው መመልከት የሚኖርብዎ።

ዝርዝር ጉዳዮችን መመልከት
- ቃላት
- ተዛምዶዎች

*ቃላትን ያስተውሉ*

ጽሑፉ ውስጥ ያሉትን ቁልፍ ቃላት በማስታወሻ ይያዙ። ቃላት የክፍሉን ይዘት ከመወሰናቸውም በላይ የክፍሉንም ትርጉም የሚረዱት በእነርሱ ላይ በመመሥረት ነው። አንድ ጥቅስ ወስዶ በአንድ ገጽ ወረቀት ላይ ማጥናትን ጠቃሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። እርስዎም ጥቅሱን በሙሉ በገጹ መጀመሪያ ላይ ይጻፉና ቁልፍ በሆኑት ቃላት ሥር ያሥምሩባቸው። የሚያጠኑዋቸው ቁልፍ ቃላት፥ ረጃጅም፥ ያልተለመዱና የሚደጋገሙትን ነው።

አስተውሎት የሚሹ ቃላት

- *ረጃጅም ቃላት*
- *ያልተለመዱ ቃላት*
- *የሚደጋገሙ ቃላት*

## >> የድርጊት እርምጃ <<

*መጽሐፍ ቅዱስዎን ከፍተው መዝሙር 117ን ያውጡ። ከዚያም ቁጥር አንድ ላይ ያለውን ጥቅስ አንድ ገጽ ወረቀት ራስጌ ላይ ይጻፉና፥ ቁልፍ በሆኑ ቃላት ሥር ያሥምሩባቸው። ቁጥር ሁለት ላይ የሚገኘውን ጥቅስ በዚሁ አካኋን ሁለተኛ ገጽ ወረቀት ላይ ይጻፉት። ይህን ሲያደርጉ ምስጋና፥ ፍቅር፥ ቸርነት፥ እውነት፥ ዘላለማዊነት የተባሉትን ቃላት ያጠናሉ።*

---

### *ተዛምዶዎችን ያስተውሉ*

ሊያስተውሏቸው የሚገቡ አንዳንድ ተዛምዶዎች:-

- ሰዋሰዋዊ ተዛምዶዎች:- ጥቅሱ ውስጥ ቃላት እንዴት ተቀናጁ? መሠረታዊ አስተውሎቶች:- ጊዜን፥ (ኃላፊን፥ የአሁንንና የወደፊትን)፥ ቁጥርን፥ (ነጠላ፥ ብዙ)፥ ጾታ፥ (ተባዕታይ፥ አንስታይና ግዑዝ)
- አመክንዮአዊ ወይም ሎጂካል ተዛምዶዎች:- በክፍሉ ውስጥ አሳቦች እንዴት ተቀናጁ? ደራሲው አሳቡን አሳማኝ በሆነ ማስረጃ እንዴት አቀነባበረው?
- ቅደም ተከተላዊ ወይም መልክዓ-ምድራዊ ተዛምዶዎች።

  ክፍሉ ውስጥ የተገለጡት ጊዜያትና ስፍራዎች የትኞቹ ናቸው?
- ሥነ-ልቡናዊ ተዛምዶዎች:- በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስለ ክፍሉ የተገለጡ ሥነ-ልቦናዊ አሳቦች አሉ?
- ዐውደ ንባባዊ ተዛምዶዎች:- ክፍሉ በምን ዐውደ ንባብ ውስጥ ቀረበ? በክፍሉ አጠገብ ያለውን ዐውደ ንባብና ሰፋ ብሎ ያለውን ዐውደ ንባብ መመልከት ያስፈልጋል።

  - - የመጽሐፍ ቅዱስ ዐውደ ንባብ
  - - የሚያነቡት መጽሐፍ ዐውድ
  - - የክፍሉ ዐውደ ንባብ
- የሥነ-ጽሑፋዊ ዓይነት ተዛምዶ (Genre):- ይህ ተዛምዶ:- ክፍለ-ምንባቡ የሚገኝበትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሥነ-ጽሑፍ ዓይነት ይመለከታል። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ጥቂት የሥነ-ጽሑፍ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው።

  -- ትምህርታዊ:- ምሳሌ፥ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶች ወይም የጳውሎስ መልእክቶች:-

-- ተራኪ፡- የታሪካዊ ድርጊቶች ትረካ

-- ሥነ-ግጥማዊ (ቅኔያዊ)፡- መዝሙረ ዳዊት፥ መጽሐፈ ምሳሌ፥ መኃልየ መኃልይና ሌሎች።

-- ምሳሌዎች፡- በዋናነት የኢየሱስ ምሳሌዎች

-- ተአምራት፡- በዋናነት በሦስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ጊዜያት፥ ማለት በሙሴና በአሮን፥ በኤልያስና በኤልሳዕ፥ በጌታና በሐዋርያት ይገኛሉ።

-- ትንቢታዊ፡- የወደፊቱን ሁኔታ የሚተነብዩ ሲሆኑ፥ የዳንኤል ከፊል መጽሐፍ፥ ትንቢተ ሕዝቅኤል፥ የዮሐንስ ራእይ፥ እንዲሁም ዐበይትና ንዑሳን የብሉይ ኪዳን ነቢያት።

## ከምንባቡ ዝርዝር አሳብ ውስጥ ፍቺውን ወይም ትርጉሙን መፈለግ

ምልከታ የአንድ ምንባብ ዝርዝር አሳብን የሚመለከት ሲሆን፥ ፍለጋ ደግሞ፥ የዝርዝሮቹን ትርጉም ይመለከታል። አጠቃላይ አሳቡን የማንመለከት ከሆነ፥ ዝርዝሮቹን ማየቱ ጥቅም የለውም። (የክፍሉን ጭብጥ አሳብ መረዳት፥ የተመለከትናቸውን ነገሮች ከመተርጎም ጋር ይያያዛል። ስለዚህ ምልከታና ትርጉም ፍለጋ በአብዛኛው በአንድ ላይ ቢከናወኑ ይመረጣል። መተርጎም፥ በመሠረቱ ምልከታዎን የመጠየቅና ጥያቄዎቹን የመመለስ ሥራ ነው።

ከዝርዝር ጉዳዮች ትርጉምን መፈለግ ——
- ጥያቄዎችን ማቅረብ
- ጥያቄዎችን መመለስ
- መልሶችን መተንተን
- መልሶችን መተግበር

*ጥያቄዎችን ማቅረብ*

ጥያቄዎችን መጠየቅ አለብዎ። መጠየቅ፥ በማንኛውም የትምህርት ዘርፍ የግንዛቤ ወይም የግኝት ጥበብ ነው። በነባርና በአዳዲስ ተማሪዎች መካከል ያለው ግልጥ ልዩነት፥ ብዙ ጠቃሚ ጥያቄዎችን የማንሣት ችሎታ ጉዳይ ነው። ስለ ቃላቱ ይጠይቁ። አንድን ክፍል ለመረዳት ይጠቅማሉ ብለው ምልክት ባደረጉባቸው ቃላት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመገንዘብ ይጠይቁ።

| ዝርዝሮችን መመልከት | ትርጉምን መፈለግ |
|---|---|
| + ቃላት | + ለቃላት የሚቀርቡ ጥያቄዎች |
| + ተዛምዶዎች | + ለተዛምዶዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎች |

## ስለ ቃላት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ቃላቱ ዛሬ ያላቸውን ትርጉም ይጠይቁ። በእንግሊዝኛ ወይም በራስዎ ቋንቋ በተጻፈ መዝገበ ቃላት ውስጥ ይመልከቷቸው። ጥሩ መዝገበ ቃላት፥ በአሁኑ ጊዜ ያለውን ፍቺ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል በነበሩ ዘመናት የነበረውን ትርጉምም ያስረዳል። የብዙ ቃላት ትርጉም በዓመታት ውስጥ ተለዋውጧል። ቃላቱ በተጻፉበት ዘመን ትርጉማቸው ምን እንደ ነበር ለማወቅ ይጠይቁ። መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትና ዐውደ ጥበብ (Encyclopedia) ውስጥ ይፈልጓቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ደራሲው፥ እንዲሁም ሌሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ደራሲያን፥ በሌላ ስፍራ እንዴት ቃላቱን እንደተጠቀሙባቸው ለመረዳት ይጠይቁ።

ላነሷቸው ጥያቄዎች መልስ የሚያገኙባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ። ሕዳጋቸው ላይ መግለጫ ያላቸው መጽሐፍ ቅዱሶች፥ አንድ ቃል ሌላ ስፍራ የሚኖረውን ቁልፍ አጠቃቀም ሊያመለክቱዎት ይችላሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላትን ዝርዝር የያዘ መጽሐፍ (Concordance) ለዚህ ተግባር ግዙፍ ጠቀሜታ አለው። በሚያጠኑት ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ሐረጎችንና የተደጋገሙ ገለጣዎችን ለመረዳት፥ እነዚሁኑ ጥያቄዎች ማንሣት ይኖርብዎታል።

## ለተዛምዶዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎች

ማንኛውም ቋንቋ የራሱ የሆኑ ብዙ የተለዩ ሁኔታዎች አሉት። የቃላትን ትርጉም ከተረዱና የቋንቋውን ተለዋዋጭነት ለመገንዘብ ከቻሉ፥ ቋንቋዎች ሁሉ እምብዛም አያስቸግሩም። በቃላት መካከል ያለው ተዛምዶ፥ በአብዛኛው ጎኑ የሰዋስው ጉዳይ ነው። ሰዋስው፥ አንድ ዓረፍተ ነገር የሚገልጠውን፥ ከዛም ዓረፍተ ነገር ጋር ተዛማጅ የሆኑትን ሌሎች ዓረፍተ ነገሮች ባጠቃላይ የሚገልጡትን አሳብ ለይተን ለመገንዘብ ይረዳናል። በልጅነቴ የሰዋስውን ሕግጋት ሳላውቅ ነው በሰዋስው መጠቀም የተማርኩት። ሰዋስው በመኪናና በነጂው መካከል እንዳለ ግንኙነት ሆኖ አገኘሁት። እንዴት እንደሚሠራ እውቀቱ ሳይኖረኝ፥ መኪና እነዳለሁ። በመሆኑም መኪናው ሲበላሽ የማደርገው ነገር መቆም ብቻ ነው! ልክ እንዲሁ፥ እንግሊዝኛዬ ሲበላሽብኝ፥ እንዴት ማስተካከል እንደሚገባኝ

አላውቅም ነበር። በመጨረሻ ሰዋስውን በሚገባ ተረዳሁ። ሰዋስውን በአንድ ቋንቋ ቢረዱ፥ አንድን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ በሌላ ቋንቋም ለመተንተን ይረዳዎታል።

የአንድን ጥቅስ ዝርዝር በምንመለከትበት ጊዜ፥ ለተመሳሳይ ተዛምዶዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን እናነሣለን። እነሱም ሰዋስዋዊ፥ ምክንያታዊ፥ ቅደም ተከተላዊና ሌሎች ተዛምዶዎች ናቸው።

### ሰዋስዋዊ ተዛምዶዎች

የማቴዎስ 16፡18ን ዝርዝሮች ቢመለከቱ፥ ኢየሱስ ትንቢትን ወይም የወደፊት ጊዜን እንደተጠቀመ ይረዳሉ፥ "ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ" ማቴዎስ 28፡19 ውስጥ ደግሞ፥ የሥላሴን ሦስት አካላት ሲጠቅስ፥ ስም የሚለውን ቃል በነጠላ ቁጥር ነው የተጠቀመበት። በግሪክኛ የሚጠቀሙ ከሆኑ፥ ዮሐንስ 10፡30 ውስጥ "እኔና አብ አንድ ነን" በሚለው ዓረፍተ ነገር፥ "አንድ" የሚለው ቃል ግዑዝ ጾታን የሚያመለክት መሆኑን ይረዳሉ (አጽንኦት የእኔ)።

### አመክንዮአዊ (Logical) ተዛምዶዎች

አመክንዮአዊ ተዛምዶዎች፥ ደራሲው የሚያቀርበውን ጉዳይ፥ ትኩረቱን ወይም ለማስጨበጥ የሚፈልገውን አሳብ ለመገንዘብ ይረዱናል። ከመጽሐፍ ቅዱስ በተወሰዱትና ቀጥሎ በተገለጡት ማብራሪያዎች ውስጥ ያሠመርኩባቸውን ቃላት ወይም ፊደል ልብ ይበሉ። እንዲህ ያሉ ቃላት፥ በቃላት መካከል ያለውን ዝምድና ለመረዳት ይረዱናል። እነዚህን ቃላት እንደ ቁልፍ ቃላት አድርገን የምናጠናቸው አይደሉም። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ቃላት አጫጭር የሆኑና በዝርዝር አተረጓጎም ላይ ግን ትልቅ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ናቸው።

- መነሻና ውጤት፡-"እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እንወደዋለን"(1ኛ ዮሐ. 4፡19)።
- ምክንያት፡- "እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ" (ቆላ. 3፡1)
- ውጤት፡- ሐዋርያው ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን መንጋ በታማኝነት ስለሚጠብቁ እረኞች ሲናገር፡- "የእረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብር አክሊል ትቀበላላችሁ" (1ኛ ጴጥ. 5፡4) ብሏል። የታማኝ እረኝነት ውጤት፥ ዋናው እረኛ የሚያመጣው ሽልማት ነው።

ወይም አሁን የምንጽናናበት የመነጠቅ አስተምህሮ ጠቃሚነት የሚታነጸው "ስለዚህ" በሚለውና 1ኛ ተሰሎንቄ 4፡18 (ከ1ኛ ተሰ. 4፡13-18 ጋር ያነጻጽሩት) ውስጥ በተጠቀሰው ቃል መነሻ ወይም ውጤት ላይ ነው።

- ንጽጽር፡- ኤፌሶን ምዕራፍ 2 ስለ ቀድሞው መንፈሳዊ ሕልውናችን ይናገራል። (ቁጥር 1-3) "ነገር ግን እግዚአብሔር" (ቁጥር 4) የሚለው ሐረግ "ነገር ግን" ከሚለው ቃል ጋር ተያይዞ የአሁኑን መንፈሳዊ ሕልውናችንን ከቀድሞው ጋር ያነጻጽራል።
- ውድድር "በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና" (1ኛ ዮሐ. 4፡4) ለሰብአዊ ታማኝነት የሚፎካከሩ ሁለት ወገኖች ተወዳድረዋል።
- ቅድመ ሁኔታ፡- 2ኛ ዜና መዋዕል 7፡14፡ "ሕዝቤ... ቢ... "ለጥያቄዎቻችን ከእግዚአብሔር መልስ የማግኛ ቅድመ ሁኔታ፥ ስሙን መጥራታችን ነው።
- ዓላማ፡- ኤፌሶን 4፡12፡- እግዚአብሔር የተለዩ መሪዎችን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠበትን ዓላማ ሲገልጥ "ለመሥራትና..." ይላል።

እነዚህ ሁሉ አመክንዮአዊ ተዛምዶዎች የተገለጡት፥ በቃላትና በቃላት እድገት ነው።

## ቅደም ተከተላዊ ወይም መልክዓ-ምድራዊ ተዛምዶዎች

እነዚህ ተዛምዶዎች፥ በተለይ ታሪካዊ ጉዳዮችና ተአምራዊ ሁኔታዎችን የመሰሉ ተራኪ ሥነ-ጽሑፎች ገላጭ አከፋፈል ወይም ቢጋርን (Descriptive outline) በማዘጋጀት ጊዜ ይጠቅማሉ። ሁለት ምሳሌዎችን እነሆ፡-

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተዘጋጀው በቅደም ተከተላዊና መልክዓ-ምድራዊ ተከታታይነት ነው። ይህ ቅደም ተከተላዊ ሐዋርያት ሥራ 1፡8 ውስጥ ቀርቧል።

- ኢየሩሳሌም፡-(1፡1-8፡3) ኢየሩሳሌም ውስጥ የክርስትና እምነት መስፋፋት።
- ሰማርያ፡- (8፡4-12፡25) የክርስቲያኖች በስደቱ ምክንያት መበተን ያስከተለውን ውጤት ልብ ይበሉ። ጽሑፉን በሚተረጉሙበት ጊዜ፥ ሉቃስ፥ በወንጌል ሥርጭት ውስጥ

የእግዚአብሔር ሉዓላዊ እጅ ያለበት መሆኑን ሲገልጥልን፥ ይህን ዘዴ በሥነ-ጽሑፋዊ መሣሪያነት የተጠቀመበት መሆኑን ይገነዘባሉ።

- የዓለም ዳርቻ (13፡1-28፥31)።

ሉቃስ 17፡11-19 ውስጥ ለአሥሩ ለምጻሞች የተደረገላቸው ተአምር በተመሳሳይ ሁኔታ ሊደረስበት ይቻላል።

- ፈውስ ይፈልጉ የነበሩትን አሥሩን ኢየሱስ ይፈውሳቸዋል (ቁጥር 11፡14)
- ከዚህ በኋላ ትረካው ለማመስገን በተመለሰው አንድ ተፈዋሽ ላይ ያተኩራል (ቁጥር 15-19)።

ትንቢተ ዮናስ ለቅደም ተከተላዊና መልክዓ-ምድራዊ ጥናት ተመቻችቶ የቀረበ ነው።

- ዮናስ እስራኤል ውስጥ በአገልግሎት ላይ (1፡1-2)
- ዮናስ ወደ ጠርሴስ ለመሸሽ ጀልባ ውስጥ (1፡3-14)
- ዮናስ ዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ እየጸለየ (1፡15-2፡10)
- ዮናስ ነነዌ ውስጥ እየሰበከ (3፡1-10)
- ዮናስ ነነዌ አቅራቢያ በቁጣ ፊቱን በማስከፋት ዳስ ጥላ ሥር ተቀምጦ (4፡1-11)።

## ሥነ-ልቡናዊ ተዛምዶዎች

ጥቅሶችን በመተርጎም ጊዜ ሥነ-ልቡናዊ ተዛምዶዎችን መመልከት፥ ጉዳት ይኖረው ይሆናል። ምክንያቱም፥ ሥነ-ልቡናዊ የሚለው ቃል ባሕላዊ አመለካከትንና፥ በመሰለን መተርጎምን እንደሚገልጥ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላልና። ይሁን እንጂ፥ ምሳሌዎችን፥ ተአምራትንና ከሰብአዊ ግንኙነቶች ጋር የተዛመዱ ነገሮችን ለመገንዘብ ሙከራ በምናደርግበት ጊዜ፥ ሥነ-ልቡናዊ ጉዳዮችን ለመረዳት ጥረት ማድረጉ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ በእረኛውና በበጎቹ መካከል ያለውን ርኅራኄ የሞላበት ግንኙነት ልብ እንላለን (መዝ. 23፤ ዮሐ.10)። እረኛ ለበጎቹ ያለውን ፍቅር ልብ ማለቱ፥ መለኮታዊው እረኛ ለሕዝቡ ያለውን ፍቅር ለመገንዘብ ይረዳል።

እንዲሁም የአሥሩን ለምጻሞች የመፈወስ ተአምር በትክክል ለመረዳት፥ በአይሁዳውያንና በሳምራውያን መካከል ያሉትን አለመግባባቶች ወይም ልዩነቶች ለይቶ ማወቅና፥ ኢየሱስን ከራሱ ወገን ከሆኑት ሰዎች ይልቅ፥ ከተለየ ወገን የሆነው አንዱ ሰው ያመሰገነው ለምን

እንደሆነ መረዳት ተገቢ ነው። ሉቃስ እነዚህ ሁለት ሕዝቦች፥ (አይሁዳውያንና ሳምራውያን) ለኢየሱስ ያላቸውን ምስጋና በተመለከተ፥ ሥነ-ልቡናዊ ትኩረት ባለው መንገድ በግልጥ አነጻጽሯል። ኢየሱስ ፈውስ የሚያስፈልጋቸውን አሥር ሰዎች ፈወሰ (ሉቃስ 17፥ 11-14)፥ ዘጠኙ ግን፥ ፈውስ ምስጋና የሚያስፈልገው ነገር እንደሆነ አድርገው አልቆጠሩትም። ትረካው፥ ምንም እንኳን አይሁዳዊ ባይሆን ምስጋና ወዳቀረበው ሰው ያመለክታል (ሉቃስ 17፥ 15-19)።

ስለ ተአምራት በሚተርኩት ክፍሎች፥ ጸሐፊዎቹ በሰዎች መካከል ስላሉ ግንኙነቶች የሚሰጡት ዝርዝር ሥነ-ልቡናዊ ገለጣ ጥልቅ በሆነ ሁኔታ የክፍሉን አሳብ እንድንገነዘብ ይረዱናል።

## ዐውደ ንባባዊ ተዛምዶዎች

ማንኛውም ምንባብ፥ በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ፥ በአንዱ መጽሐፍ ወይም በንባብ ክፍሎቹ ሥነ-ጽሑፋዊ ዐውደ ንባብ የተከበበ ነው።

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዐውደ ንባብ።* መጽሐፍ ቅዱስ ባጠቃላይ አንድ ትልቅ ታሪክ ሲሆን፥ እግዚአብሔር ታሪክን የሚመለከትበት አተያይ ነው። የዓለማትና የሰው አፈጣጠር፥ በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች በብሉይ ኪዳን መሠራት፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ቀዳማይ ምጽአት፥ ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የሚገኘውን ድነት እኩል የመውረሳቸው ምሥጢር መገለጥ እና፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ሁሉ ነጻ የሚያወጣ መለኮት መሆኑን የሚያስገነዝብ፥ በጊዜና በቦታ የተወሰነችው ዓለማችን የመጨረሻ ሁኔታ ሁሉ ማለት ነው። የጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ ይዘት፥ ከዓለም መፈጠር እስከ አዲሲቱ ዓለም መከሠት ድረስ ያለውን ታሪክ ያካትላል።

ይህን አጠቃላይ ገጽታ የተመለከቱ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ብዙ አይደሉም። በመሆኑም ከዘፍጥረት፥ ወይ ከማቴዎስ ወንጌል ወይ ከኢሳይያስ አንድ ጥቅስ ይወስዱና ስለ ጥቅሱ ጥሩ አሳብ ይፈነጥቃሉ። ይህን በማድረጋቸው ምናልባት ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ አልወጡ ይሆናል፤ ቢሆንም እነርሱ የሚሉት ክፍሉ የሚለውን ነው? ብሎ መጠየቅ ጠቃሚ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን አጠቃላይ ዐውደ ንባብ ቀጥሎ በተገለጠው መሠረት ማገናዘብ ይኖርባቸዋል። ታሪካዊ ዐውዱን በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ታሪካዊ ሂደት፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዐውዱን፥ ባሕላዊ ዐውዱን እና ሥነ-መለኮታዊ ዐውዱን ሁሉ መመልከት አለባቸው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም ሥነ-ጽሑፋዊውን ዐውድ (አገባብ) በሚመለከት ከሕግጋት (የሙሴ መጻሕፍት)፥ ታሪክ ውስጥ የተወሰደ አንድ ጥቅስ ሲተረጎም፥ የታሪካዊ ጽሑፍን ባሕርያት በማገናዘብ ሊሆን ይገባል።

መዝሙረ ዳዊትን ስናጠና ደግሞ፥ የሥነ-ግጥምን ወይም የቅኔን ባሕርያት በማገናዘብ ሊሆን ይገባል።

መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ሥነ-ጽሑፋዊ ዘዴዎች የተጻፈ መሆኑን መረዳቱ በቂ ነው። በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባቦችን፥ ከደራሲዎቹ መልእክት፥ ቅርፅ እና አጻጻፍ ዘዴ አንጻር ነው ልንተረጉማቸው የሚገባ። ባሕላዊ አገባብም ግንዛቤ ሊሰጠው ይገባል። ለምሳሌ የአሞጽ ተደራሲያን ወይም አድማጮች ከጳውሎስ ተደራሲያን ወይም አድማጮች ይለያሉ፤ በሥነ-መለኮታዊው አስተምህሮ ብቻ ሳይሆን፥ በባሕልም።

በሥነ-መለኮታዊ አገባብ መሠረት ብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉና ሕግጋትን የያዘ አንድ ክፍል፥ በጳውሎስ መልእክት ውስጥ ያሉት ሥነ-ምግባራዊ ዝርዝሮች በሚተረጎሙበት መንገድ ሊተረጎም አይችልም።

ስለዚህ፥ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ድረስ ያሉትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች አጠቃላይ ገጽታ መገንዘቡ ተገቢ ነው። ጥቆማ፡- አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ታሪክ ለመረዳት ካልቻሉ፥ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የተጻፈ መጽሐፍ ይፈልጉና ያንብቡ። በተጨማሪ በተለያዩ መንፈሳዊ ጸሐፊዎች የተዘጋጁ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎችንና መሰል መጻሕፍትን ቢያነቡ በጣም ይረዱዎታል።

*የመጽሐፉ አገባብ።* እያንዳንዱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ መጽሐፍ፥ በመንፈስ ቅዱስ በተመራ ደራሲ የተጻፈ ነው። እያንዳንዱ መጽሐፍ የተጻፈበት አጻጻፍ በዓላማም ተመርጧል። ዓላማው ደግሞ በይዘቶቹ ላይ ተጽዕኖ አድርጓል። ስለሆነም ዓላማውን ለመረዳት፥ የመጽሐፉን ይዘት ይመልከቱ። ይህ ዓላማ በተራው መልእክቱን ከማብራራትዎ በፊት እንዲተረጉሙት ይረዳዎታል።

ለመግለጫነት፥ እንደ ኢዮብ መጽሐፍ ያለውን ይውሰዱና ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ያንብቡት። በቀላሉ ሲገለጥ፥ ታሪኩ ኢዮብ ስለተባለ አንድ ጻድቅና ባለጠጋ ሰው ነው። ባለታሪኩ እጅግ በከፋ ሥቃይ ውስጥ አልፏል። ሦስት ጓደኞቹ፥ ሦስት ጊዜ ከኢዮብ ጋር ባደረጉት ስብሰባ፥ የሥቃዩንም ምክንያት እንዲገነዘብ ሊረዱት ይፈልጋሉ። ነገር ግን፥ በእያንዳንዱ የምክራቸው ጊዜ ወደተሳሳተ ምክንያት ነው የሚያመለክቱት። አራተኛ ጓደኛው ወደ እውነት የተጠጋ ቢሆንም፥ ለኢዮብ ሕልውናዊና ሥነ-መለኮታዊ ጥያቄ የመጨረሻ መልስ የመጣለት፥ በኃያሉ እግዚአብሔር ብርቱ የቃል መገለጥና ሥራዎች አማካይነት ነው።

መጽሐፉን በሚያጠኑበት ጊዜ፥ ትረካው ውስጥ ያሉትንና ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ክፍፍሎች ልብ ይላሉ (ቁጥሮቹ የሚያመለክቱት ምዕራፎቹን ነው)።

መግቢያ የኢዮብ ሥቃይ 1-2

የመጀመሪያ ስብሰባ 3-14

ሁለተኛ ስብሰባ 15-21

ሦስተኛ ስብሰባ 22-31

የኤሊሁ ንግግሮች 32-37

የእግዚአብሔር መልስ 38-41

ማጠቃለያ፤ የኢዮብ ሥቃይ መወገድ 41

እነዚህን ክፍፍሎች በአእምሮዎ ይዘው መጽሐፉን ሲያጠኑና፥ "እኔ ግን የሚቤዠኝ ሕያው እንደሆነ... አውቃለሁ" ወደሚለው ተወዳጅ ጥቅስ ሲደርሱ፥ ጥቅሱን ወዲያውኑ በሁለተኛው ዙር ንግግሮች ባለው የኢዮብ መልስ ውስጥ ሊያኖሩት ይችላሉ (19፡25)። ጥቅሱ፥ በተስፋ መቁረጥና ተስፋ ቢስነት ውስጥ የተነገረ ዋና መግለጫ ነው እንጂ፥ ስለ ትንሣኤ በዋናነት የሚያወራ ክፍል አይደለም። ከኢዮብ ጓደኞች አንዱ የሆነው ባልዳዶስ፥ ኃጢአተኛ ከሞት በኋላ የሚጠብቀውን ዕጣ አስመልክቶ ለሰጠው አስተያየት የተሰጠም መልስ ነው። ወዲያውም፥ በታላቅ ሥቃይ በሚያልፈው ሰው ውስጥ ተስፋና በሕያው እግዚአብሔር መታመን ይታያሉ።

የመጽሐፉን ሙሉ ይዘት ማወቅዎ፥ ደራሲው በጽሑፉ ለማለት የፈለገውን ቁም ነገር አዘል ዋና ጉዳይ ለመረዳት ይጥሩ ዘንድ ይረዳዎታል። ደራሲው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልእክት መረዳት ነው የማንኛውም የመተርጎም ሥራ ዓላማ።

*ጥቆማ፦* የአንድን መጽሐፍ ይዘትና ዓላማ ለማጥናት ከሚጠቅሙ ምንጮች ጥቂቶቹ፥ ማጥኛና ማጣቀሻ ያላቸው መጽሐፍ ቅዱሶች ናቸው። እንዲህ ያሉት መጻሕፍት ብዙ ጊዜ በመግቢያቸው ላይ ጠቃሚ አስተያየቶች አሏቸው። የአስተያየት አቅራቢዎች አስተያየቶች የደራሲውን ዓላማና አከፋፈል ወይም ቢጋር በተመለከተ የሚቀርቡት አሳብ ጥቂት ይለያይ ይሆናል። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ፥ አስተያየቶቹ የጸሐፊውን ዓላማና አከፋፈሉን ለመረዳት እንደተጨማሪ መረጃ ይጠቅሙዎታል። መጀመሪያ መጽሐፉን እራስዎ ቢያጠኑት ይመረጣል። ከዚያ በኋላ ግን ግንዛቤዎን ከሌሎች ምሁራን አስተያየቶች ጋር ያነጻጽሩት። ይህ አሠራር፥ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መጻሕፍትን በተመለከተ ቀለል፥ በሌሎቹ ላይ ግን ከበድ ይል ይሆናል። ነገር ግን ተስፋ አይቁረጡ፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሰባኪ፥ የስብከቱ ክፍል ያለበትን መጽሐፍ ለመረዳት የሚያስችል ተግባራዊ እውቀት ሊኖረው ይገባልና።

*የስብከቱ ክፍለ ምንባብ።* የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሠረታዊ ክፍል፥ ጥቅሱ ወይም ዓረፍተ ነገሩ ሳይሆን፥ አንቀጹ ነው። በያንዳንዱ እሁድ ማቅረብ ያለብንን ስብከት በምንመርጥበት ጊዜ፥ ገላጭ ስብከት ጊዜና ድካምን የሚቆጥብልን መሆኑን ቀደም ሲል አስረድቻለሁ። በሚያጠኑበት ጊዜ ጽሑፉ በአንቀጾች የተከፋፈለ መሆኑን ይረዳሉ። በአብዛኛው በእያንዳንዱ የስብከት ጊዜ አንድ አንቀጽ ሊሰብኩም ይችላሉ።

አንድ ጸሐፊ፥ አሳቡን እቀደመው ምንባብ ውስጥ ባሉ አሳቦች ላይ በሚመሠርትበት ጊዜ፥ የክፍሉ ዐውደ ንባብ ወሳኝ ነው። አንቀጹን በሞላ በአንድ የስብከት ጊዜ ለመጨረስ አይቻል ይሆናል። የጽሑፉን የመጀመሪያና ሁለተኛ ነጥቦችን ወይም ጉዳዮችን ይሆናል ሊሰብኩ የሚችሉት። እንዲህ ከሆነ፥ አንድ መልእክት በሚያዘጋጁበት ጊዜ፥ ከክፍሉ በፊትና አንዳንዴም ቀጣዮቹን ዐውዶች (ዐውደ ንባብ) ማጥናት ይኖርብዎታል።

የአንድን መጽሐፍ ትርጉም በሚያጠኑበት ጊዜ፥ ዐውደ ንባቡን መረዳቱ ያለውን ጠቀሜታ ለመገንዘብ እንደ ምሳሌ ይረዳዎ ዘንድ፥ አንደኛ ጴጥሮስ መጽሐፍ ይመልከቱ። 2፡13 ላይ ያለው ዋና ጉዳይ መገዛት ነው። 3፡7 ላይ ወደተጠቀሰው የባሎች ኃላፊነት በቀጥታ ሄደን ቢሆን ኖሮ ግን፥ ጽሑፉ ውስጥ የነበረውንና "እንዲሁም እናንተ ባሎች" የሚለው ቃል ያለውን ኃይል ምናልባት አንረዳም ነበር። ጴጥሮስ ስለመገዛት ወይም እራስን ለሌላ ስለመስጠት ተናግሯል። አግባብ ያልሆነ ሁኔታ ቢኖርም እንኳን ለመንግሥት ባለሥልጣናትና ለሌሎች ጌቶች ተገዙ ይላል። "መገዛት" የሚለው አሳብ ዐውደ ንባቡ ላይ ያለውን ኃይል (ተጽዕኖ) ከሳትን፥ በምናቀርበው ስብከታችን በቤተሰባዊ ግንኙነት ውስጥ ያለውን አንድ ቁልፍ ጉዳይ ሳንነካው እንቀራለን። ይሄውም በባልና በሚስት መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት፥ አንዱ ለሌላው መገዛት፥ አክብሮትና ታማኝነት ነው። "ባል የሆኑ ሰባኪዎች" ምናልባት ያን ቃል ሊመለከቱት አይፈልጉ ይሆናል።

## የተለያዩ ሥነ-ጽሑፎች ተዛምዶ

እዚህ አጉልተን የምናሳየው፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላሉት የተለያዩ ሥነ-ጽሑፎች የተሰጠውን ጥቆማ ነው። አንድ ጽሑፍ የተጻፈበት የአጻጻፍ ስልት በጽሑፉ አተረጓጎማችን ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። ለምሳሌ አንድን በትረካ ዘዴ የተዘጋጀ ጽሑፍ በመልእክትነት ከተጻፈው በተለየ መንገድ እናየዋለን።

የአንድ ተራኪ ጽሑፍ ዝርዝሮች ሁሉ ለአድማጮችዎ ወይም ለአንባቢዎች ተግባራዊ ፋይዳ እንዳላቸው አድርገው አያቅርቡ። ታሪካዊ

ዝርዝሮች ቢጠቀሱ አቀራረቡን ተወዳጅ ያደርጉታል። ያ ማለት ግን፥ ታሪኮቹ ሁሉ በዛሬው ሕይወታችን ተግባራዊ ይሆናሉ ማለት አይደለም። እንደ ምሳሌ ያገለግለን ዘንድ፥ የታሪካዊ ድርጊት ዓይነተኛ ትረካ የሆነውን ትንቢተ ዮናስን እንመልከት። የዮናስን ታሪክ ስንሰብክ፥ ጀልባ ውስጥ መግባት የለብንም ብለን አሳብ አናቀርብም። ከዚያ ይልቅ፥ ከእግዚአብሔር ሸሽተን እርሱ ከሌለበት ስፍራ መድረስ ያለመቻላችንን እውነት መግለጥ ይኖርብናል። የትንቢተ ዮናስ መጽሐፍ የመጀመሪያው ክፍል ትረካ የሚገልጠው፥ ስለተስማሚ የመጓጓዣ ዘዴ ሳይሆን፥ ለታወቀው የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለመታዘዝ ነው። የትረካው ዝርዝር ገለጣዎች ታሪካዊ ድርጊቱን በማመልከት ምንባቡ ውስጥ በልዩ ሁኔታ የተገለጠውን ሥነ-መለኮታዊ እውነት እንድንገነዘብ ይረዱናል።

ሌላው ምሳሌ የጳውሎስ ነው። ጳውሎስ ትንሹ ኤሽያ በሚባለው አካባቢ በእግር የተጓዘና በእባብ የተነደፈ ቢሆንም፥ ክርስቲያኖች ተመሳሳዩን ማድረግ አለባቸው ብለን ልንሰብክ አንችልም። ነገር ግን ወንጌልን ወደ አስቸጋሪ አካባቢዎች በቀዳሚነት ስንወስድ፥ አደጋዎች ይገጥሙን ይሆናል ብለን ልንሰብክ እንችላለን።

ትግበራ ላይ ያተኮረ ስብከት ለማቅረብ ሲባል የሚከናወኑ እንዲህ ያሉ ትርጉማዊ ማስተካከሎች በአብዛኛው፥ በተርጓሚው ወይም በሰባኪው አሳብ የሚሠሩ ናቸው።

ስብከታዊና ትግበራዊ ማስተካከሎች አንዳንድ ጊዜ "መመሪያ ማውጣት" (Principalization) ይባላሉ። በሌላ አነጋገር ከአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በተግባር ላይ የሚውል መርህ ለማግኘት ሲባል ከክፍሉ ሥነ-መለኮታዊ መመሪያን ብዙም ግልጥ ባልሆነ መንገድ ማውጣት ነው።

በእግዚአብሔር ቃል አቀነጃጀት ሂደት፥ ከእርምጃ 3 እስከ 5 ባለው ክፍል ይህ አሠራር በደኅና ሁኔታና በትክክል የሚሠራበትን ዘዴ አሳያለሁ። "መመሪያን የማውጣት" ዘዴን በተመለከተ፥ ስለ አንዳንድ አደጋዎች ላስጠነቅቅዎ ይገባል። የመርሕዎ መነሻ ከክፍሉ የወጣ እንጂ፥ በክፍሉ ላይ በእኛ የተጫነ መሆን የለበትም። ከጽሑፉ ቅንጅትና ዝርዝር ጉዳዮች ጋር መዛመድ አለበት። ይህን በተመለከተ ዘግየት ብዬ እመለስበታለሁ።

በወንጌላት ውስጥ ያሉ ምሳሌዎች በሚተረጎሙበትና በሚሰበኩበት ጊዜ፥ የሥነ-ጽሑፍ ዓይነት (Genre) ወሳኝ ነው። ብዙውን ጊዜ ምሳሌዎቹ የሚያተኩሩት አንድ ዋና መልእክት በማስተላለፍ ላይ መሆኑ ችላ ሊባል አይገባም። አንድ ሰባኪ በአንድ ምሳሌ ውስጥ ባሉት ዝርዝር ጉዳዮች ሁሉ ተነሥቶ ተግባራዊ መመሪያ ሊያወጣ አይገባም። የጌታን ተአምራት

በተመለከተም እንዲሁ። ይህን የመሰለ ሁኔታ ያለው ሌላ የሥነ-ጽሑፍ ዓይነት የዳዊትና የኢዮብ ግጥም ነው። ትንቢታዊ ሥነ-ጽሑፍ የራሱ የሆኑ ባሕርያት አሉት። ትንቢቶችን በምንተረጉምበት ጊዜ፥ ትንቢታዊ ባሕርይውን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል። ለምሳሌ፤ ዳንኤል 9፡24 እና 10፡2 ውስጥ የተጠቀሰውንና "ሱባዔ" ወይም "ሳምንት" የሚለውን ቃል በምናነጻጽርበት ጊዜ፥ በሁለቱ ክፍሎች ያሉት "ሳምንታት" የሚያመለክቱት የተለያየ የጊዜ ርዝመትን እንደሆነ እንረዳለን። አራት መቶ ዘጠና ቀን፥ ዳንኤል 9፡24-27 ውስጥ የተጠቀሰውን ትንቢት ለመፈጸሚያ በጣም አጭር ጊዜ ነው። ዳንኤል እየጾመ በሕይወት ለመኖር፥ ሀያ አንድ ዓመት በጣም ይረዝምበታል (10፡3)።

## የጥያቄዎች ማጠቃለያ

አንድ ሰባኪ፥ አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለመረዳት የሚያነሣቸውን ጥያቄዎች ለማስታወስ ከሚጠቅሙት ቀላል መንገዶች አንዱ፥ ጥያቄዎችን በአራት መክፈል ነው።

1. መነሻ ወይም ዳራ (Background) ጥያቄዎች
2. የመረጃ ጥያቄዎች
3. የትርጉም/የፍች ጥያቄዎች
4. የትግበራ ጥያቄዎች።

- የመነሻ/የዳራ ጥያቄዎች፡ ለምሳሌ፥ የቆላስይስ ታሪካዊ መነሻ ወይም ዳራ፥ በጳውሎስ መልእክት ይዘት ላይ ምን ተጽዕኖ አለው?
- የመረጃ ጥያቄዎች፡ ጳውሎስ እንዴት ነው በቆላስይስ መልእክቱ ውስጥ እራሱን የሚገልጠው (1፡1-2)?
- የትርጉም/የፍች ጥያቄዎች፡ ለምንድነው ጳውሎስ እራሱን በዚህ ሁኔታ የሚገልጠው? ከክርስቶስ ጋር ለአዲስ ሕይወት መነሣት ማለት ምን ማለት ነው (ቆላ. 2፡12)?
- የትግበራ ጥያቄዎች፡ እንዴት ነው አሳባችንን ከላይ ባሉት ነገሮች ላይ የምናሳርፈው (ቆላ. 3፡2)?

## ጥያቄዎችን መመለስ

አሁን ወደ ከባዱ የትርጉም/የፍች ሥራ መጣን። ጥያቄዎቹን በምንመልስበት ጊዜ፥ ምንባቡን ጠንቅቀን ለማወቅ በምናደርገው ሙከራ፥ ወደምንፈልገው አቅጣጫ እንዳንወስደው መጠንቀቅ አለብን። ተርጓሚው ወይም ማብራሪያ ሰጪው የሚፈልገው፥ ግልጥና የተለመደውን መጽሐፍ

ቅዱስን የመፍታት ዘዴ (አንዳንዶች “ቃል በቃል” ሌሎቹ ደግሞ “ሰዋሰዋዊና ታሪካዊ አፈታት” የሚሉት)፥ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉምን ወይም ፍችን የመገንዘቢያ ዋና ጠቃሚ መንገድ፥ መጽሐፉን በራሱ መንገድ መፍታት ነው።

እዚህ የዝግጅትዎ ደረጃ ላይ ከደረሱ እንግዲህ፥ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትዎ የሚረዱዎትንና የሚያገኙዋቸውን መጻሕፍት ሁሉ ይሰብስቡ። መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈባቸውን የመጀመሪያ ቋንቋዎች የሚያውቁ ከሆኑ፥ ጥሩ ማጣኛ ያለው መጽሐፍ ቅዱስ፥ ላለዎት የመጽሐፍ ቅዱስ እትም የሚሆን የቃላት ዝርዝር ያለበት ጥቅስ ማውጫ (Concordance) እና የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ መጻሕፍት ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ይኑሩዎት እላለሁ። እነዚህ የግድ አስፈላጊዎች ናቸው። ለጥያቄና መልስዎችዎ ተጨማሪ ነገር ያገኙ ዘንድ እነዚህን ያንብቧቸው። እነዚህን መጻሕፍት የሚጠቀሙባቸው ለዝግጅትዎ እንደ መርጃ ብቻ መሆኑን አይርሱ። በመልእክት ዝግጅትዎ ሂደት እዚህ ደረጃ እስኪደርሱ አይጠቀሙባቸው። እዚህ ከመድረስዎ በፊት ካገላበጧቸው፥ በጥያቄዎችና በማጠቃለያ ሥራዎችዎ ላይ ተጽዕኖ ያሳድሩባቸዋል። ይህ ደግሞ፥ የስብከት ክፍሉ ከራስዎ ጋር እንዲዋሃድ የሚያደርገውን የዝግጅት ሂደት ያደናቅፈዋል።

### *መልሶችን መተንተን*

ሮበርት ትሬይና የተባሉ የሥነ-መለኮት ሰው “Methodical Bible Study” በሚለው ጽሑፋቸው ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጎም ጊዜ ስለሚገጥሙ ሦስት አደጋዎች ይናገራሉ። እነሱም፦

- *የተሳሳተ ትርጉም፦* ለአንድ ምንባብ የተሳሳተ ትርጉም መስጠት
- *ግማሽ ትርጉም፦* የምንባቡን ሙሉ ትርጉም አለማረጋገጥ
- *የተጋነነ ትርጉም፦* ለአንድ ምንባብ እውስጡ ከተገለጠው ትርጉም በላይ መስጠት።

አንድ ምንባብ እንዴት መፈታት ወይም መተርጎም እንደሚገባው በመግለጡ ረገድ ብዙ ተጽፏል። የአንባቢያንን ወይም የአድማጫችንን ደረጃ በተመለከተ ግን፥ መልስዎችዎን በሚቀጥሉት መመዘኛዎች ይተንትኗቸው።

- *የተዓማኒነት መመዘኛ፦* ትርጉምዎ ተዓማኒ ስለመሆኑ ጥሩ ማስረጃ ለማቅረብ ይችላል? ማለት እርስዎ ለክፍሉ የሰጡት ትርጉም ደራሲው ያን ክፍል በሚጽፍበት ጊዜ ሊገልጥ ከፈለገው አሳብ ጋር አንድ ነው?

- *የአንድነት መመዘኛ፦* በቃላቱ፥ በማረጋገጫዎችና በጥቅሶች ትርጉም መካከል የፍች ወይም የትርጉም አንድነት አለ? በትርጉሙ ውስጥ የሚጋጭ ወይም አብሮ የማይሄድ አሳብ አለ? ለምሳሌ አንድ ጊዜ የሰማሁት ከ1ኛ ዮሐንስ በተወሰደ ስብከት ላይ "ወንድም" የሚለውን ቃል ሰባኪው በስብከቱ የመጀመሪያ ክፍል ለክርስቲያኖች ተጠቅሞ፥ በስብከቱ ሁለተኛ ክፍል ግን ክርስቲያን ላልሆኑ ሰዎች ሲጠቀምበት ሰምቻለሁ።
- *የተዛማጅነት መመዘኛ፦* ትርጉምዎ ከምዕራፉ ሌሎች ክፍሎች፥ ከመጽሐፉና ከአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይስማማል? አስቸጋሪ የሚመስሉ ነገሮችን ሊገልጥ ይችላል? ለምሳሌ፥ ጳውሎስ፥ ጢሞቴዎስ ማንኛውንም ሥጋ ይበላ ዘንድ መፍቀዱን ከብሉይ ኪዳን ክልከላ ጋር አነጻጽረው እንዴት ይገልጡታል?
- *የግልጥነት መመዘኛ፦* ትርጉምዎ ቀላል ነው፥ ወይስ ከባድ? ግልጥ ነው ወይስ ምሥጢራዊ? በቀላሉ የተገለጠና ለመረዳት የማያስቸግር፥ ወይስ በስውርና በተመሰቃቀለ ዝርዝር አሳብ የተሞላ?
- *የታማኝነት መመዘኛ፦* ጽሑፉን ከራስዎ ወይም ከሌሎች (ምሳሌ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎን ወይም የቤተ እምነትዎን) ውሳኔና አስተሳሰብ አንጻር ላለመተርጎም ጥንቃቄ ያደርጋሉ?

*ልብ ሊሉት የሚገባ ነገር፦* ትርጉሞቻችን ስሕተት-አልባዎች አይደሉምና፥ ትርጉማችንን ሊያስለውጡ የሚችሉ አዳዲስ ማስረጃዎችና ጥያቄዎች ለማስተናገድ ዝግጁ መሆን አለብን።

### የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብ ትርጉምዎን መመዘን

1. እውነተኛነት
2. አንድነት ወይም ወጥነት
3. ተዛማጅነት
4. ግልጥነት
5. ታማኝነት

### *መልሶችን መተግበር*

ስብከት፥ አሳብን (Information) ማስተላለፊያ መንገድ ብቻ አይደለም። የሰዎችን ሕይወት የሚለውጠውን መልእክት የማስተላለፍ

ሥራም ነው። የምንሰብከው መልእክት የሰዎችን ሕይወት መለወጥ አለበት። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እውነት እንዲኖሩት መገፋፋት ነው። የሰባኪው ኃላፊነት፥ የእግዚአብሔርን ቃል በሕይወት የመተግበሪያ መርሆችን ማስጨበጥ ብቻ ሳይሆን፥ መርሆዎቹ በዕለት ተዕለት ሕይወት እንዴት መተግበር እንደሚኖርባቸው መጠቆምም ነው። አድማጮች ወይም አንባቢያን የሰሟቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያዎች እንዴት ተግባራዊ ለማድርግ እንደሚችሉ ራሳቸው ያስቡ ብለን ልንተዋቸው አይገባም።

መጀመሪያ እኛ እራሳችን መጽሐፍ ቅዱስን በሕይወታችን መተርጎም አለብን። ከዚያ በኋላ ነው፥ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እውነት ከሕይወታቸው ጋር እንዴት እንደሚያዋሕዱት ማሳየት የምንችለው። የስብከት ዝግጅታችን እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊው መልእክት ላይ ተመሥርተን፥ ለአድማጮቻችን ስለሚናገረው ነገር በማሰላሰል ላይ ነን። የምናጢነው ክፍል፥ ከወቅቱ የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር ያለው ተዛምዶ ወይም ጠቀሜታ ምንድነው?

ወደ መተግበሪያው ዘዴ ከመግባታችን በፊት፥ ሮይ. ቢ. ዙክ የተባሉ ጸሐፊ ትግበራን አስመልክቶ የሰጡትን ጥሩ ማብራሪያ እነሆ፡-

> “በመጽሐፍ ቅዱስ ገለጣዊ ስብከት ወይም ማስተማር ማዛመድ እንዲህ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ ለወቅቱ ያለውን ጠቃሚ አሳብ በመግለጥ ያንንም ጠቃሚ አሳብ እንዴት በተግባር ላይ ማዋል እንደሚቻል በማሳየት አድማጮች ያንን ለውጥ ይተገብሩ ዘንድ መጋበዝና ማነሣሣትም ነው።”

ማዛመድ በይዘት ላይ ያተኮረ ሲሆን አማኞች ሊያምኑ ስለሚገባቸው ወይም በሕይወታቸው ስፍራ ሊሰጧቸው ከሚገቧቸው ነገሮች ጋር ይያያዛል። ድርጊትን በተመለከተ ደግሞ አማኞች ሊታዘዙ ወይም ሊያደርጉ የሚገባቸው ነገር ላይ ያተኮረ ሊሆን ይችላል። እነዚህ አቅጣጫዎች ብዙ ጊዜ ማዛመድን (መተግበርን) አስመልክቶ ተቀላቅለው ይገኛሉ። ምክንያቱም፥ ሰዎች የሚተገብሩት ፋይዳ አላቸው ብለው የሚያምኑባቸውን ስለሆነ ነው።

ትክክለኛውን ማዛመድ ለማከናወን ይችሉ ዘንድ፥ የሚከተሉትን ተገቢ ጥያቄዎች መጠየቅ አለብዎት።

- ክፍሉ ከአሁኑ ዘመን ጋር ያለው ተገናኝነት ምንድነው?
- ከጽሑፉ የሚያወጣው ማዛመድ ምን ዓይነት ነው? ይዘት፥ ድርጊት፤ ወይም በይዘት ላይ የተመሠረተ ድርጊት?

- የማዛመድ ዘዴዬ በእርግጥ በዚህ ክፍል ላይ የተመሠረተ ነው? ከበስተጀርባው የክፍሉ ሥልጣንና ተዓማኒነት አለ?
- ይህ ሥራዬ ከክፍሉ የወጣ ማዛመድ መሆኑን አንባቢዬን ወይም አድማጮቼን የሚያሳምናቸው ምንድነው?
- ሰዎች ክፍሉ ከእነርሱ ሕይወት ጋር ያለውን ግንኙነት የሚገባቸው ስለመሆኑ እርግጠኛ የምሆነው እንዴት ነው? ክፍሉ ለሕይወታቸው ያለው መልእክት ሁልጊዜ ለአድማጮች ግልጥ ይሆናል ብለን ልናስብ አንችልም። ማዛመድ በራሱ ወዲያው የሚከናወን ነገር አይደለም። ሰዎች የሚሰሙትን እውነት ከሕይወታቸው ጋር የማዛመድ ዝንባሌ የላቸውም። ይልቅስ እውነቱ፥ ከሌላ ሰው ጋር ያለውን ግንኙነት ማገናዘብን ይመርጣሉ።

ክፍሉን በሚያጠኑበት ጊዜ፥ ለግሎና ለስብከትዎ ያለውን የማዛመጃ ነጥቦች ይፈልጋሉ። አንዳንድ ጊዜም፥ መልእክትዎን አዘጋጅተው ከመጨረስዎ በፊት እንኳን፥ እነዚህን ከክፍሉ ያገኟቸውን አሳቦች በሕይወትዎ መተግበር ይጀምራሉ። እነዚህን ከክፍሉ ይወጣሉ የሚሏቸውን የማዛመድ አሳቦች ይመዝግቧቸው። በክፍሉ የማይደገፉ ወይም ከክፍሉ አሳብ ጋር የማይስማሙትን (ደረጃ 3) ደግሞም ከዓላማዎ ጋር የማይሄዱትን የተዛምዶ አሳቦች (ደረጃ 4) በኋላ ያስወግዷቸዋል። ኢውጂን ላውርይ የተባለ የሥነ-መለኮት ሰው "መልእክትዎን በሚያዘጋጁበት ጊዜ ሁሉ እንደ ምሁርና ሰባኪ ሆነው ሊያዘጋጁት ይገባል" ብሏል።

## >> የድርጊት እርምጃ <<

እስቲ ክፍሉን ማጥናት በሚለው የመጀመሪያ ደረጃ የስብከት ቅንጅት ሂደት እንጠቀም። ከመልእክቶች ኤፌሶን 6፡10-12ን እንመልከት። ክፍሉን በሚያጠኑበት ጊዜ፥ የዚህን የመጀመሪያ ደረጃ ሂደት ይመርምሩ።

እያንዳንዱን ጥቅስ በተናጠል በአንድ ወረቀት ላይ ይሥሩት። ጥቅሱን በሙሉ ይጻፉት፤

ቁ. 10 በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።

ቁ. 11 የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ፥ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።

ቁ. 12 መጋደላችሁ ከሥጋና ከደም ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር፥ በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።

## ዝርዝሮቹን ማጥናት

> ቃላትን ልብ ይበሉ

ትርጉማቸውን ከመዝገበ ቃላት፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ወይም ዐውደ ጥበብ (Encyclopedia)፥ ተመልክተው ያጥኑ። አጠቃቀማቸውን ደግሞ፥ ከቃላት ዝርዝር (Concordance) እና ሕዳጋዊ (Marginal) ጥቅሶች ያጥኑ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ፥ ብርቱ፥ ዕቃ ጦር፥ ሽንገላ፥ መጋደል፥ አለቆች፥ ከሥልጣናት፥ ሠራዊት፥ የሚሉ ቃላትን ያገኛሉ።

> ተዛምዶዎችን ይመልከቱ

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ባሉት ቃላት መካከል ያሉትን ተዛምዶዎች ይመልከቱ። በቀረውስ፥ በጌታ፥ በኃይሉ ችሎት፥ የዲያቢሎስን ሽንገላ፥ ከሥጋና ከደም፤ እና ቁጥር 12 ውስጥ የተጠቀሱት መንፈሳዊ ጠላቶች።

## ትርጉምን ወይም ፍችን መፈለግ

> ጥያቄዎችን ይጠይቁ

ለምንድነው ጳውሎስ ቁጥር 10 ውስጥ "በቀረውስ" ያለው? ያለ ጌታ ብርቱ ለመሆን ይቻላል? ወይስ የጌታ ኃይል የሚያስፈልገው ቁጥር 12 ውስጥ ከተገለጡት ተቃዋሚ ኃይላት የተነሣ ነው? የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር "ሁሉ" ለምን ያስፈልጋል?

> ጥያቄዎችን ይመልሱ

"በቀረውስ" የሚለው ቃል ትርጉም "ከፍተኛው ጠቃሚ ነገር" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ይህም አጠቃላይ ከኤፌሶን መልእክት ጋር ወይም ከምዕራፍ 4-6 ካለው ጋር ሊሆን ይችላል። የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር "ሁሉ" ያስፈለገበት ምክንያት የሕይወት ደካማ ጎናችንን ከሰይጣን አጠቃላይ ጥቃት ለመከላከል ነው።

> መልሶችን ይተንትኑ

ከላይ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች በመጠቀም፥ መልሶችዎን ይተንትኑ። በተጨማሪም ማብራሪያ መጻሕፍትን በመመልከት፥ ሌሎች የእግዚአብሔር ሰዎች ስለ ጽሑፉ የተናገሩትን ልብ ይበሉ። ለምሳሌ አንደኛው ማብራሪያ ሰጪ እንዲህ በማለት ይጽፍ ይሆናል፥ 'ልበሱ' የሚለው ግሪክኛ ትእዛዛዊ አንቀጽ የሚገልጠው፥ አማኞች የራሳቸውን ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ በቅፅበት የመልበስ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ነው።

> መልሶቹን ከሕይወት ጋር ማዛመድ

የኛ አጸፋ የሚያስፈልገው የሰይጣን "አጣዳፊ" ጥቃት የቱ ነው? በአሁኑ ዘመን ከሰይጣን ጋር የሚደረጉ አንዳንድ የውጊያ ሁኔታዎችን ያሰላስሉ። በውጊያው ውስጥ በክርስቶስ በርትተን የምንቆምባቸውን መንገዶችና እርስዎ፥ እንዲሁም ሕዝቦችዎ ዘዴዎቹን የሚተገብሩባቸውን ሁኔታዎች ይመዝግቧቸው።

**ደረጃ 1፦ ክፍለ ምንባቡን ያጥኑት (የደረጃ 1 አከፋፈል ወይም ንድፍ)**

I. ምልከታ

ሀ. ቃላትን ልብ ይበሉ

1. ረጃጅም ቃላት
2. ያልተለመዱ ቃላት
3. የተደጋገሙ ቃላት

ለ. ግንኙነቶችን ልብ ይበሉ

1. ሰዋስዋዊ ተዛምዶዎች
2. አመክንዮአዊ (Logical) ተዛምዶዎች
3. ቅደም ተከተላዊ ወይም መልክዓ-ምድራዊ ተዛምዶዎች
4. ሥነ-ልቡናዊ ተዛምዶዎች
5. አገባባዊ ተዛምዶዎች
   ሀ) የመጽሐፍ ቅዱስ ዐውደ ንባብ
   ለ) የመጽሐፍ ቅዱሳዊው መጽሐፍ ዐውደ ንባብ
   ሐ) የክፍሉ ዐውደ ንባብ
6. ሥነ-ጽሑፋዊ ግንኙነቶች
   ሀ) ማስተማር
   ለ) ትረካ
   ሐ) ግጥም/ቅኔ
   ረ) ምሳሌዎች
   በ) ተአምራት
   ተ) ትንቢት

II. መፈለግ

ሀ. ጥያቄዎችን ማቅረብ

1. ለቃላት የሚቀርቡ ጥያቄዎች

ሀ) እነዚህ ቃላት በዚህ ዘመን ያላቸው ትርጉም ምንድነው?

ለ) በተጻፉበት ጊዜ የነበራቸው ትርጉም ምን ነበር?

መ) መጽሐፍ ቅዱስ፥ ደራሲው እና ደራሲዎች ሌላ ስፍራ እንዴት ነው በቃላቱ የተጠቀሙባቸው?

2. ለተዛምዶዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎች

ሀ) ሰዋስዋዊ ግንኙነቶች

1) ጊዜ
2) ቁጥር
3) ጾታ

ለ. አመክንዮአዊ (Logical) ግንኙነቶች

1. መነሻና መድረሻ

2. ምክንያት

3. ውጤት

4. ንጽጽር

5. ውድድር

6. ሁኔታዎች

7. ዓላማ

መ. ቅደም ተከተላዊ ወይም መልክዓ-ምድራዊ ግንኙነቶች

ረ. ሥነ-ልቡናዊ ግንኙነቶች

ሰ. አገባባዊ ግንኙነቶች

1. የመጽሐፍ ቅዱስ አገባብ

ሀ) ታሪካዊ አገባብ

ለ) የመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ሥነ-ጽሑፋዊ አገባብ

መ) ባሕላዊ አገባብ

ረ) ሥነ-መለኮታዊ አገባብ

2. የመጽሐፉ አገባብ

3. የክፍሉ አገባብ

ሸ. ሥነ-ጽሑፋዊ ግንኙነቶች

1. ማጠቃለያ፦ የጥያቄዎች ዓይነት

ሀ) የመነሻ (Background) ጥያቄዎች

ለ) የእውነት ጥያቄዎች

መ) የፍቺ ወይም ትርጉም ጥያቄዎች

ረ) የትግበራ ጥያቄዎች

ቀ. ጥያቄዎችን መመለስ

በ. መልሶችን መተንተን "አምስት መመዘኛዎች"

1. እውነተኛነት

2. አንድነት ወይም ወጥነት

3. ተዛማጅነት

4. ግልጥነት

5. ታማኝነት

ተ. መልሶችን መተግበር

1. ምን ዓይነት ትግበራ?

2. ትግበራው ምንድነው?

3. የትግበራ እርግጠኛ መሠረት ምንድነው?

4. አድማጮች ወይም አንባቢያን፥ የትግበራው መሠረት የጽሑፉ ሥልጣን ስለመሆኑእርግጠ ኞች እንዲሆኑ ላደርጋቸው የምችለው እንዴት ነው?

# 2

# ክፍለ ምንባቡን ማቀናጀት

>> የምንባቡ ውስጣዊ አካል (አጥንቱ) <<

ደረጃ 7: ስብከቱን መስበክ

ደረጃ 6: ስብከቱን ማቀናጀት

ደረጃ 5: የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ

ደረጃ 4: የዓላማ መሸጋገሪያ ወይም ድልድይ

ደረጃ 3: የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ

**ደረጃ 2: ክፍለ ምንባቡን ማቀናጀት**

ደረጃ 1: ክፍለ ምንባቡን ማጥናት

ደረጃ 2 በክፍለ ምንባቡ ጥናትዎ ላይ ይገነባል (ክፍል 1)። በዚህ የስብከት አዘገጃጀት ዘዴ አንዱ ዋና ነገር፥ የመጽሐፉ ደራሲ ክፍሉን ያቀናጀበትን መንገድ መረዳት ነው። በዚህ ሁኔታ ደራሲው የሚለውን መስበክ ብቻ ሳይሆን፥ አባባሉንም እናንላዋለን። ደረጃ 2፥ የስብከት ክፍሉን የተለያዩ ንዑስ ክፍሎችን እንዴት እንደምናገኝ ፍንጭ ይሰጠናል። በዛም ላይ ተመሥርተን የእያንዳንዱን ንዑስ ክፍል አሳብም ጠቅለል ባለ መልኩ ለማስቀመጥ ይረዳናል።

ደረጃ 2

የስብከት ምንባቡን ክፍሎች ማቀናጀት

የስብከት ምንባቡን ክፍሎች ፍሬ አሳብ ማውጣት

## የስብከት ምንባቡን ክፍሎች ማቀናጀት

የምንባቡን ቅንጅት የምናገኘው፥ በሁለት የቅንብር አመልካቾች፥ ማለት በሰዋስዋዊ ቁልፎችና በርእሰ ጉዳይ ምልክቶች አማካይነት ነው።

### *ሰዋስዋዊ ቁልፎች*

ሰዋስዋዊ ቁልፎች የሚባሉት፥ አጫጭር ቃላት ወይም የቃላት ክፍሎች ሆነው፥ በጽሑፉ ቅንብር ላይ ትልቅና ሰፊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው።

አጫጭር ቃላት የደራሲውን አሳብና ትኩረት የሚገልጡ የአጻጻፍ መሠረቶች ሆነው ሳለ፥ ብዙ ጊዜ ይዘለላሉ። ደረጃ 1 ውስጥ በቃላትና በአንቀጾች መካከል የሚኖረውን "አመክንዮአዊ ወይም ሎጂካል ተዛምዶ" አስመልክቶ የሰጠሁትን አስተያየት ያስታውሱ ይሆናል።

አንድን ወሳኝና አጭር ቃል የሚመለከት አንድ ምሳሌ እነሆ፦ "ዮሐንስ ስለራበው ወደዚህ መጣ. . . የሚለውን አጭር ዓረፍተ ነገር ይያዙ፥ "ስለ" የሚለው ቃል፥ ሁለት ፊደሎች ብቻ ናቸው ያሉት። የዓረፍተ ነገሩን አሳብ ለመረዳት ግን ቃሉ ወሳኝ ነው። "ስለ" የሚለው ቃል ዮሐንስ የመጣበትን ምክንያት ይገልጣል።

መጽሐፍ ቅዱሳዊው ጽሑፍ፥ እንዲህ ባለ የትርጉም ኃይል የተሞሉ ብዙ ቃላትና የቃላት ክፍሎች አሉት። ከነዚህ ቃላት ጥቂቶቹ ካላቸው አጠቃላይ ትርጉማቸው ጋር ቀጥሎ ቀርበዋል።

## >> የድርጊት እርምጃ <<

ዕዝራ 7፡10 ውስጥ እንዲህ ይላል፥ "ዕዝራ የእግዚአብሔርን ሕግ ይፈልግና ያደርግ ዘንድ፥ ለእስራኤልም ሥርዓትንና ፍርድን ያስተምር ዘንድ ልቡን አዘጋጅቶ ነበር"

ደረጃ አንድን ለማከናወን፥ በረጃጅም፥ ባልተለመዱና በተደጋገሙ ቃላት ላይ ምልክት እያደረጉ ጽሑፉን ያንብቡት። ይህን የሚያደርጉት ለጥናትና ለማሰላሰል ነው።

በደረጃ ሁለት ክንውን የምንባቡን ቅንጅት ያገኙታል፤ የደራሲው ዋና ዋና እና ንዑሳን ነጥቦች ይለያሉ።

ዕዝራ 7፡10 ውስጥ "እና" የሚለውን የተደጋገመ መስተጻምር ልብ ያድርጉ፥

ዕዝራም የእግዚአብሔርን ሕግ <u>ይፈልግ</u>

*እና*

<u>ያደርግ ዘንድ</u>

ለእስራኤልም ሥርዓትን እና ፍርድን <u>ያስተምር</u> ዘንድ ልቡን አዘጋጅቶ ነበር።

ጥቅሱ በቀላሉ በሦስት ተከፍሏል። ይህን በሦስት የተከፈለ ምንባብ፥ ጥቅሱ ላይ በግድ በተጨመረ አሠራር ከመከፋፈል ይልቅ፥ ከክፍሉ ከራሱ እንዲወጣ በርግጠኛነት ለመግለጥ ይችላሉ። "ሥርዓት" በሚለውና "ፍርድ" በሚሉት ቃላት መካከል ሁለተኛው መስተጻምር፥ "እና" አለ። ለዚህኛው መስተጻምር፥ ቀደም ብሎ ከተጠቀሰው "እና" ጋር ተመሳሳይ ክብደት መስጠት ይኖርብዎ ወይም አይኖርብዎ እንደሆን

መወሰን አለብዎ። "እና" የሚሉት መስተጻምሮች ጥቅሱ ውስጥ ያሉትን ሁለት ሐረጎች ያያይዛሉ። ከእያንዳንዱ ሐረግ በኋላም "ዘንድ" የሚለው ኢ-ውሱን ቃል ይገኛል። የዚህን ቅንጅት ሁኔታ ቀጥሎ እገልጣለሁ።

ይህን ጥቅስ በመጨረሻ ለስብከት የሚያቀናጁት ከሆነ፥ መልእክትዎ ከሦስት የበለጡ ፍሬ ነገሮች አይኖሩትም (አንድ ስብከት፥ ያነሱ ወይም የበዙ ፍሬ ነገሮች ይኖሩት ይሆናል። ይህን ጉዳይ ዘግየት ብለን እንመለስበታለን)። ይህን ጥቅስ ወይም ፍሬ ነገር የሚመለከተው የመልእክትዎ ክፍል ሦስት ፍሬ ነገሮች ብቻ ነው ሊኖሩት የሚገባ።

. . . . . . . . . . . . . . . . . .

ለናሙና የሚሆን፥ ግን ለበለጠ ማጣቀሻነት የሚጠቅም ሠንጠረዥ ቀጥሎ ቀርቧል። እነዚህ አጫጭር ቃላት ሲገጥሙዎ፥ የቃላቱን የትርጉም ደረጃ ለመረዳት ሠሌዳውን ይመልከቱ። ለምሳሌ "ስለ" የሚለው ቃል ቢገጥምዎ፥ የዚያ ምንባብ ክፍል ትርጉምዎ፥ በመነሻ፤ በምክንያት፤ በውጤትና በዓላማ ዙሪያ የሚሽከረከር ይሆናል።

መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት የመጀመሪያ ቋንቋ ሊጠቀሙ ለማይችሉ ሰዎች የምሰጣቸው ምክር፥ "አስተማማኙ ቅንጅታዊ ሥራ፥ ክፍሉን በጥቅስ ቁጥር መከፋፈል ነው" የሚል ይሆናል። የጥቅስ፥ የአንቀጽና የምዕራፍ ክፍፍሎች በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተደረጉ ባይሆኑም እንኳ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ ምሁራን ክፍሉን በሚያጠኑበት ጊዜ የወሰኗቸው ክፍፍሎች ናቸው። እነዚህም ክፍፍሎች አሳብንና ቅንጅቶችን በአስተማማኝ ሁኔታ ይገልጣሉ። በቁጥሮች ውስጥ ያሉ ሥርዓተ ነጥቦች እንኳን ቅንጅትን ያመለክታሉ። ስለዚህ አራት ነጥቦችን፥ ድርብና ነጠላ ሠረዞችን፥ እንዲሁም የቃለ አጋኖንና ሌሎችንም ልብ ለማለትዎ እርግጠኛ ይሁኑ።

## ቅንጅትን የሚያሳዩ ሰዋስዋዊ ቁልፎች

| ፍች/ትርጉም | ቅንጅት አመልካች አጫጭር ቃላት |
|---|---|
| መነሻ:- | ስለ፥ ምክንያቱም፥ በመሆኑ/ከሆነ፥ እንደ |
| ምክንያት:- | ስለ፥ ምክንያቱም፥ በመሆኑ/ከሆነ፥ እንደ፥ ከ. . ./እንደ |
| ውጤት:- | እንደ /ከ. . . ይሆን ዘንድ፥ ስለዚህ፥ የሚ. . .፥ የመ. . .፥ ስለ |
| ዓላማ:- | እንዲ. . ./ለማ. . .ለ፥ እስከ፥ ወደ፥በ. . . |
| መንገድ/ማድረጊያ :- | በ፥ ከ፥ በ. . .በኩል፥ ውስጥ |

| | |
|---|---|
| ጊዜ፡- | እስከ፥ ለ፥ ሲሆን፥ መቼም፥ ከ፥ በ. . . በኩል የ፥ውስጥ፥ በ፥ እንደ . . . ፥ በተቃራኒ፥ ከ-ጋር፥ስለ፥ ለ. . . ሲል |
| ስፍራ፡- | የትም፥ የት፥ ከ፥ በ፥ በ. . . በኩል፥ ውስጥ፥ ከ. . . ጋር፥ ስለ፥ እስከ |
| ሁኔታ፡- | ልክ እንደ፥ በትክክል፥ እንደ፥ በ፥ ለ |

*ማስታወሻ፡-* እዚህ ያልተካተቱ ሌሎች አጫጭር ቃላት በጥናትዎ ጊዜ ይገጥሙዎ ይሆናል። ይህ ሲሆን፥ ፍቺያቸውን እንደ አገባባቸውና በሚፈጥሩት ስሜት መሠረት ሊለዩ ይችላሉ። በተጨማሪም፥ እዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የሚገኘውንና ኤፌሶን 6፡10-12 ላይ ተመሥርቶ የቀረበውን የጽሑፍ አቀነጃጀት መግለጫ ይመልከቱ።

## *የይዘት ርእሰ ጉዳይ ምልክቶች*

አንዳንድ ጊዜ ቅንጅትን በሰዋስው ለመግለጥ ያዳግታል። ከዚያ ይልቅ፥ የአንድ ጽሑፍ ቅንጅትን ቀጥሎ ባሉት ሁኔታዎች ለመለየት ይቻላል፥

- በይዘት ለውጦች
- በአዲስ ርእሰ ጉዳይ መከሠት
- በድግግሞሽ
- በአባባል ዘይቤ መለወጥ. . . ወዘተ.

የአባባል ዘይቤ ለውጥ ምሳሌ፥ ደራሲው አንድ ነገርን ሲገልጥ ቆይቶ፥ ወዲያውኑ ወደ ትእዛዛዊ ሁኔታ ሲለውጥ ነው። የአንድ ጽሑፍን ቅንጅት በሚመለከቱበት ጊዜ፥ ይህን መሰሉን ለውጥ ሊገነዘቡ ይገባል።

## *የስብከት ክፍሉን የማቀናጃ አራት ደረጃዎች*

ቀጥሎ ያሉት አራት ደረጃዎች የሚያጠኑዋቸውን የጽሑፍ ክፍሎች ለማቀናጀት ይረዱዎታል።

- ቅንጅቱ ውስጥ ያሉትን ሰዋስዋዊ ወይም የይዘት ምልክቶችን ይለዩዋቸው።
- ዋና ዋናዎቹን ምልክቶች ከንዑሳን ይለዩዋቸው። ክፍሉን በማቀናጀት ረገድ ከንዑሳን ምልክቶች ይልቅ፥ ዋና ዋናዎቹ የበለጠ ፋይዳ አላቸው።
- የዋና ዋናዎቹን ምልክቶች ትርጉም ወይም ኃይል ልብ ያድርጉ።

- በምልክቶቹ አንጻራዊ ጠቀሜታ መሠረት፥ የጽሑፉን አከፋፈል ወይም ንድፍ ያዘጋጁ።

ይህ የማቀናጀት ደረጃ፥ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ምልክቶችን ከንዑሳኑ ለመለየት የሚሞከርበት ነው። የሰው አካል፥ የሰውነት ክፍሎችን አንዱን ከሌላው የሚለያዩ ትንንሽና ትልልቅ አጥንቶች እንዳሉት ሁሉ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽሑፎችም (ሌሎች ጥሩ ጽሑፎችን ጨምሮ)፥ ትልልቅና ትንንሽ አጥንቶች ይኖሩዋቸዋል። የምንባቡን ዋና እና ንዑስ አከፋፈል ለመረዳት፥ የራስዎንና የሌሎች ሰዎችን ብያኔ ይጠቀማሉ። ምንባባችን ከትልልቅና ትንንሽ አጥንቶች የተሠራ መሆኑን ካሰብን፥ መከናወን ያለባቸው አራት ደረጃዎች ቀጥሎ ተገልጠዋል።

## ትላልቅ እና ትንንሽ አጥንቶች (ቅንጅትን መረዳት)

+ አጥንቶቹን ሁሉ ለይተው ይወቋቸው።

+ ትልልቆቹን አጥንቶች ከትንንሾቹ ይለዩ።

+ የትልልቆቹን አጥንቶች ፍች ወይም ኃይል ይረዱ።

+ አጥንቶቹን እንደጠቃሚነታቸው በቅደም ተከተል ይጻፏቸው።

አንድን ክፍል ለመተንተን፥ እነዚህን አራት ደረጃዎች እንዴት ነው የምንጠቀምባቸው? ያብራሯቸውና ቀጥሎ ባለው ሁኔታ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ በሚወሰዱት ምሳሌ አማካይነት ይገልጧቸዋል።

*መጀመሪያ፥ ቅንጅት አመልካቾችን ለይተው ይወቋቸው።* አንድ ጥቅስ አንድ ገጽ ወረቀት ላይ ጽፈዋል። ረጃጅሞቹን፥ ያልተለመዱትንና የተደጋገሙትን ቃላት፥ እንዲሁም ሐረጎችን ከለዩዋቸው በኋላ (ደረጃ 1)፥ ትናንሽ ቃላት ሆነው ለትልልቆቹ ቃላቶች ኃይል የሚሰጧቸውን በመክበብ ከሥር በማሥመር ወይም በልዩ ቀለም በማድመቅ ይለዩዋቸው። እነዚህን ደረጃዎች ለመለማመድ እስቲ ቀጥሎ ባለው ቀላል ዓረፍተ ነገር ይጠቀሙ። "ታደሰ የሚባለው ሰውዬ ስለታመመ፥ ለሕክምና ከቤቱ ሆስፒታል ተወሰደ"። ዓረፍተ ነገሩ ቅንጅቱን የፈጠሩ ሦስት አጫጭር ቃላት አሉት። እነሱም፥ "ስለ፥ ለ፥ ከ" የሚሉት ናቸው።

*ሁለተኛ፥ ዋና ዋናዎቹን ቅንጅት አመልካቾች ከንዑሳኑ ይለዩዋቸው።* ከላይ የተጠቀሱትን ቅንጅት አመልካች ሦስት ቃላት ይፈልጉ። ሦስቱም፥ ስለ፥ ከ፥ ለ የሚሉት፥ ጽሑፉን ለመፍታት ወይም ለመተርጎም አስፈላጊ ቢሆኑም፥ ዓረፍተ ነገሩን በመረዳት ረገድ ግን እኩል ክብደት የሚሰጣቸው አይደሉም። "ስለ" የሚለው ቃል አጥንትና አጥንትን የሚያያይዝ ስለሆነ "ከ" እና "ለ" ከሚሉት ይበልጥ ጠቃሚ

ነው። "ስለ" የሚለው ቃል የዓረፍተ ነገሩን ሁለት ክፍሎች ያገናኛል። "ከ" የሚያያይዘው ቤቱ እና ሆስፒታል የሚሉትን ሁለት ቃላት ብቻ ነው። በጣም ጠቃሚ የሆኑትን የአጥንት አገናኞች፥ ጠቀሜታቸው ካነሰው ይለዩዋቸው።

*ሦስት፥ የዋና ዋናዎቹን አመልካቶች ትርጉም ወይም ኃይል ይረዱ።* እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርሱ፥ "ቅንጅትን የሚያሳዩ ሰዋሰዋዊ ቁልፎች" የሚለውን ይመልከቱ። አንዳንድ ጊዜ፥ በአጥንት የተመሰሉትን የምንባቡን ክፍሎች መለየት ይኖርብዎታል። ይህን የሚያደርጉት፥ በደንብ እንዲገነዘቧቸው ነው። ሌላ ጊዜ ደግሞ አጥንቶቹን በመለያየት ላይ እያሉ፥ ኃይልና ተግባራቸውን ብቻ ተገንዝበው ይጠቀሙባቸዋል።

ከላይ በምሳሌነት በተጠቀምንበት ናሙና ዓረፍተ ነገር፥ "ስለ" የሚለው ቃል የምክንያቱን ምንነት ወይም ትርጉም ያስተላልፋል። ያነሰ ጠቀሜታ ያለውና "ከ" የሚለው ፊደል፥ በዚህኛው አገባብ ስፍራን ያመለክታል። "ለ" የሚለው ደግሞ ዓላማን ወይም ምክንያትን ያስረዳል።

*በመጨረሻ፥ በምልክቶቹ አንጻራዊ ጠቀሜታ መሠረት፥ የምንባቡን አከፋፈል ወይም አስተዋጽኦ ይሥሩ።* ምንባቡን ማቀናጀቱ፥ ምንባቡን በደራሲው ትኩረት መሠረት ለመንደፍ ይረዳዎታል። የዋና ቅንጅት ቁልፎችን ከንዑሳን ቅንጅት ቁልፎች የመለየቱ ሥራ፥ ዝርዝሮቹን የሚያካትተውን ቅንብር ለመገንዘብ ይረዳዎታል።

የደራሲውን የትኩረት አቅጣጫ በመከተል በሚያቀናጁበት ጊዜ፥ ያንን ትኩረት በክፍሉ አስተዋጽኦ ላይ ለማሳየት ይሞክራሉ። በትላልቅ አጥንቶች ምሳሌነት የሚለዩዋቸው ከንድፉ በስተግራ ይሆናሉ። በትንንሽ አጥንቶች የተመሰሉት ደግሞ ከንድፉ በስተቀኝ ይጻፋሉ። የንድፍዎ ቅደም ተከተል ይህን መምሰል አለበት።

I.

   ሀ.

      1.

         ሀ)

            I)

               (ሀ)

II.

   ሀ.

      1. ወዘተ.

ቅንጅታዊ አመልካቾች ወይም አጥንት አገናኞች፥ የሚያገናኟቸውን ቃላት አንጻራዊ ጠቀሜታ ያመለክታሉ። ያነሰ ጠቀሜታ ያላቸው ደግሞ፥ በአከፋፈሉ ጊዜ፥ በገጹ ላይ ወደ ቀኝ እልፍ እያሉ ይጻፋሉ።

-ዋና አመልካቾች፡ የሮማዉያን ቁጥሮች - I. ፥II. ፥III. ፥ . . . ወዘተ.

-ቀጣዩ ደረጃ፡ ፊደሎች ሀ፥ ለ፥ መ . . . ወዘተ.

-ቀጣዩ ደረጃ፡ ተዋረዳቸውን በነጥብ የሚያመለክቱ ቁጥሮች 1. ፥ 2. ፥ 3. . . .ወዘተ።

-ቀጣዩ ደረጃ፡ በግማሽ ቅንፍ ያሉ ፊደሎች ሀ)፥ ለ)፥ መ)፥ . . .ወዘተ።

-ቀጣዩ ደረጃ፡ በግማሽ ቅንፍ ያሉ ቁጥሮች - 1)፥ 2)፥ 3)፥ . . .ወዘተ።

-ቀጣዩ ደረጃ፡- በሙሉ ቅንፍ ያሉ ፊደሎች፡- (ሀ)፥ (ለ)፥ (መ)፥ ወዘተ.

-ቀጣዩ ደረጃ፡- በሙሉ ቅንፍ ያሉ ቁጥሮች፡- (1)፥ (2)፥ (3)፥ ወዘተ.

“ታደሰ፥ ለሕክምና ከቤቱ ወደ ሆስፒታል ተወሰደ” የሚለው ናሙና ዓረፍተ ነገራችን፥ አንድ በትልቅ አጥንት የሚመሰል አገናኝ ስለአለው፥ በሁለት ተከፍሏል።

I. ታደሰ ወደ ሆስደታል ተወሰደ

II. ምክንያቱ፡ ስለታመመ

ከዓረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ጋር የሚዛመዱ ሁለት ትንንሽ አጥንቶች አሉ፤ “ከ” እና “ለ” የሚሉት። በመሆኑም በዓረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል፥ አስተዋጽኦ (Outline) ሁለተኛ ደረጃ ላይ ሁለት ፍሬ ነገሮች ይኖርዎታል።

I. ታደሰ ሆስፒታል ተወሰደ

ሀ. ታደሰ ከቤቱ ወደ ሆስፒታል ተወሰደ

ለ. ታደሰ ለሕክምና ወደ ሆስፒታል ተወሰደ

II. ታደሰ ሆስፒታል የተወሰደበት ምክንያት መታመሙ ነው።

ዓረፍተ ነገሩ ሁለተኛ ክፍል ውስጥ ቅንጅታዊ ምልክቶች ስለማይታዩ፥ ከ2 ሥር የሚደረደሩ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ የአከፋፈል ደረጃዎች የሉም። አከፋፈል ወይም (Outline) በሚያዘጋጁበት ጊዜ፥

ሁለተኛ ደረጃ ሳይኖርዎ ሦስተኛው፥ ሦስተኛው ሳይኖርዎ አራተኛ...ወዘተ ሊኖርዎ አይችልም። የአንድ ጽሑፍ ክፍፍልን ሲያወጡ፥ በቀደመው የክፍፍል ደረጃ ላይ ነው የሚገነቡት።

እስቲ ዕዝራ 7፡10 ላይ በመመሥረት አቀነጃጀትን ላስረዳ።

"ዕዝራም የእግዚአብሔርን ሕግ ይፈልግና ያደርግ ዘንድ፥ ለእስራኤልም ሥርዓትንና ፍርድን ያስተምር ዘንድ ልቡን አዘጋጅቶ ነበር"።

መጀመሪያ፥ ቅንጅት አመልካች የሆኑ ቃላትን (ትርጉሙ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ አጫጭር ቃላት) ይለዩዋቸው። እነዚህን ያገኛሉ፦ እና፥ ይ፥ ያ፥ ያ፥ ዘንድ፥ ለ፥ ዘንድ። ቀጥሎ ደግሞ ዋና ዋና አመልካቾችን ከንዑሳን ይለዩ። እዚህ ጥቅስ ውስጥ ያሉት ዋና ዋና አመልካቾች፥ ዘንድ ፥ ለ፥ እና፥ ለ፥ እና፥ ለ የሚሉት ናቸው። ንዑሳኑ አመልካቾች ከነዚህ ተለይተው የታወቁት ናቸው። ለምሳሌ ሦስተኛው "እና"።

የዋና ዋና አመልካቾችን ፍች ወይም ትርጉም ይገንዘቡ።

- "ዘንድ" የሚለው ቃል ጥቅሱን ከዚያ ቀድሞ ከነበረው ጥቅስ ጋር ያዛምደዋል እንጂ፥ ስለዚህኛው ጥቅስ ቅንጅት የሚገልጠው ነገር የለም።
- "ይ"፥ "ያ"፥ "ያ" የሚሉት ፊደሎች ጥቅሱ ሦስት ላይ የሚከፈልበትን ሁኔታ ያሳያሉ።
- "እና" የሚለው ዋና አመልካች ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል። የሚያመለክተውም ጥቅሱ የተጣመረበትን ሁኔታ ነው።

የጽሑፉን አከፋፈል ወይም ንድፉን ይሥሩ። ከሰዋስዋዊ ወይም ይዘት ለውጦች በመነሣት፥ ሦስት ዋና ዋና ነጥቦችን ለማውጣት ይቻላል።

ዕዝራም..

I. የእግዚአብሔርን ሕግ ይፈልግ

እና

II. ያደርግ

ዘንድ

III. ያስተምር

ዘንድ

ሀ. ሥርዓትን

እና

ለ. ፍርድን ለእስራኤል ልቡን አዘጋጅቶ ነበር።

የዕዝራ ጽሑፍ እንዴት በጥሩ ሁኔታ በሦስት ነጥቦች እንደተከፈለ ያስተውሉ። ሦስተኛው ነጥብ ሁለት ንዑሳን ነጥቦች አሉት። ይህ የሆነው፥ "እና" በሚለው ንዑስ የቅንጅት አመልካች መስተጻምር ምክንያት ነው። የዚህ ምንባብ መልእክትዎ ዋና ክፍል ታውቋል።

## የምንባቡን ዋና ዋና ክፍሎች ፍሬ አሳብ ይጻፉ።

የአንድን ክፍል ፍሬ አሳብ ጠቅለል አድርጎ መጻፍ (Summary) ጥሩ ነገር ነው። ይህም የሚያጠኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፥ ምዕራፍ፥ የምዕራፍ ክፍል ወይም ሙሉ መጽሐፍ ዋና ፍሬ አሳብ ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲ ያቀረበውን ነጥብ እርግጠኛነት ለማጠናከር ሲል የሚገልጣቸው ብዙ ዝርዝሮች አሉ። በዚህ መሠረት የምንባቡን አካሄድ በመለየት ላይ እያሉ፥ የምንባቡን ዋና ኃይል ልብ ይላሉ። ደራሲው የሚያተኩርበትን ርእሰ ጉዳይና የሚያቀርበውን ጭብጥ በመጨረሻ ለመረዳት ይቻልዎ ዘንድ፥ የምንባቡን ዋና ዋና አሳቦች በአጫጭር ዓረፍተ ነገሮች ጠቅለል አድርገው ይግለጡ (ይጻፉ)።

ምንባቡን በአጭሩ መጻፉ፥ የምንባቡን ዋና አሳብ ወይም ኃይል ለመለየት ይረዳዎታል። በተጨማሪም ይህ የሚረዳዎት በስብከት ዝግጅትዎ የሚቀጥለው ደረጃ ላይ ማለትም ክፍሉን በአንድ ማዕከላዊ አሳብ ዙሪያ በሚያቀናብሩበት ጊዜ ነው (ደረጃ 3)።

ክፍሉን በአጭሩ ለማቅረብ ሲፈልጉ፥ የክፍሉን ቅንጅት በሚተነትኑበት ጊዜ ወደ ጻፉት አከፋፈል (Outline) ይሂዱ። ከዚያም በክፍፍሉ ዋና ዋና ደረጃዎች ውስጥ የሰፈሩ አሳቦችን ወደ ሙሉ ዓረፍተ ነገርነት በመለወጥ በአጭሩ ይጻፏቸው።

የዕዝራ 7፡10ን ዋና ዋና ክፍሎች ቀጥሎ ባለው ሁኔታ በአጭሩ ለመጻፍ ይቻላል።

I. ዕዝራ የእግዚአብሔርን ሕግ ይፈልግ ዘንድ ልቡን አዘጋጀ (10ሀ)

II. ዕዝራ ሕጉን ያደርግ ዘንድ ልቡን አዘጋጀ (10ለ)

III. ዕዝራ ሕጉን ለእስራኤል ያስተምር ዘንድ ልቡን አዘጋጀ (10መ)

ሀ. የእግዚአብሔርን ሥርዓት ያስተምር ነበር

ለ. የእግዚአብሔርን ፍርድ ያስተምር ነበር

### >> የድርጊት እርምጃ <<

ወደ ኤፌሶን 6፡10-12 እንመለስና፥ ደረጃ 2 በሆነው ማቀናጀትና ማሳጠር እንሥራው። ቀደም ሲል፥ የአንድን ጽሑፍ ቃላትና ግንኙነት

ማጥናትን ደረጃ 1 ውስጥ ሠርተዋል። ይህን ክፍል በጥንቃቄ ሲያጠኑ፥ የመልእክትዎን ሥልጣን በራስዎ አሳብ ሳይሆን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ላይ የሚያደርጉ ገላጭ ሰባኪ ይሆኑ ዘንድ ጥናቱ ይረዳዎታል።

ቁ. 10 በቀረውስ በጌታ ና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ

ቁ. 11 የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ፥ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።

ቁ. 12 መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለም ና። ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ፥ ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር ፥ በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።

## ማቀናጀት

አንድን ምንባብ የማቀናጀት አራት ደረጃዎችን ይሠራሉ። ከላይ ባለው ጽሑፍ ውስጥ በተለየ አጻጻፍ የተጻፉትንና የተሰመረባቸውን ቃላት ወይም የቃላት ክፍሎች ይወቋቸው፥ ይለዩዋቸው፥ ይገንዘቧቸው፥ አከፋፈላቸውንም ይሥሩ። ይህን ሁሉ ሲያደርጉ፥ ኤፌሶን 6፡10-12ን ከፍተው በጥንቃቄ እንዲያነቡ አሳስብዎታለሁ።

ጥቅሶቹን በተመለከተ አንዳንድ ፍንጮች

ቁጥር 10 ውስጥ "በቀረውስ" የሚለው ቃል ይህን ጥቅስ ከቀደመው ጥቅስ (ክፍል/ምንባብ) ጋር ያዛምደዋል። ደራሲው አዲስ አሳብ በመጀመር ላይ መሆኑን ስለሚያመለክት፥ ቃሉ ጠቃሚ ነው። "በ" የሚለው ፊደል ሁለት ጊዜ የገባ ሲሆን፥ የፊደሉ ሁለቱም ክንውኖች፥ በተለመደው አጣማሪ ቃል "ና" ስለተገናኙ በሁለቱም ስፍራ እኩል ጠቀሜታ አለው። "በጌታ" እና "በኃይሉ" የሚሉት ሁለት ቃላት አከፋፈል (Outline) አስተዋጽኦ በሚሠራበት ጊዜ እኩል ኃይል የሚሰጣቸው ናቸው። "በ" የሚለው ፊደል በቃሉ ውስጥ የሚኖረውን ኃይል ወይም ትርጉም መወሰን አለብን። "በ" ማድረጊያን ወይም መንገድን የሚያመለክት መሆኑን ለመረዳት፥ ወደ ኋላ ይመለሱና የሰዋሰዋዊ ቁልፍ ሠንጠረዥ ገጽ 48 ላይ ይመልከቱ፤ በጌታ ብርቱ የመሆኛውን መንገድ ማለት ነው።

እነዚህን ፍንጮች በመያዝ የቁጥር 10 ቅንጅትን ለመሥራት ይሞክሩ።

ቁጥር 11 ውስጥ ሁለተኛው "የ" ዓረፍተ ነገሩ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ በጣም ዝቅተኛ ነው። "ት...ዘንድ" የሚለው ቃል ጠቃሚ አባባል ነው። ይህ ቃል፥ ምክንያትን፥ ውጤትን ወይም ዓላማን ሊገልጥ እንደሚችል ሰዋሰዋዊው ሠንጠረዣችን ያስረዳናል። ምክንያት፥ ውጤት

እና ዓላማ አንዳንድ ጊዜ ይደራረቡ ይሆናል። ለዚህ ዓረፍተ ነገር አገባብ ምክንያትን እንመርጣለን። ያን የምናደርገው፥ ቁጥር 12 ውስጥ የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር የሚለበስበትን ምክንያት ደራሲው ስለሚገልጥ ሲሆን፥ የመጀመሪያው "የ" ያለው ጠቀሜታ ዝቅተኛ ነው።

እነዚህን ፍንጮች በመያዝ፥ ቁጥር 11ን ለማቀናጀት ይሞክሩ።

ቁጥር 12 "ችን" የሚለው ቃል ጠቃሚ ነው። ተርጓሚዎቹ በአዲስ ቁጥር በመጀመር አሳቡን በሁለት ለመክፈል መወሰናቸውን ልብ ያድርጉ። መከፋፈሉ፥ ብዙ ጊዜ ቅንጅት ውስጥ የሚታከል ወይም የሚለወጥ ነገር መኖሩን ያመለክታል። አሁን እንግዲህ በቁጥር 11 እና 12 መካከል ያለው መከፋፈል በቁጥር 11 እና 10 መካከል እንዳለው ዋና መሆን አለመሆኑን ይወስኑ። የጎላ ወይም ዋና መከፋፈል ከሆነ፥ ከዚህ ቀጥሎ እንደተመለከተው፥ ሦስት ነጥቦች አሉን ማለት ነው።

I. ቁጥር 10

II. ቁጥር 11

III. ቁጥር 12

መከፋፈሉ ቀላል ከሆነ፥ ሁለት ነጥቦች ናቸው የሚኖሩን

I. ቁጥር 10

II. ቁጥር 11-12

"አይደለምና" በሚለው ቃል መጨረሻ ያለው "ና" የቁጥር 12 ምክንያትና የዚሁ ቁጥር አሳብ ክፍል ነው። "እንጂ" የሚለው ቃል ደግሞ፥ "ሥጋና ደም" የሚለውን ሐረግ ከሌሎቹ መስተዋድዶችን ይለየዋል። ሌሎቹን ቃላት ለማመልከት "የሰይጣን አሠራር" የሚለውን ሐረግ መርጫለሁ። "ከ. . .ጋር" የሚለው ሐረግ ብዙ ጊዜ የተደጋገመ ሲሆን፥ የምናልፋቸውን የልምምድ ዓይነቶች በግልጥ ያስገነዝባል። "ከ. . .ጋር" የሚለው ቃል የተደጋገመና፥ "እንጂ" ከሚለው ቃል ጋር የተጣመረ ስለሆነ፥ ስለተለያዩ ኃይላት በሚኖረን ግንዛቤ ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል። እነዚህን የመሳሰሉ መስተዋድዶች ንድፋችን ውስጥ እኩል ስፍራ ይሰጣቸዋል።

በነዚህ ፍንጮች ላይ በመመሥረት ቁጥር 12ትን ለማቀናጀት ይሞክሩ።

የቁጥሮቹ አቀነጃጀት

ኤፌሶን 6፡10-12ትን ያቀናጀሁት ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ነው። እርስዎ ከሚሠሩት ጋር ያነጻጽሩት። እኔ የሠራሁት እንዲያ የሆነበትን ምክንያት ይመርምሩ። ለምንድነው የርስዎ የሆነውን የሆነው?

ዋና ዋና አመልካቾች፥ ዋና ዋና ነጥቦችን ይሰጣሉ።

I. "በቀረውስ" (ቁጥር 10)

II. "ልበሱ" የሚለው ትእዛዝ (ቁጥር 11-12)

የአመልካቾች የሚቀጥለው ደረጃ፥ ንዑሳን ነጥቦችን ይሰጣል።

I. "በቀረውስ" (ቁጥር 10)

ሀ. ማድረጊያው ወይም መንገዱ: "በ" ጌታ (ቁጥር 10) እና

ለ. ማድረጊያው ወይም መንገዱ: "በ" ኃይሉ ችሎት (ቁጥር 10)

II. "ልበሱ" የሚለው ትእዛዝ (ቁጥር 11-12)

ሀ. የመጀመሪያው ምክንያት "ዘንድ" (ቁጥር 11)

ለ. ሁለተኛው ምክንያት: አይደለም "ና" (ቁጥር 12)

## ማጠቃለል

የጽሑፉን ዋና ዋና ክፍሎች ያጠቃሉ። አሁኑኑ የራስዎን ዋና ዋና ነጥቦች ለማጠቃለል ይሞክሩ። ከዚያም "ዋና ዋናዎቼን ነጥቦች እንዲህ ያጠቃለልኳቸው ለምንድነው?" ብለው በጥንቃቄ ያስቡ።

የኔ ማጠቃለያ ይሄውልዎ

I. ብርቱ የመሆኛው መንገድ፥ በጌታና በኃይሉ ችሎት ነው (ቁጥር 10)

II. የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር መልበሱ ያስፈለገበት ምክንያት፥ የዲያብሎስን ሽንገላ ለመቃወም ነው (ቁጥር 11-12)።

ማስታወሻ:- ማጠቃለያ ከዋና ቅንጅት አመልካቾች ቀጥሎ የሚመጣ መሆኑን ልብ ያድርጉ።

ኤፌሶን 6፡10-12 ላይ ተመሥርቼ ያዘጋጀሁት ሙሉ ቅንጅት ቀጥሎ ያለው ነው። የዚህ ነጥብ አሠራር ከገባዎ፥ የቅንጅቱን ቁም ነገር ይረዳሉ።

I. ብርቱ የመሆኛው መንገድ፥ በጌታና በኃይሉ ችሎት ነው (ቁጥር 10)።

ሀ. በጌታ ብርቱ መሆን አለብን (ቁጥር 10)።

ለ. በኃይሉ ብርታት ብርቱ መሆን አለብን (ቁጥር 10)።

II. የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር መልበሱ ያስፈለገበት ምክንያት፥ የዲያቢሎስን ሽንገላ ለመቃወምና የሰይጣንን አሠራር ለመታገል ነው (ቁጥር 11-12)።

ሀ. የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ የመልበሱ አስፈላጊነት የመጀመሪያ ምክንያት፥ የዲያቢሎስን ሽንገላ በርትቶ ለመቋቋም ነው (ቁጥር 11)።

ለ. የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ የመልበሱ አስፈላጊነት ሁለተኛ ምክንያት የዲያብሎስን ሽንገላ ለመቃወም ነው (ቁጥር 11)።

1. ትግላችን ከሥጋና ደም ጋር አይደለም (12)።

2. ትግላችን ከሰይጣን አሠራር ጋር ነው (12)።

ሀ) የሰይጣን አሠራር አለቆች አሉበት።

ለ) የሰይጣን አሠራር ሥልጣናት አሉበት።

ሐ) የሰይጣን አሠራር የዓለም ገዦች አሉበት።

መ) የሰይጣን አሠራር በሰማያዊ ስፍራ ያሉ መንፈሳውያን ሠራዊት አሉበት።

ሊሰብኩ ለፈለጉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አሁን በጣም የተሟላ አከፋፈል (Outline) አለዎት። ይህ መጽሐፍ ቅዱስን የሚሰብኩበት፥ በጣም ጠቃሚና ሥልጣን ያለው መንገድ ነው። በስብከት ዝግጅት ጊዜ፥ ደረጃ 2ን አልፈው ባይሄዱ እና በንድፉ ላይ ተመሥርተው ቢሰብኩ እንኳን፥ ለመጽሐፍ ቅዱስ ታማኝ ለመሆንዎ እርግጠኛ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፥ ወደ ስብከት መድረክዎ ከመሄድዎ በፊት ያደረጉት ዝግጅት ይህ ብቻ ከሆነ፥ ስብከትዎ መልእክት ከመሆን ይልቅ፥ ሌክቸር ይመስላል። ገላጭ ስብከትን የሚመለከቱ የአንዳንድ ገጽታዎች ማስገንዘቢያ፥ ወደፊት ይቀርባል። ማድረግ ያለብዎት ደረጃዎቹ ላይ መውጣት ከመጀመርዎ በፊት፥ መሠረቱን መሥራት ነው።

# 3

# የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ

**>> የክፍለ ምንባቡ "ልብ" <<**

ደረጃ 7፡ ስብከቱን መስበክ

ደረጃ 6፡ ስብከቱን ማቀናጀት

ደረጃ 5፡ የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ

ደረጃ 4፡ የዓላማ መሸጋገሪያ ወይም ድልድይ

**ደረጃ 3፡ የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ**

ደረጃ 2፡ ክፍለ ምንባቡን ማቀናጀት

ደረጃ 1፡ ክፍለ ምንባቡን ማጥናት

ተርጓሚዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎችን፥ እያንዳንዳቸው አንድ ዋና እና ተለይቶ የሚታወቅ አሳብ ባላቸው አንቀጾች ይከፋፍሏቸዋል። እንደውም አንድ አንቀጽ ማለት፥ አንድ ዋና አሳብ ያለው ማለት ሊሆን ይችላል። ይህ ዋና አሳብ እኔ "የክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ" የምለው ነው። እያንዳንዱ ማዕከላዊ አሳብ፥ ሁለት ክፍሎች አሉት።

እነርሱም ርእሰ ጉዳይና ጭብጡ ናቸው

የምንጠቀምበት የገላጭ ስብከት ትርጉም ልዩ ትኩረት "የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልን ማዕከላዊ አሳብ ለወቅቱ በሚሆን መልኩ ማቅረብ" ነው። ማዕከላዊ አሳቡ ሰባኪው ፈልጎ ሊያገኘው የሚገባው የስብከት ክፍሉ ልብ ነው። ይህ ማዕከላዊ አሳብ አንዳንድ ጊዜ ሌላ መጠሪያ አለው፥ "የክፍለ ምንባቡ መልእክት"፥ "ዋና ትኩረት"፥ "የመልእክቱ ማሠሪያ" ወይም "ትልቁ አሳብ" ይባላል።

## የማዕከላዊ አሳብ ክፍሎች

ርእሰ ጉዳይ (ርእስ)

ጭብጥ (መልእክት)

ማዕከላዊው አሳብ፥ የክፍለ ምንባቡን ርእሰ ጉዳይና ጭብጡን ያካተተ፥ በክፍሉም ውስጥ ያሉት ዝርዝር ጉዳዮች ሁሉ የሚጠነጠኑበት ዓረፍተ ነገር ነው። ልናስተላልፍ የምንፈልገው አድማጮቻችን ሊሰሙት፥ ሊገነዘቡትና ሊታዘዙት የሚገባ አንድ ዋና ነጥብ (መልእክት) ስለሆነ፥ የክፍለ ምንባቡን ዋና አሳብ ከወቅቱ ጋር በማገንዘብ እናስተላልፋለን። የክፍለ ምንባቡን ማዕከላዊ አሳብ ግን በሚገባ ሳንገልጥ አድማጮች ያገኙት ይሆናል ብለን ከተውነው፥ የእግዚአብሔርን እውነት በመቀበልና

ይሆናል ብለን ከተውነው፥ የእግዚአብሔርን እውነት በመቀበልና በማስተላለፍ ተግባር ውስጥ አስፈላጊ አይደለንም።

ማዕከላዊ አሳብን አስመልክቶ የጉዳዩ ሊቃውንት ከጻፉት ጥቂቱን ቀጥሎ አቀርባለሁ፤

*"ጽሑፍዎን ወደ አንድ ቀላል ዓረፍተ ነገር ያሳጥሩትና ዓረፍተ ነገሩን እንደ ድር ይዘርጉት፤ ከዚያም ክፍሉን እራሱን እንደ ማግ ይጠቀሙበት። ይህን እያደረጉ፥ በተካተተባቸው ልዩ ልዩ ቃላት አማካይነት ዋናውን አሳብ ይገልጣሉ። ቃሉ የአድማጭዎን አእምሮ ሰርስሮ እንዲገባ ያድርጉ። በቀላሉ የማይነቀል ይሆናል፥" (ቻርልስ ሳይመን)*

*"ስለዚህ የገላጭ ስብከት ትርጉማችን የሚያረጋግጠው 'ገላጭ ስብከት ማለት፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ፅንሰ-አሳብ ማቅረብ ነው' በሚለው መርሕ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው። ይህ የሚያረጋግጠው ማንኛውም ስብከት በሌሎች አሳቦች የሚደገፍ የአንድ ዋና አሳብ አብራሪ ተርጓሚና አዛማጅ ሲሆን አሳቦቹም ከአንድ ወይም ከብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚወጡ ናቸው።" (ሀዶን ሮቢንሰን)*

## የክፍለ ምንባቡን ማዕከላዊ አሳብ ለይቶ መረዳት

የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ፥ የምንባቡን ዝርዝር አሳቦች ሁሉ በአንድ ላይ የሚሰበስብና ትርጉም የሚሰጣቸው የምንባቡ ዋና አሳብ ነው። "የመልእክቱ ወይም የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ" የሚለውንና ደረጃ 5 ውስጥ የተሰጠውን ተመሳሳይ ገለጣ ልብ ይበሉ። ልዩነቱ የመጨረሻው ቃል በ"ክፍለ ምንባብ" ፈንታ "ስብከት" መሆኑ ነው።

*የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ ምን ይመስላል?*

ማዕከላዊ አሳብ፥ አንድ ሙሉ ሰዋስዋዊ ዓረፍተ ነገር ሆኖ ነው ሁልጊዜ የሚቀመጠው። ከአንድ ዓረፍተ ነገር ያነሰ ከሆነ፥ አሳብ ተብሎ ሊገለጥ አይችልም።

*የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ ምን ምን ይይዛል?*

**ሁለት ክፍሎች አሉት**

- የክፍለ ምንባቡ ርእሰ ጉዳይ፡- የክፍለ ምንባቡ ርእሰ ጉዳይ፥ "ደራሲው እመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ ውስጥ የሚናገረው ስለምንድነው?" ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል።

የክፍለ ምንባቡ ውስጥ ስለሚናገርበት ርእሰ ጉዳይ ምን በማለት ላይ ነው?›› ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል።

> ርእሰ ጉዳይ፦ ደራሲው ምንባቡ ውስጥ የሚናገረው ስለምንድነው?

> ጭብጥ፦ ደራሲው ምንባቡ ውስጥ ስለሚናገርበት ጉዳይ ምን እያለ ነው?

*የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ ከየት ነው የሚገኘው?*

የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ፥ የክፍሉን አስተዋጽኦ ካዘጋጁበት ከደረጃ 2 ላይ የሚያገኙት ነው። በእያንዳንዱ ሰዋስዋዊ ወይም የይዘት ማሳያ መሠረት፥ ክፍሎችን ከፋፍለው አሳይተዋል። ንዑሳን ሰዋስዋዊ ወይም የይዘት ምልክቶች፥ ንዑሳን ክፍሎችን ያመለክታሉ። ዋና የይዘት ወይም ሰዋስዋዊ ምልክቶች፥ ዋናዎቹን ክፍሎች ይገልጣሉ። እያንዳንዱ ዋና ክፍል አንድ ርእሰ ጉዳይ አለው። ደራሲው እነዚህን ርእሰ ጉዳዮች ያያያዘበት መንገድ፥ የትልቁን ክፍል ማዕከላዊ አሳብ እንዲያገኙ ይረዳዎታል።

እስቲ ኤፌሶን 4፡7-16ን ተጠቅሜ ላብራራ፤ እርስዎ ደግሞ ይህንኑ ዘዴ አጠር ላለው ምንባብ፥ ለኤፌሶን 6፡10-12 ያውሉታል። ልምምዱን ከመጀመርዎ በፊት፥ ቀጥሎ ያለውን የኤፌሶን 4፡7-16 ክፍል፥ በዝግታና በጥንቃቄ ሦስት ጊዜ ያንብቡት።

ቁ 7. ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን፥ ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን።

ቁ 8. ስለዚህ፦ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ፥ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ ይላል።

ቁ 9. ወደ ምድር ታችኛ ክፍል ደግሞ ወረደ ማለት ካልሆነ፥ ይህ ወጣ ማለትስ ምን ማለት ነው?

ቁ 10. ይህ የወረደው፥ ሁሉን ይሞላ ዘንድ፥ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው።

ቁ 11. እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ።

ቁ 12፥ 13. ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆን ዘንድ።

ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስከንደርስ ድረስ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆን ዘንድ።

ቁ 14. እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኮል፥ በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ንፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህ እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደፊት አይገባንም።

ቁ 15. ነገር ግን፥ እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ።

ቁ 16. ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።

1. ከቁጥር 7-11 ያለው ክፍል ወደ ሰማይ ያረገው መሢሕ (ክርስቶስ)፥ ስጦታዎችን ሰጠ ስለሚለው አንድ ነገር ነው የሚናገረው። (የይዘት ለውጥ፥ ጽሑፉን ማቀናጀ ከሆኑት ምልክቶች አንዱ መሆኑን ያስታውሱ።) ከ7-11 ያሉት ቁጥሮች የሚገልጡት፥ አንድን ርእሰ ጉዳይ ነው።

ክፍሉን መክፈል የሚኖርብዎ ቁጥር 11 ወይም 12 ላይ መሆኑን መወሰን አለብዎት። እኔ ግን የማስተምረው፥ ሰፋ ያለውን ክፍል (ከቁጥር 7-16) ያለውን እንደ መሆኑ፥ ክፍሉን ቁጥር 12 ላይ ልከፍለው ወስኛለሁ። ከክፍሉ ሁለት ጊዜ የምሰብክ ብሆን ኖሮ፥ ቁጥር 7-10 እና 11-16ትን እሰብክ ነበር። ይህን የማደርገው፥ ቁጥር 11 መጀመሪያ ላይ ያለውን ሰዋስዋዊ ቁልፍ እያንሳሁ ነው።

2. ቁጥር 12 እና 13 የሚነግሩን፥ ጌታ ስጦታዎቹን የሰጠበትን ዓላማ ወይም ምክንያት ነው። ቁጥሮቹ መጨረሻ ገደማ፥ ‘‘ዘንድ’’ የሚለውን ቁልፍ ቃል ልብ ያድርጉ። የሰዋስዋዊው ቁልፎች ሠሌዳዎ (ገጽ 47-48)፥ ‘‘ዘንድ’’ የሚለው ቃል ምክንያትን ወይም ዓላማን የሚገልጥ መሆኑን ያስረዳል። በዚህ ምንባብ፥ ቁጥር 12 እና 13፥ መሢሑ ስጦታዎችን የሚሰጥበትን ምክንያት ወይም ዓላማ ነው የሚገልጡት። እነዚህ ቁጥሮች፥ ከዚህም ሌላ፥ ተመሳሳይ ጉዳይ ወይም ነጠላ ጭብጥን ይጠቅሳሉ። ስጦታዎቹ የተሰጡት፥ ቤተ ክርስቲያን እስክታድግ ለማነጫ ነው።

3. ከቁጥር 14-16 ያሉት ክፍሎች፥ የስጦታዎችን ልገሳ ውጤት ይነግሩናል (ቁጥር 7-13)። እነዚህ ጥቅሶች ክርስቶስ በሰጠው ስጦታ ምክንያት የሚመጣው የጋራ እድገት ውጤቶችንም ያብራራሉ። ‘‘እንግዲህ’’ የሚለውን የቁጥር 14 የመጀመሪያ ቃል ልብ ያድርጉ። ይህ ቃል ከቁጥር 14-16 ያለውን ክፍል በመቆጣጠር፥ ከ7-13

ያሉትን ቁጥሮች ውጤት ያመለክታል። እነዚህ ቁጥሮችም ተመሳሳይ ጉዳይ ወይም ነጠላ ጭብጥ አላቸው።

የክፍሉን ማዕከላዊ አሳብ ለማግኘት ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ክፍሎች ርእስ ጉዳዮች፥ ጭብጦች፥ ዋና ዋና ነጥቦች፥ እና ጠቅለል ያሉ አሳቦችን በአንድ ላይ ያያይዟቸዋል። ወደ ክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ ለመድረስ የክፍሉን አሳብ በትክክል መረዳትዎና አሳቡን በበቂ ሁኔታ መግለጥዎን ማረጋገጥ ይኖርብዎታል። የክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ የሚያጠኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ልዩ በሆነ ሁኔታ የሚገልጥና የክፍሉንም መልእክቶች የሚሸፍን መሆን አለበት። አንድን ክፍለ ምንባብ ለስብከት በምናዘጋጅበት ጊዜ፥ ደረጃ 3ን ከመሥራታችን በፊት ደረጃ 1ንና 2ን ማጠናቀቁ አስፈላጊ ነው።

ለኤፌሶን 4፡7-16 የጻፍኩት የክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ እነሆ! ወደ ሰማይ ያረገው ክርስቶስ ስጦታዎችን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠበት ዓላማ፥ ለአገልግሎት በተዘጋጁና በኅብረት በሚሠሩ አገልጋዮች አማካይነት ቤተ ክርስቲያን በቃሉ እውቀት የበሰለችና በአገልግሎቱ የጸናች እንድትሆን ለማድረግ ነው።

እስቲ ይህን ቃል እንከፋፍለው። ርእስ ጉዳይ፥ ደራሲው የሚናገረው ስለምንድነው? ደራሲው እራሱ ስለሚናገረው ነገር ምንድነው የሚለው?

**ጭብጥ**

የአንድ አንቀጽ ርእስ ጉዳይ፥ ከአንቀጹ አሳብ ጋር በትክክል መገናኘት አለበት። ‘‘ከኤፌሶን 4፡7-16 ባለው ክፍል፥ ደራሲው ስለምንድነው የሚናገረው?’’ ብዬ ስለ አንቀጹ ርእስ ጉዳይ ምንነት ብጠይቅዎ፥ እና እርስዎም፥ ‘‘ስለ መንፈሳዊ ስጦታ’’ ነው ቢሉኝ፥ መልስዎ ትክክል ነው። ነገር ግን ከክፍሉ አሳብ ጋር ብቻ የተገናኘ አይደለም። ምክንያቱም እርስዎ የሰጡኝ ርእስ ጉዳይ፥ ለሮሜ 12፥ ለ1ኛ ቆሮንቶስ 12 ወይም ለ1ኛ ጴጥሮስ 4፡7ትም ይስማማል። እንደዚሁም በመልስዎ፥ ርእስ ጉዳዩ ‘‘አካሉን ማነጽ ነው’’ ሊሉ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ፥ ርእስ ጉዳዩ ትክክል ይሆናል፤ የአንቀጹን አሳብ በሙሉ በመጠቅለል ረገድ ግን ‘‘በቂ’’ አይደለም።

የአንድን ክፍል ትክክለኛና አሳቦቹን ሁሉ የሚሸፍን ማዕከላዊ ርእስ ጉዳይ ለማግኘት፥ ከክፍሉ ያገኟቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ሁሉ በውስጡ ማካተት አለብዎ። ሰዋስዋዊ ወይም የይዘት ምልክቶች፥ የክፍሉን ዋና ርእስ ጉዳይ (ደራሲው የሚናገረው)፥ የቱ መሆኑን ይገልጡልዎታል። አሁን በምናጠናው ምንባብ ደራሲው የሚናገረው፥ ወደ ሰማይ ያረገው ክርስቶስ፥

መንፈሳዊ ስጦታዎችን የሰጠበትን "ዓላማ" ነው። በክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ ውስጥ ይህን "ዓላማ" የሚገልጡ ቃላት ወይም ፅንሰ-አሳቦችን ካላስገቡበት ማዕከላዊ አሳቡ የክፍሉን አሳብ በትክክል አይገልጠውም።

**ጭብጡ (መልእክቱ)**

የርእሰ ጉዳዩ መልእክት /ጭብጥ ምንድነው? ደራሲውስ ስለ ርእሰ ጉዳዩ ምን ይላል? ደራሲው ቀጥሎ ያለውን ነው የሚለው፤ ክርስቶስ ስጦታ የሰጠበት ዓላማ ለአገልግሎት በተዘጋጁና በኅብረት በሚሠሩ አገልጋዮች አማካይነት ቤተ ክርስቲያን በቃሉ እውቀት የበሰለችና በአገልግሎቷ የጸናች እንድትሆን ለማድረግ ነው። ስለዚህ የዚህ ክፍለ-ምንባብ ማዕከላዊ አሳብ ሙሉ ዓረፍተ ነገር ይህ ነው። ወደ ሰማይ ያረገው ክርስቶስ፥ ስጦታዎችን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠበት ዓላማ፥ ለአገልግሎት በተዘጋጁና በኅብረት በሚሠሩ አገልጋዮች አማካኝነት ቤተ ክርስቲያን በቃሉ እውቀት የበሰለችና በአገልግሎቷ የጸናች እንድትሆን ለማድረግ ነው።

### >> የድርጊት እርምጃ <<

ከኤፌሶን 6፡10-12 ባለው ክፍል ላይ በመመሥረት፥ ከላይ የተመለከተውን መልመጃ ይሥሩ። የዚያን አጭር አንቀጽ ማዕከላዊ አሳብ፥ ማለት ርእሰ ጉዳይና ጭብጥ (መልእክት) ያውጡ።

. . . . . . . . . . . . . . . . .

## የጽሑፍ ሥራዎ ቅንጅት

በእግዚአብሔር ቃል አቀነባበር ሥራ ሂደት እዚህ ሲደርሱ፥ በክፍሉ ላይ ያደረጉትን ዝርዝር ጥናት (ደረጃ 1-3)፥ በአንድ ወይም በሁለት ገጾች ላይ ማሰባሰብ ያስፈልግዎታል። ከዚያ ነው መልእክትዎ አቅጣጫ የሚይዘው (ደረጃ 4-7)። ጥናትዎን በሚከተለው መንገድ ለማቀናበር በቂ ጊዜ ሊሰጡት ይገባል። ናሙና አሠራሮች እነሆ!

- ለክፍለ-ምንባቡ ጊዜያዊ ርእስ ይስጡት። ይህ የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ፥ "ርእሰ ጉዳይ" ሊሆን ይችላል።
- ከተቻለ፥ የክፍለ ምንባቡን አካሄድ ወይም አሳብ በማሳየት በራስዎ አባባል ክፍሉን በቀላል አገላለጥ ይጻፉት/ይተርጉሙት። ክፍለ ምንባቡን በቀላል አገላለጥ በሚያቀርቡበት ጊዜ፥ ደራሲው አሳቡን ያቀረበበትን መንገድ የተረዱ ለመሆንዎ እርግጠኛ ይሁኑ። ይህን የሚመለከት ምሳሌ ኤፌሶን 4፡11-13 ላይ ተመሥርቶ ወደፊት ይቀርባል።

- ክፍለ ምንባቡን ማዕከላዊ አሳብ ይጻፉ፤ (ርእሰ ጉዳይና ጭብጡን ወይም መልእክቱን በሙሉ ዓረፍተ ነገር ይጻፏቸው። ዓረፍተ ነገሩ ረጅም መሆን አያስፈልገውም፤ ግን በቂ ወይ ሙሉ መሆን አለበት። በሥራዎ ሂደት ግልጥ ሊያደርጉትና ሊያሳጥሩት ይችላሉ።)
- አከፋፈሉን (ቢጋሩን) ይጻፉ (ዋና ዋናዎቹና ንዑሳን ነጥቦች ሁሉ በሙሉ ዓረፍተ ነገር መጻፍ አለባቸው።)

ክፍሉን በተመለከተ ፥ የመልእክት ዝግጅት ሂደቱን እዚህ ላይ ይጨርሳሉ።

. . . . . . . . . . .

## የክፍለ-ምንባብ ዝግጅትዎ አሠራር ናሙና

የምንባቡ ርእስ

(የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል)

ቀላል አገላለጥ ወይም ትርጉም

ቁጥር 1

ቁጥር 2

ቁጥር 3

የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ

ርእሰ ጉዳይ

ጭብጥ

**ሙሉ ገለጣ፡-** የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ ርእሰ ጉዳዩንና ጭብጡን፥ (መልእክቱን) በአንድ ዓረፍተ ነገር ያሰፍራል።

አከፋፈል (Outline)

I.

ሀ.

1.

2.

ለ.

1.

2.

III.

*ሀ.*

*ኤፌሶን 4፥ 11-13 ላይ የተመሠረተ አሠራር ናሙና*

**መለኮታዊ ስጦታዎች የተሰጡበት ዓላማ**

ኤፌሶን 4፥ 11-13 (የ1980 ዓ.ም እትም)

**ቀላል አገላለጥ ወይም ትርጉም** (Paraphrase)

ቁ 11 እርሱም (ወደ ሰማይ ያረገው ክርስቶስ)፥ አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ አንዳንዶቹ የወንጌል ሰባኪዎች፥ አንዳንዶቹ የምእመናን እረኞች፥ አንዳንዶቹ አስተማሪዎች፥ እንዲሆኑ ስጦታዎችን ሰጠ።

ቁ 12 ይህን ያደረገው፥ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ (ለማዘጋጀት)፥ ምእመናንን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ለማዘጋጀት ነው።

ቁ 13 እንዲሁም የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ በእምነት ወደሚገኘው አንድነት ደርሰን፥ ክርስቶስ ፍጹምና ሙሉ እንደሆነ፥ እኛም ሙሉ ሰው እንድንሆን ነው።

**የክፍለ- ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ**

*ርእሰ ጉዳይ፦* ወደ ሰማይ ያረገው ክርስቶስ ሰዎችን ለቤተ ክርስቲያን እንደ ስጦታ የሰጠበት ምክንያት

*ሟሟያ፦* ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን ወደ መምሰል ታንጻ ታድግ ዘንድ ነው።

*የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ፥ ሙሉ ዓረፍተ ነገር፦* ወደ ሰማይ ያረገው ክርስቶስ፥ ሰዎችን ለቤተ ክርስቲያን እንደ ስጦታ የሰጠበት ዓላማ፥ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን ወደ መምሰል ታንጻ ታድግ ዘንድ ነው።

**አከፋፈል** (Outline)

I. ወደ ሰማይ ያረገው ክርስቶስ በአራት ምድብ የተከፈሉ ሰዎችን ለቤተ ክርስቲያን እንደ ስጦታ ሰጠ።

ሀ. አንዳንዶችን ሐዋርያት አድርጎ ሰጠ።

ለ. አንዳንዶችን ነቢያት አድርጎ ሰጠ።

ሐ. አንዳንዶችን ወንጌላውያን አድርጎ ሰጠ።

ረ. አንዳንዶችን መጋቢያንና አስተማሪዎች አድርጎ ሰጠ።

II. እነዚህን ሰዎች የሰጠበት ዓላማ፥ ቤተ ክርስቲያን ትታነጽ ዘንድ ነው። (ቁጥር 12)

ሀ. እነዚህ ሰዎች የተሰጡት፥ ቅዱሳንን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ለማዘጋጀት ነው። (12)

ለ. ቅዱሳንን የማዘጋጀት ውጤቱ፥ የአካሉ መታነጽ ነው። (12)

III. ሰዎቹ የተሰጡት፥ ቤተ ክርስቲያን በአንድነት ክርስቶስን ወደ መምሰል እስክታድግ ድረስ ቅዱሳንን ለማዘጋጀት ነው። (13)

ሀ. እነርሱ የተሰጡት፥ ሁላችንም በእምነት ወደሚገኘውና የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ ላይ ወደተመሠረተው አንድነት እስክንደርስ ድረስ ቅዱሳንን ለማዘጋጀት ነው። (13)

ለ. ሙሉ ሰው እስክንሆን ድረስ ቅዱሳንን ለማዘጋጀት ነው። (13)

መ. ሁላችንም ፍጹም ክርስቶስን ወደመምሰል እስክናድግ ድረስ ቅዱሳንን ሊያዘጋጁ ነው። (13)

## >> የድርጊት እርምጃ <<

መዝሙር 117 ላይ በመመሥረት ከ1-3 ያሉትን ደረጃዎች እንከልሳቸዋለን። ከመዝሙሮች ሁሉ አጭርና ቀላል የሆነው መዝሙር 117፥ በክፍል ትምህርት ጊዜ ለመሥራት ይወደዳል። በሚቀጥሉት ገጾች ላይ የሰፈሩትን መልመጃዎች ማጥናት ከመጀመርዎ በፊት፥ መዝሙር 117ን ደጋግመው ያንብቡት።

ቁ 1. አሕዛብ ሁላችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑት፥ ወገኖችም ሁሉ ያመስግኑት፤

ቁ 2. ምሕረቱ በእኛ ላይ ጸንታለችና፥ የእግዚአብሔርም እውነት ለዘላለም ትኖራለች። ሃሌ ሉያ።

## ደረጃ 1፡- ክፍለ ምንባቡን ያጥኑ

መዝሙረ ዳዊትን በሚያጠኑበት ጊዜ፥ "አመስግኑ፥ ሁሉ፥ ሕዝቦች፥ አሕዛብ፥ ምሕረቱ፥ እውነት" የሚሉ ቃላትን ያስተውሉ። ቃላቱን ሲያጠኑ፥ መልእክትዎን የሚያለብስ "ሥጋ" ያገኙበታል።

## ደረጃ 2፡- ክፍለ ምንባቡን ያቀናጁ

ከላይ የተመለከትነውን የመዝሙረ ዳዊት ክፍል ቅንጅትን በሚመለከት ወሳኙ ፊደል "ና" የሚለው ነው- (ቁጥር ሁለት ውስጥ

ጸንታለችና የሚለው ሰዋሰዋዊ ቁልፍ)። የምንባቡ አጥንት ቀጥሎ ያለውን አከፋፈል ሊመስል ይችላል።

1. *መዝሙረኛው፥ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑት* ይላል (ቁ.1)

2. የእግዚአብሔር ምሕረትና እውነት መመስገን አለበት (ቁ.2)

## ደረጃ 3፦ የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ

የዚህ *መዝሙር* ርእስ ጉዳይ ምንድነው? በደንብ ያሰላስሉና ቀጥሎ ያለውን ዓረፍተ ነገር ይጨርሱት

*መዝሙር* 117 ውስጥ ደራሲው የሚገልጠው______________

______________________________________________________።

ደራሲው የሚገልጠው፥ "ጌታን ስለማመስገን" ነው ብለው ከመለሱ በከፊል ትክክል ነዎት። በከፊል ያልኩበት ምክንያት፥ "ና" ለሚለው ጠቃሚ ሰዋሰዋዊ ቁልፍ በቂ ትኩረት ስላልሰጡት ነው። ደራሲው የሚገልጠው "ጌታን ስለማመስገን" ብቻ አይደለም። (አብዛኛዎቹን የምስጋና መዝሙሮች በተመለከተ፥ ይህ መልስ ትክክል ነው)። እዚህ ላይ ግን ደራሲው የሚገልጠው፥ "ሰዎች እግዚአብሔርን ለምን ሊያመሰግኑት እንደሚገባ ነው።" ይህን ትኩረት የሚያገኙት "ጸንታለችና" በሚለው ቃል መጨረሻ ባለው ፊደል፥ "ና" ላይ ነው። (ሥራዎን በሰዋሰዋዊው ሠሌዳ ላይ አመሳክረዋል?)

የምንባቡ መልእክትስ ምንድነው? ደራሲው፥ እራሱ ስለሚናገረው ነገር የሚለው ምንድነው? ቀጥሎ ያለውን ዓረፍተ ነገር ይጨርሱት፤

ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገን የሚኖርባቸው _______

______________________________________________________።

ሥራዎን በሚገባ ካከናወኑ፥ የክፍለ ምንባቡን ማዕከላዊ አሳብ በተመለከተ ቀጥሎ ያለውን የሚመስል ዓረፍተ ነገር ያገኛሉ፥ የዓለም ሕዝቦች በሙሉ እግዚአብሔርን ማመስገን የሚኖርባቸው፥ ስለ ምሕረቱና ስለ እውነቱ ነው።

ከላይ ያለውን ዓረፍተ ነገር በሚገባ ያሰላስሉት። እንዴት እንዳገኙሁት ሊረዱ ይችላሉ? የእግዚአብሔር ቃልን የመግለጥ እርግጠኛ ፍላጎት ካለዎ፥ ደራሲው አበክሮ የሚናገረውን፥ ማለት የክፍሉን እውነት፥ በሕዝብዎ አእምሮ ውስጥ ለማስረጽ ይጥራሉ። ትክክለኛውን ማዕከላዊ አሳብ ለማግኘት፥ ይህን የተረጋገጠ፥ ምናልባትም አድካሚ አሠራር ሊጠቀሙበት ይገባል። የክፍሉ አሳብ እንዲዋሐድዎም የማድረጊያ ድንቅ

*መንገድ ይህ ነው። እንዲያ ሲሆን፥ ክፍሉን በአእምሮ መሸምደድ አይኖርብዎትም። ለስብከት በተዘጋጁበት ጊዜ በሚገባ ያውቁታል።*

## >> የድርጊት እርምጃ <<

ቀጥሎ ላለው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ፥ ማዕከላዊ አሳቡን ለማግኘት ይሞክሩ፤ ኤፌሶን 6፡1-4።

1. ልጆች ሆይ፥ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ ይህ የሚገባ ነውና

2.፥ 3. መልካም እንዲሆንልህ፥ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም፥ አባትህንና እናትህን አክብር፥ እሷም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት።

4. እናንተ አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሳጽ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጧቸው።

ርእሰ ጉዳይ ________________________________________

________________________________________________________።

ጭብጡ፡- __________________________________________

________________________________________________________።

የክፍለ ምንባቡን ማዕከላዊ መልእክት። __________________

________________________________________________________።

ከቁጥር 1-3 ላለው ጽሑፍ፥ ማዕከላዊ መልእክትዎ ምን ሊሆን ይችላል?

ርእሰጉዳይ ________________________________________

________________________________________________________።

ጭብጡ ____________________________________________

________________________________________________________።

የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ መልእክት _____________________

________________________________________________________።

የክፍለ ምንባቡ ቁጥር 4 ማዕከላዊ አሳብ ምንድነው?

ርእሰ ጉዳይ ________________________________________

________________________________________________________።

ጭብጡ ________________________________________

________________________________________________________፡፡

የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ__________________________

________________________________________________________፡፡

የኤፌሶን 6፡10-12ን ማዕከላዊ መልእክት ሠርተዋል፤ ቀጥሎ ይጻፉት።

ርእሰ ጉዳይ ________________________________________

________________________________________________________፡፡

ጭብጡ________________________________________

________________________________________________________፡፡

የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ __________________________

________________________________________________________፡፡

# 4

# የዓላማ መሸጋገሪያ

>> የስብከቱ "አንጓል" <<

ደረጃ 7: ስብከቱን መስበክ

ደረጃ 6: ስብከቱን ማቀናጀት

ደረጃ 5: የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ

**ደረጃ 4: የዓላማ መሸጋገሪያ ወይም ድልድይ**

ደረጃ 3: የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ

ደረጃ 2: ክፍለ ምንባቡን ማቀናጀት

ደረጃ 1: ክፍለ ምንባቡን ማጥናት

አሁን እጠቅላላው ስብከት አዘገጃጀት ወሳኝ ክፍል ላይ ደርሰናል። ይህን መሸጋገሪያ በሚያቋርጡበት ጊዜ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ከማጥናት ወይም ቃሉን ከመተርጎም፥ ቃሉን ወደ መስበክ ወይም ወደ ማስተማር ተግባር ይሸጋገራሉ። ደረጃ 4 የዓላማ መሸጋገሪያ ድልድይ የሚያንጹበትና የሚሻገሩበት ነው። ደረጃ 4፥ ገላጭ ስብከታችን አድማጮቻችን ካሉበት ሁኔታ ጋር አብሮ የሚሄድ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ዋናው ነው። በዚህ ጊዜ፥ የስብከት ዝግጅቱ ቀዳሚ ሥራ ተከናውኗል። የስብከቱ የላይ አካል፥ "ሥጋ" (ደረጃ 1)፥ ውስጠኛ አካል "አጥንት" (ደረጃ 2)፥ እና "ልብ" (ደረጃ 3) ተለይተው ታውቀዋል። የአካሉ አጥንቶች ቅንብር፥ ዋና ዋናዎቹ ነጥቦች፥ ንዑሳን ነጥቦችና፥ ንዑሰ-ንዑሳን ነጥቦች ሰዋሰዋዊና ይዘታዊ ቁልፎችን ተከትለው ተሠርተዋል። ስለዚህ አሁን ወደ ስብከቱ አንጓል ወይም ወደ ስብከቱ ዓላማ ደርሰናል።

## የዓላማ ዓላማ

ዓላማ፥ የስብከቱ አንጓል እንደመሆኑ መጠን፥ የመልእክት ዝግጅትና ስብከት ሁኔታዎችን ይቆጣጠራል። የስብከቱ ትክክለኛና የተረጋገጠ ዓላማ ከሚሰጠው ጥቅሞች ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ተዘርዝ ረዋል።

- የስብከትዎ መግቢያ፥ በስብከትዎ በሚጠቀሰው አስፈላጊ ነገር ላይ እንዲያተኩር ያደርጋል።

- አንድ ስብከት ውስጥ ሊካተት ወይም ከስብከቱ ሊወገድ የሚገ ባውን ነገር ይወስናል።
- የስብከቱን ማጠቃለያም ሆነ፥ የሚነሡ የማዛመድ አሳቦችን ለመወሰን ይረዳል። የስብከቱን ዓላማ ለመፈጸም የሚረዱ ምሳሌዎችን ለመምረጥ ያገለግላል።
- ስብከቱ ግቡን መምታቱን ለመረዳት የሚያስችል ሚዛናዊ መለኪያ ይሰጣል።
- ከሁሉም ይልቅ፥ የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ የሚያነሳው ርዕሰ ጉዳይ ምን መምሰል እንዳለበት ለማወቅ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

የስብከት ዓላማ፥ ከስብከት ምንባቡ ወደ ስብከቱ ዋና መሸጋገሪያ በመሆን ረገድ ያለውን አገልግሎት አጋንኜ ለማቅረብ አልችልም።

## የስብከቱን ዓላማ መወሰን

እንዴት ነው አንድ ሰባኪ የስብከቱን ዓላማ የሚያገኘውና የሚገልጠው? የስብከትን ዓላማ የምናገኘው (የዓላማ መሸጋገሪያ ድልድይ የምንሠራው)፥ ከዚህ በታች ያለውን ጥያቄ በመጠየቅና፥ እራሳችን ለጥያቄው መልስ በመስጠት ነው፤ "በዚህ የስብከት ክፍል ማዕከላዊ አሳብ መሠረት፥ አድማጮች እንዲረዱትና እንዲታዘዙት እግዚአብሔር የሚፈልገው ምንድነው?"

እዚህ ላይ ዋናው ትኩረት፥ የስብከት ክፍሉ ዓላማ አለመሆኑን ልብ ያድርጉ። ዓላማው፥ የክፍሉን ማዕከላዊ አሳብ ለመወሰንና ዝርዝር አሳቦችን ዐውደ ንባቡን በማጥናት ሥራዎ ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል። በርግጥ የስብከቱ ዓላማ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲው(ያኑ) ከአንባቢዎቻቸው ይጠብቁት ከነበረው መልስ ጋር ተያያዥነት ይኖረዋል።

## የስብከትዎን ዓላማ እና የስብከት ክፍሉን ዓላማ ማገናኘት

በክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ ላይ የተመሠረተውን የስብከትዎን ዓላማ በሚጽፉበት ጊዜ፥ ስምምነትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ሁለት ጥያቄዎችን መመለስ አለብዎ፤

1. የስብከቱ ዓላማ ከስብከት ክፍሉ ዓላማ ጋር የሚስማማ መሆኑን ለማረጋገጥ ሥነ-መለኮታዊ (ነገረ መለኮታዊ) ወይም በክፍሉ ጥናት ላይ

የተሠረተ ማስረጃ ለማቅረብ እችላለሁ? ይህ ጥያቄ፥ አንድ ሰባኪ ለሚሰብከው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ታማኝ እንዲሆን ይረዳዋል።

2. ስብከቴ ከአድማጩ ወይም አንባቢዩ ፍላጎት ጋር የተስማማ ለመሆኑ፥ ሶሲዮሎጂያዊ ወይም ሥነ-አእምሯዊ ድጋፍ አለኝ? ይህ ጥያቄ፥ አንድ ሰባኪ ለአድማጩ የሚጠቅም ነገር እንዲያቀርብ ይረዳዋል።

የስብከት ክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ የሚመሠረተው፥ በዋናነት በሚሰበከው ምንባብ ላይ ነው። እንግዲህ፥ በስብከት ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ ላይ በመመሥረት፥ የሕዝቡን ግንዛቤና ታዛዥነት በሚመለከት ምን ላደርግ እችላለሁ?

አድማጮችዎን ወይም አንባቢዎችዎን በሚገባ ማወቅ ያስፈልግዎታል። የዓላማዎን መሸጋገሪያ በሚያቀናብሩበት ጊዜ፥ ቀጥሎ ያለውን ዋና ጥያቄ ይጠይቁ:- ከዚህ ጽሑፍ ማዕከላዊ አሳብ ጋር በተዛመደ፥ የአድማጩ ፍላጎቶችና ሁኔታዎች ምንድናቸው?

አድማጮችዎን የሚያውቋቸው፥ ከነሱ ጋር ጊዜ በማሳለፍ ነው። ለሁሉም አድማጭ የሚሆኑ ጥሩ ስብከቶች የሉም። "የርቀት" የእረኝነት አገልግሎት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚደገፍ፥ ወይም በጉባኤ የሚወደድ አይደለም።

## የዓላማ መሸጋገሪያ

**ቁጥር 1 ጉዳይ:- የአድማጮቼ ፍላጎቶችና ሁኔታዎች ምንድናቸው?**

ሁለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች ላይ፥ ማለት ኢሳይያስ 19፥18-25 እና ኤፌሶን 4፥7-16 ላይ በመመሥረት የደረጃ 4ን አሠራር ልግለጥ። እርስዎ ደግሞ ኤፌሶን 6፥10-12ን ይሠሩታል።

*ኢሳይያስ 19፥18-25*

ቁ 18 በዚያ ቀን በግብፅ ምድር፥ በከነዓን ቋንቋ የሚናገሩ፥ በሠራዊት ጌታ፥ በእግዚአብሔርም የሚምሉ፥ አምስት ከተሞች ይሆናሉ። ከነዚህም አንዲቱ፥ የጥፋት ከተማ ተብላ ትጠራለች።

ቁ 19 በዚያ ቀን በግብፅ ምድር መካከል ለእግዚአብሔር መሠዊያ፥ በዳርቻዋም ለእግዚአብሔር ዓምድ ይሆናል።

ቁ 20 ይህም ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር፥ በግብፅ ምድር ምልክትና ምስክር ይሆናል። ከሚያስጨንቋቸው የተነሣ፥ ወደ እግዚአብሔር ይጮኻሉና፥ እርሱም መድኃኒትንና ኃያልን ሰድዶ ያድናቸዋል።

ቁ 21 በዚያም ቀን እግዚአብሔር በግብፅ የታወቀ ይሆናል፥ ግብፃውያንም እግዚአብሔርን ያውቃሉ። በመሥዋዕትና በቁርባን ያመልካሉ። ለእግዚአብሔርም ስእለት ይሳላሉ፥ ይፈጽሙትማል።

ቁ 22 እግዚአብሔርም ግብፅን ይመታታል፥ ይፈውሳታልም። ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ። እርሱም ይለመናቸዋል፥ ይፈውሳቸውማል።

ቁ 23 በዚያ ቀን ከግብፅ ወደ አሦር መንገድ ይሆናል፤ አሦራዊውም ወደ ግብፅ፥ ግብፃዊውም ወደ አሦር ይገባል፤ ግብፃውያንም ከአሦርያውያን ጋር ይሰግዳሉ።

ቁ 24፥ 25 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፥ ሕዝቤ ግብፅ፥ የእጄም ሥራ አሦር፥ ርስቴም እስራኤል፥ የተባረከ ይሁን ብሎ ይባርካቸዋልና በዚያ ቀን፥ እስራኤል ለግብፅና ለአሦር ሦስተኛ ይሆናል፤ በምድርም መካከል በረከት ይሆናል።

የመካከለኛው ምሥራቅ ችግር በ1991 ዓ.ም. የዓለምን ትኩረት ስቦ ነበር። በመላው አሜሪካ ደግሞ፥ የድካምና የድል፥ የኀዘንና የኃይል፥ የደስታና የንቀት ምስቅልቅል ስሜት ገንኖ ታይቷል። በዚህ አሳሳቢ ጊዜ፥ በዳላስ ሴሚናሪና በዊተን ኮሌጅ የአምልኮ ፕሮግራም ላይ በስብከት ማገልገል ነበረብኝ። በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ፥ በጊዜው ባሕረ ሰላጤው ውስጥ ይደረግ የነበረውን ጦርነት የሚደግፋና የሚቃወሙ ቡድኖች ነበሩ።

ለስብከቴ የመረጥኩት ክፍል ኢሳይያስ 19፡18-25 ነበር። በስብከት ዝግጅቴ ሂደት፥ ደረጃ 1 እና 2ን ካከናወንኩ በኋላ፥ ደረጃ 3 ላይ ደረስኩ።

የዚህ ክፍል ማዕከላዊ አሳብ እንደሚከተለው ነው፦ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ያሉ የእስራኤል ጠላቶች፥ ወደ ፊት በሚመሠረተው የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፥ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝቦች ወደ መሆን ይለወጣሉ።

የዚህ ትንቢታዊ ገለጣ ማዕከላዊ አሳብ የሚገልጠው፥ እሩቅ ስላለ (ያለፈና ወደፊት የሚሆን) አሳብ ቢሆንም፥ አሁንም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ። በመሆኑም መሰበክ አለበት፤ ምክንያቱም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ሁሉ እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያለበትና ጠቃሚ ነው።

መሸጋገሪያው (ደረጃ 4)፥ የስብከቴን ትኩረትና ኃይል ለመለየት ይረዳኛል። ከዚህ ክፍል ምንባብ ብዙ ዓላማዎች ሊሰበኩ ይችላሉ። የተስማሚነት ጥያቄን ከጠየቅሁ በኋላ ቀጥሎ ያሉትን ጻፍኩ፥

1. የእግዚአብሔር የማዳን ጸጋ አንድ ቀን ለእስራኤል ጠላቶች የሚደርሳቸው መሆኑን ለማረጋገጥ

2. የመካከለኛው ምሥራቅ ፖለቲካዊ ችግር አንድ ቀን መፍትሔ የሚያገኝ የመሆኑን ተስፋ ለመስጠት

እነዚህ ዓላማዎች ከመጽሐፍ ቅዱስና ከአድማጮቼ ፍላጎት ጋር ይስማማሉ። እነዚህን ብቻ ተግባር ላይ ባውል እንኳን፥ በነሱ ላይ ተመሥርቼ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ላስተምርና ለአድማጮቼ አንድ ተስፋ ላስጨብጣቸው እችላለሁ።

ለአይሁድ አድማጮች፥ ከራሳቸው ብሉይ ኪዳን ላይ በመነሣት ዓላማ 1ን ብሰብክላቸው እወዳለሁ። ዓላማ 2ን መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ለሚገኙ ዓረባውያን አማኞች አስተምሬአቸዋለሁ። ለአሁኑ ስብከቴ ግን፥ ሦስተኛ ዓላማ ለመፈለግ ወሰንኩ። ይህም ቢሆን፥ ከመጽሐፍ ቅዱስና ለአድማጮቼ (ለተንጻውና ለተከፋፈለው አሜሪካዊ አድማጭ)፥ የሚስማማ መሆን አለበት። የጻፍኩትም የስብከቴ ዓላማ እንዲህ የሚል ነበር። አድማጮቼ፥ አሁን ካለባቸው ታሪካዊ የጦርነት ፍርሃት ባሻገር፥ እግዚአብሔር ወደፊት በሚመሠረተው መንግሥቱ፥ ለመካከለኛው ምሥራቅ ያለውን ዓላማ እንዲጨብጡ መርዳት።

ከክፍሉ ሊሰበኩ የሚችሉ ስብከቶች ቁጥር ገደብ የላቸውም ማለት አይደለም። ነጻ የሚያደርግዎትም ሆነ የሚገድብዎት፥ የክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ ነው። የክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ በሚፈቅድልዎ መጠን፥ በተለያዩ ዓላማዎች ላይ ተመሥርተው የተለያዩ መልእክቶችን ሊሰብኩ ይችላሉ። የመልእክቱን ዓላማ ከመረጡ በኋላ፥ ለሚያገለግሉት አድማጭ በሚስማማ መንገድ ማቀናጀት አለብዎ።

### *ኤፌሶን 4:7-16*

ከኤፌሶን 4፡7-16 ካለው ክፍል ማዕከላዊ አሳብ በመነሣት፥ አንድ ሰው ሊሰብክባቸው የሚቻሉት፥ ቢያንስ ሦስት ዓላማዎች አሉ። ለክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ በደረጃ 3 ላይ የያዙትን ማስታወሻ ይመልከቱ። ዓላማዎቹ እነሆ!

1. በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለ እያንዳንዱ አማኝ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ያለው መሆኑን ለአድማጮች ማሳወቅ

2. አማኞችን ለአገልግሎት ያስታጥቋቸው ዘንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ማነሣሣት

3. ቤተ ክርስቲያን ትታነጽ ዘንድ፥ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ዕቅድ እንዳለው አማኞችን በማስገንዘብ፥ ይህንንም ዓላማውን በሕይወታቸው እንዲለማመዱት ማነሣሣት

በአጠቃላይ ሁኔታዎችና በአንድ ልዩ ሁኔታ ላይ በመመሥረት፥ ዓላማ ቁጥር 3ን መረጥኩ። በአጠቃላይ፥ እውቀትን ከማስጨበጥ ይልቅ፥ በባሕርይ ለውጥ ላይ ያተኮረ ዓላማ ያለው መልእክት ብሰብክ እወዳለሁ። በባሕርይ ለውጥ ላይ ያተኮረ ዓላማ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መልእክት ላይ ይመሠረታል። ይህን በማደርግበት ጊዜ፥ እውቀትን ለማስጨበጥ ዓላማዬ ታማኝ ሆኜ፥ በአድማጮች ሕይወት ላይ ለውጥ እንዲታይም መጠየቅ እችላለሁ።

በተለይ ቤተ ክርስቲያኔ ውስጥ ያሉትን አድማጮችና የቤተ ክርስቲያኔን ፍላጎት ከግንዛቤ ማስገባት ይኖርብኛል። ዓላማ 3 ከቤተ ክርስቲያኔ ሁኔታ ጋር ይስማማል። በሌላ ስፍራ፥ መልእክቴን ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብቻ በማቀርብበት ጊዜ፥ ዓላማ 2ን እከተላለሁ። ይህ ማለት፥ በአንድ የስብከት ክፍል ላይ በመመሥረት፥ ክፍሉን በሁለት ዓይነት መንገድ፥ ለሁለት የተለያዩ አድማጮች ልሰብክ እችላለሁ። ይህ ሲሆን፥ የሁለቱ ስብከቶች አብዛኛው ክፍል ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል።

## >> የድርጊት እርምጃ <<

በንባብዎ ከመግፋትዎ በፊት፥ ለኤፌሶን 6፡10-12 ከጻፉት የክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ በመነሣት የዓላማ መሸጋገሪያውን ያግኙ። የአድማጮችዎን ፍላጎቶችና ሁኔታዎች ከግንዛቤ ያስገቡ። "... ዘንድ" በሚል መዝጊያ የዓላማ መሸጋገሪያዎን ይጻፉ። የዓላማ መግለጫዎች ሁል ጊዜ "ዘንድ" የሚለው ቃል ይኖራቸዋል። ለሚያቀርቡት ክፍል ማዕከላዊ አሳብ ብዙ ዓላማዎች ይኖርዎት ይሆናል። አሁን ማንበብዎን ይቀጥሉ።

የዚህ ክፍለ ምንባብ (ደረጃ 3)፥ ማዕከላዊ አሳብ ቀጥሎ ያለውን ይመስላል:-

*ርዕሰ ጉዳይ (Theme):-* የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ መልበስ ያስፈለገበት ምክንያት

*ጭብጥ (መልእክቱ):-* የዲያቢሎስን ሽንገላ ለመቃወምና ከአሠራሩ ጋር ለመታገል ያስችለናል።

*ሙሉ መግለጫ:-* የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ መልበስ፥

የዲያቢሎስን ሽንገላ ለመቃወምና፥ ከአሠራሩ ጋር ለመታገል ያስችለናል።

ከዚህ ማዕከላዊ አሳብ በመነሣት የሚሰብኳቸው አንዳንድ ዓላማዎች ምንድናቸው? (ደረጃ 4)። ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ሰፍረዋል፡-

1. የዲያቢሎስን አሠራርና መንገዶቹን ለሕዝብ ማሳወቅ
2. ከዲያቢሎስ ጋር ላለባቸው ትግል፥ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ይለብሱ ዘንድ ሰዎችን ለማበረታታት

እነዚህ ሁለት ዓላማዎች፥ በትክክል ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተወሰዱ ናቸው። የመጀመሪያው በማወቅ፥ ሁለተኛው ደግሞ በሕይወት ለውጥ ላይ ያተኩራሉ። እኔ ግን በሁለት ምክንያቶች ሁለተኛውን ዓላማ እመርጣለሁ። ይሄውም አንደኛ፥ የሕይወት ለውጥ ዓላማን አስመልክቼ እየሠራሁ፥ የማሳወቅ ዓላማንም ልፈጽም እችላለሁ። በሌላ በኩል፥ የዚህ ክፍል ዓላማ፥ እውቀትን ከማስተላለፍ የሰፋ ነው። ሁለተኛ፥ የአድማጮቼ ፍላጎት፥ ስለ ሰይጣን ከማወቅ ብቻ ይልቅ፥ እንዴት ሊቃወሙት እንደሚገባ መረዳት ነው። ይበልጥ ግልጥ ለማድረግ፥ ዓላማው የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ "ምንነት" እና "እንዴት" መልበስ እንዳለባቸው ለአድማጮች ማስገንዘብ አይደለም፤ እሱ ከቁጥር 13-17 ባለው ክፍል ይገኛል። አጥብቀን መያዝ የሚኖርብን የክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ የሚኖሩትን ዓላማዎች ነው፤ አድማጮች የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሊለብሱ የሚገባበት ምክንያት።

. . . . . . . . . . .

*ስለሚቀጥለው ደረጃ (ደረጃ 5) ፍንጭ፡-* የዓላማ መግለጫዎ አብዛኛውን ጊዜ በጥሬ ቅርፁ የሚሰጠው፥ የስብከት ማዕከላዊ አሳብን ርእሰ ጉዳይ ነው።

# 5

# የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ

**>> የስብከቱ "ልብ" <<**

ደረጃ 7፡ ስብከቱን መስበክ

ደረጃ 6፡ ስብከቱን ማቀናጀት

**ደረጃ 5፡ የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ**

ደረጃ 4፡ የዓላማ መሸጋገሪያ ወይም ድልድይ

ደረጃ 3፡ የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ

ደረጃ 2፡ ክፍለ ምንባቡን ማቀናጀት

ደረጃ 1፡ ክፍለ ምንባቡን ማጥናት

ከደረጃ 1-3 ባለው ክፍል ለሥራችን የሚያስፈልጉ ነገሮችንና የክፍለ ምንባቡን ማዕከላዊ አሳብ አግኝተናል። ማዕከላዊ አሳቡም የአድማጮቻችንን ሕይወት በሚነካ መልኩ እንዲተላለፍ አቅጣጫ (የዓላማ መሸጋገሪያ) ቀርፀንለታል (ደረጃ 4)። የሚቀጥሉት ሦስት ደረጃዎች የስብከትዎን መልእክት ያስገኙልዎታል።

ከ5-7 ያሉት ደረጃዎችም መሠረታዊ እርምጃዎች ናቸው። ከ1-3 ያሉ ደረጃዎችን በመሥራት ብቻም መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እውነት ለማስተማር ይችላሉ። ደረጃ 4ን በመጨመር፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠይቀውን ነገር ያውጃሉ። ከደረጃ 5-7 ያሉት ሥራዎች ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እውነትና የቃሉን ትግበራ አግባብነት ባለውና በሚያነሣሣ ሁኔታ እንዲያውጁ ያስችሉዎታል።

ደረጃ 5 ውስጥ የምንሠራው፥ የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ነው። በዚህ ሥራ ወቅት፥ የክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ (ደረጃ 3)፥ በዓላማው (ደረጃ 4)፥ ውስጥ እንዲያልፍ ይደረጋል። ከዚያም በክፍሉ ለተገለጠው የእግዚአብሔር አሳብ አድማጮች እንዲታዘዙ በስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ አማካይነት ለወቅቱ የሚሆን መልእክት ሆኖ ይቀርባል።

የስብከት ማዕከላዊ አሳብ ዝግጅትን አስመልክቶ፥ ለግንዛቤ ይረዳዎ ዘንድ፥ ጥቂት እውቅ ሰባኪያን ያሉትን ቀጥዬ አቀርባለሁ፡-

> "አንድ ስብከት፥ ከእግዚአብሔር ለሕዝቡ የተሰጠ ሕያው ቃል እንደ መሆኑ፥ በስፍራውና በጊዜው በአድማጮቹ ላይ ተጽዕኖ

ማሳደር አለበት። አድማጮቹ ዝርዝር ነገሮችን እንዲያስታውሱ መጠበቅ የለብንም። ዋናውን አሳብ ግን ማስታወስ አለባቸው። ምክንያቱም የመልእክቱን ዝርዝር አሳቦች ሁሉ የሚያቀናብሩት፥ የስብከቱን ዋና አሳብ እንዲጨብጡና የመልእክቱም ኃይል እንዲሰማቸው ለመርዳት ነው።›› (ጆን. አር. ስቶት)

የስብከቱ ርእሰ ጉዳይ (Subject) የሚመልሰው፥ ‹‹ስብከቱ ስለምንድነው?›› የሚለውን ጥያቄ ይሆናል። ስብከቱ፥ ሁለትም ሆነ አሥር ነጥቦች ይኑሩት። አንድ ዋና አሳብ ሊኖረው (ስለ አንድ ዋና ነገር ሊናገር) ይገባል። (ጆን. ኤ. ብሮአደስ)

ለስብከት ዝግጅት ዋናው አስፈላጊ ነገር፥ ‹‹ዋና አሳብ›› ያለው መሆኑ ነው። አንድ ዋና አሳብ ወይም ርእስ ሳይኖር፥ ስብከት ሊኖር አይችልም። ሄንሪ ጀምስ የተባለ የልብ ወለድ ድርሰት ደራሲ ‹‹አሳብ አንድን ታሪክ ለመጻፍ ልክ እንደ ‘ፅንስ’ ወይም ‘ዘር’ ነው። ለማንኛውም የፈጠራ ሥራ ወይም የጥበብ ሥራ አሳብ የመጀመሪያ መነሻ ይሆናል›› ብሏል። ‹‹የስብከትዎ ዋና አሳብ በተመሳሳይ ሙሉው ስብከት የሚያድግበት የመነሻ ዘር (ፅንስ) ነው።›› (ጆን ክሊንገር)

ስብከትን አስመልክቶ፥ ከላይ በተጠቀሱት ሰዎች ሳይቀር አሳቡን የሚጠቅሱለት ሌላ እውቅ ጄ. ኤች. ጆዌት የሚባል ሰው፥ እንዲህ ይላል፥

‹‹የአንድን ስብከት ጭብጥ (ዋና አሳብ) ጥርት ባለና ግልጥ በሆነ (በውስጡ ሌሎች ንዑስ አሳቦችን አካቶ የያዘ) ዓረፍተ ነገር ልንገልጥ እስካልቻልን ድረስ፥ መልእክቱ ለስብከት ወይም ለጽሑፍ የተዘጋጀ አይደለም የሚል እምነት አለኝ። ጥርት ያለ ዓረፍተ ነገር መጻፉ፥ በጣም ከባድ፥ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ቢሆንም፥ በጥናቴ ጊዜ ከማደርጋቸው ሥራዎች ሁሉ የላቀ ጠቀሜታ እንዳለው እረዳለሁ። ጥርት ያለ ዓረፍተ ነገር ለመጻፍ፥ ግራ የሚያጋቡና ግልጥ ያልሆኑ ቃላትን ለማስወገድ፥ እንዲሁም የስብከቱን ፍሬ አሳብ በትክክል ለመግለጥ የሚያስችሉ ቃላትን በጥንቃቄ ለመምረጥ፥ እራስን ማነጣጣትንና ማሰብን ይጠይቃል። አንድን ስብከት በማዘጋጀት ጊዜ፥ የስብከቱን ዋና አሳብ በዚህ መልኩ ማዘጋጀት ዋናና መሠረታዊ ጉዳይ ነው። የአንድ ስብከት ዋና አሳብ ልክ ደመና እንዳልጋረዳት ሙሉ ጨረቃ ፍንትው ብሎ እስካልታየ ድረስ ስብከቱ ለመስበክም ሆነ ለመጻፍ ደርሷል ብዬ አላምንም።››

# የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ ዝግጅት

የአንድን ስብከት ማዕከላዊ አሳብ አስፈላጊነትና ጥቅም አጉልቶ ማመልከቱ ቀላል ነው። ችግሩ፥ ማዕከላዊ አሳቡን ማግኘቱ ነው። በዚህ መጽሐፍ በቀረበው የስብከት አዘገጃጀት ዘዴ ላይ የተገለጡት ደረጃዎች ወደ ስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ ሊደርሱ የሚችሉበትን መንገድ ሊያመለክቱዎ ይገባል። ደረጃዎቹ አንዱ በሌላው ላይ የሚገነቡና በቅደም ተከተል የሚመጡ ናቸው።

ሂደቱ በጥንቃቄ የተቀናጀ ነው። የደረጃ 1 ጥናታችንና አስተዋጽኦው (ደረጃ 2)፥ በክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ (ደረጃ 3)። የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ በስብከቱ ዓላማ ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል (ደረጃ 4)። ከስብከቱ ዓላማ ውስጥ ነው የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ማውጣት ያለብን (ደረጃ 5)።

ማዕከላዊ አሳብ የመፈለጊያ አሠራሮችን አውቀዋል (ደረጃ 3)። ክፍሉ ነጠላ ርእሰ ጉዳይ እንዳለው ሁሉ፥ ስብከትዎም ነጠላ ርእሰ ጉዳይ ሊኖረው ይገባል። የስብከትን ማዕከላዊ አሳብ ለማግኘት ቁልፍ ጥያቄዎችን ማቅረብ ያለብዎ፥ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው ደራሲ ይልቅ ለራስዎ ነው።

### የስብከት ማዕከላዊ አሳብ

> ርእሰ ጉዳይ፡ የምናገረው ስለምንድነው?

> ጭብጥ (መልእክት)፡ ስለምናገረው ነገር የምለው ምንድነው?

ርእሰ ጉዳይዎን ለማዳበር የሚረዳዎ አንድ ዋና አሳብ እነሆ! *“ብዙ ጊዜ፥ የስብከቱን ዓላማ ወደ ስብከቱ ጭብጥ (መልእክት) ለመለወጥ ይቻላል”*

ይህን የኤፌሶን 4፡11-16ን ማዕከላዊ አሳብ በመጠቀም ላብራራ። (ደረጃውን የምሠራው ከቁጥር 11-13 ላለው ክፍል ብቻ ነው። ይህን የማደርገው፥ የአንድ አንቀጽ ክፍሎች በየራሳቸው ሊሰበኩ እንደሚችሉ ለማሳየት ነው። በተጨማሪም መልሶቹን በሙሉ ወዲያውኑ ልሰጥዎ አልፈልግም። የቁጥር 7-16ን ማዕከላዊ አሳብ ከቁጥር 11-16 ማዕከላዊ አሳብ ለይተው ሊያመለክቱ ይችላሉ?)

ደረጃ 3 *ርእሰ ጉዳይ፦* ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ለማሳደግ ያለው ዕቅድ።

*ጭብጥ፦* አማኞች ያድጉና አካሉን (ቤተ ክርስቲያኑን) በማነጽ ተግባር እንዲሳተፉ ያስታጥቃቸዋል (ያዘጋጃቸዋል)።

ደረጃ 4 የስብከቱ ዓላማ (ዓላማ ከክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ ክልል ሳይወጣ የተለያዩ አቅጣጫዎችን ሊይዝ ይችላል)፥ ክርስቶስ ለእያንዳንዱ አባል ያለውን ዕቅድ አማኞች ለጉባኤያቸው መንፈሳዊ መታነጽ ያውሉት ዘንድ ለማነሣሣት

ደረጃ 5 የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ (ዓላማውን በግርድፉ ወደ ክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ ፍሬ ነገርነት ልንለውጠው እንችላለን። ይህን የምናደርገው በጥያቄ መልክ ነው)። አካሉን በማነጽ ረገድ ክርስቶስ ለእያንዳንዱ የአካሉ ክፍል ያለው ዕቅድ ምንድነው? የስብከቱን ጥሬ ማዕከላዊ አሳብ የጊዜው መልእክት ማድረግ የምንጀምረውና፥ ማራኪ ወደሆነ ስብከትነት የምንለውጠው እዚህ ነው። የምንሰብከው ፍሬ ነገር ግን፥ "ክርስቶስ፥ ለአካሉ መታነጽ ለእያንዳንዱ የአካሉ ክፍል ያለው ዓላማ" ነው።

የስብከት ማዕከላዊ አሳብ ጭብጥ (መልእክት)፥ የተለያዩ መልኮች ሊኖሩት እንደሚችሉ ልብ ያድርጉ።

1. ለርእሰ ጉዳዩ ማስረጃ ወይም ትክክለኛነቱን ማረጋገጫ ማቅረብ ሊሆን ይችላል። ይህ መለኮታዊ ዕቅድ በእርግጥ አካሉን በመገንባት ውጤታማ ይሆናል? አንድ ሰው ቁጥር 11 እና 16ን የሚሰብክ ከሆነ፥ ዋናው ትኩረት ማረጋገጫ መስጠቱ ላይ ይሆናል።

2. ከላይ በተገለጠው ርእሰ ጉዳይና መልእክት መሠረት፥ ርእሰ ጉዳዩ የሚያስፈልገው መብራራት ሊሆን ይችላል። የስብከቱ ነጥቦች የሚያብራሩት ርእሰ ጉዳዩን ወይም ሙሉ አሳቡን ሊሆን ይችላል።

3. የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ በውስጡ ለርእሰ ጉዳዩ ከአንድ በላይ ጭብጦች (መልእክቶች) ሊኖሩት ይችላሉ። ለምሳሌ፥ ኤፌሶን 4፥7-16 ውስጥ፥ "ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ እድገት ያለው ዕቅድ" የሚለው ርእሰ ጉዳይ፥ ሦስት አቅጣጫዎች አሉት።

መልእክት 1. . . (ቁጥር 7-11)

2. . . (ቁጥር 12-13)

3. . . (ቁጥር 14-16)

እኔ የስብከት ማዕከላዊ አሳብ ቅርፅ አድርጌ የመረጥኩት የኋለኛውን "ባለ ብዙ መልእክት" ነው። ይህን ያረግሁት፥ ምንባቡ በቀላሉ በሦስት ስለሚከፋፈል ነው። ይህን ቀላል አከፋፈል፥ ከምንባቡ

ቅንጅት ለይተነዋል (ገጽ 61 ላይ ደረጃ 2ን ይመልከቱ)።

ቀጥሎ ያለውን፥ ለኤፌሶን 4፡7-16 እንደተዘጋጀ የስብከት ማዕከላዊ አሳብ አቀርባለሁ።

ርእሰ ጉዳይ፦ መለኮታዊ ዕቅድ ለአካሉ ግንባታ

መልእክት፦ 1. የጌታ ኃላፊነት ለቤተ ክርስቲያን ስጦታዎችን ማደል ነው (4፡7-11)።

2. የመሪው ኃላፊነት ቤተ ክርስቲያንን ማዘጋጀት ነው። (4፡12-13)

3. የምዕመናን ኃላፊነት ቤተ ክርስቲያን መሆን የሚገባትን እንድትሆን ማስቻል ነው(4፡14-16)

ይህን ማዕከላዊ አሳብ፥ ቀደም ሲል ደረጃ 3 ውስጥ ለዚሁ ክፍል ከተሰጠው ማዕከላዊ አሳብ ጋር ማስተያየት ያስፈልግዎ ይሆናል (ገጽ 61)

## በጊዜው ላሉ ሰዎች የሚሆን አድርጎ ማቅረብ

*ስብከቱ ጊዜውን የሚመለከት (የወቅቱ መልእክት) እንዲሆን ለማድረግ የተለያዩ አቀማሚዎችን ልንቃኝ ይገባል።*

ከላይ በገለጥኩት የስብከቴ ማዕከላዊ አሳብ፥ “አካሉን የማነጽ መለኮታዊ ዕቅድ” በሚለው፥ ስብከቴን ለአድማጮቼ የሚስማማ ለማድረግ “አካል ማነጽ” እና “ዕቅድ” የሚሉ በሚስቡና ምስልን አእምሮ ውስጥ ለመፍጠር በሚችሉ ቃላት ተጠቅሜአለሁ። ይህ አቀራረብ፥ መልእክቱ በአድማጮች አእምሮ ውስጥ እንዲቀረፅ ያደርጋል። የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ፥ እንደ ስብከቴ ርእስ ሆኖም ያገለግለኛል።

### *ቃላትን በጊዜው ያሉ ሰዎች የሚረዷቸው እንዲሆኑ ማድረግ*

ይህ ሥራ፥ በመሠረቱ ውጤትና ኃይል ይኖራቸው ዘንድ፥ ቃላትን በጊዜው ያሉ አድማጮች የሚረዷቸው እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ምናልባት በቀላሉ የሚታወቁና ምሳሌያዊ የሆኑ ቃላትን እንጠቀም ይሆናል። አንድ ሰባኪ፥ የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ በሚያዘጋጅበት ጊዜ፥ ያለምንም ገደብ በምናቡ ተጠቅሞ፥ አድማጮቹ ላይ በጎ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ቃላትን ሊመርጥ ይችላል።

### *አድማጮቻችንን መረዳት*

የሚሰብኩት፥ ለኤፌሶን ሰዎች፥ ወይም ለሙሴ አድማጮች አይደለም። ለራስዎ ጉባኤ ነው። በመሆኑም፥ የስብከትዎ ማዕከላዊ አሳብ

መልእክት፥ በአድማጮችዎ ላይ ያነጣጠረ መሆን አለበት። ለምሳሌ፥ “የኤፌሶን ሰዎች ተግዳሮት ገጥሟቸው ነበር” ከማለት ይልቅ፥ “ተግዳሮት አለብን” ይላሉ። ይህን ሲያደርጉ፥ የስብከትዎ ማዕከላዊ አሳብ ብትን ብርሃን ከመሆን ይልቅ፥ ስብከትዎን በሚያደምጠው የተለየ አድማጭ ላይ ያነጣጠረ ጨረር ይሆናል። የስብከትዎ ማዕከላዊ አሳብ የሚመሠረተው፥ ሥልጣን ያለው የብርሃን ምንጭ በሆነው በስብከት ክፍል ላይ ነው።

*ድግግሞሽ*

ኤፌሶን 4፡7-16 ላይ ተመሥርቼ በሦስት በመክፈል ባቀረብኩት ማዕከላዊ አሳብ፥ ጠቃሚ ቃላትን በተመሳሳይ ፊደላት እንዲጀምሩ አድርጌያቸዋለሁ። ቃላቱም የጌታ፥ የመሪው፥ የምዕመናን የሚሉትና ማደል፥ ማዘጋጀት፥ ማስቻል የሚሉት ናቸው። ይህን ያደረግሁት፥ ሰዎች ዋና ዋና ነጥቦችን ያስታውሱ ዘንድ ለመርዳት ነው። ስብከትን ከወቅቱ ሁኔታ ጋር የተገናኘ አድርጎ ማቅረብ ጥሩና አስፈላጊ ሲሆን፥ ዋና ቃላቶች በተመሳሳይ ፊደላት እንዲጀምሩ ማድረግ ግን፥ የግድ አስፈላጊ አይደለም። አንዳንድ ሰባኪዎች ግን፥ በተመሳሳይ ፊደላት በሚጀምሩ ቃላት ነጥቦቹን ማቅረብ እንዳለባቸው ያስባሉ። ይህ ዘዴ የሚያስፈልገው፥ ስብከቱ ግልጥ እንዲሆን ለመርዳት እንጂ፥ የስብከት ክፍሉን ያለአግባብ ለመጫን አይደለም። ዋና ዋና ቃላት በተመሳሳይ ፊደል እንዲጀምሩ ማድረጉ አስፈላጊ የሚሆነው፥ የመልእክቱን ዋና አሳብና ዋና ዋና ነጥቦችን ግልጥና ለማስታወስ የሚቀሉ እስካደረገ ድረስ ነው።

## ስብከትን በጊዜው ላሉ ሰዎች የሚሆን የማድረጊያ አንድ ምሳሌ

የስብከትዎ ማዕከላዊ አሳብ፥ የማይረሳና አድማጮችዎን የሚመለከት ይሆን ዘንድ፥ በጊዜው የሚነገሩ ቃላትን ይምረጡ። ይህ የአጻጻፍ ዘዴ ጉዳይ ነው። አድማጮችዎን በሚገባ ሲያውቋቸው፥ ማዕከላዊ አሳብዎን በነሱ አባባልና በሚገባቸው መንገድ መግለጥን ያውቁበታል። ራእይ 4፡1-11 በመጠቀም አሠራሩን ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሁኔታ አቀርበዋለሁ። የጽሑፉን ማዕከላዊ አሳብ ለመረዳት ምንባቡን ይመልከቱት።

ቁ 1. ከዚያ በኋላም አየሁ፤ እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ፥ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ፦ ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ አለ።

ቁ 2. ወዲያው በመንፈስ ነበርሁ፤ እነሆም ዙፋን በሰማይ ቆሞአል፤ በዙፋኑም ላይ ተቀማጭ ነበረ።

ቁ 3. ተቀምጦም የነበረው፥ በመልኩ የኢያስጲድንና የሰርዲኖን ዕንቁ ይመስል ነበር። በመልኩም፥ መረግድን የመሰለ ቀስተ ደመና በዙፋኑ ዙሪያ ነበረ።

ቁ 4. በዙፋኑ ዙሪያም ሀያ አራት ዙፋኖች ነበሩ፤ በዙፋኖቹም ላይ ነጭ ልብስ ለብሰው፥ በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው ሀያ አራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው ነበር።

ቁ 5. ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ፥ ነጎድጓድም ይወጣል፤ በዙፋኑም ፊት ሰባት የእሳት መብራቶች ይበሩ ነበር። እነርሱም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።

ቁ 6. በዙፋኑም ፊት ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር ነበረ። በዙፋኑም መካከል፥ በዙፋኑም ዙሪያ በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት እንስሶች ነበሩ።

ቁ 7. ፊተኛውም እንስሳ አንበሳን ይመስላል። ሁለተኛውም እንስሳ ጥጃን ይመስላል፤ ሦስተኛውም እንስሳ እንደ ሰው ፊት ነበረው። አራተኛውም እንስሳ የሚበርረውን ንስር ይመስላል።

ቁ 8. አራቱም እንስሶች፥ እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አሏቸው። በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዓይኖች ሞልተውባቸዋል፥

ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ የነበረውና ያለው

የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ።

ቁ 9. እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም። እንስሶቹም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው ለእርሱ ክብርና ውዳሴ ምስጋናም በሰጡት ጊዜ፥

ቁ 10፥ 11 ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች፥ በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ:-

"ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፥ ስለ
ፈቃድህም ሆነዋልና፥ ተፈጥረውማልና፥ ክብር ውዳሴ፥
ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል"

እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።

*ደረጃ 3 የመልእክቱ ማዕከላዊ አሳብ፡-* የታሪክን ሂደት ለመምራት ብቸኛ ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ዙፋን፥ በሰማያዊው መንግሥት ነዋሪዎች ታውቋል።

*ደረጃ 4 ዓላማው፡-* ይህን አሳብ ይዤ ወደ ብዙ አቅጣጫዎች ለመሄድ እችላለሁ፤ በተለይም ዮሐንስ ይህን መልእክት የጻፈላቸውን የመጀመሪያ አንባቢያን ከግንዛቤ ካገባሁ። ደረጃ 4 ውስጥ ያነሣናቸውን ተስማሚ የመሆን ጥያቄዎች ያስታውሳሉ? (ገጽ 71-72)። ሁለት የተለያዩ ስብከቶችን ለማዘጋጀት ሊረዱ የሚችሉ ሁለት ዓላማዎች እነሆ፡-

1. በስደት ላይ ያሉ ክርስቲያኖችን፥ ሁሉን ቻይ በሆነውና በታሪክ ሁሉ ላይ ገዢ በሆነው በእግዚአብሔር እንዲበረታቱ ለማድረግ፥ (ልክ ምንባቡ በዮሐንስ ዘመን የነበሩትን አማኞች እንዳጽናና እና ወደፊትም በሚመጣው የመከራ ዘመን የሚኖሩትን እንደሚያጽናና)።

2. አማኞች እግዚአብሔርን በሕይወታቸው ላይ ሙሉ በሙሉ ያነግሡት ዘንድ ለማበረታታት፡- እዚህ ላይ የተስማሚነትን ጥያቄ እንደገና ማንሣት ይኖርብናል። የዮሐንስ ራእይ እንደ ቁሳር እና ወደፊት ደግሞ፥ የክርስቶስ ተቃዋሚ ሆኖ እንደሚነሣው ሰው፥ ሕይወታቸውን እራሳቸው የሚመሩ የሚመስላቸውን ሰዎች በመቃወም የተጻፈ ነው ብዬ ላስረዳ እችላለሁ።

ሁለተኛውን ዓላማ መርጫለሁ። አድማጮቼ በሕይወታቸው ላይ እግዚአብሔር ያለውን ሚና እራሳቸው ሊይዙት በጣም ተፈትነዋል።

*ደረጃ 5 የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ፡-* መነሻ የሚሆን አንድ የስብከት ማዕከላዊ አሳብ ይዤ ቀርቤአለሁ። የስብከቱ ዓላማ እንዴት በጥያቄ መልክ ወደ ስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ ርእሰ ጉዳይነት እንደተለወጠ ልብ ይበሉ።

ርእሰ ጉዳይ፡- ሰማያዊ ዙፋን ላይ ለመቀመጥ መሞከር የማይኖርብዎት ለምንድነው? ወይም የእግዚአብሔርን የመግዛት ሚና መጫወት የማይኖርብዎት ለምንድነው?

ጭብጥ (ፍሬ ነገር)፡- ምክንያቱም ሰማያውያን ፍጡራን ሁሉ ሉዓላዊ ዙፋን የእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ተቀብለዋል።

ይህ ርእሰ ጉዳይና ጭብጥ (ፍሬ ነገሩ)፥ የጽሑፉን አሳብ በትክክል ያንጸባርቃል። ከአድማጮቼ ጋርም በበቂ ሁኔታ የተዛመደ ይሆናል። እኔ ግን የስብከቴን ማዕከላዊ አሳብ ማራኪ በሆነና በማይረሳ ሁኔታ ልገልጠው ፈለግሁ። (ይህ ድርጊቴ ሙሉ የሆነውን የስብከቴን ማዕከላዊ አሳብ፥ በንግግሬ መሀል ከመግለጥ አላገደኝም)

ውስጥ፥ ማለት በመግቢያው፥ በዐብይ መልእክቱና በማጠቃለያው ስለምጠቀምበት፥ አድማጮቼ ያስታውሱታል። ዓረፍተ ነገሩ ትግበራዊ ኃይልም አለው። ይህ ለራሴም የሚሆን መልእክት አድርጌ እወስደዋለሁ። የእግዚአብሔር የሆነውን ቦታ ለመያዝ በምፈተንበት ጊዜ ራሴን "ከዙፋኑ ማውረድ" እንዳለብኝ ያሳስበኛል።

## >> የድርጊት እርምጃ <<

ኤፌሶን 6፡10-12ን በመጠቀም፥ ልክ አንድ የሥነ-ጥበብ ሰው እንደሚያደርገው፥ ያስቡ፥ ያስታውሱ፥ ያሰላስሉ እና ተስማሚውን የስብከት አሳብ ይሥሩት፤ እንደገናም ይሥሩት። ቀጥሎ ያለውን ክፍል ከማጥናትዎ በፊት ይህን እንዲያደርጉ እመክርዎታለሁ። በዚህ የስብከት አዘገጃጀት ዘዴ ውስጥ የቀረበውን የአሠራር አሳብ ለመተግበር ያደረግሁት ሙከራ እነሆ!

ደረጃ 3 የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ፡- የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ሁሉ መልበሱ ያስፈለገበት ምክንያት፥ የዲያቢሎስን ሽንገላ ለመ ቃወምና፥ ከአሠራሩ ጋር ለመታገል ነው።

ደረጃ 4 ዓላማ፡- ሰዎች የዲያቢሎስን ሽንገላ ለመቃወም ይቻላቸው ዘንድ፥ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ እንዲለብሱ ለማበረታታት

ደረጃ 5 የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ፡- ዓላማውን ወደ ስብከቱ ማዕከላዊ አሳብነት መለወጥ

<u>ርእሰ ጉዳይ</u>፡- ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ሁሉ መልበስ የሚኖርባቸው ለምንድነው?

<u>ጭብጥ</u>፡- የዲያቢሎስን ሽንገላ ለመቃወምና ከአሠራሩ ጋርም ለመታገል።

እዚህ ላይ፥ ፍሬ አሳቡን ወደሚታወስ ትምህርታዊ ዓረፍተ ነገር በመለወጥ፥ ከተሰበከበት ጊዜ ጋር እንዲስማማ ማድረጉ ይጠቅማል። ፍሬ አሳቡንና መልእክቱን ቀጥሎ በተመለከተው አካኋን እንደገና ሊጽፉት ይችላሉ።

<u>ርእሰ ጉዳይ</u>፡- ከሰይጣን ጋር ላለብዎ ውጊያ የእግዚአብሔር ብርታት በቂ የሚሆነው ለምንድነው?

<u>መልእክት</u>፡- ሽንገላውን ለመቃወምና አሠራሩን ለመታገል ስለሚያስችልዎት።

# 6

# ስብከቱን ማቀናጀት

>> የስብከቱ ውስጣዊ አካል "አጥንቱ" <<

ደረጃ 7: ስብከቱን መስበክ

**ደረጃ 6: ስብከቱን ማቀናጀት**

ደረጃ 5: የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ

ደረጃ 4: የዓላማ መሸጋገሪያ ወይም ድልድይ

ደረጃ 3: የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ

ደረጃ 2: ክፍለ ምንባቡን ማቀናጀት

ደረጃ 1: ክፍለ ምንባቡን ማጥናት

በአጠቃላይ አነጋገር፥ ስብከቶች ሦስት ሂደቶች አሏቸው። እነርሱም:- መግቢያ፥ የስብከቱ ዋና አካልና መደምደሚያ ናቸው። ስብከቱን ማቀናጀት፥ ከሦስቱ ሂደቶችና ባጠቃላይ ከእያንዳንዳቸው ጋር ይዛመዳል። ሂደቶቹን በተናጠልና በአንድነት የማስፋፋቱ ሂደት፥ ስብከቱን ለማቀናጀት ይረዳል።

የአንድን ስብከት ሦስት ሂደቶች የማዳበሪያ ብዙ መንገዶች አሉ። ይሁን እንጂ፥ አንድ ሰው፥ ስብከቱን በየትኛውም መንገድ ቢያቀናጀው፥ ስብከቱ አንድነትን፥ ቅደም ተከተልንና እድገትን ማሳየት ይኖርበታል። አንድነቱ የሚገኘው፥ የስብከቱን አጠቃላይ ሂደት በክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ፥ በዓላማው መሸጋገሪያና በስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ ዙሪያ እንዲያተኩር በማድረግ ነው። ቅደም ተከተልና እድገት፥ በስብከቱ ንድፋዊ ቅንብርና በመልእክቱ ዋና አካል ቅንብር በኩል መገለጥ ይኖርባቸዋል። የስብከቱ ንድፋዊ ቅንብር፥ ደረጃ 4 ውስጥ ያኖሩትን ዓላማ ከግቡ ከማድረስ ጋር ይያያዛል። የስብከቱ ዋና አካል ቅንብር ደግሞ፥ የሚሰብኩበትን የስብከት ክፍል ያንፀባርቅ ዘንድ፥ በዋና አካሉ ውስጥ ካሉት ክፍሎች ዝግጅት ጋር ይዛመዳል።

ብዙ ጊዜ፥ የስብከቱ ዋና አካል አከፋፈል (Outline)፥ ደረጃ 2 ውስጥ ያለውን የስብከት ክፍለ ምንባብ አከፋፈል ይከተላል። (ይህ ሲባል ግን ቃላቶቹንም ሆነ ቅደም ተከተሉን እንዳለ መውሰድ ማለት አይደለም።) የስብከቱን ዋና አካል ክፍፍል፥ በጊዜው ላለው አድማጭ በሚሆን መልኩ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ይሆናል። በሚሰብኩት ክፍል ውስጥ ያሉ ቃላት ኃይል ኖሯቸው ወደ አድማጮች ጆሮ የሚገቡ እንዲሆንልዎ በርትተው ይሥሩ።

በመሠረቱ ስብከቶች ከሁለቱ በአንደኛው መንገድ ማለት፥ በመንእሳዊ (Deductive) ወይም በሥርፀታዊ መንገድ (Inductive) ይዳብራሉ። እነዚህን ሁለቱን የመለያ አጭር መንገድ፥ የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ ያለበትን ስፍራ መመልከት ነው። በመንእሳዊ ስብከት፥ ወደ ስብከቱ ዋና ክፍል እንኳን ከመግባትዎ በፊት ነው፥ ማዕከላዊ አሳቡ የሚገለጠው። ሥርፀታዊ ስብከት ውስጥ ግን፥ የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ የሚገለጠው፥ እንደ ስብከትዎ ማጠቃለያ ወይም ማረጋገጫ ነው። በስብከት ክፍሉ ላይ ተመሥርተው የስብከትዎን ማዕከላዊ አሳብ ሊያብራሩት እስከቻሉ ድረስ፥ ስብከትዎን የሚያቀናጁባቸው ብዙ ዓይነት መንገዶችን እንደ አመቺነቱ ለመጠቀም ይችላሉ።

## ትንንሽና ትልልቅ ውስጣዊ አካላት ወይም አጥንቶች

ደረጃ 2 ውስጥ የተገለጠውን የትልልቅና ትንንሽ አጥንቶች ምሳሌያዊ ገለጣ ያስታውሳሉ። ደረጃ 6 ውስጥ ስብከቱን ለማቀናጀት ይረዳን ዘንድ አጥንቶችን የማቀናጀት ተግባር ማከናወን ይኖርብናል። የስብከትዎ ትልልቅ አጥንቶች፥ የመልእክቱ መግቢያ፥ ዋናው መልእክት (አካል) እና ማጠቃለያው ናቸው። መካከለኛ መጠን ያላቸው የመልእክትዎ አጥንቶች፥ ንዑስ መግቢያውና የመልእክቱ ዋና ዋና ነጥቦች ናቸው። ትንንሾቹ አጥንቶች ደግሞ በዋና ዋና ነጥቦች መካከል የሚገኙት ንዑሳን ነጥቦች ናቸው። የስብከትዎን ንድፍ በሚሠሩበት ጊዜ፥ ዋና ዋናዎቹ ነጥቦች፥ ንዑስ ነጥቦችና የንዑስ ንዑስ ነጥቦች ሊኖራቸው ይችላሉ። ስብከቱን በምንጽፍበት ጊዜ፥ ይህን አጥንት ሥጋ እናለብሰዋለን (ደረጃ 7)።

ስብከት ውስጥ የሚገኙ ውስጣዊ አካላት (አጥንቶች)

<u>ትልልቅ አጥንቶች</u> <u>መካከለኛ መጠን</u> <u>ትንንሽ አጥንቶች</u>

መግቢያ ⟶ ንዑስ መግቢያ
ዋና ክፍል (አካል) ⟶ ዋና ዋና ነጥቦች ⟶ መሸጋገሪያዎች
⟶ ንዑሳን ነጥቦች
↓
ንዑስ ንዑስ ነጥቦች

*ማጠቃለያ*

አንድ ስብከት ቀጥሎ ባለው ሠሌዳ የተገለጠው ዓይነት አቀነባበር ይኖረዋል። እዚህ ምዕራፍ ውስጥ ወደተጠቀሱት ሌሎች ጉዳዮች ከመተላለፍዎ በፊት ቅንብሩን በሚገባ ለመረዳት ይሞክሩ።

## የስብከት አቀነጃጀት

### የስብከቱ ርእስ

### የመጽሐፍ ቅዱስ የስብከቱ ክፍለ-ምንባብ

I. የስብከቱ መግቢያ

  ሀ. ንዑስ መግቢያ

II. የስብከቱ ዋና ክፍል (አካል)

  ሀ. የመጀመሪያው ዋና ክፍል

    1. የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል

      ሀ) የመጀመሪያው የንዑስ ንዑስ ክፍል

      ለ) ሁለተኛው የንዑስ ንዑስ ክፍል

    2. የሁለተኛው ንዑስ ክፍል

  ለ. ሁለተኛው ዋና ክፍል

    1. የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል

    2. የሁለተኛው ንዑስ ክፍል

  መ. ሦስተኛው ዋና ክፍል

III. ማጠቃለያ

ሦስቱ ትልልቅ አጥንቶች፥ ማለት መግቢያው፥ ዋናው ክፍል (አካሉ) እና ማጠቃለያው የስብከቱ ዋነኛ ሂደቶች መሆናቸውን አይዘንጉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ሌሎች ሁለተኛ ሂደቶች አሉ። የሂደቶቹ ቁጥር ይለያያል። ትልልቆቹ አጥንቶች ማለት፥ መግቢያው፥ ዋናው ክፍል (አካሉ) እና ማጠቃለያው፥ የስብከቱ ንድፋዊ ቅንብር ናቸው። የስብከቱ ዋና አካል ክፍሎች ማለት፥ ክፍሎች፥ ንዑሳን ክፍሎች እና የንዑሳን ንዑሳን ክፍሎች፥ ደግሞ የስብከቱ አካላዊ ቅንብር ናቸው። አካላዊ ቅንብር በመጽሐፍ ቅዱሳዊው የስብከት ክፍል ላይ የሚያተኩር የስብከቱ ክፍል ነው።

ይህ በንድፋዊ ቅንብርና በአካላዊ ቅንብር መካከል ያለ ልዩነት ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት የሚነሣን ሌላ ጥያቄ ለመመለስ ይረዳናል። የአንድ ስብከት አቀነባበር ሊከተል የሚገባው የስብከት ክፍለ ምንባቡን ነው ወይስ አድማጩን? በዚህ መጽሐፍ የቀረበው የስብከት አዘገጃጀት መንገድን በተመለከተ ይህ ጥያቄ በተወሰነ ደረጃ አግባብነት የለውም። የመጽሐፍ ቅዱሳዊው የስብከት ክፍለ ምንባብ ማዕከላዊ አሳብ፥ ሰባኪው በስብከት ክፍሉ ውስጥ የሌለን የራሱን አሳብ እንዳይጨምር ክፍሉን

ይጠብቃል። ቢሆንም፥ ጥያቄው ከተነሣ ዘንድ እኔ የምለው፥ የስብከቱ አካሄድ (ንድፋዊ ቅንብሩ) አድማጩ ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል (ንድፋዊ ቅንብሩ፥ የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብና የዋና ዋና ነጥቦች ቃላት አቀማመጥ ጥምር)። የስብከቱ ዋና አካል (አካላዊ ቅንብሩ) ደግሞ በስብከት ክፍሉ ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል። በአድማጮች ሁኔታ ላይ የምናደርገው ትኩረት በስብከቱ ውጫዊ ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። በስብከት ክፍሉ ላይ የምናደርገው ትኩረት ደግሞ በስብከቱ ውስጣዊ ክፍልና ይዘት ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። ስብከት ግን በምንም ዓይነት ሰባኪው ላይ ያተኮረ መሆን የለበትም። (ከሰባኪው ሁኔታ አንጻር መቅረብ የለበትም።)

| **ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ አንጻር** | **ከአድማጮች አንጻር** |
|---|---|
| <u>ስብከቱ ከክፍለ ምንባቡ ጋር ሲዛመድ</u> | <u>ስብከቱ ከአድማጮች ጋር ሲዛመድ</u> |
| . የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ | . የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ<br>. የአጠቃላዩ ስብከት ቅንጅት |
| . ንዑስ መግቢያ | . መግቢያ |
| . የስብከቱ ዋና ክፍል ቅንጅት | . ትግበራ |
| | .ማጠቃለያ |

## >> የድርጊት እርምጃ <<

አሁን፥ ገጽ 88 ውስጥ እንደተገለጠው፥ የስብከት መዋቅሩን አንዳንድ ዝርዝር ነገሮች ልንጨምር እንችላለን።

### የስብከቱ ርእስ
### የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍለ ምንባብ

> የስብከቱ ዋና መግቢያ። የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ የሚሰፍረው እመግቢያው መጨረሻ ላይ ነው። ይህ የሚሆነው፥ ስብከቱ መንእሳዊ (Deductive) ከሆነ ነው። ሥርፀታዊ (Inductive) ስብከት ውስጥ የሚገለጠው፥ የመልእክትዎ ርእሰ ጉዳይ ብቻ ነው።

> ንዑስ መግቢያ። በንዑስ መግቢያው ውስጥ ብዙ ነገሮች ሊካተቱ ይችላሉ። መነሻውን (ዳራውን) እና ዐውደ ንባቡን ይግለጡ፤ ወደ ዋናው ክፍል (አካሉ) መሸጋገሪያ ያብጁ፤ ዋና ዋናዎቹን ክፍሎች ያስተዋውቁ፤ የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ወይም ርዕሰ ጉዳዩን እንደገና ይግለጡ፤ የምንባቡ ክፍል የሚከፋፈልበትን ሁኔታ ያስረዱ፤ የክፍሉን ማዕከላዊ አሳብ ወይም የመጀመሪያውን ዋና ነጥብ ወይም የስብከቱን የመጀመሪያ ክፍል ይግለጡ።

> የስብከቱ ዋና ክፍል ወይም አካል

I. የመጀመሪያው ዋና ክፍል (ስብከቱ ዋና ክፍል ውስጥ የሚገኙ ዋና ክፍሎች ቁጥር፥ የክፍለ ምንባቡን ደረጃ 2 ውስጥ በሚያዋቅሩበት ጊዜ በሚገኙ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ይመሠረታል።) የዚህን ዋና ክፍል፥ ንዑስ ክፍሎች ለመግለጥዎእርግጠኛ ይሁኑ።

ሀ. የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል አግራጭ:

አግራጭ ከፈለጉና ሥራው አሰልቺ ካልሆነብዎ፥ የዚህን ንዑስ ክፍል ንዑሳን ክፍሎች ያቅርቡ።

1. የመጀመሪያው ንዑስ ንዑስ ክፍል

2. ሁለተኛው ንዑስ ንዑስ ክፍል

አግራጭ: ንዑሳን ክፍሎች 1 እና 2ን እንደገና ይከልሷቸው።

ለ. ሁለተኛው ንዑስ ክፍል እዚህ ሲደርሱ የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ መንእሳዊ (Deductive) ስብከት ውስጥ ወይም ርዕሰ ጉዳዩን (Theme) ሥርፀታዊ (Inductive) ስብከት ውስጥ ወይም ቀደም ሲል የሰፈሩትን ንዑሳን ክፍሎች አለዚያም ከክፍሉ የመጀመሪያውን፥ እንደገና ስለመከለስዎ እርግጠኛ ይሁኑ።ከዚያም ወደ ሁለተኛው ዋና ክፍል ይሸጋገሩ።

II. ሁለተኛው ዋና ክፍል (በመጀመሪያው ዋና ክፍል እንደሠሩት ያድርጉ)፥ የዚህን ዋና ክፍል ንዑሳን ክፍሎች ለመግለጥዎ እርግጠኛ ይሁኑ።

ሀ. የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል

ለ. ሁለተኛው ንዑስ ክፍል

እዚህ ሲደርሱ፥ የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ በመንእሳዊ (Deductive) ስብከት ወይም ፍሬ አሳቡን ሥርፀታዊ (Inductive) ስብከት ውስጥ፥ ወይም ቀደም ሲል የሰፈሩትን ንዑሳን ክፍሎች፥ ያለዚያም ዋና ክፍሎቹን እንደገና ስለመፈተሽዎ እርግጠኛ ይሁኑ። ከዚያ ወደሚቀጥለው ዋና ክፍል ይሂዱ።

III. ሦስተኛው ዋና ክፍል (ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ክፍሎች እንዳደረጉት ይሥሩ) የስብከቱ ዋና አሳብ በሥርፀታዊ (Inductive) ስብከት እዚህ ይገለጣል። በመንእሳዊ (Deductive) ስብከት ደግሞየስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ለማጉላትና ደግሞም ለመከለስ እዚህ ይደገማል። ከዚህ ቀጥሎ የሚሄዱት ወደ ማጠቃለያው ነው።

> ማጠቃለያ

## >> የድርጊት እርምጃ <<

ቀጥሎ ያለው የአንድ ስብከት መዋቅር ምሳሌ ሲሆን፥ ደረጃ 5 ውስጥ ከተጠቀምንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተወሰደ ነው። በቅንፍ ውስጥ የገለጥኳቸው ማስታወሻዎች አሠራሩን እንዲገነዘቡ ይረዱዎታል። እነዚህን ከ1-5 ያሉ ደረጃዎች በሚመለከቱበት ጊዜ፥ መጽሐፍ ቅዱስዎን ገልጠው ይህን ክፍል በሚገባ ያጥኑት።

### የአካል ግንባታ
### ኤፌሶን 4፡7-16

> መግቢያ፡- የቤተ ክርስቲያናችን አካል፥ እድገትና የተግባር እንቅስቃሴ ወይም የ"አካል ግንባታ" የሚያስፈልገው መሆኑን በመግቢያዎ ይግለጡ።

የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ ርእሰ ጉዳይ፡ ለአካሉ እድገትና ሥራ መለኮታዊው ዕቅድ ምንድነው?

> ንዑስ መግቢያ፡- የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ ጭብጥ (የመለኮታዊውን ዕቅድ ሦስት አቅጣጫዎች ያስተዋውቁ። የመለኮታዊውን ዕቅድ የመጀመሪያ አቅጣጫ በድጋሚ ከገለጡ በኋላ፥ በስብከቱ አካል ውስጥ ያለውን የመጀመሪያ ነጥብ መሥራትዎን ይቀጥሉ።)

> አካል

I. የጌታ ኃላፊነት ለቤተ ክርስቲያን ስጦታዎችን መስጠት ነው (ቁጥር 7-11) (ጌታ የሚሰጣቸውን ሁለት ዓይነት ስጦታዎች ይግለጡ።)

ሀ. ክርስቶስ ስጦታዎችን ለሰዎች ሰጠ (ቁጥር7-10)

ለ. ክርስቶስ ሰዎችን እንደ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ (ቁጥር 11)፥ (ክርስቶስ እንደ ስጦታ የሰጣቸውን አራት አይነትሰዎችን ይግለጡ)

1. ሐዋርያትን ሰጠ (ቁጥር 11ሀ)
2. ነቢያትን ሰጠ (ቁጥር 11ለ)
3. ወንጌላውያንን ሰጠ (ቁጥር 11መ)
4. መጋቢያንንና አስተማሪዎችን ሰጠ (ቁጥር 11ሠ)

II. የቤተ ክርስቲያን መሪ ኃላፊነት ቤተ ክርስቲያንን ማዘጋጀት (ማስታጠቅ) ነው (12-13) (መሪው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለበትን ኃላፊነት ይግለጡ፤ ምን ማድረግና ለምን ያህል ጊዜ ማድረግ እንደሚኖርበት)

ሀ. የቤተ ክርስቲያን መሪ ኃላፊነት ምንድነው? ቤተ ክርስቲያንን ማዘጋጀት (ቁ. 12)

1. ቅዱሳንን ማዘጋጀት (ቁ. 12ሀ)

2. ለአገልግሎት ማዘጋጀት (ቁጥር 12ለ)

3. አካሉን ለማነጽ ማዘጋጀት (ቁጥር 12መ)

ለ. እስከ መቼ ነው ይህን የሚያደርጉት? ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስንእስክትመስል (ቁጥር 13)

1. የኅብረት አንድነት (ቁጥር 13ሀ)

2. ሙሉ ሰው የመሆን አንድነት (ቁጥር 13ለ)

3. ክርስቶስን የመምሰል አንድነት (ቁጥር 13መ)

III. ቤተ ክርስቲያንን ለማጠንከር ምእመናን ያለባቸው ኃላፊነት (ቁጥር 14-16)፥ (የሕዝቡን ሁለት የኃላፊነት አቅጣጫ ይግለጡ)

ሀ. ከእንግዲህ በመንፈስ ሕፃናት አይደሉም (ቁጥር 14)

1. በመንፈስ ሕፃናት የሆኑ ምእመናን አይጸኑም

2. በመንፈስ ሕፃናት የሆኑ ምእመናን ድልሎች ናቸው

ለ. ወደ መንፈሳዊ ሙሉ ሰውነት እንዲያድጉ ይጠበቅባቸዋል (ቁጥር 15-16)

1. በእውቀት እንዲያድጉ (ቁጥር 16)

2. በአገልግሎት እንዲያድጉ (ቁጥር 16)

> ማጠቃለያ

. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

የስብከቱን አካላዊ መዋቅር አስመልክቶ የቀረቡ አስተያየቶች።

1. ዋና ዋና ነጥቦች ሁሉ ሙሉ ዓረፍተ ነገሮች ናቸው። በሙሉ ዓረፍተ ነገር የሚገለጡ እንጂ፥ የሚወዛወዙ ቃላት ወይም የተንጠለጠሉ አርእስት አይደሉም። ንዑስ ነጥቦችንም በተቻለ መጠን በሙሉ ዓረፍተ ነገሮች ይጻፏቸው።

2. ዋና ዋና ነጥቦች የሚመሳሰሉበት ደረጃ አለ። ይህ መመሳሰል ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ መውጣትና በስብከቱ ውስጥ መቅረብ አለበት።

3. ሁሉም ስብከቶች ሦስት ዋና ዋና ነጥቦች ባይኖራቸውም፥ ብዙዎቹ ያላቸው መሆኑን እንገነዘባለን። የዋና ዋና ነጥቦች ብዛት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ ባለው ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ይመሠረታል።

በመሥራት ላይ ወዳለነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፥ ኤፌሶን 6፡ 10-12 እንሂድና እንቀጥል። የዚህ ምንባብ ስብከት አካል መዋቅር ሊሆን የሚችል ሥራ እነሆ።

I. ልዑል የሆነው የእግዚአብሔር ኃይል ለማንኛውም ምእመን ይደርሳል። (ቁጥር 10-11ሀ)

ሀ. ብርቱ መሆን አለባችሁ (ቁጥር 10)

1. በጌታ የበረታችሁ ሁኑ (ቁጥር 10ሀ)

2. በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ (ቁጥር 10ለ)

II. ልዑል የሆነው የእግዚአብሔር ኃይል ከሰይጣን ጋር ላለባችሁ ውጊያ በቂ ነው (ቁጥር 11ለ-12)

ለ. የእግዚአብሔርን ጦር ዕቃ ሁሉ መልበሳችሁ የዲያቢሎስን ሽንገላ ትቋቋሙ ዘንድ ይረዳችኋል (ቁጥር 12)

1. የሰይጣን አሠራር የሥጋና የደም አይደለም

2. የሰይጣን አሠራር መንፈሳዊ የስልጣን ተዋረድ አለው።

ሀ) ገዢዎች አሉ

ለ) ሠራዊቶች አሉ

መ) የክፋት ሠራዊቶች አሉ

ረ) መንፈሳውያን ሠራዊቶች አሉ

## የስብከት ክፍሎች

እስከ አሁን የስብከትን አካላዊ ቅንብር ተመልክተናል። አሁን ደግሞ የንድፉን ቅንብር እንድንመለከት እፈልጋለሁ። አሁን ጠለቅ ወዳለው የስብከት አዘገጃጀት መንገድ በመቃረብ ላይ ነን።

*ርእስ*

ስብከትዎ ርእስ ያስፈልገዋል። ያም በተለያዩ ጊዜያት ከስብከቱ ውስጥ ይወጣል። የስብከትዎን ማዕከላዊ አሳብ ለጊዜው አድማጮች እንዲሆን በማድረጉ ረገድ ብዙ ከሠሩ፥ ጭብጡን ወይም ፍሬ አሳቡን (የማዕከላዊ አሳቡን) እራሱን ርእስ ሊያደርጉት ይችላሉ። ራእይ 4ን አስመልክቼ በሰጠሁት ምሳሌ፥ "ከወንበርህ ውረድ" ብዬዋለሁ። ይህን ቃል እንደ ፍሬ አሳብና እንደ ርእስ ነው የተጠቀምኩበት።

የስብከትዎ ርእስ የሰዎችን ትኩረት የመሳብ ጉልበት ያለው ማስታወቂያ መምሰል ነው ያለበት። ሠዓሊያን ለሥዕሎቻቸው ርእስ እንደሚሰጡ ሁሉ፥ ርእስ ለስብከትዎ የሚሰጡት መለያ ወይም መታወቂያ ነው። በመሆኑም ትክክለኛ ርእስ መሆን አለበት። ሊያቀርቡ ከሚችሉት

ስብከት በላይ በርእስዎ ቃል አይግቡ። አንድ ጊዜ "እግዚአብሔርን የማግኛ መንገድ" በሚል ርእስ ባደረግሁት ንግግር የተነሣ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች በርእሱ ስለተነሣው ጉዳይ ላላቸው ጥያቄ መልስ ሊሹ ወደ እኔ መጡ። ምናልባት ባነሣሁት ርእስ አማካይነት ብዙ ቃል ገብቼ ይሆናል! ርእስዎ ለሰዎች አሳብ የሚጥም መሆን አለበት። ጥያቄን መጠቀም ብዙ ጊዜ የአድማጮችን የማወቅ ፍላጎት ይቀሰቅሳል። ርእስ ግልጥና አጭር ሊሆን ይገባል። መግቢያዎን በሚገልጡበት ጊዜ፥ በስብከትዎ ማዕከላዊ አሳብ ወይም በማጠቃለያው ውስጥ ተፈጥሯዊ ምልክቶችን ቢጠቀሙ ርእስዎን ያደምቁታል።

### *የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉን ማንበብ*

የሚሰብኩትን ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መግለጡ ጥሩ ነው። ይህ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉን ለመከታተል የሚፈልጉ ሰዎች እንደ ፍላጎታቸው ለማድረግ ይችሉ ዘንድ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉን መግለጥ ወይም ማንበብ የሚችሉባቸው ብዙ አማራጭ ጊዜዎች አሉ።

- የሚያቀርቡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በሳምንታዊ ጽሑፍ ወይም በማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ ሊያሳውቁ ይችላሉ። በሚቀጥለው ሳምንት የሚያቀርቡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ካሳወቁ፥ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመምጣታቸው በፊት ያነቡታል። ወይም ይህንኑ የስብከትዎን ክፍል ምንባብ ዘወትር ወደ ስብከትዎ በመምጣት ቀዳሚ ለሆኑ ሰዎች ሊያሰራጩ ይችላሉ።
- ስብከትዎን ለመጀመር ከመነሣትዎ በፊት ቀደም ብሎ አንድ ሰው የሚሰብኩበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሊያነበው ይችላል። አልፎ አልፎም እንደ አስፈላጊነቱ ሊነበብ ይችላል።
- ስብከትዎ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ከመግባትዎ በፊት ጥቂት የቅድሚያ ገለጣ ሊያደርጉ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉን ማሳወቅ (ቀደም ሲል ተነቦ ከሆነ)፥ ወይም ክፍሉን ማንበብ ለስብከቱ ጥሩ መሸጋገሪያ ይሆናል። የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉን ቢያንስ ሁለት ጊዜ ያሳውቁት። ከዚያም ከመግቢያው እስከ ንዑስ መግቢያው ድረስ ባለው ርቀት በሚጓዙበት ጊዜ የጉባኤው ተሳታፊዎች ክፍሉን እስኪያገኙት ድረስ ጥቂት ጊዜ ይስጧቸውና ለሦስተኛ ጊዜ ይግለጡት።
- የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉን መግቢያ ላይ ከሚያነሷቸው አሳቦች

መጨረሻ ላይ ሊያሳውቁ ይችላሉ። (ይህን "ቅድመ መግቢያ" እለዋለሁ። ከዚህ በታች የተገለጠውን ይመልከቱ)። የሚያነቧቸው ጥቅሶች ቀጥሎ ሊያብራሯቸው የሚፈልጓቸውን መሆን አለባቸው።

### *መግቢያ*

መግቢያዎ ሦስት ገጽታዎች (Dimensions) አሉት፤ እነሱም፥ ቅድመ መግቢያ፥ ዋና መግቢያ እና ንዑስ-መግቢያ ናቸው።

#### **ቅድመ መግቢያ**

ቅድመ መግቢያ መግለጫዎችን መስጠቱ የተለመደ ነገር ነው። ምናልባት ቀደም ብሎ አንድ ሰው መዝሙር ስለዘመረ ምስጋና ያስፈልገው ይሆናል (መዝሙሩ ለምስጋና ባይበቃ እንኳን እውቅና መስጠት!)። ወይም ደግሞ ማስታወቂያ እንዲናገሩ የሚያስፈልግዎ ሁኔታ ይገጥምዎ ይሆናል። ያለዚያም ተጋባዥ ሰባኪ ወይም ተናጋሪ ሆነው፥ ያን ዕድል በማግኘትዎ፥ አጭር የምስጋና ንግግር ማድረግ ይኖርብዎ ይሆናል።

እንዲህ ያሉ ንግግሮች፥ የዋናው መግቢያዎ አካል በሆነው ንዑስ መግቢያ ውስጥ የሚደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ። ከስብከትዎ ጋር ምንም ግንኙነት ባይኖራቸውም፥ በሰባኪና በአድማጮች መካከል መቀባበልን በመፍጠሩ ረገድ ምትክ የማይገኝለት ጥቅም አላቸው። ይህ ብቻም አይደል፥ ለሄዱበት አገልግሎትና ሰፋ ላለ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ትኩረት የሚሰጡ መሆንዎንም ያስገነዝባሉ። በጉባኤው መሀል የመነቃቃትና የመግባባት ስሜት መፍጠር አለብዎት። የጉባኤው ተሳታፊዎች፥ መጽሐፍ ቅዱሶቻቸውን ገልጠው፥ እርስዎ ክፍሉን በሚያነቡበት ጊዜ እንዲከታተሉ መጋበዝ ያስፈልግዎ ይሆናል። ቅድመ መግቢያዎን እንዳጠናቀቁ ሊጸልዩ ይችላሉ።

ቅድመ መግቢያዎን በአፍታ ዝምታ ወይም በጸሎት ካጠናቀቁ በኋላ፥ ወደ ስብከትዎ በመግባት ላይ መሆንዎን ለጉባኤው ምልክት ይሰጣሉ። ወደ ዋናው መግቢያ በመተላለፍ ላይ ስለመሆንዎም ፍንጭ ይስጡ።

#### **ዋናው መግቢያ**

ለአንድ ስብከት ውጤታማነት ጠንካራ ዋና መግቢያ የሚጫወተው ሚና እጅግ የላቀ ነው። የጉባኤው ተሳታፊዎች ቀሪውን የስብከት ክፍል (በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ደቂቃዎች)፥ በጉጉት እንዲጠብቁ ካላደረጓቸው፥ ተሳታፊነታቸውን አቋርጠው ወደ ቤታቸው ይሄዱ ይሆናል። ጠንካራና ዋና መግቢያ አራት ነገሮች አሉት። እነዚህ ነገሮች የተዋሐዱና በጥቅል

የተቀመጡ ስለሆኑ፥ ልዩ በሆነ ቅደም ተከተል አይደለም እዚህ የሰፈሩት። ውጤታማ ዋና መግቢያ እነዚህን አራት ግቦች የሚፈጽም ሊሆን ይገባል።

*ትኩረት ይሳቡ!* የጉባኤን ትኩረት መሳብ፥ በአንድ መልኩ ሲታይ በዋና መግቢያው ሊከናወኑ ከሚገባቸው ከአራት ነገሮች ቀላሉ ነው። ተናጋሪው ስብከቱን ለመጀመር ወደ መድረክ በሚያመራበት ጊዜ የጉባኤውን ትኩረት በመሳብ ላይ ነው። ይሁን እንጂ፥ የጉባኤውን ትኩረት እስከ መጨረሻው ለመሣብ፥ ሰባኪው ከጉባኤው ፍላጎት ጋር ተዛምዶ ያለው ጉዳይ ማንሣት አለበት።

*ፍላጎት መቀስቀስ!* የስብከቱ መግቢያ ዋና ዓላማ አድማጮች (ተደራስያን) የሚሉትን ነገር ለመስማት ፍላጎት እንዲያድርባቸው ማድረግ ነው። በስብከት ጊዜ ፍላጎትን መቀስቀስ ወሳኝ ስልት ነው። ስብከቱ እንዲያመጣ የሚፈልጉትን ለውጥ ለማወቅ በቂ ዝግጅት ያድርጉ። መልካም ስብከትን ለመለካት አንዱ መንገድ ስብከቱ ምን ያህል ወቅታዊ እንዲሆንና የአድማጮችንም ጥያቄ እንደሚመልስ በሚገባ ማወቁ ነው።

አንድ ሰባኪ ምን ዓይነት ፍላጎት መቀስቀስ አለበት? ለሚለው ነገርስ አሳቡን የሚያገናኘው ከየት ነው? ቀደም ሲል በተጠቀሰው ንድፍ መሠረት አሳቡን የሚያገኘው በደረጃ 4 ላይ ከተወሰነው ዓላማ ነው። ይህም የዓላማ መሸጋገሪያው ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያስገነዝበናል። ዓላማው የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ብቻ ሳይሆን፥ በዋናው መግቢያ ላይ መነሣት ያለበትን ጥያቄ ይጠቁመናል። አድማጮች (ተደራስያን) የሚሉትን ነገር ልብ እንዲሉት ለማድረግ ምርጡ መንገድ በማዕከላዊው አሳብ ጭብጥ ዙሪያ ጥያቄዎችን ማንሣት ነው።

ለምሳሌ በኤፌሶን 4 ላይ የሚያቀርቡት ስብከት ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሊያነሣ ይችላል፦

- ስንቶቻችሁ ቤተ ክርስቲያናችን ያለችበትን ችግር ለማወቅ ትፈልጋላችሁ?
- ቤተ ክርስቲያናችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመታዘዝ ምን ማድረግ አለባት?
- ስንቶቻችሁ ቤተ ክርስቲያናችን በሚገባ ታድግ ዘንድ ግድ ይላችኋል?
- እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን እድገት ያለውን ዕቅድ እንዴት ለማወቅ እንችላለን?

በርካታ ሰዎች እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ዝግጁ ናቸው፤ ደግሞም በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ያለውን ችግር ለማወቅና ችግሩንም ለመፍታት ፈቃደኞች ናቸው።

የሚሰብኩት በኤፌሶን 6፥10-12 ላይ ከሆነ፥ የአድማጮችዎን ፍላጎት በሚከተለው መንገድ ሊቀሰቅሱ ይችላሉ፦ "የዛሬው መልእክቱ ሰይጣንን እንዴት ድል ማድረግ እንችላለን?" የሚል ነው። ያነሡት ጥያቄ፥ አማኞች ከመንፈሳዊ መንገዳቸው እንዲስቱ ለማድረግ ዘወትር የሚያደባውን ጠላት እንዴት ማሸነፍ እንደሚችሉ የሚያስገነዝብ ነው። ጥያቄውን ሲያነሡ አድማጮችዎ ስብከቱን እንዲሰሙ አጥጋቢ ምክንያት እየሰጡ ነው?

*ርእሰ ጉዳዩን ይግለጡ!* አድማጮችዎ እርስዎ የሚገልጡትን ነገር ለመስማት ፍላጎት እንዲያድርባቸው ለማድረግ በዋናው መግቢያ ላይ የሚያነሷቸው ነገሮች ከማዕከላዊው አሳብ ጭብጥ ጋር የተያያዙ መሆን አለባቸው። ማለትም የዛሬው መልእክቴ ቁጣን ስለ መቆጣጠር ነው ብለው ስለ ሰማያዊ አካላት ሊናገሩ አይችሉም። በዋናው መግቢያዎ ላይ የስብከቱ ርእሰ ጉዳይ ምን እንደሆነ ለአድማጮችዎ መግለጥ አለብዎ። መንእሳዊ ስብከትን የሚከተሉ ከሆነ፥ በዋናው መግቢያዎ ላይ የስብከቱን ሙሉ ማዕከላዊ አሳብ መናገር አለብዎ።

በኤፌሶን 6፡10-12 ላይ የሚሰብኩ ከሆኑ፥ የስብከትዎን ጭብጥ ከዚህ የሚከተለው መሆኑን ይግለጡ፦ "ሰይጣንን ድል ለማድረግ መለኮታዊ ኃይል ወሳኝ ነው"።

*ዓላማውን ይግለጡ!* የዓላማውን መሸጋገሪያ ስለ ጻፉ፥ የስብከቱን ዓላማ ይግለጡ። ለአድማጮችዎ "ዛሬ. . .እፈልጋለሁ" በማለት ይናገሩ። ኤፌሶን 4ን እንደ ምሳሌ ብንወስድ፥ እንዲህ ለማለት ይችላሉ፦ "ዛሬ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያናችን አባል የእግዚአብሔርን ዕቅድ በተግባር ለመፈጸም በምናደርገው አገልግሎት ተሳታፊ እንዲሆን ለመምከር እፈልጋለሁ"። ይህ የዓላማ መግለጫ የስብከቱን መድረሻ ይጠቁማል። የዓላማው መግለጫ፥ አድማጮች በጉዞው ተሳታፊ እንዲሆኑ ይጋብዛል። ሰዎች የትም በማይሄድ አውቶቡስ አይሳፈሩም።

ይህን የዓላማ መግለጫ የሚያገኙት፥ ከእርምጃ 4 ማለትም ከዓላማው መሸጋገሪያ እንደሆነ ልብ ይበሉ። እንግዲህ እነዚህ የመግቢያው አራት ክፍሎች ወይም ዓላማዎች ናቸው። አራቱንም ቢያካትቷቸው የአድማጮችዎን ትኩረት ለመሳብ ይጠቅምዎታል።

### የውጤታማ መግቢያ ግቦች

- የአድማጮችን ትኩረት መሳብ
- የአድማጮችን ፍላጎት መቀስቀስ
- ለአድማጮች ርእሰ ጉዳዩን መግለጥ
- የስብከቱን ዓላማ መግለጥ

የዋናው መግቢያ ርዝመት የአድማጮችን ፍላጎት ለመቀስቀስ፥ ለአድማጮች የስብከቱን ርእሰ ጉዳይና ዓላማውን ለመግለጥ በቂ መሆን አለበት። ለመግቢያው የሚመድቡት ሰዓት እንደየስብከቱ ሊለያይ ይችላል። በመግቢያው ላይ ለሚያነሷቸው ነገሮች በቂ ጊዜ ይስጡ፤ ይሁንና አድማጮችዎ፥ የመግቢያዎ መደምደሚያ የመላው ስብከትዎ መደምደሚያ ነው ብለው እንዳያስቡ ረጅም አያድርጉት።

በዋናው መግቢያ ላይ፥ "ባለፈው ሳምንት ይህን ምንባብ ወይም ጭብጥ (ከቀደመው ምንባብ) ተመልክተን ነበር፤ በዚህ ሳምንት ደግሞ ተከታዩን ምንባብ እንመለከታለን" በማለት አይጀምሩ። እንዲህ ዓይነቱ ክለሳ መደረግ ያለበት በቅድመ መግቢያ ላይ ነው (ይህም ከዋናው መግቢያ በፊት በግልጥ መነገር አለበት)። ክለሳው በንዑስ መግቢያው ላይ ቢካተት የተሻለ ይሆናል። ዋናው መግቢያዎ የዚህን ሳምንት ምንባብና ስብከት ብቻ የሚመለከት መሆን አለበት።

### ንዑስ መግቢያ

የምንባቡን ዳራ ወይም መቼት መናገር ያለብዎ ከመግቢያው ቀጥሎ ነው። ይህን "ንዑስ መግቢያ" በማለት ሰይሜዋለሁ። ወደ ስብከቱ ፍሬ ነገር ስላልገቡ፥ የምንባቡን ታሪካዊና ዐውዳዊ ዳራ የሚናገሩበት ጊዜ ይህ ነው። ይህንንም የሚያደርጉት፥ የስብከቱን ዓላማ (ደረጃ 4)፥ ከግብ ለማድረስ የሚረዳዎ ከሆነ ብቻ ነው።

በንዑስ መግቢያው ሥር ከዚህ የሚከተሉት ነገሮች ሊካተቱ ይችላሉ፦

- የዕለቱ ምንባብ ክፍል የተወሰደው ከየት እንደሆነ ይግለጡ ወይም ያስታውሱ፤ ለምሳሌ ጳውሎስ ካላመኑ ሰዎች ጋር ስለ መጋባት በ1ኛ ቆሮንቶስ 7 ውስጥ ተናግሯል። ምንባቡን ካላገኛችሁት "አሁን አውጡትና አማኝ ካልተገኘ የማያምን ሰው ለማግባት ይቻላልን? የሚለውን ጥያቄ እንመልስ።" ክፍሉን አውጡት።" ለማለት ይችላሉ።
- ተከታታይ ስብከት ከሆነ ርእሱን ይከልሱ፤ ለምሳሌ "ክርስቲያኖች በማኅበረሰቡ ውስጥ እንዴት መኖር አለባቸው የሚለውን ርእስ እየተመለከትን ነው። ዛሬ ገላትያ 6፡10 እንመለከታለን።" በማለት።
- የምንባቡ ዳራ/መቼት፦

  -- የምንባቡ ታሪካዊ ዳራ፤ ለምሳሌ "ዳዊት መዝሙር 51ን የጻፈው እግዚአብሔርን ከበደለ በኋላ ነው"

ይቻላልን? የሚለውን ጥያቄ እንመልስ።” ክፍሉን አውጡት።” ለማለት ይችላሉ።

- ተከታታይ ስብከት ከሆነ ርእሱን ይከልሱ፤ ለምሳሌ “ክርስቲያኖች በማኅበረሰቡ ውስጥ እንዴት መኖር አለባቸው የሚለውን ርእስ እየተመለከትን ነው። ዛሬ ገላትያ 6፡10 እንመለከታለን።” በማለት።
- የምንባቡ ዳራ/መቼት፡-

  -- የምንባቡ ታሪካዊ ዳራ፤ ለምሳሌ “ዳዊት መዝሙር 51ን የጻፈው እግዚአብሔርን ከበደለ በኋላ ነው”

  -- የምንባቡ ምንባባዊ ዳራ፤ ለምሳሌ “የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 2 እስከ 3 በእስያ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የተጻፉ ሰባት መልእክቶችን ይዘዋል። ዛሬ የምንመለከተው፥ ለሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን የተጻፈውን ሰባተኛውን መልእክት ነው”።

  -- የምንባቡ ሥነ-ጽሑፋዊ ዳራ፤ ለምሳሌ “መዝሙር 119 ግጥማዊ ነው”።

  -- ተከታታይ ስብከት ከሆነ፥ “ባለፈው ሳምንት ኤፌሶን 4፡1- 6 መሠረት በማድረግ ስለ ክርስቶስ አካል አንድነት አጥንተን ነበር። በዚህ ሳምንት ስለ ክርስቶስ አካል የጀመርነውን ጥናት በመቀጠል፥ አካሉ በእግዚአብሔር አሳብ መሠረት እንዴት ማደግ እንዳለበት እንነጋገራለን” በማለት ይናገሩ።
- የፍሬ ነገሩን ውቅር በአጭሩ ይግለጡ፤ ለምሳሌ “የዛሬው ምንባባችን ማለትም 1ኛ ቆሮንቶስ 13 ሦስት ዐበይት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ክፍል ከቁ. 1-3 ሲሆን፥ ስለ ፍቅር ታላቅነት ይናገራል። ሁለተኛው ክፍል ከቁ. 4-7 ሲሆን፥ ስለ ፍቅር ባሕርይ ይናገራል። ሦስተኛው ክፍል ከቁጥር 8-13 ሲሆን፥ ስለ ፍቅር ዘላለማዊነት ይናገራል” በማለት።

በመጨረሻም የስብከቱን ጭብጥ ወይም ማዕከላዊ አሳብ በድጋሚ ይናገሩ።

በዋናው መግቢያ ላይ ከንዑስ መግቢያ አይጀምሩ።

### *የስብከቱ ዋና አካል (ክፍል)*

#### ንድፉን ያቀቅሩ

ስለ ንድፉ አወቃቀር ስንነጋገር (ስለመላው ስብከት፥ ማለትም ስለ መግቢያው ፍሬ ነገርና መደምደሚያው)፥ የአድማጮችን ማንነት ከግምት

ውስጥ በማስገባት ነው። አድማጮች ከምንለው ነገር ጋር ሊስማሙ ወይም ጨርሶ ላይቀበሉ ይችላሉ። ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሊያጤኗቸውና ልብ ሊሏቸው ይገባል፦ ሰዎች በስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ የተገለጠውን የእግዚአብሔር እውነት ለመቀበል የሚያዳግታቸው ለምንድን ነው? የስብከቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ስብከቱን እንዴት ላዋቅረው? የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ የሰዎችን ሕይወት ይለውጥ ዘንድ እንዴት ልንደፈው?

በአድማጮችዎ መካከል የተለያዩ ሰዎች አሉ። ስብከትዎ ለሁሉም የሚሆን መልእክት ሊኖረው ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ አድማጮችዎ የተለያየ አቋም ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ከአድማጮችዎ መካከል ብዙዎቹ አንድ ዓይነት ሰዎች ይሆኑ ይሆናል። ስብከትዎን ሲያዋቅሩ እያንዳንዱን ቡድን ሊያስቡ ይገባል። ስብከትዎን በሚያቀርቡበት ጊዜ፥ ሰዎች እግዚአብሔርን፥ ቃሉን፥ ሕዝቡንና እርስዎን በተመለከተ የሚወስዱት ቢያንስ ሦስት አቋም አላቸው።

- ምን ገዶኝ የሚሉ አሉ! አንዳንድ ሰዎች በስብሰባው ላይ ባልተገኘሁ ኖሮ ይላሉ። ተቃዋሚ አይደሉም፤ ነገር ግን ስለ እግዚአብሔርና ስለ ቃሉ ግድ የላቸውም። በዚያ የተገኙት ቤተሰቦቻቸው ወይም ወዳጆቻቸው ስለጋበዟቸው ብቻ ነው። ወይም ደግሞ በዚህ ሳምንት የሚሄዱበት ስላጡ ብቻ ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ የሚናገሩት ነገር የሰዎቹን ፍላጎት የሚቀሰቅስ መሆን አለበት። ካልሆነ በዚያ በመቆምዎ ያገኟትን የመሰማት ዕድል እንኳ ያጡ ይሆናል።
- አላውቅም የሚሉ አሉ! ከአድማጮችዎ መካከል አንዳንዶቹ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ቃሉ፥ ስለ ሕዝቡም ሆነ ስለ እርስዎ ብዙ የሚያውቁት ነገር የላቸውም። ስብከትዎ መልካም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት ሊኖረው ይገባል የሚባለው ለዚህ ነው።
- አላምንም የሚሉ አሉ! እነዚህ ደግሞ እርስዎ የሚናገሩትን እውነት ወይም ያ እውነት ከሕይወታቸው ጋር ያለውን ተዛማጅነት የሚጠራጠሩ ናቸው። አንዳንዶች እርስዎ የሚሉትን ነገር ከፍልስፍና አንጻር ሊያጤኑት ይችላሉ። "የሚናገረው እውነት የተጨበጠ ነው? ስብከቱ ወጥ ነው?" በማለት ስብከቱን ከተግባራዊነቱ አንጻር ያጤኑታል። "እውነቱ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ነው? ይሠራል?" ሊሉ ምናልባትም፥ "ሰባኪ ሆይ፥ የምትለው ነገር ሲሰሙት መልካም ይመስላል፤ በገሃዱ ዓለም ግን አይሠራም" ይሉዎት ይሆናል።

በስብከቱ ጊዜ እነዚህን የመሳሰሉ አስተያየቶች ሊሰሙ ይችላሉ። ስብከትዎን ሲያዘጋጁ፥ እንደዚህ ያለ አሳብ ያላቸውን ሰዎች አሸንፈው

አድማጮችዎ የተለያዩ ሰዎች ከሆኑ፥ ስብከትዎን የሚያቀርቡ ባቸው መንገዶች የተለያዩ መሆን አለባቸው።

## የስብከቱ ዋና አካል ቅንጅት

የስብከቱ ዋና አካል ቅንጅት ከስብከቱ ክፍለ ምንባብ ቅንጅት ጋር ተመሳሳይ ነው፤ አንድ ዓይነት ግን አይደለም። የስብከት ክፍሉ ሦስት ዋና ዋና ነጥቦች ካሉት፥ ስብከቱም ብዙ ጊዜ ያንኑ ያህል ዋና ዋና ነጥቦች ይኖሩታል። በመጀመሪያው ዋና አሳብ ሥር ሁለት ንዑስ አሳቦች ካሉት፥ የስብከቱም ፍሬ ነገር እንዲሁ ይሆናል።

ይህን ዝምድና በሚከተለው ሠሌዳ እንመልከት:-

| <u>እርምጃ 2 (ምንባብ)</u> | <u>እርምጃ 6 (ስብከት)</u> |
|---|---|
| 1. ቁጥር 1-3 | መግቢያ |
| 2. ቁጥር 4- 6 | ፍሬ ነገር |
| 3. ቁጥር 7-8 | 1. ቁጥር 1-3 |
| | 2. ቁጥር 4- 6 |
| | 3. ቁጥር 7-8 |
| | መደምደሚያ |

እንግዲህ የስብከቱ ዋና አካል ቅንጅት፥ በስብከት ክፍሉ ቅንጅት ላይ ተመሥርቷል ማለት ነው።

አንዳንድ ጊዜ የስብከቱ ዋና አካል የአከፋፈል ቅደም ተከተል ከስብከት ክፍሉ አከፋፈል ቅደም ተከተል ጋር አንድ ዓይነት ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ይነሣል። መልሱ፥ አብዛኛውን ጊዜ አዎን! ይሁንና በስብከቱ ንድፍ የሚወሰንበትም ጊዜ አለ የሚል ይሆናል። የስብከቱ ዓላማ (እርምጃ 4)፥ ከግብ የሚደርሰውና አሳብዎም ግልጥ የሚሆነው፥ ቅደም ተከተሉን በመቀያየር ከሆነ፥ በመጀመሪያ ከቁጥር 4 እስከ 6 ያለውን ከሰበኩ በኋላ ከቁጥር 7 እስከ 8 ከዚያም ከቁጥር 1 እስከ 3 ያለውን ለመስበክ ይችላሉ። ልብ ይበሉ! የምንባቡ አንጓዎች እንደተያያዙ ናቸው። ማለትም ከቁጥር 1 እስከ 8 የሚሰብኩ ከሆኑ፥ ቁጥር 4ን እና 5ን ነጥለው በማውጣት በዚያ ላይ መስበክ የለብዎትም። ከቁጥር 4 እስከ 6 አንድ ክፍል ከሆነ፥ ይህንኑ ተከትለው መስበክ ይኖርብዎታል። የምንባቡን ክፍፍል መጠበቅ አለብዎት። አብዛኛውን ጊዜ ስብከትዎ የምንባቡን ተከታታይነት ያንጸባርቃል። የስብከትዎ ቢጋር አዘገጃጀት ከዚህ የሚከተሉት ባሕርያት ይኖሩታል።

*አንድነት* - ስብከቱ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አንድ ወጥ መሆኑ

*ቅደም ተከተል* - የስብከቱ ክፍሎች ከመላው ስብከት ጋር ተያያዥ መሆናቸው

*ምጥነት* - የስብከቱ ክፍሎች ተመጣጣኝ ርዝመት ያላቸው መሆኑን

*ርምደት* - እያንዳንዱ ዐቢይ አሳብ ስብከቱን ወደፊት ማራመድ መቻሉ

ገለጣዊ ስብከትን በሚገባ ለመግለጥ የሚቻልበት ዘዴ ከዚህ በታች ያሉት ነጥቦች ይጠቁማሉ።

1) *አሳቡን ይግለጡ!* አድማጮችዎ እርስዎ የሚሉትን ነገር በትክክል እንዲረዱት ወቅታዊና ግልጥ ቋንቋ ይጠቀሙ።

2) *ለአሳቡ መሠረት ይስጡ!* ለሚሉት ነገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ይስጡ።

3) *የአሳቡን ምንጭ ይግለጡ!* ለማስተላለፍ የሚፈልጉትን አሳብ እንዴት ከስብከት ክፍሉ እንዳገኙት ይግለጡ።

4) *አሳቡን ያብራሩ!* ይህ የአሳቡን ትርጉም ይበልጥ የሚያብራሩበት ጊዜ ነው። አሳቡን ለማብራራት ጥናትዎን (እርምጃ1) ይጠቀሙ። አድማጮችዎ ንግግርዎን በሚገባ እንዲረዱ በምሳሌዎች ይጠቀሙ። አንድ ተናጋሪ ሁልጊዜ መጀመር ያለበት፥ አድማጮቹ ከሚያውቁት ነገር ነው። ከሚታወቀው ወደማይታወቀው ማለትም፥ አድማጮችዎ ከሚረዱት በመነሣት፥ እርስዎ እንዲገነዘቡልዎ ወደሚፈልጉት አሳብ ያምሩ።

5) *አሳቡን ያዛምዱ!* አንዳንድ ጊዜ አሳቡ ወዲያውኑ መዛመድ አለበት። ሌላ ጊዜ ደግሞ፥ አሳቡን ካብራሩ በኋላ ለማዛመድ ይችላሉ። የሚያዛምዱት አሳብ በስብከቱ ውቅርና፥ የስብከቱ ዓላማ የተፈለገውን ግብ እንዴት ይመታል በሚለው ይወሰናል። ወደ በኋላ ስብከትን ከሕይወት ጋር ስለ ማዛመድ በሰፊው እንነጋገራለን።

ባጠቃላይ፥ ስብከቱ መንእሳዊ ስልትን የሚከተል ከሆነ፥ ማለትም እያንዳንዱ ዐቢይ አሳብ ራሱን ችሎ የሚቆም ከሆነ፥ ስብከቱን የምናዛምደው፥ እያንዳንዱን ዐቢይ አሳብ ከተናገርን በኋላ ነው። የመጀመሪያውን ዐቢይ አሳብ እንናገራለን፤ ከዚያም ስብከቱን እናዛምዳለን። ሁለተኛውን ዐቢይ አሳብ እንናገራለን፤ ከዚያም ስብከቱን እናዛምዳለን። እንዲህ እያለ ይቀጥላል። ስብከቱ ሥርፀታዊ ስልትን የሚከተል ከሆነ፥ ማለትም እያንዳንዱ ዐቢይ አሳብ እያደገ ወደ ስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ የሚገሰግስ ከሆነ፥ ስብከቱን የምናዛምደው፥ በስተ መጨረሻ ነው።

ወደ በኋላ ስብከትን ከሕይወት ጋር ስለ ማዛመድ በሰፊው እንነጋገራለን።

ባጠቃላይ፥ ስብከቱ መንእሳዊ ስልትን የሚከተል ከሆነ፥ ማለትም እያንዳንዱ ዐቢይ አሳብ ራሱን ችሎ የሚቆም ከሆነ፥ ስብከቱን የምናዛምደው፥ እያንዳንዱን ዐቢይ አሳብ ከተናገርን በኋላ ነው። የመጀመሪያውን ዐቢይ አሳብ እንናገራለን፤ ከዚያም ስብከቱን እናዛምዳለን። ሁለተኛውን ዐቢይ አሳብ እንናገራለን፤ ከዚያም ስብከቱን እናዛምዳለን። እንዲህ እያለ ይቀጥላል። ስብከቱ ሥርፀታዊ ስልትን የሚከተል ከሆነ፥ ማለትም እያንዳንዱ ዐቢይ አሳብ እያደገ ወደ ስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ የሚገሰግስ ከሆነ፥ ስብከቱን የምናዛምደው፥ በስተ መጨረሻ ነው።

መንእሳዊ ስልትን ተከትሎ መስበክ በጣም ቀላል ነው። ብዙ ስብከቶች ይህን ስልት ይከተላሉ። እያንዳንዱ ዐቢይ አሳብ (ምናልባትም የመጀመሪያው ደረጃ ንዑስ አሳቦች) ከ1-5 ከላይ የተጠቀሱትን ይከተላሉ። ሥርፀታዊ ስልትን ተከትሎ የሚሰበክ ስብከት 1-4 ያሉትን ይከተላል። አምስተኛው (አሳቡን ማዛመድ የሚመጣው በስተ መጨረሻ ነው።

ከዚህ በታች የተመለከተው ሠንጠረዥ መንእሳዊና ሥርፀታዊ ስልቶችን በንጽጽር ያቀርባል። እዚህ ላይ የተጠቀምሁት፥ ወደ ንድፍ ውቅር (እርምጃ 6) የተለወጠውን ባለ ሁለት አሳብ የስብከት ክፍለ- ምንባብ ውቅር (እርምጃ 2) ነው።

| <u>መንእሳዊ</u> | <u>ሥርፀታዊ</u> |
|---|---|
| I. መግቢያ፡ | I. መግቢያ፡ |
| የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ በሙሉ መናገር | የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ በከፊል ማስተዋወቅ |
| II. አካል፡ | II. አካል፡ |
| ሀ. 1 ፥ 2፥ 3፥ 4 | ሀ. 1፥ 2፥ 3፥ 4 |
| -ማዛመድ | |
| ለ. 1፥ 2፥ 3፥ 4 | ለ. 1፥ 2፥ 3፥ 4 - |
| -ማዛመድ | -ማዛመድ<br>እዚህ ላይ ሊሆን ይችላል |
| III. መደምደሚያ | III. መደምደሚያ<br>(ማዛመድን ሊጨምር ይችላል።) |

## ሽግግሮች

የስብከቱን ዋና አካልና ዐቢይ አሳቦች አስተዋጽኦ በሚያዘጋጁበት ጊዜ፥ እያንዳንዱ አስተዋጽኦ ከርእሰ ጉዳዩና ከቀደመው ክፍል ጋር ይተሣሠር ዘንድ ተገቢ ሽግግር ያስፈልግዎታል። መሸጋገሪያዎች አሳቡ ቀልጥፎ እንዲራመድ ያደርጋሉ። በሌላ አነጋገር በስብከቱ መካከል ለሚደረገው እንቅስቃሴ እንደ ድልድይ ያገለግላሉ። ስለሆነም፥ አድማጮች አእምሯዊና ሥነ-ልቡናዊ ወንዞችን ለመሻገር አይገደዱም። የመሸጋገሪያ ቃሎች፥ አድማጮች የስብከቱን አካሄድ በጥሞና እንዲከታተሉ ዋስትና ይሰጣሉ።

ብርቱ የመሸጋገሪያ ቃሎች፦

- የስብከቱን ርእሰ ጉዳይ አሰልቺ ባልሆነ ድግግሞሽ ይከልሳሉ።
- ስብከቱ ያለ መሰናከል/ችግር እንዲራመድ ያደርጋሉ።
- አንዱን አሳብ ከሌላው ጋር ግራ በማያጋባ መንገድ ያያይዛሉ።
- ስብከቱ ያለ ሽምደዳ በቀላሉ ለማስታወስ የሚቻል እንዲሆን ያግዛሉ።
- የስብከቱ ውቅር ሥርዓት ያለው እንዲሆን ያደርጋሉ።

እንግዲህ ተገቢ የመሸጋገሪያ ቃሎች ስብከቱ አንድነትና ቅደም ተከተል፥ እንዲሁም ወደፊት የሚሄድ እንዲሆን ለማድረግ ይረዳሉ።

**መሸጋገሪዎች ስብከቱ**

> አንድነት፥

> ቅደም ተከተልና

> ወደፊት የመራመድ ዋስትና እንዲኖረው ያደርጋሉ።

የሰውነታችንን አጥንት ምሳሌ እንደገና ብንወስድ፥ የመሸጋገሪያ ቃሎች በትልልቅ አጥንቶች መካከል፥ በትንንሽ አጥንቶች መካከል፥ እንዲሁም በትልልቅና በትንንሽ አጥንቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ያሳያሉ።

ከዚህ በታች የተለያዩ የመሸጋገሪያ ዓይነቶች እንዳሉ ለማመልከት ተሞክሯል። እነዚህን ዓረፍተ ነገሮች የሚያዘጋጁት፥ እንደ ስብከትዎ ውቅር ነው። (የንድፋዊ መዋቅርና፥ አካላዊ መዋቅር)

- *ሐረግ መሸጋገሪያ፤* አያያዥ ሐረጎችን ይጠቀሙ። ለምሳሌ፥ ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን፥ በሁለተኛ ደረጃ፥ ባንጻሩም፥ በተቃራኒው፥ . . .።

- *ሐሳብ መሸጋገሪያ፤* ወደ ተከታዩ አሳብ ከመሄድዎ በፊት የመጀመሪያውን አሳብ ይከልሱት። ይህን ለማድረግ ብዙ መንገዶች አሉ፦
  - *ቅደም ተከተላዊ መሸጋገሪያ፤* "በመጀመሪያ የተመለከትነው አሳብ. ." "አሁን ደግሞ ሁለተኛውን አሳብ እንመለከታለን"
  - *አመክንዮአዊ መሸጋገሪያ፤* አንድን አሳብ በማስረጃ እየደገፉ ለማብራራት ያገለግላል። በተለይ በሥርፀታዊ የስብከት ቅንጅት።
  - *ተምሳሌታዊ መሸጋገሪያ፤* አሳብዎን ለመወከል ተምሳሌቶችን ይጠቀሙ። ለምሳሌ፥ የሕንጻ ተምሳሌት መጠቀም ይችላሉ፦ "የእምነታችን መሠረት . . . .፤ ላእላይ መዋቅሩ. . ."
  - *ሥነ-ልቡናዊ መሸጋገሪያ፤* ቅደም ተከተላዊ ወይም ምክንያታዊ ቃሎችን ከመናገር በአድማጮችዎ ሕሊና ውስጥ የሚገኙ ጉድኝቶችን ይጠቀሙ፤ "ይህን ተመልክተናል፤ አሁን ደግሞ ይህን እንመለከታለን"።
- *አካላዊ መሸጋገሪያ፤* በዐቢይና በንዑስ አሳቦች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለጥ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን መጠቀም ይቻላል። እጅን፥ ግንባርን ወዘተ። ስለ አካላዊ እንቅስቃሴ በእርምጃ 7 ላይ እንነጋገራለን።

### መተግበር (ከሕይወት ጋር ማዛመድ)

ስብከት ከሕይወት ጋር ካልተዛመደ፥ መንፈሳዊ ድርቀትን ያስከትላል። ስብከቱ በይዘቱ እንከን የሌለው ቢሆንም እንኳ፥ የአድማጮችዎን ሕይወት ካልለወጠ ምንም ትርጉም የለውም። መተግበር አድማጮችዎ የቃሉን እውነት ከመቀበል ቃሉን በተግባር ወደ ማዋል የሚያሸጋግሩበት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶቹን ሲጽፍ፥ አብዛኛውን ጊዜ ስለ አንድ ነገር ከተናገረ በኋላ (በግሪክ ሐተታዊ ዓረፍተ ነገር)፥ ወደ ትእዛዝ (በግሪክ ትእዛዛዊ ዓረፍተ ነገር)፥ ይሸጋገር ነበር። አድማጮች በሕይወታቸው እንዲተገብሩት የሚፈለገው ነገር ወቅታዊና ተጨባጭ መሆን አለበት።

- *ወቅታዊ ማድረግ፤* ቀደም ሲል የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ለተለያዩ አድማጮች በተለያየ መንገድ እንዴት ማዛመድ እንደሚቻል ተነጋግረናል። አድማጮቻችን የተለያዩ ሰዎች ናቸው። ልዩ ልዩ መንፈሳዊ፥ ባሕላዊ፥ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች አሏቸው። ከአድማጮች ሕይወት ጋር የሚዛመደው ስብከት

እንደሆነ በግልጥ ይንገሯቸው። እግዚአብሔር ከእነርሱ የሚፈልገው፥ እንዲቀደሱ መሆኑን መናገሩ ብቻ በቂ አይደለም። አሁን ባሉበት ሁኔታ ቅድስና ምን እንደሆነ የሚያሳይ ግልጥ ምሳሌ ይስጧቸው።

በሕይወታቸው የሚተገብሩትን ነገር ወቅታዊና ተጨባጭ ለማድረግ፥ በምንባቡ ማዕከላዊ አሳብና በአድማጮችዎ መካከል ተዛማጅነት መኖሩን ማረጋገጥ አለብዎ። እነዚህ ተዛማጆች፥ ነገረ መለኮታዊና መንፈሳዊ ናቸው። ቀደም ሲል በራእይ 4 ምንባብ ላይ የተጠቀምሁባቸውን ምሳሌዎች መሠረት በማድረግ፥ ስብከቱ እንዴት ነገረ መለኮታዊና መንፈሳዊ ይዘት ሊኖረው እንደሚችል ለመዘርዘር እሞክራለሁ።

እርምጃ 3 ውስጥ ለራእይ 4፡1-11 የነደፍሁት የምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ ከዚህ የሚከተለው ነው፦ “እግዚአብሔር ዓለምን ለማስተዳደር ብቻውን ሙሉ ሥልጣን ያለው መሆኑ በሰማይ ነዋሪዎች ዘንድ የታወቀ ነው”። ነገረ መለኮታዊና መንፈሳዊ ተዛምዶዎች የምንባቡን ማዕከላዊ አሳብ ከአድማጮቼ ጋር ያያይዙታል።

- ነገረ መለኮታዊ ተዛምዶ

  - የእግዚአብሔር ባሕርይና ሥራ፤ የዚህ ዓለም ገዥ እግዚአብሔር መሆኑን እንገነዘባለን፤ በመሆኑም እርሱ አምላክ ነው።

  - የእግዚአብሔር ሕዝቦች ባሕርይ፤ እዚህ ላይ ኅብረተሰብን እናያለን፤ ለምሳሌ ሀያ አራቱ ሽማግሌዎችና የተዋጁ ሕዝቦች።

  - የፍጥረት/የፍጡራን ባሕርይ፤ መላእክት እግዚአብሔርን ያመልካሉ፤ እኛም እግዚአብሔርን ማምለክ አለብን።

- መንፈሳዊ ተዛምዶ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ትርጉም ያለውና ግላዊ ኅብረት ለማድረግ ይቻላል። እዚህ ላይ የመጀመሪያዎቹ ተደራሲዎችስ? ብዬ እጠይቃለሁ። ያኔ የነበሩ ሰዎች የክርስቶስ ተቃዋሚነት መንፈስ ይታይባቸው ነበር? ዮሐንስ የሚናገረው ስለ ምንድንነው? አንባቢዎቹ ክፍሉን እንዴት ተረዱት? የያኔዎቹንና የአሁኖቹን ሰዎች ባሕርይ በተመለከተ ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ፦

  - ከእነርሱ ጋር የምንመሳሰለው በምንድነው? እኛም የእግዚአብሔር ነን፤ ስለዚህ እርሱን ማምለክ አለብን።

  - ከእነርሱ ጋር የማንመሳሰለው በምንድነው? እኛ የሰማይ ነዋሪዎች አይደለንም (ህልውናችን ከሰማይ ነዋሪዎች ጋር

- መንፈሳዊ ተዛምዶ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ትርጉም ያለውና ግላዊ ኅብረት ለማድረግ ይቻላል። እዚህ ላይ የመጀመሪያዎቹ ተደራሲዎችስ? ብዬ እጠይቃለሁ። ያኔ የነበሩ ሰዎች የክርስቶስ ተቃዋሚነት መንፈስ ይታይባቸው ነበር? ዮሐንስ የሚናገረው ስለ ምንድንነው? አንባቢዎቹ ክፍሉን እንዴት ተረዱት? የያኔዎቹንና የአሁኖቹን ሰዎች ባሕርይ በተመለከተ ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ፡-

  - ከእነርሱ ጋር የምንመሳሰለው በምንድነው? እኛም የእግዚአብሔር ነን፤ ስለዚህ እርሱን ማምለክ አለብን።

  - ከእነርሱ ጋር የማንመሳሰለው በምንድነው? እኛ የሰማይ ነዋሪዎች አይደለንም (ህልውናችን ከሰማይ ነዋሪዎች ጋር ባይመሳሰልም፥ ይህ ግን እግዚአብሔርን ከማምለክ እንደማያግደን በግልጥ ማሳየትአለብዎ)።

  - እነርሱን መምሰል ያለብን በምንድነው? በአምልኮ

  - እነርሱን መምሰል የማንችለው በምንድነው? አንዳንድ ሰዎች በሐሰተኛው ክርስቶስ ምክንያት መከራ ሲበረታባቸው፥ ፊታቸውን የታሪክ ጌታ ከሆነው ከእግዚአብሔር ለመመለስ ይፈተናሉ። (ይህን ምንባብ ሲያጠኑ እኔ ከደረስኩበት የተለየ ዓላማ ይዘው ሊነሡ ይችላሉ። የእኔ አሳብ የአማኞችን ሕይወት የሰማዩ አምላክ እንዲገዛው መምከር ነው)።

ከሕይወት ጋር ሊዛመዱ የሚችሉ ብዙ ነገሮች ሊወጡለት የሚችል ምንባብ ሲሆን፥ እኔ ግን እንደ ሰብከቴ ዓላማ ወቅታዊና ተጨባጭ የሆኑትን ብቻ ወስጃለሁ። ከሕይወት ጋር የሚዛመዱትን ነገሮች ከመምረጤ በፊት ወደ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ እሄዳለሁ። ይህን የማደርገው፥ የራሴን ሳይሆን ታማኝ በመሆን የክፍሉን አሳብ ለማስተላለፍ ነው።

## ከሕይወት ጋር ለሚዛመዱት ነጥቦች ስፍራ መወሰን

ከሕይወት ጋር የሚያዛምዷቸውን ነጥቦች በስብከቱ መሀል (መንእሳዊ ስልትን የሚከተሉ ከሆነ) ወይም በስብከቱ መጨረሻ (ሥርፀታዊ ስልትን የሚከተሉ ከሆነ)፥ ሊያመጧቸው ይችላሉ። ከሕይወት ጋር የሚያዛምዷቸውን ነጥቦች አስፈላጊ በሆነበት ጊዜና ስፍራ ሊያመጧቸው ይችላሉ። ይሁንና ከዚህ የሚከተሉትን ነገሮች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለብዎ፡- የስብከቱን ውቅር፥ የስብከቱን ዋና አካል ውቅር፥ የስብከቱን ዓላማና የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ። ምናልባት በአንዱ የስብከት ክፍል ላይ

የሚያተኩሩት በማዕከላዊ አሳብ የተወሰነ ክፍል ላይ ሊሆን ይችላል። እንደዚህ ሲሆን፥ አብረው የሚሄዱትን የማዛመድ አሳቦች ያንኑ ጊዜ ያቅርቡ። ከሕይወት ጋር የሚያዛምዱቸው ነጥቦች የሚመጡት በስብከቱ መጨረሻ ከሆነ፥ ቀደም ሲል ላነሷቸው አሳቦች እንደ ማጠቃለያ አይመልከቷቸው። ከሕይወት ጋር የሚያዛምዱቸው ነጥቦች የስብከቱ ተቀጥላ አይደሉም። በመሆኑም በቂ ጊዜና ስፍራ ሊሰጧቸው ይገባል።

## ከሕይወት ጋር የሚዛመዱትን ነጥቦች ማዳበር

በስብከቱ መጨረሻ ላይ አድማጮችዎ ከዚህ ለሚከተሉት ሦስት ዐበይት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት መቻል አለባቸው፦

ሰባኪው የተናገረው ምንድን ነው?

የስብከቱ ዓላማ ምንድነው?

ለስብከቱ የምሰጠው ምላሽ ምንድነው?

የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብና የስብከቱ ዋና አካል "ሰባኪው የተናገረው ምንድነው?" ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት አለባቸው። ከሕይወት ጋር የሚዛመዱት ነጥቦችና፥ በሥርዓት የተዋቀረው የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ፥ "የስብከቱ ዓላማ ምንድነው?" ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት አለበት። ከሕይወት ጋር የሚዛመዱት ነጥቦች "ለስብከቱ የምሰጠው ምላሽ ምንድነው?" የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል።

እርምጃ 4 ውስጥ ያጎለበቱት ዓላማ ከሕይወት ጋር የሚያዛምዳቸው ነጥቦች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ይጠቁምዎታል። ዓላማዎ ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ ድልድይ ይሆንዎታል። በምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ መሠረት እግዚአብሔር አድማጮቼ እንዲያስተውሉትና እንዲታዘዙት የሚፈልገው ነገር ምንድነው? ብለው ይጠይቁ። የጻፉት ዓላማ የድርጊት ግሦች ሊኖሩት ይገባል። (በሰዋስው እነዚህ የድርጊት ግሦች ይባላሉ)። ጥቂቶቹን ልዘርዝራቸው፦ ልመክራችሁ፥ ላሳስባችሁ፥ ላጽናናችሁ፥ ላደፋፍራችሁ። (ለመለወጥ አይሞክሩ! ይህ የመንፈስ ቅዱስ ኃላፊነት ነው። ደግሞም ለማስገደድ አይሞክሩ! እግዚአብሔርም እንኳን ማንንም አያስገድድም)።

ከዓላማዎ በመነሣት የስብከቱ ዓላማ ምንድነው? እንዲሁም ለስብከቱ የምሰጠው ምላሽ ምንድነው? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ያዘጋጁ። መልሶቹ ከሕይወት ጋር ለሚያዛምዱቸው ነጥቦች መሠረት ይሆኑዎታል። ለእነዚህ ጥያቄዎች ያዘጋጁትን መልስ በሌላ ወረቀት ላይ ይጻፉት። በኋላ ተገቢ ያልሆኑትንና የተንዛዙትን ለማስቀረት ያመችዎታል።

ከምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ ነው። ለተነሡት ውጥረቶች መልስ የምናገኘው ከስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ ነው። በሌላ አነጋገር፦

- የስብከቱ ምንነት የሚወጣው፥ ከቅዱሳት መጻሕፍት ነው፤ የምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ ጠቅለል አድርጎ ይገልጠዋል።
- የስብከቱ ማዛመድ የሚወጣው ከሕይወትና የክፍሉን ማዕከላዊ አሳብና የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ከሚያገናኘው የዓላማ መሸጋገሪያ ነው።
- ለስብከቱ የሚሰጠው መልስ የሚወጣው ሰባኪው የእግዚአብሔርን አሳብ ከሕዝቡ ሁኔታ ጋር እያዛመደ ከሚያቀርበው መልእክት ነው።

በእግዚአብሔር እውነት ሊተገበሩ የሚገባቸው አምስት የሕይወት ፈርጆች አሉ። ከሕይወት ጋር የሚያዛምዷቸውን ነጥቦች ሲያጎለብቱ፥ እነዚህን አምስት ፈርጆች ልብ ይበሉ። ይህም የእግዚአብሔር እውነት እንዴት ለውጥ ሊያመጣና ሕዝቡም እንዴት ሊታዘዙት ይችላሉ የሚለውን ለማጤን ይረዳዎታል።

## አምስቱ የሕይወት ፈርጆች

እግዚአብሔር ምን ዓይነት ሰዎች እንድንሆን ይፈልጋል፦

1. በግል ሕይወታችን
2. በቤት ሕይወታችን
3. በሥራ ወይም በጥናት ሕይወታችን
4. በቤተ ክርስቲያን ሕይወታችን
5. በማኅበረሰባዊ ሕይወታችን

ቴክሳስ ሳን አንቶኒዮ በተባለ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመስበክ ወደ መድረክ ከመውጣቴ በፊት፥ መጋቢው ወደ ጥናት ክፍሉ ወሰደኝ። በዚያም በግድግዳው ላይ መጋቢው በየስብከቱ ያነሣቸው ጥያቄዎች ተጽፈው አየሁ። ጥያቄዎቹ መልካም ሆነው ስላገኘኋቸው ለእናንተም ላካፍላችሁ፦

## የሕይወት ጎዳናዎች

ይህ እውነት፦ ሕይወታችንን የሚለውጠው እንዴት ነው፦

1. አሳባችንን በተመለከተ- ለእግዚአብሔር፥ ለሌሎች ሰዎችና ለሁኔታዎች

2. እግዚአብሔርን ማወቃችንን በተመለከተ

3. ዓመላችንን በተመለከተ - ልናጎለብተው የሚገባ ልማድ፥ ልናስወግድው የሚገባ ልማድ፥ ልናጸናው የሚገባ ልማድ

4. ኅብረታችንን በተመለከተ- ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሰዎች ጋር

5. መነሻ አሳባችንን (Motives) በተመለከተ- ትክክለኛ የሆነን ነገር ትክክለኛ ባልሆነ ምክንያት አደርጋለሁ?

6. እሴቶቻችንንና የምናስቀድመውን ነገር በተመለከተ- በሕይወታችን ትልቁን ስፍራ የምንሰጠው ለማንና ለምንድነው? ይህን ስፍራ ሊይዝ የሚገባው ማንና ምንድነው?

7. ባሕርያችንን በተመለከተ

እነዚህን የሕይወት ጎዳናዎች ከአምስቱ የሕይወት ፈርጆች ጋር ያዋሕዷቸው። ከዚያም ለእርስዎና ለአድማጮችዎ ለመታዘዝ በሚያመች መንገድ ያዘጋጁት።

## ስብከት ማጎልበት ከመተግበር ጋር

እዚህ ላይ በስብከት ውስጥ የሚታየውን እንቅስቃሴ ለማመልከት አንድ ምሳሌ እወስዳለሁ። በቅድሚያ ምንባቡን እነሆ፦

ይቅርታ ነጻ ያወጣል!
ማቴዎስ 18፥21-35

ቁ 21 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ ጌታ ሆይ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? አለው።

ቁ 22 ኢየሱስ እንዲህ አለው፦ እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም።

ቁ 23 ስለዚህ መንግሥተ ሰማያት ባሮቹን ሊቆጣጠር የወደደን ንጉሥ ትመስላለች።

ቁ 24 መቆጣጠርም በጀመረ ጊዜ እልፍ መክሊት ዕዳ ያለበትን አንድ ሰው ወደ እርሱ አመጡ።

ቁ 25 የሚከፍለውም ቢያጣ እርሱና ሚስቱ፥ ልጆቹም፥ ያለውም ሁሉ እንዲሸጥና ዕዳው እንዲከፈል ጌታው አዘዘ።

ቁ 26 ስለዚህ ባሪያው ወድቆ ሰገደለትና ጌታ ሆይ ታገሠኝ እከፍልሃለሁ አለው።

ቁ 27 የዚያም ባሪያ ጌታ አዘነለትና ለቀቀው፤ ዕዳውንም ተወለት።

ቁ 28 ነገር ግን ያ ባሪያ ወጥቶ ከባልንጀሮቹ ከባሮቹ መቶ ዲናር ዕዳ

*ያለበትን አንዱን አገኘና፥ ዕዳህን ክፈለኝ ብሎ ያዘና አነቀው።*

*ቁ 29 ስለዚህ ባልንጀራው ባሪያ ወድቆ ታገሠኝ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው።*

*ቁ 30 እርሱም አልወደደም። ሄዶ ግን ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወኅኒ አኖረው።*

*ቁ 31 ባልንጀሮቹ የሆኑ ባሮችም ያደረገውን አይተው እጅግ አዘኑ፤ መጥተውም የሆነውን ሁሉ ለጌታቸው ገለጡ።*

*ቁ 32 ከዚያ ወዲያ ጌታው ጠርቶ አንተ ክፉ ባሪያ ስለ ለመንከኝ ያን ዕዳ ሁሉ ተውሁልህ፤*

*ቁ 33 እኔ እንደ ማርሁህ ባልንጀራህ የሆነውን ያን ባሪያ ልትምረው ለአንተስ አይገባህምን? አለው።*

*ቁ 34 ጌታውም ተቆጣና ዕዳውን ሁሉ እስኪከፍል ድረስ ለሚያሠቃዩት አሳልፎ ሰጠው።*

*ቁ 35 ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል።*

እርምጃ 3፡- የምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ- ይቅር የተባለው ባሪያ ይቅርታ ለማድረግ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ለእሥር ተዳረገ።

እርምጃ 4፡- ዓላማዬ ይቅር የተባሉ ሰዎች ይቅር አለማለትን እንዲያስወግዱ ለመምከር ነው።

እርምጃ 5፡- የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ ከሞላ ጎደል ይህን ይመስላል፡-

*ርእሰ ጉዳይ* - ይቅር የማይሉ ሰዎች ምን ይሆናሉ?

*ሞብዖ* - ባገኙት ይቅርታ ደስ አይሰኙም፤ በወኅኒም ይጣላሉ።

ከሕዝቡ ሁኔታ ጋር እንዴት እንደማዛምደው ጥቂት ካሰብሁ በኋላ፥ የምንባቡን ማዕከላዊ አሳብ መሠረት በማድረግ የስብከቴን ማዕከላዊ አሳብ አገለብታለሁ። ዓላማዬ አድማጮቼ ይቅር ለማለት በሚቸገሩበት ጊዜ ሁሉ ለማስታወስ የሚችሉትን ነገር መናገር ነው። የስብከቴ ማዕከላዊ አሳብ ይህን ይመስላል፡- *"ይቅርታ ማድረግ ነጻ ያወጣል፤ ይቅር አለማለት ለእሥር ይዳርጋል።"*

እርምጃ 6፡- በዚህ ምዕራፍ እስከ አሁን ድረስ የስብከት መሸጋገሪያንና መተግበርን ጨምሮ ስለ ንድፍ አቀነባበር፤ ስለመግቢያና፥ ስለአካላዊ ቅንብር ስንነጋገር ቆይተናል።

*መግቢያ፤* እዚህ ላይ በአድማጮቼ ሕይወት ሊኖር ስለሚችል ይቅር አለማለት እናገራለሁ። ይቅር ያላሉት ሰው ሊኖር ይችላል፤ ጓደኞቻቸውን፥ አለቃቸውን፥ ዘመዳቸውን፥ ባሎቻቸውን፥ ሚስቶቻቸውን ይቅር ያላሉ ይኖራሉና።

መግቢያዬን ስጨርስ፥ አድማጮቼ ይቅር አለማለት የሚያስከተውን ውጥረት ያስተውላሉ። መራርነት ክፉ መሆኑን እንዲያስቡ እረዳቸዋለሁ። "በተደጋጋሚ የሚበድለኝን ሰው ይቅር ማለት ያለብኝ ስንት ጊዜ ነው?" በማለት ጥያቄ እጠይቃለሁ።

*የመሸጋገሪያ ቃል፤* ጴጥሮስ ኢየሱስን ተመሳሳይ ጥያቄ ጠይቆታል (ቁ. 21)።

*ንዑስ መግቢያ፤* ዐውደ ምንባቡን ለማስተዋወቅ ምንባቡን መሠረት አደርጋለሁ (ቁ. 21-22)።

*የዋናው አካል አስተዋጽኦ፤*

I. *ይቅርታ ማድረግ ነጻ ያወጣል* (ቁ. 21-27)

II. *ይቅር አለማለት ለእሥር ይዳርጋል* (ቁ. 28-35)

*መታጠር፤* ዓላማዬ በአድማጮቼ ሕይወት ያለውን ይቅር አለማለት መውቀስ በመሆኑ፥ ዋናው ትኩረቴ "ይቅርታ ማድረግ ነጻ ያወጣል" በሚለው ላይ አይሆንም። አድማጮቼ ይቅር የተባሉ ሰዎች መሆናቸውን እጠቅሳለሁ። የእግዚአብሔር ባለ ዕዳዎች መሆናችንን፥ እንደዚያም ባሪያ ይቅር መባላችንን አወሳለሁ። ዓላማዬ የእግዚአብሔርን ታላቅ ይቅርታ ለማስታወስ ከሆነ፥ "የስብከቱ ዓላማ ምንድነው?" እንዲሁም "ለስብከቱ የምሰጠው መልስ ምንድነው?" በሚለው አቅጣጫ የእግዚአብሔርን ታላቅ ይቅርታ እየጠቀስሁ እናገራለሁ።

ነገር ግን ዓላማዬ በአድማጮቼ ሕይወት ያለውን ይቅር አለማለት መውቀስ ነው። ስለዚህ በሁለተኛው ነጥብ ላይ ብዙ ትኩረት እሰጣለሁ። ይህን በተመለከተ ምንባቡ "የስብከቱ ዓላማ ምንድነው?" ለሚለው ጥያቄ መልስ አለው። እግዚአብሔር ይቅር ብሎን ከሆነ፥ እኛም ይቅር እንድንል ምንባቡ አበክሮ ይለምነናል።

አንድ ስብከት ሊመልሳቸው የሚገቡ ሦስት ጥያቄዎችን ከዚህ ምንባብ ጋር አያይዤ ሳጤን፥ ቀጥሎ ያለውን ውጤት አገኘሁ፦

- የማስተላልፈው እውነት ምንድነው? *ይቅርታ ማድረግ ነጻ ያወጣል፤ ይቅርታ አለማድረግ ያደርቃል።*
- ይህ እውነት የሚያመጣው ለውጥ ምንድነው? *የበደሉንን ሰዎች ይቅር ማለት አለብን። ምናልባት ባሎቻችሁ ቸልተኛ ሆነውባችሁ*

ወይም ታማኞች ሳይሆኑ ቀርተው ይሆናል፥ ምናልባት ሚስቶቻችሁ በቤት ውስጥ አክብሮት አያሳዩአችሁ ይሆናል። ምናልባት ወዳጃችሁ ከድቷችሁ ይሆናል። በስብከቴ መግቢያ እነዚህን አንድ በአንድ እነግቸዋለሁ።

ይህን እውነት እንዴት ልንታዘዘው ይገባል? የበደላችሁን ሰው ይቅር የምትሉት እንዴት ነው? ለአድማጮቼ ብዙ ጥያቄዎችን እሰነዝራለሁ። በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ይቅርታ ላይ አተኩራለሁ፤ ከዚያም ከበደላቸው ሰው ጋር እንዲያነጻጽሩት አደርጋለሁ። የሚበልጠውን በደል የፈጸመው ማን ነው? እናንተ ልትከፍሉት የማትችሉት ዕዳ ከተተወላችሁ፥ ሊከፍል የማይችለውን ዕዳ እንዴት አትተዉትም? ሁለተኛ የበቀል አሳብ ከእናንተ ይወገድ። ሦስተኛ የእናንተም ጥፋት ሊኖር እንደሚችል አስቡ። በደሉን በሙሉ በባለ ዕዳው ላይ አታላክኩ። አራተኛ ይቅርታችሁን የምትገልጡበት መንገድ ፈልጉ።

ከሕይወት ጋር ያዛመዷቸውን ነጥቦች በተመለከተ ጥያቄ ሊነሣ እንደሚችል ይገምቱ። ምክንያቱም ሰዎች (እኔን ጨምሮ)፥ የሚነገረው እውነት ሌሎችን እንጂ እኔን አይመለከተኝም እንላለን። በስብከትዎ መጨረሻ ላይ ይህን የመሰሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይሞክሩ። ለውጤታማ ስብከት ከሰጠኋቸው ትርጉሞች አንዱ፥ ስብከቱ ሰዎች ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ይሰጣል የሚል አሳብ ይገኝበታል።

ይቅር አለማለትን በተመለከተ አድማጮቼ ያነሷቸዋል ብዬ የገመትኳቸውን ጥያቄዎች እዚህ ላይ ጠቅሻቸዋለሁ። ብዙዎቹ "እላምንም" (ገጽ 100-101 ይመልከቱ) የሚሉ ናቸው። አድማጮቼ የሰሙት እውነት ለእነርሱ እንዴት ሊሠራ እንደሚችል ማወቅ ይፈልጋሉ። ስለዚህ ለጥያቄአቸው መልስ ለማዘጋጀት እሞክራለሁ።

- እንደ በደለኝ ባያውቅስ?
- ሁል ጊዜ ይቅር ስለው እንዲሞላቀቅ አያደርገውም? ለምሳሌ አንድ ባለ ዕዳ በየጊዜው እንዲበደረኝ ማድረግ ሞኝነት አይሆንም?
- ግንኙነቱ ሊታደስ ባይችልስ? ለምሳሌ የቀድሞዋ ሚስቴ ሌላ ሰው ብታገባስ?
- የበደለኝ ሰው ቢሞትስ?

ያስታውሱ፤ ስብከትዎ ከአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚነገር ነው። አድማጮችዎ የእግዚአብሔርን እውነት መረዳት የሚጀምሩት ወደ ስብከቱ ፍሬ ነገር በሚሄዱበት ጊዜ ቢሆንም፥ ነገሩ ጥርት ብሎ የሚታያቸው ከሕይወታቸው ጋር ሲያዛምዱላቸው ነው።

## ምሳሌዎች

የአንድ ስብከት ውጤት አብዛኛውን ጊዜ ከያዛቸው ምሳሌዎች ጋር ይዛመዳል። ይህ በየትም ዓለም እውነት ነው። መልካም ተናጋሪዎች ብዙ ምሳሌዎችን ይጠቀማሉ። እስቲ ከጌታ ከኢየሱስ ጀምረው እርስዎ የሚያውቋቸውን መልካም ሰባኪዎች ያስቡ። ሁሉም ግሩም ተራቾች ናቸው። ለምን? ምክንያቱም ታሪኮች ወይም ምሳሌዎች ለንግግራቸው ጉልበት ይሰጡላቸው ነበር። አድማጮችን ከሚታወቀው ወደማይታወቀው ይወስዷቸዋል።

## የምሳሌዎች ፋይዳ (ጠቀሜታ)

የምሳሌዎች ዓላማ መግለጥ ወይም ማብራራት ነው። በምሳሌዎች የምንጠቀመው ስብከታችንን ለማርዘም ከሆነ ተሳስተናል። ምሳሌዎች የሚያስፈልጉት ስብከቱን ግልጥ ለማድረግ እንጂ ርዝመት ለመጨመር አይደለም። የሚነገረውን እውነት ሰዎች እንዲረዱት ያደርጋሉ፤ ይሁንና የስብከቱ ትኩረት መሆን የለባቸውም። ምሳሌ የምንናገረው ሰዎችን ለማዝናናት አይደለም (ምንም እንኳ የማዝናናት ባሕርይ ቢኖራቸውም)፤ አድማጮች የሚነገረውን እውነት በሚገባ እንዲረዱ ለማገዝ ነው። አንዳንድ ጊዜ ብርቱ ምሳሌ ስናገኝ ስብከቱ ከምሳሌያችን ጋር እንዲገጥም ሙከራ እናደርጋለን። በዚህ ጊዜ፥ ስብከቱ የምሳሌውን አቅጣጫ ይከተላል፤ እንዲያ ሲሆን፥ አድማጮቻችን የሚያስታውሱት ሊተላለፍ የተፈለገውን እውነት ሳይሆን ምሳሌውን ብቻ ይሆናል። የዓላማ መሸጋገሪያ ወሳኝ ነው የሚባልበት ሌላው ምክንያት ይህ ነው። የዓላማው መሸጋገሪያ ተገቢውን ምሳሌ እንድንጠቀም ይረዳናል። ምሳሌዎች የስብከታችን ትኩረት መሆን የለባቸውም። ምሳሌዎችን መናገር ደስ ሊያሰኝ ይችላል፤ ይሁንና መድረኩ ላይ የቆሙት ምሳሌ ለመስበክ አይደለም። በዚያ ያሉት ምሳሌዎችን ጨምሮ የተለያዩ ውጤታማ ዘዴዎችን በመጠቀም መጽሐፍ ቅዱስን ለመስበክ ነው።

መልካም ሰባኪ ምሳሌዎችን ይጠቀማል፤ ይሁንና ምሳሌዎችን መጠቀም ያለበት በትክክለኛው ስፍራ፥ ጊዜና ለትክክለኛ ዓላማ መሆን አለበት።

እዚህ ላይ የምሳሌዎችን ጠቀሜታ በተመለከተ ጥቂት ምክሮችን ልሰንዝር፦

**ምሳሌዎች**

. አለመረዳትን ያስወግዳሉ

. አሳብ የሚበትኑ ነገሮችን ያስወግዳሉ

. መርሳትን ያስወግዳሉ
. ድግግሞሽን ያስወግዳሉ
. ደንታ ቢስነትን ያስወግዳሉ

♦ *አለመረዳትን ያስወግዳሉ፤* ምሳሌዎች ነገርን ይገልጣሉ። በምንናገረው እውነት ላይ ብርሃን ይፈነጥቃሉ፤ የስብከቱንም አቅጣጫ ያመለክታሉ። አድማጮች መልእክቱን እንዲረዱና ሰባኪውም ራሱን በሚገባ እንዲገልጥ ይረዳሉ። አንድ ሰው በቪዲዮ ካሜራ በሚቀርፅበት ጊዜ፥ ነገሮች ጥርት ብለው እንዲታዩ መብራት ይጠቀማል። ልክ እንዲሁ ምሳሌዎች፥ በአድማጮች ሕሊና ነገሮች ጥርት ብለው እንዲታዩ ብርሃን ይፈነጥቃሉ። በጨለማ ውስጥ በቪድዮ ካሜራ ጥርት ያለ ምስል ለመቅረፅ አይቻልም።

♦ *አሳብ የሚበትኑ ነገሮችን ያስወግዳሉ፤* በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰውን የስብከት ዘዴ የሚከተሉ ከሆነ፥ ለአድማጮችዎ የሚጠቅም ነገር ለመስጠት ብዙ ነገሮችን ይቀስማሉ። የምንባቡን ሐተታዊ ጥናት ካጠናቀቁ በኋላ፥ ታሽቶና በምሳሌዎች ተቀምሞ ያልተዘጋጀውን ስብከት ይዘው ይቀርቡ ይሆናል። በዚህ ጊዜ የሚናገሩት ነገር ሰዎችን ሊያሰለቻቸው ይችላል። ስብከቱ ከሕይወታቸው ጋር ምንም ዝምድና ከሌለው በእርግጥም ይሰለቻሉ። የእርስዎ ኃላፊነት ስብከቱ እንዳይሰለች ብቻ ሳይሆን፥ ግልጥነት እንዲኖረው ማድረግም ነው። ምሳሌዎች የአድማጮችዎን ፍላጎት የመቀስቀስና አሳባቸውን እስከ መጨረሻው የመያዝ ኃይል አላቸው።

♦ *መርሳትን ያስወግዳሉ፤* መልካም ምሳሌዎች የአድማጮችን ፍላጎት መቀስቀስ ብቻ ሳይሆን፥ አሳባቸውንም እስከ ስብከቱ መጨረሻ ድረስ የመያዝ ጉልበት አላቸው። ምሳሌዎች ልክ እንደ ፎቶግራፍ የድሮ ትዝታን ለመቀስቀስ ይችላሉ። አድማጮችዎ ከዚህ በፊት ከሚያውቁት ነገር ጋር ሕሊናዊና ሥነ-ልቡናዊ ትድኝት እንዲያደርጉም አሳባቸውን ይኮረኩራሉ፥ የሚናገሩት እውነትም ኩልል ብሎ እንዲፈስ ያደርጋሉ።

♦ *ድግግሞሽን ያስወግዳሉ፤* አንድ ሰባኪ ይበጃል ብሎ የያዘው የስብከት ዘዴ ወጥመድ ሊሆንበት ይችላል። በተፈጥሮ ነገሮችን አሳምሮ የማቅረብ ስጦታ ከሌለዎ፥ ንግግርዎን በሚስብ መንገድ ለማቅረብ ብዙ መድከም አለብዎት። ከለመዱት አካሄድ ነጻ የመውጫ አንዱ መንገድ፥ በስብከትዎ መካከል ልዩ ልዩ ምሳሌዎችን መጠቀም ነው። ይህም የአስተሳሰብዎንና የአነጋገርዎን ዘዴ ሰፋ እንዲያደርጉ ግድ ይልዎታል። አድማጮችዎ ልዩ ልዩ እንደመሆናቸው፥ ምሳሌዎችዎም ልዩ ልዩ ቢሆኑ አድማጮችዎን ይመስጣሉ። በተለይ ወጣቶች መልካም ምሳሌዎችን ይወዳሉ። ልጆች (የኔ ያልሆኑ) ስለ ስብከቱ ጥሩነት ሲናገሩ፥ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቅሱት

አለብዎት። ከለመዱት አካሄድ ነጻ የመውጫ አንዱ መንገድ፥ በስብከትዎ መካከል ልዩ ልዩ ምሳሌዎችን መጠቀም ነው። ይህም የአስተሳሰብዎንና የአነጋገርዎን ዘዴ ሰፋ እንዲያደርጉ ግድ ይልዎታል። አድማጮችዎ ልዩ ልዩ እንደመሆናቸው፥ ምሳሌዎችዎም ልዩ ልዩ ቢሆኑ አድማጮችዎን ይመስጣሉ። በተለይ ወጣቶች መልካም ምሳሌዎችን ይወዳሉ። ልጆች (የኔ ያልሆኑ) ስለ ስብከቱ ጥሩነት ሲናገሩ፥ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቅሱት የተናገርኩትን ምሳሌ ነው። የተናገርኳቸው ምሳሌዎች ስብከቱን እንዲያደምጡ አድርገዋቸዋል።

♦ *ደንታ ቢስነትን ያስወግዳሉ!* ምሳሌዎች ስብከቱ ጥርት ብሎ እንዲገለጥ ለማድረግ ይረዳሉ። ስብከቱን ከሕይወት ጋር በሚያዛምዱበት ጊዜ፥ ለሚናገሩት እውነት ሰዎች ይታዘዙ ዘንድ በምሳሌዎች ይጠቀሙ። ስብከቱን ከሕይወት ጋር ለማዛመድ በምሳሌዎች በመጠቀም፥ ስብከቱ በሥራ ላይ ሊውል እንደሚችል ያረጋግጣሉ። ይህም ሰዎች የተባለውን ነገር ላለመታዘዝ ምንም ምክንያት እንዳይኖራቸው ያደርጋል።

## ምሳሌዎችን መፈላለግ

ስብከትዎን በሚያዘጋጁበት ጊዜ ምሳሌዎችን ቢፈልጉና ቢጸልዩ እግዚአብሔር ይሰጥዎታል። ምን ለመመሰል እንደሚፈልጉ ሲያስቡ ምርጥ ምሳሌዎችን ሊያገኙ ይችላሉ። ሕሊናዎ ስብከቱን ሲያውጠነጥን ዓይኖችዎ ተገቢውን ምሳሌ በመፈለግ ይጠመዳሉ።

ምሳሌዎችን ለማግኘት ብቸኛው መንገድ፥ ሕይወትን መመልከት ነው። ቢቸር የተባለ ሰው ሰባኪዎች ምሳሌ እንዴት ሊያገኙ እንደሚችሉ ሲናገር፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃሎችን ይጠቀማል፦ "ዓይን ካለህ እይበት፤ ጆሮ ካለህ ስማበት፤ ልብ ካለህ አስተውልበት"። አካባቢውን የሚያይ ሰው ምሳሌ አያጣም። ስለሆነም አካባቢዎን ይመልከቱ! ይመልከቱ! አሁንም ይመልከቱ!

ምሳሌዎችን የሚቀዱባቸው አራት ምንጮች አሉ።

**የምሳሌ ምንጮች**

. የገዛ ሕይወትዎ

. የሌሎች ሰዎች ሕይወት

. የማንኛውም ሰው ሕይወት

. እርስዎ እራስዎ የሚፈጥሯቸው (የሚቀምሯቸው)

የገዛ ራስዎ ሕይወት ተቀድቶ የማያልቅ የምሳሌ ባሕር ነው። የራስዎን ምሳሌዎች በሚገባ ስለሚያውቋቸው ብዙ ምርጥ ምሳሌዎች

አለማወቃቸው እርግጠኛ ይሁኑ። ማለትም በኢትዮጵያ ለሚኖሩ አድማጮች በቂ ገለጣ ሳይሰጡ፥ ስለ አሜሪካን የእርስ በርስ ጦርነት ለመናገር አይሞክሩ። እጅግም ምሁር ከሆኑና ከጥንት ሥነ-ጽሑፎች ለመጥቀስ ከፈለጉ፥ አድማጮችዎ እርስዎ የሚሉትን ነገር ጨርሶ ሊያስተውሉት እንደማይችሉ ልብ ይበሉ። ስለ ምዕራባውያን ባሕል ምንም ግንዛቤ ለሌላቸው ሰዎች፥ የእነ ሆሜርና አሪስቶትል (አሪስጣጣሊስ) ወይም የእነ ሉተርና ካልቪን ታሪክ አሰልቺ ሊሆንባቸው ይችላል።

የሌሎች ሰዎችን ታሪክ በምሳሌነት ሊጠቀሙ ይችላሉ። ለምሳሌ ከአድማጮችዎ መካከል ደስታ ወይም መከራ የደረሰባቸውን ሰዎች በመውሰድ ምሳሌ አድርገው መጠቀም ይችላሉ። ምናልባት ሁሉም ስለ ምድር መናወጥ፥ ስለ አውሮፕላን መከስከስ ወይም ስለ ምርጫ የሚያውቁት ነገር ሊኖርና ከዚያ ጋር ራሳቸውን ሊያነጻጽሩ ይችላሉ።

አዲስ ነገር በመፍጠር የተካኑ ሰው ከሆኑ፥ በማንም ሰው ላይ ያልደረሱ ታሪኮችን ሊፈጥሩ ይችላሉ። እነዚህም ሐሰተኛ ታሪኮች ሳይሆኑ፥ ልብ ወለድ ታሪኮች ናቸው። ለምሳሌ የኢየሱስን ልደት ባበሰረው መልአክና በእረኞቹ መካከል ሊደረግ የሚችል የአሳብ ልውውጥ ሊፈጥሩ ይችላሉ።

## የምሳሌዎች አጠቃቀም

አንድን ምሳሌ በአግባቡ ለመጠቀም፥ የሚመስሉት ጉዳይ ከምሳሌው መቅደም አለበት። ይህም ሰዎች እርስዎ የሚያነሡትን ነጥብ እንዲያስተውሉና እንዲያስታውሱት ይረዳቸዋል። የምሳሌ ቅደም ተከተል ከዚህ የሚከተለውን ይመስላል:-

**የምሳሌዎች አጠቃቀም :-**

1. አሳቡን መግለጥ
2. ወደ ምሳሌው መሸጋገር
3. አሳቡን በምሳሌ ማብራራት
4. ወደ አድማጮች መሸጋገር
5. አሳቡን መከለስ ወይም በድጋሚ መናገር ነው።

የመዝሙር 133ን አሳብ ለመግለጥ የተጠቀምሁበት ምሳሌ ቅደም ተከተል እነሆ:-

1. *አሳቡ!* በጋራ ዓላማ ላይ ስናተኩር አንድነት ይኖረናል።

2. *ወደ ምሳሌው መሸጋገር!* ይህ እውነት ... ተመስሎ እናገኘዋለን።

3. *ምሳሌ፤* በአላስካ የሚኖሩ ፈረሶችና አህዮች ጠላታቸው የሆነውን ጅብ የሚከላከሉት በተመሳሳይ መንገድ ነው። ፈረሶቹ የመጣባቸውን ጠላት ለመከላከል ግንባር ለግንባር ገጥመው በኋላ እግሮቻቸው እየተፋለሙ ጠላታቸውን ያባርራሉ። አህዮችም እንደ ፈረሶቹ ክብ ይሠራሉ። ነገር ግን እግሮቻቸው ወደ ውስጥ፥ ራሶቻቸውን ወደ ውጭ አድርገው እርስ በርስ በመራገጥ ያልቃሉ።

4. *ወደ አድማጮች መሸጋገር፤* እኛም ጠላታችንን ድል ለማድረግ ልክ እንደ አላስካ ፈረሶች ማድረግ አለብን።

5. *ሐሳቡን መከለስ፤* እንግዲህ በአንድ ዓላማ ጠላታችንን ለማሸነፍ አንድነት ወሳኝ ነው።

አሁን ምሳሌዎችን መጠቀም ያለብን መቼና ምን ያህል ነው ወደሚለው እንመጣለን። የስብከቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ስንነሣ የሚገጥመን ትልቅ ፈተና፥ ብዙ ምሳሌዎችን መጠቀሙ ነው። ለመናገር የምንፈልጋቸውን ምሳሌዎች በሙሉ ለማንሣት ጊዜ የለንም። ስለዚህ በሚፈለገው መጠን ለመጠቀም መዘጋጀት አለብን።

በምሳሌዎች የሚጠቀሙት የት ላይ ነው? እርቃኑን የሆነና አሰልቺ የሚመስለን የስብከታችን ክፍል ሁሉ ምሳሌ ይሻል። ሁልጊዜ ምሳሌ የሚያስፈልጋቸው ክፍሎች፡-

- *መግቢያው፤* የአድማጮችን አሳብና ትኩረት ለመጨበጥ።
- እያንዳንዱ ዐብይ አሳብ፤ አብዛኛውን ጊዜ በንዑስ አሳቦችም ላይ አጫጭር ምሳሌዎችን፥ እጠቀማለሁ።
- *መደምደሚያው፤* ስብከቱን ከፍጻሜ ለማድረስ

ምሳሌ የት ላይ መጠቀም እንዳለብዎ ለመወሰን፥ የስብከትዎን ፍሬ ነገር እያሰቡ ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ፡-

- የዝምድና ጥያቄ፤ የምጠቅሰው ምሳሌ አሳቦችን በትክክል ይገልጥልኛል? የምናገረው "ጌታ ኢየሱስ ዘወትር ከእናንተ ጋር ይሆናል" የሚለውን ከሆነ፥ ይህ ራሱ ገለጣ ይፈልጋል። ሰዎች እንዲህ በማለት ሊጠይቁ ይችላሉና፡- "ልናየው ካልቻልን ከእኛ ጋር መሆኑን እንዴት እናውቃለን?" ይህን ጥያቄ ለመመለስ ምሳሌ ያስፈልጋል። ሰዎች ከሚጠቀሙበት መጓጓዣ አንድ ምሳሌ ልንወስድ እንችላለን። በአውሮፕላን ወይም በመርከብ ስንጓዝ፥ ካፒቴኑን በዓይናችን እናየው ይሆናል። ይሁንና ካፒቴኑ በጉዞአችን ሁሉ ከእኛ ጋር ነው። ልክ፥ እንዲሁ ኢየሱስም በመንፈሳዊ ጉዞአችን ሁሉ ከእኛ ጋር ነው።

- የተዓማኒነት ጥያቄ፤ አድማጮቼ የምናገረውን እውነት እንዲያስተውሉ፥ እንዲያምኑና እንዲቀበሉ ለማድረግ ምን ምሳሌ ልጠቀም? ለምሳሌ የተሳፈርሁበት ጀልባ በማዕበል ስትመታ፥ የጀልባዋ ካፒቴን ሁኔታውን ተቆጣጥሮ ተሳፋሪዎቹን እንዴት ከሞት እንዳዳነን ገልጬ ልጠቀምበት እችላለሁ።
- የዝምድና ጥያቄ፤ ምን ምሳሌ ብጠቀም ነው አድማጮቼ የምናገ ረውን እውነት ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱት የሚረዳቸው? ለምሳሌ በዚያች ጀልባ ውስጥ ሆኜ የምጨነቀው ጭንቀት ለጀልባዋ ደኅንነት ወይም ለካፒቴኑ ችሎታ የሚያደርገው ምንም አስተዋጽኦ የለም።

ብዙ ዓይነት ምሳሌዎች አሉ፤ የተለያዩ ሰዎች ከአንዱ ዓይነት ምሳሌ ሌላውን ይመርጣሉ። ለአንዱ አስቂኝ የሆነው ለሌላው አስቂኝ ላይሆን ይችላል። እንዲሁም አንዳንዶች ረቂቅ ንግግሮችን በቀላሉ ሲያስተውሉ፥ ሌሎቹ ደግሞ አይረዷቸውም። አጫጭር ታሪኮች በየትም ስፍራ የተለመዱ ቢሆኑም፥ ለአድማጮችዎ ለማስተላለፍ የሚፈልጉትን መልእክት በትክክል ለማድረስ ተስማሚ የሆነውን ታሪክ መምረጥ አለብዎ።

በዚህ ሁሉ የአድማጮችዎን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገቡ። ማለትም አድማጮችዎ ምሳሌዎቹን ይረዱ ዘንድ እውነትን ለማስተላለፍ ሁነቶችን የሚተርኩበትን መንገድ ልብ ይበሉ። በስብከትዎ ውስጥ ለማካተት የሚፈልጉትን ምሳሌ ሲያስቡም፥ ከዚህ የሚከተለውን ጥያቄ ይጠይቁ፡- ከምንባቡ ውስጥ ምሳሌ የሚያስፈልገውና ከአድማጮቼ የመረዳት አቅም ጋር የሚጣጣመው ምሳሌ የቱ ነው? ከሚያውቁት እውነት ወደማያውቁት እውነት የሚወስዳቸው ምሳሌስ ምንድነው?

*መደምደሚያው*

መደምደሚያ ስብከቱን ሙሉ ያደርገዋል። የተለያዩ ክፍሎችን ያዋሕዳል። የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ይከልሳል፤ ቀደም ሲል የተነሡ ጥያቄዎችን ይመልሳል፤ አድማጮች እንዲታዘዙ ይጋብዛል።

መደምደሚያው ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦችን ይይዛል። በስብከቱ ዋና አካል ላይ ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች ካልተጨመሩ፥ መደምደሚያው ይህን ማካተት አለበት።

መደምደሚያው የስብከቱ የመጨረሻ ክፍል ሲሆን፥ ስብከቱም የሚቋጨው በዚሁ ነው። ሰባኪው አድማጮች እግዚአብሔር ከእነርሱ

ለሚፈልገው ነገር ምላሽ ይሰጡ ዘንድ፥ የምንባቡን ማዕከላዊ አሳብ የሚከልሰው እዚህ ነው። መደምደሚያው ሁለት ሥራዎች አሉት፦ ስብከቱን ያስተሣሥራል፤ ለተነሡ ጥያቄዎች መፍትሔ ይሰጣል። አድማጮች በስብከቱ ውስጥ የተነሡትን ታላላቅ አሳቦች እጥር ምጥን ባለ መንገድ የሚያገኙት በመደምደሚያው ላይ ነው። በመግቢያው ላይ የተተለመው አቅጣጫ የሚጨበጠውም እዚህ ነው።

### የተሳሳተ መደምደሚያ

የተሳሳቱ መደምደሚያዎች እጅግ ተስፋ አስቆራጭ ናቸው። እንዲህ ያሉ ችግሮችን ለመከላከል ጥቂት ምክሮች ከዚህ በታች ተሰንዝ ረዋል፦

- ድንገት አይጨርሱ። የሚወዱት መዝሙር እየተዘመረ ሳለ ገና የመጀመሪያዎቹ ሦስት መሥመሮች እንደተዘመሩ ቢቋረጥ ምን ይሰማዎታል?
- የተሳሳተ ምልክት አይስጡ። አንዳንድ ሰባኪዎች ስብከታቸውን ከመጨረሳቸው በፊት መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ያጥፋሉ። አድማጮች ይህን በማየት ሰባኪው ዝም ብሎ የቀጠለው ለምን እንደሆነ ግራ ይጋባሉ። አንዳንድ ሰባኪዎች “በመጨረሻ” ይሉና ስብከታቸው መጨረሻ ያጣል። ይህ ቃል የተሳሳተ ምልክት ነው።
- ብዙ መደምደሚያ ለመስጠት አይሞክሩ። አንድ ፓይለት አውሮፕላኑን ዝም ብሎ እያሳረፈ ቢያስነሣ፥ አሁንም እያሳረፈ ቢያስነሣ፥ ምን ይሰማዎታል? “መድረሻ የለውም እንዴ?”አይሉም?
- በመደምደሚያዎ ላይ አዲስ አሳብ አያንሡ።
- ከስብከቱ የሚረዝም መደምደሚያ አያብጁ።
- ወደ መደምደሚያዎ ሳይደርሱ፥ መደምደሚያ አይስጡ። እንዲህ ካደረጉ፥ አድማጮችዎ የጨረሱ መስሏቸው ወጥተው ሊሄዱ ይችላሉ።
- መደምደሚያውን እንደ ተራ ነገር አይቁጠሩት። መደምደሚያዎ የስብከቱ ዐቢይ ክፍል እንጂ ማዳመቂያ አይደለም። መደምደሚያዎ አስፈላጊ መስሎ ካልታያቸው፥ አድማጮችዎ ተገቢውን ትኩረት አይሰጡትም።

### የላቀ መደምደሚያ

አንድን ስብከት በላቀ መንገድ ለመደምደም የሚረዱ ምክሮች እነሆ፡-

- የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ከዋና ዋና ነጥቦች ጋር ባጭሩ በግልጥ መናገሩ አስፈላጊ ነው።
- ሰዎች የሰሙትን ቃል በመታዘዝ ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱት አቅጣጫ መጠቆም የላቀ ጠቀሜታ አለው።
- የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ለአድማጮች በሚገባና በአንድ ዓረፍተ ነገር መግለጥ በጣም ጥሩ ነው።
- የመልእክቱን ማዕከላዊ አሳብ ሊገልጥ የሚችል የመጨረሻ ታሪክ መናገር። ታሪኩም የምሳሌን ሦስቱን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፤ እነርሱም ገላጭነት፥ ተዓማኒነትና ዝምድና ናቸው።

ከሕይወት ጋር የሚያዛምደውን ነጥብ ለማካተት ያሰቡት በስብከቱ መጨረሻ ላይ ከሆነ፥ መደምደሚያው የሚፈልጉትን ውጤት ያመጣ ዘንድ፥ ቀደም ሲል ስለመተግበር አርእስተ ጉዳዮች የተናገርናቸውን ሁሉ በሚገባ ያጢኑ።

መደምደሚያውን በተመለከተ ከአድማጮችዎ የሚጠበቁት ምንድነው? ከአድማጮችዎ የሚጠበቁት የተናገሩትን ቃል በተግባር እንዲያውሉት ነው። ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሲታዘዙ ማየት እጅግ የሚያስደስት ነውና።

# 7

# ስብከቱን መስበክ

>> የስብከቱ "ሥጋ" <<

<u>**እርምጃ 7: ስብከቱን መስበክ**</u>

እርምጃ 6: ስብከቱን ማቀናጀት

እርምጃ 5: የስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ

እርምጃ 4: የዓላማው መሸጋገሪያ ወይም ድልድይ

እርምጃ 3: የክፍለ ምንባቡ ማዕከላዊ አሳብ

እርምጃ 2: ክፍለ ምንባቡን ማቀናጀት

እርምጃ 1: ክፍለ ምንባቡን ማጥናት

አሁን የምንሄደው፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ የቀረፁትን ምስል ወደ ማሰማመሩ ነው። ስብከቱን መጻፍና መስበክ የስብከት ዝግጅቱን ሂደት ከፍጻሜ ያደርሳል። አንድን ስብከት በሚገባ ለመስበክ፥ በመጀመሪያ ስብከቱን በጽሑፍ እንዲያሰፍሩት እመክ ርዎታለሁ። ስብከቱን መጻፍ በመጨረሻ ለማሰማመር ይረዳል። ከዚያም ስብከቱን ለማቅረብ ይዘጋጁ።

| <u>**ስብከትን መጻፍ**</u> | <u>**ስብከትን መስበክ**</u> |
|---|---|
| *ልብ ሊሏቸው የሚገቡ ነገሮች* | |
| - የስብከቱ ይዘት | - የሰባኪው ዘዴ |
| - የስብከቱ ንድፍ | - የሰባኪው አቀራረብ |

## ስብከቱን መጻፍ

አሁን የስብከቱ ሥራ ወይም ዝግጅት በሙሉ ተጠናቋል ለማለት ይቻላል። ከዚህ በኋላ የሚቀረው፥ ስብከቱን በጽሑፍ ማስፈር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ሳለሁ፥ ስብከቴን በጽሑፍ እንዳቀርብ ለመጀመሪያ ጊዜ በመጠየቁ ትልቅ ብስጭት ተሰምቶኝ ነበር። ብዙ ጊዜ የሰበከ ሰው ስብከቱን በጽሑፍ ማስፈር እንደሚያስፈልገው አልተረዳሁም ነበር። ትእዛዙ የስብከቴን አቀራረብ ይቀይረዋል የሚል ሥጋት አደረብኝ። ይባስ ብሎ መምህሬ ምንም ማስታወሻ ሳልይዝ ስብከቴን እንዳቀርብ አዘዘኝ። ይህም ለዓመታት ያዳበርሁትን የስብከት ዘዴ

ድምጥማጡን የሚያጠፋው መሰለኝ። ምንም ምርጫ ስላልነበረኝ የታዘዝሁትን ሁሉ ፈጸምሁ። ለመሆኑ ስብከቱን በሚገባ በጽሁፍ ካዘጋጁ በኋላ ያለ ምንም ማስታወሻ መስበኩ ምን ፋይዳ አለው? ወደ መድረክ ይዘውት የማይሄዱ ከሆነስ ስብከቱን አንድ በአንድ መጻፉ ምን ረብ አለው?

ከዚህ ትምህርት በኋላ፥ በምሰብክበት ጊዜ ማስታወሻ ይዞ ስለመስበክ የነበረኝ አመለካከት ተቀየረ። የስብከቴም አቀራረብ ተለወጠ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ለመስበክ ወደ መድረክ ስወጣ ማስታወሻ አልይዝም። ስብከቴን ሳቀናብር ብርቱ ዝግጅት ስለማደርግ አስፈላጊነቱ እምብዛም አይታየኝም። እንዲህ ማለት ግን ማስታወሻ የለኝም ማለት አይደለም። ስብከቶቼ ሙሉ በሙሉ በጽሑፍ ሰፍረዋል። እንዲያውም ብዙ የምደገፈው በማስታወሻዎቼ ላይ ነው።

በስብከትዎ ሊሉት የሚፈልጉትን ሁሉ ቃል በቃል በጽሑፍ ያስፍሩት። "በስብከትዎ ሊሉ የሚፈልጉትን ሁሉ ቃል በቃል በጽሑፍ ያስፍሩት" በማለት የተናገርሁትን ልብ ይበሉ። ወደ መድረክ ሲወጡ በጻፉት መልክ ላይናገሩ ይችላሉ። የሚናገሩትን ነገር መንፈስ ቅዱስ ሊለውጠው ይችላል። እርሱ የሚፈልገውን ነገር ለመናገር መብት አለው። እርግጥ ነው እርሱ ከዝግጅትዎ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ንቁ ተሳታፊ ነው። ዝግጅት ሲጀምሩ የጥናት ጊዜዎን ለእርሱ አስረክበዋል። ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዲታዘዙ ሲጋብዙም እርሱ በዚያ ውስጥ ነበር።

ስብከቱን በጽሑፍ ማስፈር ብዙ ጥቅም አለው:-

- የስብከቱን እድገት በቀላሉ ለማየት ይረዳዎታል፤ በየደረጃው ለማጎልበትም ይጠቅምዎታል።
- ስብከቱ በጽሑፍ ከሰፈረ፥ ከእርስዎ ጋር በቀላሉ ይዋሐዳል።
- አዳዲስና የተሻሉ አሳቦችን ሲያገኙ ስብከቱን ለማሻሻል ይረዳዎታል።
- ስብከቱን በምሳሌዎች፥ በመሸጋገሪያዎችና በመተግብሮች ለማጠናከር ዕድል ይሰጥዎታል፤ አላስፈላጊና ግልጥ ያልሆኑ አሳቦችን ለማስወገድም ይጠቅምዎታል።
- ስብከቱ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድና ርዝማኔውንም ለመቆጣጠር ያገለግልዎታል። አንድ ገጽ ስብከት ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ከተሞክሮ ለመረዳት ይቻላል። አንድ ገጽ ስብከት አምስት ደቂቃ የሚወስድብዎ ከሆነ፥ ስምንት ገጽ ስብከት ለመስበክ ወደ አርባ ደቂቃ ይወስድብዎታል።
- ስብከቱን በጽሑፍ ካሰፈሩ፥ ወደ መድረክ ሲወጡ ለማስታወስ

ይረዳዎታል። ማስታወሻዎን ወደ መድረክ ይዘው መውጣት አያስፈልግዎትም። ወደ መድረክ ከመውጣትዎ በፊት በሚገባ ካጠኑት (ቃል በቃል መያዝ ሳይሆን)፥ የስብከት ክፍሉን አውጥተው ሲሰብኩ ክፍሉ ራሱ ያስታውሶታል።

- ይህንኑ ስብከት ሌላ ጊዜ ለመስበክ ያስችልዎታል (እርግጥ እንደ አድማጮችዎ ሁኔታ ትንሽ ማስተካከያ ማድረግ ይኖርብዎ ይሆናል)። ስብከትዎን ካልጻፉ ሌላ ጊዜ ደግመው ሊሰብኩት አይችሉም።
- በአንድ ወቅት የተናገሩትን ምሳሌ ሌላ ጊዜ እንዳይደግሙት ይረዳዎታል።
- ምናልባት ስብከትዎን በመጽሐፍ መልክ ሊያሳትሙት ይችላሉ። ያም ሆነ ይህ አሁን አንድ ቋሚ ሰነድ አለዎት ማለት ነው።

ያለ ዝግጅት መልካም ስብከት የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም። ይሁን እንጂ፥ ያለ ማስታወሻ መልካም ስብከት ሊኖር ይችላል። ብዙ ጊዜ የሚሰብኩ ሰዎች ስብከታቸውን የማያዘጋጁና የማያቅዱ ከሆነ፥ አሳባቸውና ምሳሌያቸው ይደጋገማል። አስገዳጅ ሁኔታ ካልገጠመዎ በስተቀር ድንገት ተነሥተው አይስበኩ። ለመንጋው የተመጣጠነ መንፈሳዊ ምግብ ለማቅረብ የሚችሉት ሲዘጋጁ ብቻ ነው።

### *ቋንቋና ዘዬ*

አሪስቶትል በአንድ ወቅት “የምትናገረውን ነገር ማወቅ በቂ አይደለም፤ እንዴት እንደምትናገረውም ማወቅ አለብህ” ብሎ ነበር። ዘዬ በቋንቋ አማካይነት መናገር ያለብንን ነገር ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዴት መናገር እንደሚኖርብን የሚያስገነዝብ ነው። በአንዳንድ ስፍራ ዘዬ ሲባል የግል ማንነት እንደሆነ ተደርጎ ይነገራል። ይሁንና የንግግር ዘዬ የሚያመለክተው፥ የቋንቋ አመራረጣችንንና አጠቃቀማችንን ነው፤ ለአሳባችን ቅርፅ የሚሰጠው ይህ ነውና።

ጥያቄው አንድ ሰው ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ዘዬ አለው ወይም የለውም የሚለው አይደለም፤ እያንዳንዱ ሰው ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ የራሱ ዘዬ አለው። ጥያቄው ዘዬአችን ውጤታማ ነው ወይ? የሚለው ነው። የአነጋገር ዘዬን አስመልክቶ አያሌ መጻሕፍት ተጽፈዋል። ስለ ዘዬ በምንነጋገርበት ጊዜ ከባሕል አንጻር መታየት ያለባቸው ነገሮች አሉ። ከዘዬ ጋር በተያያዘ የሰባኪውን ሰብእና፥ ባሕርይ፥ ችሎታና ምናብ በተመለከተ አንዳንድ አስተያየቶችን ለመስጠት ይቻል ይሆናል።

በሚሰብኩበት ጊዜ ግልጥና በተጨባጭ ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች ይጠቀሙ። ለምሳሌ የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ሲናገሩ፥ በርካታ ትርጉም ባላቸው ቃላት አይጠቀሙ። ቃሉ ጥንድ ትርጉም ካለው፥ አድማጮችዎ እርስዎ ለማለት ወዳልፈለጉት አቅጣጫ ሊሄዱ ይችላሉ። ግልጥ ቃላት ረቂቅ ወይም አሻሚ አይደሉም። አብዛኛውን ጊዜ እጥር ምጥን ወይም ቅልጥፍ ያሉ ናቸው።

በሚሰብኩበት ጊዜ ምስል ከሳች በሆኑ ቃላት ይጠቀሙ። የሚናገሯቸው ቃላት ስሜት የሚኮረኩሩ መሆን አለባቸው። አድማጮችዎ እርስዎ የሚሏቸውን ነገሮች እንዲያዩ፥ እንዲሰሙ፥ እንዲዳስሱ፥ እንዲቀምሱ፥ እንዲያሸቷቸው ከፈለጉ፥ ምስል ከሳች በሆኑ ቃላት ይጠቀሙ። ቃሎችዎ ከድምፅ ሳጥን የሚወጡ ብቻ መሆን የለባቸውም። ምስል በሚከስቱ ቃሎች ይናገሩ። "እምነት ያለ ሥራ ዋጋ ቢስ ነው" ከማለት፥ "እምነት ያለ ሥራ ማንጠልጠያ እንደ ሌለው የኮት መስቀያ ነው" ቢሉ እጅግ የተሻለ ይሆናል። የሚመርጧቸው ቃላት የአድማጮችን ስሜት ፈንቅለው የስብከቱን ዓላማ ለመፈጸም መቻል አለባቸው። ቃላት የደስታ፥ የኀዘን፥ የቁጭት፥ የብስጭት፥ ወዘተ. ስሜት በመፍጠር ወደተፈለገው ግብ ያደርሱልናል።

## ምስል ከሳች ቃላት

(የቃል መረጣ)

*የምጠቀምባቸው ቃላት ግልጥና ተጨባጭ ናቸው?*
*አሳብንና ስሜትን ይኮረኩራሉ?*

በዚህ ዓይነት የስብከት ዝግጅት ለማደግ አድማጮችዎን ማወቅ አለብዎ። ያስታውሱ፤ ስብከትዎን የሚጽፉት ለእነርሱ ነው። መልእክትዎን ብርቱ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ የእነርሱን ሁኔታ ያጥኑ። በሚያውቋቸውና ምቾት በሚሰጧቸው ቃላት ይጠቀሙ። ከአሰልቺ አባባሎች ይቆጠቡ። ለአድማጮቼ ልነግራቸው የምፈልገው ነገር ምንድነው? ይህንንስ እንዴት ልነግራቸው እችላለሁ? በማለት ራስዎን ይጠይቁ። ከዚያም በዚሁ መሠረት የራስዎን ዘዬ ያጎልብቱ። ስብከትዎ በቀለም፥ በድምፅ፥ በጣዕም፥ በመዓዛ፥ በስሜት የተሞላ ይሁን። በዚህ አካኋን በምስል ከሳች ቃላት ካልተሞላ የተፈለገውን ውጤት ሊያመጣ አይችልም።

ስብከትዎን ሲጽፉ ለዘዬዎ እንዲረዳዎ እነዚህን ጥያቄዎች ያንሡ። የምጠቀምበት ቋንቋ ግልጥና ሊመስጥ የሚችል ነው? በማለት ራስዎን ይጠይቁ። ቃላትን፥ ዓረፍተ ነገሮችንና አንቀጾችን በጥንቃቄ ያዋቅሩ፤

ግልጥና ሊመስጡ የሚችሉ እስኪሆኑ ድረስ ደግመውና መላልሰው ያርሟቸው።

በመድረክ ላይ ለዛ ያለው ቀልድ መናገርን እንዴት ይመለከቱታል? ለዛ ያለው ቀልድ መቀለድ የሚችሉ ከሆነ፥ ችሎታዎን ቁም ነገር ለማስተላለፊያነት ያውሉት። ለዛ ያለው ቀልድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው በዚህ መልኩ ነው። ቀልዶችን የሚናገሩት ሰዎችን ለማዝናናት፥ ጊዜውን ለመሙላት ወይም ለሙገሳ ብለው አይሁን። አንድ ከደቡብ እስያ የመጣ ካህን ገና መናገር ከመጀመሩ በፊት አድማጮቹ በሳቅ መንከትከት ይጀምሩ እንደ ነበር አውቃለሁ። ከአንዳንድ ትርኢቶችና ትዕይንቶች (ለምሳሌ ሰርከስ) የምንጠብቀው እንዲህ መሰሉን ነገር ሊሆን ይችላል። በመድረክ ላይ ግን ይህ ተገቢ አይደለም።

ለዛ ያለው ቀልድ ቁም ነገርን ለማስተላለፊያነት ምርጥ መሣሪያ ነው። ሰባኪው ተቀባይነት እንዲያገኝ፥ ሰዎች ስብከቱን እስከ መጨረሻው ድረስ በተመስጦ እንዲከታተሉ፥ የተዘጉ ልቦች እንዲከፈቱና እውነት ለሰዎች በሚገባ መንገድ እንዲተላለፍ የማድረግ ኃይል አላቸው።

እንግዲህ ዘዬ ስብከትዎ ሥጋና አጥንት ነፍስ እንዲዘራ የሚያደርጉበት ነው።

### *ቅደም ተከተልና ዐበይት ክፍሎች*

ስብከትዎን ለመጻፍ በእርምጃ 6 ሥር "ስብከቱን ያዋቅሩ" የሚለውን በጥንቃቄ ይከተሉ።

### ርእስ

ርእስ የስብከቱ መታወቂያ ነው። ርእሱ ወቅታዊ፥ ግልጥና አጭር መሆን አለበት።

### የስብከቱ ክፍለ ምንባብ

እርምጃ 6 ውስጥ እንደተገለጠው፥ ምንባቡ ከተለያዩ ስፍራዎች በአንዱ ሊገለጥ ወይም ሊነበብ ይችላል።

### ቅድመ መግቢያ

ከቅድመ መግቢያ ንግግርዎ ወደ ስብከቱ መሸጋገርዎን ለአድማጮችዎ የሚጠቁሙት በጸሎት፥ ምንባቡን በማንበብ ወይም በሌላ ምልክት ሊሆን ይችላል። ቅድመ መግቢያዎን መጻፍ አያስፈልግዎትም፤ ሆኖም ምን እንደሚናገሩ ተዘጋጅተው መምጣት አለብዎ።

ምልክት ሊሆን ይችላል። ቅድመ መግቢያዎን መጻፍ አያስፈልግዎትም፤ ሆኖም ምን እንደሚናገሩ ተዘጋጅተው መምጣት አለብዎ።

### መግቢያ

መግቢያው የመስማት ፍላጎትን የሚቀሰቅስ፥ ርእሰ ጉዳዩን የሚያስተዋውቅና ዓላማውን የሚገልጥ መሆን አለበት። ስብከቱ መንእሳዊ ስልትን የሚከተል ከሆነ፥ ማዕከላዊ አሳቡ የሚናገሩት በመግቢያው መጨረሻ ላይ ነው። ሥርፀታዊ ስልትን የሚከተል ከሆነ ግን፥ በመግቢያዎ ላይ የሚናገሩት ርዕሰ ጉዳዩን ብቻ ነው።

### ንዑስ መግቢያ

የምንባቡን ዳራና ዐውድ ይናገሩ። የስብከቱን ዐቢይ ክፍል ወይም የመጀመሪያውን ዐቢይ ክፍል ይግለጡ። የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ወይም የምንባቡን ማዕከላዊ አሳብም እዚህ ሊናገሩት ይችላሉ።

### የስብከቱ ዋና አካል

በእርምጃ 6 (ገጽ 90ን ይመልከቱ) መሠረት የስብከትዎን ዋና አካል ሲጽፉ፥ ልብ ሊሏቸው የሚገቡ ነገሮች ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል፡-

I. የመጀመሪያው ዐቢይ ክፍል

የዚህን ክፍል ዐቢይ አሳብ በአንድ ዓረፍተ ነገር ይግለጡት።

የዐቢይ አሳቡን ንዑስ ክፍሎች ለመናገርዎ እርግጠኛ ይሁኑ።

ሀ. የመጀመሪያው ዐቢይ አሳብ ንዑስ ክፍል

ለዚህ ንዑስ ክፍሎች ሌላ ንዑስ ክፍል ሊያወጡለት ይችላሉ።

1. የመጀመሪያው ንዑስ ንዑስ ክፍል

2. ሁለተኛው ንዑስ ንዑስ ክፍል

ከፊለጉ ወደ ሁለተኛው ንዑስ ክፍል ከመሄድዎ በፊት የመጀመሪያውን ንዑስ ክፍል አሳብ መከለስ ይችላሉ።

ለ. ሁለተኛው ንዑስ ክፍል

የንዑስ ክፍሎቹን አሳብ ከተናገሩ በኋላ፥ የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ (በመንእሳዊ ስልት መሠረት) ወይም ርእሰ ጉዳይ (በሥርፀታዊ ስልት

አሳቡን ይግለጡ
ወደ ምሳሌ ይሸጋገሩ
አሳቡን (በምሳሌ) ያብራሩ
ወደ አድማጮች ይሸጋገሩ
አሳቡን ይከልሱ

በመንእሳዊ ስብከት የመጀመሪያውን ዐቢይ አሳብ ከሕይወት ጋር የሚያዛምዱት እዚህ ላይ ነው። ከሕይወት ጋር የሚያዛምዷቸው ነጥቦች ወቅታዊና ተጨባጭ መሆን አለባቸው።

ይህን አቀነጃጀት ለእያንዳንዱ የስብከት ክፍልዎ ይጠቀሙበት።

የመጨረሻውን ዐቢይ ክፍል ተናግረው ሲጨርሱ፥ የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ ይግለጡ፤ (በመንእሳዊ ስብከት እዚህ ላይ በድጋሚ የሚነገረው ለአፅንኦት ነው)። ለአድማጮች በሚስማማ መልኩ የተዘጋጀ፥ ተጨባጭነትና ወቅታዊነት ያለው ማዛመድ በሥርፀታዊ ስብከት እዚህ ይቀርባል።

### መደምደሚያ

መደምደሚያውን ከሕይወት ጋር የሚያዛምዱ ነጥቦችን ለመናገር፥ የስብከቱን ማዕከላዊ አሳብ በድጋሚ ለመግለጥ፥ ስብከቱን ለማጠቃለልና ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ይጠቀሙበት።

## ስብከቱን የራስ ማድረግ

ስብከቱን ከጻፉ በኋላ የራስዎ ማድረግ አለብዎ (ቃል በቃል መያዝ አለብዎ ማለት አይደለም)። ስብከቱን ከመጀመሪያ አንሥቶ መልክ ይሰጡት ስለ ነበር የራስዎ ሆኗል ለማለት ይቻላል። ምንባቡና ዝግጅትዎ፥ ወደ መድረክ ወጥተው ሲሰብኩ የጻፉትን ነገር ለማስታወስ ፍንጭ ይሆኑልዎታል። ምንም እንኳን ምሳሌዎችዎን ለማስታወስ የተለየ ዝግጅት ማድረግ ቢጠበቅብዎም፥ ስብከቱን ቃል በቃል መሸምደድ አያስፈልግዎም። ምናልባት የአቀራረብዎን ዘዬ ከስብከቱ በፊት መለማመድ ይኖርብዎ ይሆናል። ለምሳሌ ለዛ ያላቸውን ቀልዶች ለመናገር ካሰቡ፥ እንዴት መናገር እንዳለብዎ መማር ያስፈልግዎታል። አለበለዚያ አድማጮችዎ ከእርስዎ ጋር ሳይሆን፥ በእርስዎ ይስቃሉ። አንድ ጥቅስ ለመናገር ፈልገው በቃልዎ ሊይዙት ካልቻሉ፥ በትንሽ ወረቀት ላይ ጽፈው በሚፈልጉት ጊዜ ሊያነቡት ይችላሉ።

አብዛኛውን ስብከት ግን ቃል በቃል መያዝ አያስፈልግዎትም። እኔ የምመክርዎ፥ ስብከቱን ለማቅረብ በሚያጠኑበት ጊዜ ሙሉ አሳቡን፥

ለመናገር ፈልገው በቃልዎ ሊይዙት ካልቻሉ፥ በትንሽ ወረቀት ላይ ጽፈው በሚፈልጉት ጊዜ ሊያነቡት ይችላሉ።

አብዛኛውን ስብከት ግን ቃል በቃል መያዝ አያስፈልግዎትም። እኔ የምመክርዎ፥ ስብከቱን ለማቅረብ በሚያጠኑበት ጊዜ ሙሉ አሳቡን፥ ማለትም ነጥቦቹን፥ ምሳሌዎቹንና ማንኛውንም ነገር በግማሽ ገጽ ወረቀት ላይ ይጻፏቸው። እኔ የለመድሁት፥ ስብከቴን ሳጠና የስብከቴን አስተዋጽኦ በእጄ መጻፍ ነው። ይህን ሳደርግ፥ ሁለት ዓይነት ቀለሞችን እጠቀማለሁ። ለዐቢይና ለንዑስ ክፍሎች ሰማያዊ ወይም ጥቁር ቀለም፥ ለምሳሌዎች ደግሞ ቀይ ቀለም እጠቀማለሁ። በወረቀቴ ላይ ቀይ ቀለም ከሌለ ምሳሌ የለኝም ማለት ነው፤ ስለዚህ መፈለግ እጀምራለሁ። የስብከቴን አስተዋጽኦ የምጽፈው፥ ቀደም ሲል በዚሁ ምዕራፍ ስለ ስብከት አወቃቀር በተነጋገርነው መሠረት ነው።

ፍራንሲስ ባከን የተባለ ሰው እንዲህ አለ፦ "ንባብ ሙሉ ሰው ያደርጋል፤ ኮንፍራንስ ዝግጁ ሰው ያደርጋል፤ ጽሑፍ ትክክለኛ ሰው (exact man) ያደርጋል"። እኔም ይህን አሳብ እጋራለሁ፤ አንድ ቀን ሰባኪዎች "ትክክለኛ ሰው" ተብለው እንዲሚጠሩ አምናለሁ።

## ስብከቱን መስበክ

ስብከትዎን ስድስት ደረጃዎችን በማለፍ አዘጋጅተዋል። የራስዎ ለማድረግ፥ በጽሑፍ ለማቆየትና ወደፊት ለማመሳከር ስብከቱን ጽፈውታል። አሁን የምሽጋገረው፥ ስብከቱን ወደ ማቅረቡ ሂደት ነው።

እኔ በትንሹ እንዳስተዋልሁት ከሆነ ንግግርን በተመለከተ ከም ዕራባውያን ይልቅ፥ ሌሎች ሕዝቦች የተሻለ ዕድል አላቸው። ተረትና ብዙ ብሂሎች በሚወሩበት ባሕል ውስጥ የሚያድጉ ሰዎች ከልጅነታቸው ጀምሮ የንግግር ችሎታቸውን ያዳብራሉ። የግሪኮች ፍልስፍና ተጽዕኖ ያለበት ባሕል የሚያደላው ወደ አእምሮ እውቀት ነው። አፅንኦት የሚሰጠውም ለይዘቱ እንጂ ለአቀራረቡ አይደለም። እርግጥ ይህ አጠቃላይ አመለካከት የተለዩ ሁኔታዎች አሉት።

*ቃል አልባ መግባቢያዎች*

አቀራረብ ከሰባኪው ፊት፥ አካልና ድምፅ ጋር የተሳሰረ ነው። እነዚህ ሁሉ ቃል አልባ መግባቢያ ተብለው ይጠራሉ። አንዳንድ ጊዜ ከንግግራችን ይልቅ የፊታችን፥ የአካላችንና የድምፃችን ሁኔታ ነገሩን ይበልጥ ይገልጥልናል። አንድ ጊዜ ከአንድ ወዳጄ ጋር ምሳ እየበላን ስንጫወት (ቁም ነገር ያለው ጨዋታ)፥ ሰዓቱን አሥሬ ይመለከት ነበር። የቱ ድርጊቱ ነው የሚፈልገውን መልእክት በሚገባ ያስተላለፈለት? ቃል

ነገሮችን በሙሉ ሊቆጣጠሩ ይችላሉ። ማለትም ስብከትዎ ድንቅ ሊሆን ይችላል፤ ይሁንና ቃል አልባ መግባቢያዎቹን በጥበብና በተገቢው ስፍራ ካልተጠቀሙባቸው፥ ለማለት የሚፈልጉትን ነገር ባፍጢሙ ይደፉታል።

## ፊትዎ

በዚህ ረገድ አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች የታደሉ እንደሆኑ አውቃለሁ፤ ይሁንና ይህ ተስፋ ሊያስቆርጠን አይገባም። ሰዎች ፊቴን በማየት ስለ ስብከቴ፥ ስለ ራሴና ስለ እነርሱ ምን እንደሚሰማኝ ለማወቅ ይፈልጋሉ። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፥ የአንድ ተናጋሪ ተዓማኒነት የሚለካው በፊቱ ላይ ከሚታየው ሁኔታ ነው።

ሲናገሩ ሰዎችን እያዩ ይሁን። አንድ ሰባኪ በተቻለ መጠን አድማጮቹን መመልከት አለበት። አንድ ወዳጄ ግድግዳ እያየ ነው የሚናገረው፤ ሌላው ደግሞ በመስኮት ወደ ውጭ እያየ ይሰብካል። እንዲህ ዓይነቱ ልማድ መታረም አለበት። ሲሰብኩ አድማጮችዎን እየተመለከቱ ይሁን። ጉባኤው ትልቅ ከሆነ ከግራና ከቀኝ፥ ከፊትና ከኋላ ሰዎችን ይምረጡና፥ እነሱን ትኩር ብለው እያዩ ይናገሩ።

አልፎ አልፎ ፈገግ ይበሉ። እንደ ጥርስ ሳሙና አስተዋዋቂዎች ባይሆንም፥ በሚሰብኩበት ጊዜ ፈገግ ማለቱ ተገቢ ነው። ከማንነትዎ፥ ከስብከቱ ይዘትና ከባሕሉ ጋር የሚስማማ ከሆነ ፈገግ ይበሉ። መድረክ ላይ ሲቆሙ፥ ከሲኦላዊና ከመንግሥተ ሰማያዊ ገጽታዎች አንዱን መምረጥ ይኖርብዎታል። "ስለ መንግሥተ ሰማይ ሲሰብኩ ፊትዎ ይብራ፤ ስለ ሲኦል ሲሰብኩ ፊትዎ እንዳለ ይሁን" በማለት አንድ አውቅ ሰው ተናግሯል።

ሰዎች ሰላማዊውን ፊት ከቁጡ፥ ደስተኛውን ፊት ከኀዘንተኛው፥ አፍቃሪውን ፊት ከክፉ ለመለየት ይችላሉ።

## አካላዊ ንቅናቄዎ

እንደ ፊትዎ ሁሉ አካልዎም ስለሚናገር፥ የሚገልጡትን ነገር ሊያጸና አልያም ሊያፈርሰው ይችላል።

በአካልዎና በቃልዎ መካከል ሦስት ግንኙነቶች አሉ፦

- *ንቅናቄ አልባ አካል፤* አንዳንድ ሰዎች የሚሰብኩት እንደ ጅብራ ተገትረው ነው። ከመቃብር እንደተነሣው የአልዓዛር አካል፥ በከፈን የተጠቀለሉና የማይንቀሳቀሱ ይመስላሉ።
- *ተገቢ ያልሆነ አካላዊ ንቅናቄ፤* ይህም ቢሆን እንቅፋት ነው። አካላዊ ንቅናቄዎ የሰዎችን አሳብ መስረቅ የለበትም። አልያ ሰዎች

የሚያተኩሩት ወደ አካላዊ ንቅናቄዎ ይሆናል። በልጅነቴ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የምቀመጠው ምስባኩ አጠገብ ስለ ነበር፥ ፖስተሬ ጉልበቱን ባጠፈ ጊዜ ሁሉ እቆጥር ነበር። ሌላው ሰባኪ ደግሞ ጆሮውን ሲበላው ትንሹን ጣቱን ጆሮው ውስጥ ከቶ ያክካል። አንዳንዶች ደግሞ እየሩን በቡጢ እየመቱና እየጎሰሙ የጳውሎስን ምሳሌ ያስታውሱኝ ነበር። የሰዎችን አሳብ የሚሰርቅ ነገር አያድርጉ፤ ለምሳሌ አሥር ጊዜ መነጽርዎን ከፍ አያድርጉ ወይም በኪስዎ ውስጥ ቁልፎችን አያቃጭሉ።

- *ተገቢ አካላዊ ንቅናቄ፤* አካላዊ ንቅናቄዎ ከንግግርዎ ጋር መስማማት አለበት። ሲናገሩ የአካልዎ እንቅስቃሴ አግባብ ያለው መሆን አለበት። ለምሳሌ ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲናገሩ፥ ጣቶችዎን ወደ ታች አያመልክቱ። ስለ ሁለተኛ ነጥብ ሲናገሩ፥ ሦስት ጣቶች አያሳዩ። አካላዊ ቋንቋ ለሚናገሩት ነገር ተጨማሪ ጉልበት ይሰጠዋል። አመልካች ጣትዎና ዓይኖችዎ፥ የእጅዎ መዳፍ፥ . . . ወዘተ. የየራሳቸው ቋንቋ አላቸው። በተገቢው ስፍራ ከተጠቀሙባቸው፥ ለስብከትዎ ጉልበት፥ ለአቀራረብዎም ለዛ ይሰጣሉ።

በቤታቸው ንቁ (ለምሳሌ በልጆቻቸው ልደት ጊዜ)፥ በመድረክ ላይ ግን ፈዛዛ የሆኑ ሰዎች ገጥመውኛል። አካላዊ ንቅናቄዎን በቃል ለሚናገሩት ነገር ጉልበት መስጫነት ይጠቀሙበት።

ፍርሃት ያለ ነገር ነው። ይህም ደካማ መሆንዎን በነገር ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ ያለብዎ መሆኑን ያስታውስዎታል። የሚፈሩት፥ ነገሬ አማረልኝ አላማረልኝ በማለት ከሆነ፥ ቅዱስ ያልሆነ ፍርሃት ነው። የእርስዎ ማንነት የሚወሰነው፥ በመድረክ ላይ በሚያሳዩት ነገር አይደለም። ራስዎን የሚመዝኑት በስብከትዎ ከሆነ፥ ተስፋ ወደ መቁረጥ ይገባሉ። መላ ነገርዎን ወደ እግዚአብሔርና ወደ መንፈስ ቅዱስ ይመልሱ። በእርሱ ይታመኑ። ፍርሃት ይበልጥ ወደ መንፈስ ቅዱስ እንዲያስጠጋዎና በእርሱም መደገፍን እንዲያስተምርዎ ይጠቀሙበት። ይህም በሚያገለግሉበት ጊዜ ሕዝቡ ወደ መንፈስ ቅዱስ እንጂ ወደ እርስዎ እንዳይመለከት በማድረግ ነጻ ያወጣዎታል።

አካላዊ ንቅናቄዎን በጥበብና በተገቢው ስፍራ ይጠቀሙበት። ሁል ጊዜ ራስዎን ይሁኑ፤ ለባሕልዎም ይጠንቀቁ። ሲሰብኩ ሰዎች በቪዲዮ ካሜራ እንዲቀርፁዎ ቢያደርጉና ቢመለከቱት፥ ተገቢ ያልሆኑ አካላዊ ንቅናቄዎችን እንዲያስወግዱ ይረዳዎታል።

## ድምፅዎ

የድምፅዎ ቅላጼ ከንግግርዎ ይዘት ይልቅ ስለሚናገር፥ ውጤታማ በሆነ መንገድ ይጠቀሙበት። ተገቢውን የድምፅ ከፍተና ዝቅታ እንዲሁም ፍጥነትና መጠን ማጎልበት አለብዎ።

> **የድምፅ ከፍታና ዝቅታ**

- ድምፅዎ ከፍተኛ ነው ወይስ ዝቅተኛ?
- ከፍና ዝቅ ያደርጋሉ?
- ድምፅዎን በመለወጥ የደስታ፥ የትእዛዝ፥ የአዎንታ. . . ወዘተ. መልእክት ለማስተላለፍ ይችላሉ?

> **የድምፅ ዓይነት**

- በአፍንጫ የሚፈጠር ድምፅ አለዎ? . ድምፅዎ ሻካራ ነው?
- ለስላሳ ነው?

> **የአነጋገር እና የአነባበብ ስልት**

- በግልጥና በጥንቃቄ ይናገራሉ?
- ቃሎችን በአግባቡ ይሏቸዋል?

> **ፍጥነት**

- ሲናገሩ አድማጮችዎ ገለጣውን ለመከተል እስኪቸግራቸው ድረስ ይፈጥናሉ?
- እስኪሰለቻቸው ድረስ ነገርዎን ይጎትቱታል?
- አልፎ አልፎ ገለጣዎን ቆም ያደርጋሉ?
- ፈጠን፥ ረጋ፥ ቆም በማለት እየለዋወጡ ነው የሚናገሩት?

> **የድምፅ መጠን**

- ሲናገሩ አድማጮችዎ ያለ ችግር ሊሰሙዎ በሚችሉ መጠን ድምፅዎን ከፍ ያደርጋሉ?
- ለስለስ ባለ ድምፅ ነው የሚናገሩት? በአድማጮችዎ ላይ እንደብራቅ አይጮኹም?
- የድምፅዎን መጠን ይለዋውጣሉ?

**የድምፅ መጠን**

- ሲናገሩ አድማጮችዎ ያለ ችግር ሊሰሙዎ በሚችሉ መጠን ድምፅዎን ከፍ ያደርጋሉ?
- ለስለስ ባለ ድምፅ ነው የሚናገሩት? በአድማጮችዎ ላይ እንደብራቅ አይጮኹም?
- የድምፅዎን መጠን ይለዋውጣሉ?

ሁለት ስብከቶችዎን በቴፕ ወይም በቪዲዮ ቀርፀው የድምፅዎን ሁኔታ ለመገምገም ይችላሉ። ድምፅዎ ሊደመጥ የሚችል ነው? የድምፅዎን ፍጥነትና መጠን ይቀያይራሉ? ብዙ ጊዜ የስብከት ጊዜ አጭር ስለሆነና አንገሌም እየፈጠነ ስለሚያስቸግረኝ፥ ዝግ ብዬ መናገር እንዳለብኝ ለራሴ እነግረዋለሁ። ስሰብክ ድምፄን አስተውዬ እለዋውጠዋለሁ። በእነዚህ ሁኔታዎች ችግር ካለብዎ የንግግር ትምህርት ይውሰዱ፤ ወይም በዚህ ላይ የተጻፉ መጻሕፍትን ያንብቡ። የስብከት አቀራረብዎን የሚገመግም ታማኝ ሰውም ያዘጋጁ (ባለቤትዎም ሊሆኑ ይችላሉ)። ከሁሉ በላይ ግን በጥልቅ ስሜት ይናገሩ። ስብከትዎ ጥልቅ ስሜት ሲኖረው፥ አቀራረብዎ የሰመረ ይሆናል።

ተቀጥላ 1

# መንፈስ ቅዱስና የመድረክ አገልግሎትዎ ውጤታማነት

ከዓላማ አንጻር፥ በዚህ መጽሐፍ የተብራራው የስብከት አዘገጃጀት ሂደት፥ በገላጭ ስብከት አሠራር ዘዴ ላይ ያተኩራል። ይሁን እንጂ፥ የስብከት መሠረታዊ ነገሮች ከጎደሉት፥ እጅግ በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀና የተሰበከ መልእክትም ቢሆን እንኳን፥ ባዶ ጩኸት ይሆናል። የስብከት አዘገጃጀት ዘዴዎችንና መሠረታዊ ነገሮችን የሚያገናኛቸው ቁልፍ ነገር፥ የሰባኪው መንፈሳዊ ሕይወት ነው። በእግዚአብሔር ቃል በማመን፥ እያደገ የሚሄድ መሠረታዊ ግንኙነትን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መቀጠል አለብን።

ቀጥሎ ያሉት የስብከት ዋና ነገሮች በሰባኪው፥ በስብከት ክፍሉና በስብከቱ ጊዜ ዙሪያ ሊታጡ አይገባም። ሁሉም ሰባኪው የሚኖርበትንና የሚያገለግልበትን ኃይል ከሚያገኝበት ከአብ፥ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተገናኙ ናቸው።

*ግላዊ ጉዳዮች።* መንፈሳውያንና "የጸለዩ" ሰባኪያን ብቻ ናቸው መስበኪያው መድረክ ላይ መውጣት ያለባቸው። መንፈሳዊ ሰባኪ፥ እራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ያስረክባል፤ መንፈስ ቅዱስም በበኩሉ በሰባኪው ዕለታዊ ሕይወት ውስጥ ጣልቃ እየገባ ይመራዋል። መንፈሳዊ ሰባኪ በመንፈስ ቅዱስ ይመራል። ለመድረክ አገልግሎቱ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን መጠየቅ ብቻ ሳይሆን፥ ባሕርይውን ይቆጣጠርና ይመራው ዘንድ ሁል ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይሻል፤ ራሱንም ለርሱ ያስገዛል።

ሉዊስ ስፔሪይ ቼውፈር የተባሉ የሥነ-መለኮት ሰው ግልጥና ጥልቅ በሆነ አገላለጥ እንዲህ ብለዋል፦ "ክርስቲያን ክርስቲያን የሆነው፥ ከክርስቶስ ጋር ካለው ትክክለኛ ግንኙነት የተነሣ ነው። መንፈሳዊ ሰው ግን መንፈሳዊ የሚሆነው፥ ከክርስቶስ ጋር ካለው የድነት ግንኙነት በተጨማሪ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሚኖረው ትክክለኛ ግንኙነት ነው።"

መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ለክርስቲያኖች የተሰጡ አራት የአዲስ ኪዳን ትእዛዛት አሉ። በመጀመሪያ በዋናነት የሚመለከቱት ግን ሰባኪውን ነው።

1. *ለመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር እራስዎን ያስገዙ።* ኤፌሶን 5፥18 ውስጥ የተጠቀሰው ትእዛዝ፥ በመለኮታዊውና በሰብአዊው በኩል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት ሚዛናዊ ያደርገዋል። የመንፈስ ቅዱስን የማያቋርጥ ቁጥጥር መፍቀድ የርስዎ ኃላፊነት ነው። ጀልባ ቀዛፊ፥

ጀልባውን ይገፋለት ዘንድ ከንፋስ አቅጣጫ ጋር እንደሚያስተካክል፥ (ዮሐ. 3፥6-8 ውስጥ መንፈስንና ንፋስን አስመልክቶ የተገለጠውን ምሳሌ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ)፥ እኛም እራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር እናስረክባለን። ወደ ሕይወታችን እንጋብዘዋለን፥ ራሳችንን ለቁጥጥሩ እናስገዛለን፤ በየዕለቱ፥ ያለ ማቋረጥ እና በፍላጎት።

2. *መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝነውን ነገር ሁሉ ከሕይወትዎ ያስወግዱ (ኤፌ. 4፥30)።* "የእግዚአብሔር መንፈስ" የሚለው ሙሉ ርእስ፥ ትእዛዙን መንፈስ ቅዱስን አለማሳዘን ከሚለው አሳብ ጋር ያዋሕደዋል። ሰባኪው፥ መንፈስ ቅዱስ ጥሩ መጥረጊያ ይዞ፥ ብሩህ ብርሃኑን በሕይወቱ ሥርቻ ላይ እንዲያበራ በመጋበዝ የራሱን ጉድፍና ቆሻሻ ይመለከታል። በዚህ ሁኔታ የተመሰቃቀለ ሕይወቱን ይመለከትና፥ ከእግዚአብሔር የኃጢአት ይቅርታን ከማግኘት ባሻገር፥ ቅድስና ከጎደለው ነገር ሁሉ ለመንጣት ንስሐ ይገባል (1ኛ ዮሐ. 1፥9)።

3. *ለመንፈሳዊነት ጥንካሬዎ ድጋፍ የመንፈስ ቅዱስ ኃይልን ያኑሩ።* "መንፈስን አታጥፉ" 1ኛ ተሰሎንቄ 5፥19ን ያንብቡ። ግለሰብን የሚመለከትና ለሁሉም የተሰጠ ትእዛዝ ነው። እግዚአብሔር የእርስዎን መንፈሳዊ እድገት እርስዎ ከሚፈልጉት በላይ ይፈልገዋል። ሙገሳን ወይም ልዩ ሽልማትን የመፈለግ ዓላማ በሌላው ሁኔታ የመንፈሳዊ ሕይወት እድገት የሚያገኙበትን መንገድ ይከታተሉ። ይህን ማድረግዎ መንፈሳዊ እሳት እየተቀጣጠለ እንዲቀጥል ያደርገዋል። በመሆኑም ከሥላሴ ጋር ይበልጥ ይቀራረባሉ፤ ከኃጢአት፥ ከሰይጣንና ከዓለም አስተሳሰብ ይለያያሉ። ስብከት አገልግሎት ውስጥ ከመግባትዎ በፊትም፥ ከእግዚአብሔር አጀንዳና ቀዳሚ ጉዳዮች ጋር ይሰለፋሉ።

4. *ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሚራመዱበት ጊዜ፥ ተጠግተው ይከተሉት።* በመንፈስ ተመላለሱ (ገላ. 5፥16)፤ እራሱን ችሎ የማይንቀሳቀስ መኪና በኃይለኛ ጎታች ካሚዮን እንደሚሳብ፥ በመንፈሳዊ ሕይወት እኛም እንዲሁ ነን። ኃይል ስለሌለን መንፈሳዊ እድገትን ልናፋጥነው አንችልም። ነገር ግን፥ ወደ ሌላ አቅጣጫ በመንዳት ወይም በመለያየት ሂደቱን ልናዘገየው እንችላለን። ከዚህ ይልቅ የሥጋን ፈቃድ እንዳንፈጽም መንፈስ ቅዱስ ወደፊት እንዲስበን እንፍቀድ።

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ጠንካራ ግንኙነት የሌለው ሰባኪ፥ ሥራውን ከማያስፈልግ ነገር ጋር

ይቀይጠዋል። ይህ እንዳይሆንበት፥ የተቀደሰ ኃላፊነቱን ለማከናወን ወደ መናገሪያው መድረክ ለመውጣት በሚዘጋጅበት ጊዜ፥ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመተባበር ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ኃይልን ማግኘት አለበት። ያን ጊዜ፥ እንደ መንፈስ ቅዱስ፥ እሱም ኢየሱስ ክርስቶስን በማክበርና እውነትን በጥራት በመግለጥ ተግባር ላይ ያተኩራል (ዮሐ. 16፡13-15)።

*የስብከት ክፍሉን የሚመለከቱ ነገሮች።* ሰባኪው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተገቢውን ግንኙነት የሚያደርገው በግላዊ ሕይወቱ ብቻ ሳይሆን፥ መጽሐፍ ቅዱስን በሚያጠናበት ጊዜም ነው። የመንፈስ ቅዱስና የቃሉ አንድነት የወንጌላዊነት መለያና የጥንቱና የእውነተኛው ሃይማኖት መግለጫ ሆኖ እስከ ዛሬ እንዳለ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያሳየናል። ስብከቱ የሚያካትታቸው ነገሮች ከቃሉ ጋር በዋናነት ሲገናኙ፥ ቃሉ የሚሰበክበትና የሚተላለፍበት ኃይል ደግሞ በዋናነት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ይገናኛል። ስለዚህም ቃሉንና መንፈስ ቅዱስን ልንለያይ አንችልም።

ሰባኪው መንፈሳዊነትና የችሎታ ጉድለት እያለበት በሚሰብከው ስብከት የእግዚአብሔር ክንድ ተገልጦ ውጤት በምናይባቸው ጊዜዎች ሁሉ የምንረዳው፥ ቃሉና መንፈስ ቅዱስ በአንድነት ሆነው እንዴት እንደሚሠሩ ነው። እኛ ኃጢአተኞች፥ ሞኞች ወይም ሰነፎች ብንሆንም እንኳን፥ መንፈስ ቅዱስ ስለ ራሱና ስለ እኛም ሲል ቃሉን ይጠብቃል።

ሰባኪው በመጽሐፍ ቅዱስና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚታመነውና የሚይዘው ቀጥሎ በተዘረዘሩት ጠቃሚ ነጥቦች የተነሣ ነው።

*1. እስትንፋሰ-መለኮት (Inspiration)።* 2ኛ ጴጥሮስ 1፡21 ውስጥ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፥ "በእግዚአብሔር ተልከው፥ ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ" ይላል። መንፈስ ቅዱስ የሚሰብኩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከረጅም ጊዜ በፊት ባመጣ ጊዜ እርስዎ፥ ጥናትዎና ስብከትዎ በአእምሮው እንደነበራችሁ ያውቃሉ? ካወቁ፥ የስብከትዎን ክፍል ያመጣው ያው መንፈስ ቅዱስ፥ ባለዎት አቅም የተቻለዎትን በማድረግ ኢየሱስ ክርስቶስን ያከብሩና ቃሉን በጠራ ሁኔታ ለአድማጮች ያቀርቡ ዘንድ እንደሚያስችልዎ በመተማመን ነው የሚያቀርቡትን ክፍል የሚያጠኑት። ይህ ኃይል ነው እጅግ አስቸጋሪ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በገጠመን ጊዜ ከእግዚአብሔር የሆነ የመረዳት እርግጠኛነትን የሚሰጠን።

*2. አፈታት ወይም አተረጓጎም።* የእግዚአብሔርን ቃል ለመፍታት ወይም ለመተርጎም ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ፥ መንፈስ ቅዱስ አብሮዎት ይሠራል። ለዚህ ነው ሰባኪው የመልእክቱን ክፍል ሲያጠና፥ ሲያዋቅርና የክፍሉን ማዕከላዊ አሳብ ሲፈልግ መንፈሳዊ ጥንካሬ ሊኖረው የሚገባ። የጎሉና ግልጥ የሆኑ ኃጢአቶችን ይናዘዛሉ፤ ለእግዚአብሔርና

ለቃሉ ያለዎትን ፍቅር ይገልጣሉ፤ "እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ . . . መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን" (1ኛ ቆሮ. 2፡12-13)፥ በሚለው መሠረት የስብከቱን ክፍል በመረዳቱ ረገድ መንፈስ ቅዱስ እንደሚገልጥልዎ ይተማመናሉ። መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ማጥናትዎና ስለ ፍቺው በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሙሉ በሙሉ መደገፍዎ፥ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ለተጻፈው ቃል ትክክለኛ ትርጉም ያለዎትን ቅርበት ያረጋግጣል።

*3. አብርሆት።* መንፈስ ቅዱስ ሰባኪውን ከግምት ግልጥ ወደ ሆነ ግንዛቤ ያሸጋግረዋል። የተጻፈውን የእግዚአብሔር መገለጥ ወደ መረዳት ያደርሰዋል፤ ከዚያም አልፎ፥ "ጌታ እንዲህ ይላል" ወይም "የጌታ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ. . ." ወደሚያሰኝ እምነት ያሸጋግረዋል። አብርሆት መጽሐፍ ቅዱስን በሰብአዊ እውቀት የሚተረጉመውን ክርስቲያን ያልሆነ ምሁርና፥ መጽሐፍ ቅዱስን የሚረዳ፥ የሚቀበለው፥ የሚታዘዘው እንዲሁም ትርጉሙን ተግባራዊ የሚያደርገውን አማኝ ሰባኪ ይለያቸዋል። መንፈሳዊ ሰው፥ እውስጡ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ አማካይነት የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ለመረዳትና ሁሉንም ነገር ለማመዛዘን ይችላል (1ኛ ቆሮ. 2፡10፥ 15)።

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሥራ በአማኙ አማካይነት እንዲከናወን ማድረግ ብቻ ሳይሆን (በአማኙ ሕይወት የሚያከናውናቸውን ሥራዎች ሁሉ ያካጻጽሩ)፥ ድል፥ ኃይል፥ የመንፈስ ፍሬ፥ ክርስቶስን የመምሰል ብርታት ይኖረው ዘንድ፥ የእግዚአብሔርን ባሕርይ አማኙ ውስጥ የመሙላት ሥራም አለው። ከሁሉም በላይ፥ ሰባኪው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የእግዚአብሔርን ቃል እውስጡ እንዲሠርፅ ያደርጋል። እሱ ብቻ ነው ነጭ ወረቀት ላይ ያለውን ጥቁር ኅትመት ወደ ብርቱ መሣሪያነት ሊለውጠው የሚችል (ዕብ. 4-12)። ቃሉ እንዲተገበር የሚፈልገውን ነገር ለሰባኪው ግልጥ በማድረግ፥ በግሉ እንዲገነዘበውና እንዲታዘዘው የሚረዳውም መንፈስ ቅዱስ ነው።

*ከስብከት ጋር የተያያዙ ነገሮች።* ጠቅላላው የስብከት ክንውን፥ ከስብከቱ በፊት፥ በስብከት ጊዜና በኋላ በመንፈስ ቅዱስ የታጀበ ነው።

*ከስብከት በፊት።* ለአገልግሎቱ፥ በተለይም ለስብከት አገልግሎት ያለዎት ቅዱስ ፍላጎት የሚመጣው፥ ልብዎ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ሲለወጥ ነው። እሱ ነው እንዲሰብኩ ሥልጣን የሰጠዎት። ይህ ከመለኮት የተገኘን ሥልጣንና ሹመት መረዳትዎ የስብከት ዝግጅት በሚያደርጉበት ጊዜ ሁለመናዎን ይገዛዋል። የቃሉን ፍች በሚያገኙበትና መልእክቱን በሚሰብኩበት ጊዜ፥ መንፈስ ቅዱስ በውስጥዎ ደስታን ይፈጥራል። ብቃትዎ የሚመጣው፥ ከእግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ (2ኛ ቆሮ. 3፡5)፥

ድካምና ጉድለትዎን እንደሚሞላ ያረጋግጥልዎታል። ለጉባኤዎ ተስማሚ የሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መጻሕፍትንና ክፍሎችን በሚመርጡበት ጊዜ ይመራዎታል።

ከዚያም በላይ፥ ወደ ጉባኤው ሲያመሩ መንፈስ ቅዱስ ቀድሞዎት በዚያ ይገኛል። እሱ ዓለምን ስለ ኃጢአት፥ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ በመውቀስ ላይ ነው (ዮሐ. 16፥8-11)። እርስዎ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር በሚያደርገው የማያቋርጥ ግንኙነት ውስጥ ተሳታፊ ብቻ ነዎት። በማንኛውም የስብከቱ ዝግጅትዎ ጊዜም ለራስዎ ብልሀት ወይም እውቀት አይተዉም።

*በስብከት ጊዜ።* የመስበኪያውን ቋንቋ የሚሞላው ቅባት ምንድነው? ሰባኪውስ ቅባቱን የሚያገኘው፥ እንደተቀባም ሊሰማው የሚችለው እንዴት ነው?

"የተቀደሰ ቅባት" ምን አለመሆኑን ብዙ ጊዜ ሊገልጡ ይችላሉ። ለማዝናናት፥ ለማግባባት ወይም አድማጭን ለመቆጣጠር ሲባል በሥጋ የሚደረግ ስብከት አይደለም። ስሜት ከሚሰበው ስብከትዎ ውስጥ የሚወጣ እውነት ሊኖር ስለሚችል፥ እግዚአብሔር ሥጋዊ ስብከትዎን ለዓላማው ይጠቀምበታል። በሰባኪው "ቅባት" (1ኛ ዮሐ. 2፥27) ውስጥ የተጠቀሰው "ቅባት" መንፈስ ቅዱስ እራሱ መሆኑን ነው የምረዳው ማለት "መንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠረው ሰባኪ ማለት ነው"። አንድ የነጻ ትግል ታጋይ ራሱን ለትግል እንደሚያዘጋጅ ራስዎን ማዘጋጀትዎ "በመንፈስ መነቃቃት" ይመስል ይሆናል! እውነቱ ግን "በመንፈስ ቅዱስ ያለመነቃቃት" ነው።

ሙሉ በሙሉ "በመንፈስ ቅዱስ ተነቃቅተው" ወደ መስበኪያው መድረክ ሲወጡ፥ አገልግሎትዎ፥ ስብከቱና ሕይወትዎ የመለኮት ተገዢ መሆኑ ይሰማዎታል። አገልግሎትዎ ጉድለት ያለው ቢሆንም እንኳ የሁሉ ገዢ የሆነው ጌታ ደስ መሰኘቱን ይረዳሉ። ስብከትዎ ስለሚያስገኘው ውጤት እርስዎ ኃላፊነት የለብዎትም። አድማጮች የሚሰጡትን አጸፋ በተመለከተ ሁኔታዎችን እንዲያመቻች በእርግጠኝነት ለመንፈስ ቅዱስ ይተዋሉ። መልእክትዎን በሚያቀርቡበት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚመሩ መሆንዎን በውስጥዎ ይረዳሉ። መንፈስ ቅዱስ በሰባኪውና በአድማጩ መካከል ብርቱ መቀባበል እንዲኖር የሚያስችል ብቃትና እርግጠኛነት ይሰጥዎታል። አንድ ሰባኪ፥ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ያዘጋጀውን ስብከት ያውቃል። ይሁን እንጂ፥ መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያኑ የሚናገረውን ነገር በድንገት ሲያመጣለት ከዝግጅቱ ባሻገር በመሄድ ይታዘዛል። አንድ ስብከትዎን የሰማ አድማጭ ወደ እርስዎ ቀርቦ፥ በስብከትዎ ጊዜ አጉልተው ስለመናገርዎ ወይም ስለመጥቀስዎ እንኳን

በማያስታውሱት የመልእክትዎ ክፍል፥ መነካቱን አረጋግጠልዎ የሚያውቅ ከሆነ፥ መንፈስ ቅዱስ አድማጩ ሊሰማ የሚያስፈልገውን ነገር በማሰማት እንደነካው ይገነዘባሉ። መንፈስ ቅዱስ ስብከታችንን እንዴት እንደተጠቀመበት ያለን መረዳት እንዲሁም መደነቅ ሲያድግና፥ ትሑት ሲያደርገን፥ የመቀባታችን ውጤት ነው። ለራስዎ ዘዴ፥ ስጦታዎችና ተሰጥኦዎች ተትተው ብቻዎን አይደለም መድረክ ላይ የሚቆሙት። መንፈስ ቅዱስ፥ ዓላማውን በአድማጮችዎ ላይ እያከናወነ በዚያ መኖሩ ይሰማዎታል። በስብከት ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕልውናና እውነትን ለአድማጮች የሚገልጥ መንፈስ ቅዱስ ነው። ሙትን የሚያስነሣ፥ ሕሊናን የሚያነቃ፥ አእምሮን የሚያበራ፥ እውቀትን የሚያሠርፅ፥ ልብን የሚያራራ፥ እንዲሁም መንፈስና ነፍስን የሚያነሣሣ እሱ ነው።

ጉድለት ያለበት ስብከትዎ፥ የሰዎችን ሕይወት ወደ ድነት ወይም መንፈሳዊ ብስለት ያመጣል ብለው ማመንዎ እንኳን የሚመጣው ከመለኮታዊ ቅባት ነው። ለአድማጮችዎ መንፈሳዊ ሕይወት ልዩ ትኩረትና ጥንቃቄ በማድረግ ይሞላሉ። መንፈስ ቅዱስ አድማጮች ያሉበትን ሁኔታ ተረድተው በድፍረት ለአድማጮችዎ ድነት ለውጥና ንስሐ የሚሆን ጥሪ እንዲያቀርቡ ይረዳዎታል።

*ከስብከት በኋላ።* ስብከትዎ ቢያበቃም፥ መንፈስ ቅዱስ ከሕዝብዎ ጋር የሚከናወነውን ሥራ አላበቃም። ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ (ቅዱሳን መጽሐፍት ያልጻፉትንም ጭምር) የእውነት መንፈስ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራቸው ቃል እንደገባ (ዮሐ. 16፥11-12)፥ ዛሬም ያሉት ደቀ መዛሙርቱን በእርስዎ በኩል የተሰበከውን ቃሉን ወደ አእምሮአቸው በማምጣት ያስታውሳቸዋል። በስብከትዎ ያቀረቡላቸውን የማዛመድና የመተግበር ሐሳቦችን በማስፋት አዳዲስ ሐሳቦችንና ትእዛዙን የሚፈጽሙባቸውን የመተግበሪያ መንገዶች ያሳያቸዋል። ለመታዘዝ ፈቃደኛ የሚሆኑበትንም ኃይል ይሰጣቸዋል። በስብከትዎ ጊዜ ልባቸው ወደ መታዘዝ ፍላጎት እንዲያዘነብል እንዳደረገ ሁሉ፥ ያን ዝንባሌያቸውን በተግባር የሚያውሉበትን ሁኔታ ያመቻችላቸዋል። በዚህ አካኋን እንደገና ከስብከትዎ ቀድሟል ማለት ነው።

በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እጅ ውስጥ ታላቅ መሣሪያ ለመሆን፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መንፈሳዊነትን ያሳድጉ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ስብከትም ያጎልብቱ። የስብከት ጥናትዎን መልእክቱንና ውጤቱን በጸሎት ይሸፍኑት። በጸሎትና ቃሉን በማጥናት፥ እንዲሁም የስብከቱን ጊዜ በሚያጅበው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስጪነት፥ ተራ የሆነው ሰው እንኳን እጅግ አስደናቂ ሰባኪ ሊሆን ይችላል። 2ኛ ጴጥሮስ 1፥21ን በራሴ አገላለጥ እንዲህ ልበለው:- “በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር ቃል ተናገሩ”።

በዓላት ማክበር ወይም ከነሱ ጋር የተዛመደ መልእክት መስበክ አለብዎት ማለት አይደለም።

- *ልዩ ክንውኖች።* በቤተ ክርስቲያንዎ ታሪክ የሚታሰቡ ልዩ ልዩ ክንውኖችን ማለት፥ የቤተ ክርስቲያን ህንፃ ምረቃን የመሳሰሉትን በማስታወስ፥ ከዚያ ጋር የተዛመደ ዝግጅት ሊደረግ ይገባል።
- *ያልተለመዱ ሁኔታዎች።* በከተማዎ ወይም በአካባቢው አንድ አደጋ ከደረሰ ያን አስመልክተው መስበክ ያለብዎ መሆኑን አይዘንጉ። የህንድ ጠቅላይ ሚኒስቴር ኢንድራ ጋንዲ በአጃቢያቸው ከተገደሉበት ዕለት ለጥቆ የነበረውን እሁድ አስታውሳለሁ። ኒው ዴልሂ በተባለው ከተማ ውስጥ እጅግ የከፋ ጥላቻ ነግሦ፥ እያንዳንዱ ሰውም ፍርሀት ሰፍኖበት ነበር። አገሪቱ በሀዘን ላይ ነበረች። ጥቂት ጠንካራ ሰዎች ብቻ ነበሩ፥ ያን ዕለት ከእግዚአብሔር አንድ የመጽናኛ ቃል በመፈለግ ለአምልኮ ወደየቤተ ክርስቲያኑ የሄዱት።

አንድ የስብከት ክፍል ሲመርጡ፥ ሁልጊዜ ጉባዔዎን እያሰላሰሉ ይሁን። ፍላጎቶቻቸው ምንድናቸው? እግዚአብሔር በዚህ ሳምንት፥ ወር፥ ዓመት ምን ሊያሰማቸው ፈልጓል? ከላይ የተጠቀሱትን በዓላት፥ ክንውኖችና ሁኔታዎች በስብከት ፕሮግራምዎ ውስጥ ቢያካትቱም እንኳን፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልን መስበክ ይችላሉ። ደረጃ 4 ውስጥ፥ ከአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ተነስተን በርከት ያሉ መልእክቶች ልንሰብክ እንደምንችል አይተናል። እንዲህ ያሉት ክፍሎች ካለቁብዎ፥ በልዩ ሁኔታዎች ጊዜ ርዕሳዊ ስብከት ማቅረብ ያስፈልግዎ ይሆናል።

# ተቀጥላ 3

## የስብከት መገምገሚያ መጠየቅ ተቀጥላ

ሃደን ሮቢንሰን የዳላስ ቲዮሎጂካል ሴሚናሪ አስተማሪ በነበሩበት ጊዜ፥ እሳቸውና አብረዋቸው ሥነ-ስብከት የሚያስተምሩ መምህራን የአንድን ሰባኪ ስብከት ለመገምገም የሚያስችል መጠይቅ አዘጋጅተው ነበር። ይህ መጠይቅ እስካሁንም ድረስ በሥነ-ስብከት ትምህርት አሰጣጥ መሪነትን ከያዙት ተቋሞች አንዱ በሆነው የዳላስ ቲዮሎጂካል ሴሚናሪ የሥነ-ስብከት ትምህርት ክፍሎች ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ነው። ሮቢንሰን በጻፉትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት (Biblical preaching)፥ በተባለው መጽሐፋቸው ያቀረቡትን ይህን መጠይቅ በመውሰድ፥ በዚህ መጽሐፍ ከቀረበው የስብከት አዘገጃጀት ዘዴ ጋር በሚስማማ መልኩ አስፋፍቼዋለሁ። የሚከተሉት ጥያቄዎች ስብከትዎን ሲያዘጋጁ ወይም አቀራረብዎን ሲገመግሙ እንደ መመሪያ ያገለግሉዎታል። መመሪያዎቹ የሰው ልጆች መልእክትን በሚልኩበትና በሚቀበሉበት አሠራር ላይ በመመሥረት የቀረቡ ስለሆኑ በየትኛውም አገር ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ስብከትዎን በሚያዘጋጁበትም ሆነ፥ በሚሰብኩትበት ጊዜ ሁሉ ራስዎን እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቁ።

### የስብከቱ አቀነባበር

> *ርእስ*

ወቅታዊ ነው? ኃይል አለው? ትክክል ነው? ግልጥ ነው? አጭር ነው? ርእሱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስብከቱ ስለምንመሆኑን ይገልጣል?

> ***ቅድመ መግቢያ***

- በፕሮግራሙ ላይ ከስብከቱ በፊት የተከናወኑትን ነገሮች ግንዛቤ ውስጥ ያስገባል?
- አድማጮቹ ስለ ሰባኪው ያላቸውን አመለካከት ያገናዝባል?
- አድማጮቹ ካሉበት ሁኔታ ጋር ይያያዛል?
- በቅድመ መግቢያውና በዋናው መግቢያ መካከል ያለው መሸጋገሪያ ግልጥ ነው?

> ***የስብከት ክፍሉ ንባብ***

- የስብከት ክፍሉ በሚገባ ተገልጧል?
- አድማጮች የንባብ ክፍሉን የሚፈልጉበት በቂ ጊዜ ተሰጥቷቸዋል?

- የስብከት ክፍሉ በሚገባ ተነቧል? (የስብከት ክፍሉ በተለያየ ጊዜ ሊገለጥ/ሊነበብ ይችላል።)

> ***ዋናው መግቢያ***

- የአድማጮችን ትኩረት ይስባል?
- ፍላጎታቸውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አንሥቷል?
- ወደ ስብከቱ ርእሰ ጉዳይ፥ ዋና አሳብ ወይም ወደ መጀመሪያው ነጥብ ይመራል?
- የስብከቱ ዓላማ ተገልጧል?
- ርዝመቱ ትክክለኛ ነው?

> ***ንዑስ መግቢያ***

- የስብከት ክፍሉ ወይም የስብከቱ ዳራ ግልጥ ነው?
- ለርእሰ ጉዳዩ፥ ለዓላማው ወይም ለዋና አሳቡ ጠቃሚ አስተዋጽኦ ያደርጋል?

> ***የስብከቱ አካል አስተዋጽኦ (አቀነባበር)***

- ነጥቦቹ በግልጥ ተሰጥተዋል? በክፍሉ ላይ በሚገባ ተመሥርተዋል? ለነጥቦቹ ትክክለኛነት ማስረጃ ቀርቧል?
- በሚገባ ተብራርተው ከሕይወት ጋር ተዛምደዋል?
- አዘገጃጀቱና አጠቃላይ አስተዋጽኦው ግልጥ ነው?
- ስብከቱማዕከላዊ አሳብ አለው? ሊጽፉት ይችላሉ?
- ከነጥብ ወደ ነጥብ መሸጋገሪያዎቹ ግልጥ ናቸው? ለክለሳ ይረዳሉ?
- በነጥቦቹ መካከል መያያዝ አለ?
- ዋና ዋና ነጥቦቹ ከስብከቱ ማዕከላዊ አሳብ ጋር ይዛመዳሉ?
- ንዑስ ነጥቦቹ ከዋናዎቹ ነጥቦቻቸው ጋር በግልጥ ይዛምዳሉ?

> ***የስብከቱ አቀነባበር***

- ስብከቱ አድማጮችን በሚነካ መልኩ ተቀናጅቷል?
- አመክንዮአዊ አቀነጃጀት አለው? ቅደም ተከተላዊ አቀነጃጀትስ?

> ***የስብከቱ አቀነባበር***

- ስብከቱ አድማጮችን በሚነካ መልኩ ተቀናጅቷል?
- አመክንዮአዊ አቀነጃጀት አለው? ቅደም ተከተላዊ አቀነጃጀትስ?
- በስብከቱ ሊነሡ የሚችሉ ሥነ-ልቡናዊና ኅብረተሰብአዊ ጉዳዮች በጥንቃቄ ቀርበዋል?

> ***ማጠቃለያ***

- ስብከቱ ወደ መደምደሚያው ይገሰግሳል?
- አሳቦቹ በማጠቃለያው ላይ በበቂ ሁኔታ ተገልጠዋል?
- የስብከቱ ዋና አሳብ በድጋሚ ተገልጧል?
- ውጤት ሊያመጡ የሚችሉ ጥሪዎች ወይም አሳቦች አሉ?

## ይዘት

> ***ማዕከላዊ አሳብና አተረጓጎም***

- ርእሱ አስፈላጊ ነው?
- ለስብከት ክፍሉ ወይም ለአድማጮቹ አግባብነት አለው?
- የስብከት ክፍሉ ማዕከላዊ አሳብ ተሰጥቷል? ወይም በስብከቱ በግልጥ ታይቷል?
- ስብከቱ በክፍሉ ጥናት ላይ በጥሩ ሁኔታ ተመሥርቷል?
- በየትኛው የስብከት ክፍል ላይ እንዳሉ ለአድማጮችዎ ገልጠዋል?
- ርእሰ ጉዳዩ በሚገባ ተተንትኗል? የቀረቡት አሳቦች አሳማኝ ናቸው?
- ይዘቱ ወጥነትን ያመለክታል?

> ***ድጋፍ ሰጪ ነገሮች***

- አሳቦችን ለማብራራት የቀረበው ነገር ከሚብራሩት አሳቦች ጋር በሚገባ ተያይዟል?
- ማራኪ ነው? ዓይነቱ ይለያያል? ቀጥተኛና በቂ ነው? የሚብራሩ ነጥቦችን ገልጠዋል?
- ከነጥቦቹ ወደ ምሳሌ ወይም ማብራሪያዎች ግልጥ መሸጋገሪያ አለ?

- ነጥቦቹ ከአድማጮች ጋር ግንኙነት አላቸው?
- ነጥቦቹ ማብራሪያ ከተሰጠባቸው በኋላ በድጋሚ ተገልጠዋል? ወይም ተከልሰዋል?

> *ማዛመድ*

- የማዛመድ አሳቦች የተሰጡት ትክክለኛ ቦታዎች ላይ ነው?
- ለአድማጮች በሚሆን መልኩ ቀርበዋል? በተግባር ለማዋል የሚቻሉ ናቸው?
- እና "ምን እናድርግ?" ለሚለው የአድማጮች ጥያቄ መልስ አለው?
- "አሁን ምን ይሁን" የሚለውን ጥያቄያቸውንስ ይመልሳል?

## የአቀራረብ ዘዴ

- የሰዋስው አጠቃቀሙ ትክክል ነው?
- የቃላት አጠቃቀሙ ግልጥና ድግግሞሽ ያልበዛበት ነው?
- የቃላት አጠቃቀሙ ትክክል ነው?
- የቃላት አመራረጡ ለስብከቱ ውጤታማነት አስተዋጽኦ አድርጓል?

## አጠቃላይ ውጤታማነት

- ስብከቱ ከአድማጮች ፍላጎትና አስተሳሰብ ጋር ይገናዘባል?
- ከእውቀታቸው ጋር ተዛምዷል?
- ፍላጎታቸውን ያሟላል?

## የአቀራረብ ግምገማ

> *የአሳብ አቀራረብ*

- ለሁሉም በሚሰማ ድምፅ ሰብከዋል?
- ትኩረትዎን ወደ አድማጮች በማድረግ ይናገራሉ?
- የአድማጮች ወዳጅ ሆነው ነው የቀረቡት?
- በስብከትዎ ጊዜ አነጋገርዎ ነቃ ያለ ነው?
- ቃላቶችን በሚናገሩበት ጊዜ በትክክል ይሏቸዋል?

- ድምፅዎን በማቅጠን፥ በማወፈር፥ በመቀነስ፥ በማፍጠን ወይም ዝግ በማድረግ ይናገራሉ?
- ንግግርዎን በየመሀሉ ቆም ማድረግን በሚገባ ይጠቀሙበታል?

> ***አካላዊ አቀራረብ***

- በስብከትዎ ጊዜ ሙሉ አካልዎን በተገቢው ሁኔታ ተጠቅመውበታል? በእጅ ምልክት ተጠቅመዋል?
- ምልክት አጠቃቀምዎ ድንገተኛ ወይስ ቋሚ?
- የአድማጮችን አሳብ ከሚሰርቁ ልማዶች ይቆጠባሉ?
- ፊትዎ ተገቢዎቹን ማስገንዘቢያዎች ይገልጣል?
- ትክክለኛ በሆነና አግባብነት ባለው ሁኔታ ከአድማጮች ጋር ዓይን ለዓይን ይገናኛሉ?
- የአድማጮችን ሁኔታ ያስተውላሉ?

# ተቀጥላ 4

# ርእሳዊ ስብከት

መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰበክበትን ሁለት መንገዶች አይተናል። እነርሱም ክፍለ ምንባባዊና ርእሳዊ ስብከት ናቸው። በዚህ መጽሐፍ የተብራራው የስብከት መንገድ ያተኮረው፥ በክፍለ ምንባባዊ ስብከት ላይ ነው። ነገር ግን የነገረ መለኮት ሰዎች፥ ሰባኪዎችና ወንጌላውያን ብዙውን ጊዜ የሚሰብኩት ርእሳዊ ስብከትን ነው።

በክፍለ ምንባባዊ ስብከትና በርእሳዊ ስብከት መካከል ያለው ዋና ልዩነት፥ የማዕከላዊ አሳቡ የሚገኝበት ምንጭና ቅንብሩ ላይ ነው። የክፍለ ምንባባዊ ስብከት፥ ርእሰ ጉዳይና ቅንብር በክፍለ ምንባቡ ቁጥጥር ሥር ነው። በርእሳዊ ስብከት ሰባኪው ርእሰ ጉዳዩን ይመርጣል። የስብከቱንም ቅንብር ይወስናል። በዚህ ምክንያት ብቻ አንዳንድ የሥነ-ስብከት አስተማሪዎች፥ ርእሳዊ ስብከት በሰበክን ቁጥር ተንበርክከን እያለቀስን ንስሐ መግባት እንዳለብን ይነግሩናል!

እኔ የርእሳዊ ስብከት ዋና ጥቅም አለው የምለው፥ ብዙ የዝግጅት ጊዜ ስለማያስፈልገው አይደለም! ጥሩ ርእሳዊ ስብከት ዝግጅት ይጠይቃል። ከምእመናን ሕይወትና ሁኔታ ጋር በቀላል ለመዛመድ ይችላል። ክፍለ ንባባዊ ስብከትን ለጊዜው በማቆም ወቅታዊ ጉዳዮችን የተመለከተ ስብከት መስበክ አለብዎት። የርእሳዊ ስብከት ዋና ጥንካሬ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀታቸው ዝቅተኛ የሆነና ቃሉን እንደ ሕይወታቸው መመሪያ አድርገው ለማይወስዱ አድማጮች በውስጣቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ንፅረተ ዓለም (World view) ለማስረጽ መጥቀሙ ነው።

ለርእሳዊ ስብከት ዝግጅት የሚከተለውን መንገድ እጠቁማለሁ።

## ርእሳዊ ስብከት

1. ርእስዎን ይምረጡ
2. ርእስዎን ይወስኑት
3. ርእስዎን ይገንቡት
4. ርእስዎን ይስበኩት

*1. ርእስዎን ይምረጡ፦* የሐረጋት ወይም የቃላት ማጣቀሻ (Concordance) ወይም ማገናዘቢያ ያላቸው መጽሐፍ ቅዱሶች (Reference Bibles) በመጠቀም በመቶዎች የሚቆጠሩ ርእሶችን ሊያገኙ ይችላሉ። ርእሶቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ሲሆኑ፥ ከማነሣሣት ይልቅ ለማስተማር

*የሚያገለግሉ ናቸው። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ "መንግሥተ ሰማያት" ስለ "ጸጋ" ስለ "ገንዘብ" ምን ይላል?*

ከአድማጮችዎ ሁኔታም በመነሣት ርእሶችን ሊመርጡ ይችላሉ። ርእሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠ ቢሆንም እንኳን፥ ከአድማጮችዎ ሁኔታ በመነሣት የሚመርጡት እርስዎ ኖት። ለምሳሌ በከተማዎ የተከሠተ ትልቅ አደጋ ቢኖር ወይም የሚያገለግሏቸው ሰዎች ስለ "መስጠት" መስማት ካለባቸው፥ ያን ርእስ ይዘው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ይመጣሉ።

የስብከት ርእስዎ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከአድማጮች ሁኔታ በመነሣት የተመረጠ ሊሆን ይችላል። ርእስዎን ከመጽሐፍ ቅዱስ በመነሣት ሲመርጡ በአድማጮችዎ "የእውቀትና የእምነት" ፍላጎት ላይ ያተኮረ ስብከት ሲሰብኩ፥ ከአድማጮች ሁኔታ በመነሣት ርእስዎን ከመረጡ ግን በአድማጮችዎ "የአኗኗርና የጠባይ" ፍላጎት ላይ ያተኮረ ስብከት ይሰብካሉ። የሥነ-ስብከት እድገትና መዳበር የሚመጣው መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገርባቸውንና ለአድማጮችም የሚያስፈልጉትን አርእስት በመምረጥ ነው።

ለአንድ የመጋቢዎች ኮንፈራንስ "እግዚአብሔር ልንሠራ የሰጠንን ሥራ መጨረስ" የሚል ርእስ መረጥኩ። አድማጮቼ የሞራል ውድቀት፥ ለአገልግሎት ትጋት ማጣት፥ መንፈሳዊ መታወክ፥ ተስፋ መቁረጥ እንደሚያጋጥማቸው በማወቁ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ የሚናገርበትን የብሉይና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችም ምሳሌ ያቀረቡበትን ይህን ርእስ ለመምረጥ ተነሣሣሁ። ርእሱን በኋላ የስብከት ርእስ በሚሆን መልኩ አበጃጀሁት።

*2. ርእስዎን ይወስኑት።* ርእስዎን ውሱን ማድረግ ዝግጅትዎን ያቀልልዎታል፤ የጥቅስ አመራረጥዎንም ሥርዓት ያለው እንዲሆን ያደርገዋል። የሥነ-ስብከት አዋቂዎች ስለተለመደውና ሦስት ነጥቦች ስላሉት የርእሳዊ ስብከት የሚያቀርቡት ጥያቄ፥ "ከሦስት ነጥብ ይልቅ አራት ወይም አምስት ነጥቦች ያልኖሩት ለምንድነው?" የሚል ነው። ርእስዎን በማጥበብ፥ በመተርጎምና በግልጥ በማስቀመጥ፥ ሥርዓት የሌለው የሚመስል ስብከት ባለመስበክ ከእንዲህ ካለው ትችት ለመዳን ይችላሉ። አንድ ሰባኪ ያሉትን ሰምተው ይሆናል። "ባለፈው ሳምንት ሀያ ነጥብ ያለው ስብከት ስለሰበኩ እርሱን ለማጣጣት የዛሬው ስብከቴ ምንም ነጥብ አይኖረውም።" የሚመርጡት አንድ ውሱን የሆነ ርእስ ጉዳይ (ርእሰ ጉዳይ ስንል፥ ክፍለ ምንባባዊ ፍሬ አሳባዊ እና ርእሳዊ ስብከት የሚሉትን ሁሉ ይመለከታል) ሊያጠኑትና በሚገባ ሊሰብኩት የሚችሉትን ነው።

"*ያደርጉት ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠዎትን ሥራ መፈጸም*" የሚለው ርእስ፥ "*በሚገባ መፈጸም*" ከሚለው ለጉባኤ ከሚሆን ርእስ

"በሚገባ አለመፈጸም" የሚሉትን ንዑስ አንቀጾች ለማብራራት ብዙ ጥቅሶችንና ምሳሌዎችን ለመመልከት እንችላለን። እርስዎ በጊዜና በሁኔታዎች የተወሰኑ ስለሆኑ፥ በስብከቱ አጋጣሚ በሚገባ ለመጠቀም ይችሉ ዘንድ፥ ርእስ ጉዳይዎን ውሱን ያድርጉት። አጠቃላይ ወይም ሰፊ ስብከት ለማቅረብ መሞከር፥ በዝግጅቱ ሂደት እርስዎን፤ በስብከት ጊዜ ደግሞ አድማጮችዎን ያደክማችኋል።

*3. ርእስዎን ያዳብሩት።* እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርሱ፥ ስብከትዎን ለማጎልበት የስብከት ክፍሉንና ርእሱን በማገናኘት ይሠራሉ። ርእስዎን በሚያጎለብቱበት ጊዜ፥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያድርጉ። በመጀመሪያ፥ ተስማሚዎቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያግኙና ንዑሳን ርእሶችን ያዳብሩ እንጂ፥ ተገላቢጦሹን አያድርጉ። የስብከት ርእስዎን በአድማጮችዎ ፍላጎት ላይ ተመሥርተው የሚያዘጋጁ እንደመሆንዎ፥ ርእስዎን ለመግለጥ ወይም ለማዳበር ይረዳዎ ዘንድ፥ ንዑሳን ርእሶችዎን በተገኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ተመሥርተው ያዳብሩ። የራስዎን የአሳብ ሕንጻ ከሠሩ በኋላ፥ ምርጫዎን የሚደግፍልዎ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለመፈለግ አይሞክሩ። ይህን ቢያደርጉ፥ የራስዎን አሳብ ማስረገጫ ጥቅስ ፈላጊ ሆነው ይገኛሉ። እዚህ ላይ ነው፥ ርእሳዊ ስብከት አቅጣጫውን የሚስተው። ማንኛውንም አሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ ልናገኝለት እንችላለን! በአንድ ጉዳይ ላይ እግዚአብሔር የሚለውን አሳብ ተቀብለን በስብከታችን ከማቀናጀት ይልቅ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እንደ ሽፋን በመጠቀም ለሕዝቡ ልንል የምንፈልገውን ልንናገር እንችላለን።

አንድ ሰው ንዑሳን አርእስትን በሚያዳብርበት ጊዜ፥ በዘፈቀደ የሚደረግ ምርጫን፥ የስብከት ክፍልን ያልተሟላ ትርጉም እና ግላዊ ፍላጎትን ለማስወገድ የሚችለው እንዴት ነው?

*ሀ. መሠረትዎ ትእዛዛት፥ አባባሎችና ገለጣዎች ይሁኑ።* እነዚህ ነገሮች በተለይ በመልእክቶችና በጥበብ መጻሕፍት ውስጥ ይገኛሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ ቀጥታ ትእዛዛት ለርእስዎ የሚሆኑ ንዑሳን አርእስት በእርግጠኛነት ያገኛሉ። አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እውነትን በአንድ ርእስ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያስተምር ከሆነ፥ አንድን የስብከት አሳብ ለማዳበር ያለ ችግር ሊመርጡት ይችላሉ። "እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና" (2ኛ ቆሮ. 9፡7)፥ የሚለውን ዓይነት ግልጥ አባባል እና "እንደ ቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ"፥ የሚለውን የመሰለ ትእዛዝ፥ ርእሳዊ ስብከትን ለማዳበር በብዙ ሁኔታቸው ከሁሉ ይቀልላሉ።

የርእሳዊ ስብከት ችግር የሚከሠተው፥ ከትረካዎች፥ ከሕይወት ታሪኮች እና በተለይም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱ ባለ ታሪኮች ድርጊት ውስጥ አርእስትና ንዑሳን አርእስትን በመፈለግ ጊዜ ነው። "በጥንድ የምንሠማራበት ምክንያት"፥ በሚል ርእስ ተነሥተን፥ ኖኅ እንስሳትን በጥንድ ወደ መርከብ እንዳስገባ፥ ወይም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን በጥንድ ለአገልግሎት እንዳሠማራ፥ ወይም ሐዋርያት በጥንድ የተሠማሩበትን ሁኔታ (ጳውሎስና በርናባስ)፥ ብንሰብክ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ሥልጣን ደካማ ሊመስል ይችላል። "በጥንድ መሠማራት"፥ በአሁኑ ጊዜ መከናወን ያለበት ነገር ነው፥ ብሎ ትንታኔያዊ ወይም ሥነ-መለኮታዊ በሆነ መንገድ ማስረዳቱ በጣም ያስቸግራል። የስብከትዎ ርእስ "ጉዞ ባለበት አገልግሎት ቢያንስ ከአንድ ጓደኛ ጋር የመጓዙ ጥቅም"፥ የሚል እንዲሆን በማድረግ ጥሩ መልእክት ሊያደርጉት ይችላሉ። እንዲያውም የደራሲው ዓላማ ቢሆንም ባይሆንም እርስ በእርስ መበረታታት፥ መማማርና ተጠሪነት የሚሉ ጉዳዮችም በትረካው ምሳሌዎች ውስጥ የማንጣት ጥቅም ይኖራል። በመሆኑም፥ ርእሳዊ ስብከትን ለማዘጋጀት በትረካ መጠቀምን አስመልክቼ፥ ሦስት ዘዴዎችን አቀርባለሁ።

ሀ. ስብከትዎን በስብከት ክፍሉ ዓላማ፥ በታሪኩ ሂደት ወይም በስብከት ክፍሉ አቀነባበር ላይ ይመሥርቱ። ከትረካው ውስጥ ተገቢውን ነጥብ ለመምረጥ (ይህ በክፍለ ምንባባዊ ስብከትም ያገለግላል)፥ ፍሬ ነገሮችዎን ቀጥሎ ካሉት ነገሮች መፈለግና መግለጥ ያሻዎታል።

1) የስብከት ክፍሉ *ዓላማ።* የምሰብከው፥ "እግዚአብሔር ለቃል ኪዳን ሕዝቡ የሚያደርገው ጥበቃ" የሚለውን ርእስ ከሆነ፥ ከነጥቦቼ አንዱን ለማግኘት፥ ወደ 2ኛ ነገሥት መጽሐፍ መሄድ ይኖርብኛል። ያን ነጥቤን ግን፥ "የእግዚአብሔር ጥበቃ የሚያመለክተው፥ እሱ ከሕዝቡ ጋር መኖሩን ነው"፥ በሚለውና የ2ኛ ነገሥት ዓላማ በሆነው ላይ ማሳረፍ ይኖርብኛል። የ2ኛ ነገሥት የመጀመሪያ ክፍል የተጻፈው፥ "እስራኤል ውስጥ አንድ እግዚአብሔር አለ፤ የእግዚአብሔር ሰውም እስራኤል ውስጥ ነው፤ ከማረኳቸው ኃያላን መንግሥታት ጋር ግን እግዚአብሔር የለም።" የሚለውን አሳብ አስረግጦ ለመናገር ነው።

2) የስብከት ክፍሉ *ሂደት።* "የታሪኩ ሂደት" ደራሲው ዓላማውን የሚፈጽምበት አንድ መንገድና፥ ያን ዓላማ የማግኛ ዋነኛ ዘዴ ነው። የዮሐንስ ወንጌል ዓላማ እንዲህ በግልጥ ሰፍሯል፦ "ነገር ግን

ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል" (20፡31)። ዮሐንስ የኢየሱስን ተአምራቶች ብቻ ሳይሆን፥ የጻፈበትን ዓላማ ለመፈጸም ይረዳው ዘንድም ጌታ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ያደረገውን ግንኙነት ገልጧል። ዮሐንስ ስለ ኒቆዲሞስ (ወይም ስለ ሳምራዊቷ ሴት፥ እንዲሁም ስለ ቶማስ) ሲገልጥ፥ ከጥያቄ፥ ወደ የማመን ፍላጎት ከዛም በኢየሱስ ወደማመን በማምራት ያቀረበበትን ዘዴ ሊመረምሩ ይችላሉ። ዮሐንስ በወንጌሉ ሙሉ የተጠቀመበትን ይህን አካሄድ በመከተል የኒቆዲሞስን ታሪክ ቢሰብኩ፥ ስብከትዎ ግልጥና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥልጣን ያለው ይሆናል።

3) የስብከት ክፍሉ *ቅርፅ።* የደራሲው የታሪክ ሂደት (plot) ስለ ገጸ ባሕርያት የሚገልጥ ከሆነ፥ የደራሲው አጻጻፍ ቅርፅ ከቃላት፥ ከሐረጎችና ከፅንሰ-አሳቦች የሚወጣ ይሆናል። "እምነት"፥ "ብርሃን"፥ "ዘላለማዊ ሕይወት"፥ "ኢየሱስ ለሥጋ የሰጠው ምግብ ለመንፈሳዊ ሕይወትዎ የሚሰጠውንም ያመለክታል"፥ የሚሉትን ርእሰ ጉዳዮች በደራሲው አቀራረብ መሠረት ሊመረምሯቸው ይችላሉ። እረኛ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስለማመን ለመስበክ ይፈልጋሉ እንበል። የሚሄዱት ያለ ምንም ጥርጥር ወደ መዝሙር 23 ነው። "የእስራኤል እረኛ" ወደሚለው ክፍልም ይሄዳሉ (ኢሳ. 40፤ ሕዝቅ. 34)። እነዚህ ክፍሎች፥ እግዚአብሔር የእስራኤል መሪ መሆኑን የሚገልጡ የብሉይ ኪዳን ዋና ክፍሎች ናቸው። የመጨረሻው ነጥብዎ ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም እረኛ መሆኑን (ዮሐ. 10)፥ ከገለጠበት ጋር የሚዛመድ ሊሆን ይችላል። ሰዎች በእርሱ ያምኑ ዘንድ መለኮታዊነቱን ከገለጠባቸው መንገዶች አንዱ ይህ ነው።

ወደ ኋላ ተመልሰን "ጉዞ ባለበት አገልግሎት ቢያንስ ከአንድ ጓደኛ ጋር የመጓዝ ጥቅም"፥ የሚለውን ስብከት እንደገና እናንሣ። በዚሁ መሠረት ከሉቃስ ወንጌል ወይም ከሐዋርያት ሥራ አንድ ትእዛዛዊ ርእስ ያለው መልእክት ለማቅረብ ፈለጉ እንበል። ያን በሚያደርጉበት ጊዜ፥ የደራሲውን ዓላማ፥ የታሪኩን ሂደት ወይም ቅርፅ ካገኙ የስብከት ክፍሉ ሥልጣን አለዎት ማለት ነው። ይህ ካልሆነ ግን፥ የስብከት ምርጫዎ ፍላጎትዎን ለማሟላት ሲባል፥ እንደተገኘ የሚወሰድ ይሆንና፥ መልእክትዎም የራስዎ አስተያየት የሚገለጥበት ብቻ ይሆናል። በመሆኑም የሚያገለግሉት ሕዝብ አስተያየትም ከእርስዎ የተለየ ስለማይሆን ለእግዚአብሔር እውነት ለመታዘዝ የተዘጋጀ አይሆንም። ስለሚያቀርቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተረዷቸውን ክሥተቶች አስመልክተው አስተያየ

ትዎን እንደ አማራጭ ሊሰብኩ ይችሉ ይሆናል፤ ታዛዥነትን የሚጠይቅ መመሪያ አድርገው ግን አያቅርቡት። አንድ በሐዋርያት ሕይወትና አገልግሎት የታየ ልምምድ፥ በሌላ ትእዛዛዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከተደገፈ ወይም ልምምዱ ተደጋግሞ በቃሉ ውስጥ ከታየ፥ ያን እንደ መመሪያ ለመውሰድ አስተማማኝ መሠረት ይሆንዎታል። ይህ ካልሆነ ግን፥ ለአድማጮችዎ የሚያቀርቡት አሳብ የራስዎ የአእምሮ ፈጠራ ስለሚሆን፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊም ሆነ ነገረ መለኮታዊ መሠረት አይኖረውም። በመጽሐፍ ቅዱሳዊው የስብከት ክፍሉ አሳብ፥ በደራሲው ዓላማና በሚያቀርቧቸው ዋና ዋና ነጥቦች መካከል መሰላሰልን (መያያዝን) ለመፍጠር ከቻሉ፥ ርእሳዊ ስብከትዎ የላቀ ሥልጣን የሚኖረውና፥ ያንንም የሚያስተላልፍ ይሆናል። የርእሳዊ ስብከትዎን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት ሊጠብቁ የሚችሉት በዚህ አካኋን ነው።

ኢየሱስ ፊቱን ወደ መስቀል ማቅናቱን ደራሲው ደጋግሞ ከገለጠውና፥ ጳውሎስ ሩጫውን በአግባቡ ከመፈጸሙ በመነሣት፥ ግልጥ ርእሴን እንዲህ እለዋለሁ፦ "እግዚአብሔር የሰጠዎትን ሥራ መፈጸም"። ንዑሳን አርእስቴንም ግልጥ በሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ ብቻ መሥርቻለሁ። በጣም ግልጥነት ያላቸውና ሁለት ዋና ነጥቦች ያሉት ርእሳዊ ስብከት ሊሆኑ የሚችሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችንም አግኝቻለሁ።

ሀ. ዮሐንስ 17፥4። ኢየሱስ ያከናውነው ዘንድ የተሰጠውን ሥራ በመፈጸም አብን አክብሯል።

ለ. የሐዋርያት ሥራ 20፥24። ጳውሎስ እሩጫውን ይፈጽም ዘንድ፥ ነፍሱን በእርሱ ዘንድ እንደማትከብር፥ እንደ ከንቱ ነገር ቆጠራት (በመጨረሻ 2ኛ ጢሞ. 4፥7 ውስጥ የገለጠውን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ)።

*4. የመረጡትን ርእስ ይስበኩ።* የርእሳዊ ስብከትዎ ገጽታ በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ተመሥርቶ ከሚቀርብ ስብከት ገጽታ ጋር ተመሳሳይ ነው። ቅርፅ ያለው ማዕከላዊ አሳብና፥ ግልጥ መዋቅር ያለው መልእክት ያዘጋጁና ይስበኩ። እንደማንኛውም አሳብ ሁሉ፥ የርእሳዊ ስብከት ማዕከላዊ አሳብም ርእስ ጉዳይና ጭብጥ (መልእክት) አለው። ርእስ ጉዳይ፦ በዚህ ርእስ "እግዚአብሔር ሊሠሩት የሰጠዎትን ሥራ መፈጸም" የሚል ነው። በኋላ ደግሞ፥ "ጉድለት፥ ድካምና ፍርሃት ቢኖሩም እንኳን፥ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመፈጸም እስከ መጨረሻው መጓዝ"፥ ወደሚለው ተሻሽሏል። መልእክቱ ብዙ ጠርዝና ስለት አለው፤ (የርእሳዊ ስብከቶች ሌላው ዋና ገጽታ ብዙ መልእክት ያላቸው መሆኑ ነው)።

ሀ. በሚሠሩት ሁሉ እግዚአብሔርን ያከብሩ፤ ያኔ ይሠሩት ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠዎትን ሥራ ይፈጽማሉ (ዮሐ. 17፡4)። (በኋላ እንዲህ ተለውጧል "የእግዚአብሔርን ሥራ በማከናወን እስከ መጨረሻው ይጓዙ ዘንድ፥ በተሰጠዎት አገልግሎት እሱን ከፍ ከፍ ያድርጉት")።

ለ. ሕይወትዎን በእርስዎ ዘንድ እንደማትከብር ሲቆጥሯት፥ ያከናወኑት ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠዎትን ሥራ ይፈጽሙታል (ሐዋ. 20፡24)። (በኋላ ደግሞ እንዲህ ተብራርቷል፡- "በእግዚአብሔር ሥራ እስከ መጨረሻው ለመሄድ፥ እሱ በሰጠዎት አገልግሎት ውስጥ ክብርዎን ዝቅ ያድርጉ")።

እዚህ ላይ ልገልጥ የምፈልገው ነገር፥ ርእሳዊ ስብከት በአንድ አሳብ ላይ ያተኮረና ግልጥ ስለሆነ፥ የአድማጮችን አሳብ የሚስብ ርእስ ለመምረጥና አቀናብረው ለመስበክ ይችሉ ዘንድ፥ አመቺ ሁኔታ ይፈጥርልዎታል። በስብከትዎ ሁሉ፥ በክፍለ ምንባባዊና በርእሳዊ ስብከትዎ መካከል ሚዛናዊነት እንዲኖር ያደርጉ ዘንድ አበረታታዎታለሁ። በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ተመሥርቶ የሚቀርብ ስብከት፥ በሚያጠነክር ቪታሚን፥ ርእሳዊ ስብከት ደግሞ በሚያረጋጋ አስፕሪን ይመሰላሉ። የሚያገለግሉት ሕዝብ መጠንከርና መረጋጋት ያስፈልገዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በትጋትና በእውነተኛነት ከመረጡ፥ የክፍሎቹ አመራረጥዎና አተረጓጎምዎ ከደራሲው (መለኮትና ሰው)፥ ትርጉምና ዓላማ ጋር የሚስማማ ለመሆኑ ነገረ መለኮታዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫ ካለዎት፥ ከስሕተት የተጠበቁና በእርግጠኛነት የሚሰብኩ ይሆናሉ። ሁል ጊዜ ለጸሎት መንበርከክ አለብዎት፤ ርእሳዊ ስብከት በመስበክዎ ግን ንስሐ መግባት አያስፈልግዎትም።